# ውሃውና ስሙ

## "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የድነት አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

ቅጽ 2

ከተስፋዬ ሮበሌ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ጥምቀት ቤተክርስቲያን
Ethiopian Evangelical
Baptist Church
2822 S. Jupiter Rd.
Garland, TX 75041
Tel: (214) 703-0100 Fax: (214) 703-0161
WWW.EEBC-DALLAS.ORG

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 1999 ዓ.ም.

*ውሃውና ስሙ—"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የድነት አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን ቅጽ 2*


አሳታሚ©1999

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። ያሳሳታሚው ፈቃድ አብዝቶ ማሳተምም ሆነ የተወሰነን ክፍል በተለያዩ መንገዶች ማራባት፣ በጥብቅ የተከለከለ ነው። በማንኛውም መልኩ መረጃን ለመውሰድ ከተፈለገ፣ የተወሰደው መረጃ ሥርዐቱን ጠብቆ ሊጠቀስ እንዲሁም በግርጌ ማስታወሻ ሊመላከት ይገባዋል።



የመጀመሪያ ዕትም 1999 ዓ.ም
የታተመው በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ ነው።



ጥያቄ፣ አስተያየትም ሆነ ሒስ ካልዎ ለጸሐፊው በሚከተለው አድራሻ ይጻፉ:—

ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 23045፤ ኮድ 1000
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ


*The Water and The Name: Critical Study on the Soteriology of "Jesus Only" Church*


Copyright©2007



Published by Raey Publishers
Post Office Box 2332
Addis Ababa, Ethiopia



Comments, questions, and criticisms of this book are welcome. Please address all correspondence to the following address:

Tesfa Evangelical Society For Apologetics
Post Office Box 23045, Code 1000
Addis Ababa, Ethiopia
E-mail: <apologetics@ethionet.et>
<testa_apologetics@yahoo.com>



All Rights Reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means-electronic, mechanical, photocopying, recording or otherwise-without the prior written permission of the publisher and copyright owners.



First printing 2007
Printed in the Addis Ababa, Ethiopia.

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RP-21 2M


# ሰዎች ስለዚህ መጽሐፍ ምን ይላሉ?

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት ቃል ነው። ለአማኙ የምድር ሕይወት መመሪያው ከመሆኑም በላይ፣ የዘላለም ሕይወት አብሣሪውና ማረጋገጫው ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ሳይጨምር ሳይቀንስ ሳነበበውና ለተከተለው የሕይወት እንጀራ ነው። አማኙ በቃሉ ውስጥ ግልጽ ያልሆነለት ነገር ቢኖር ያንንም እግዚአብሔር እስቲገልጥለት ይጠብቃል። ሆኖም በዘመናችን በሙሉ የማይገቡን ምስጢራት በመጽሐፍ ቅዱስ ይኖራሉ። ሙሴ ግልጥ ስለሆኑትም ስላልሆኑትም፣ "ምስጢር የሆነው ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃል ሁሉ እንከተል ዘንድ ለዘላለም የእኛና የልጆቻችን ነው" በማለት ጽፎአል (ዘዳግም 29÷29)። ሐዋርያው ጳውሎስም፣ "ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ ዐውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ ዐውቃለሁ" (1ቆሮንቶስ 13÷12) ብሎአል።

ቃሉን የመተርጐም፣ የመግለጥና የማስረዳት ተግባር የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። የዘላለም ሕይወት የሚገኘውም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያስረዳል። በዚህ ላይ ግን የራስን ሐሳብ መደራረብ አያስፈልግም። ሁሉም አስተምህሮና አስተሳሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ አለመውጣቱና መውጣቱ ይመረመራል እንጂ በሰው ከተመሠረተ በኋላ ትክክለኛ ለማድረግ የሚደረገው ሙከራ ከንቱ ነው።

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ አስመልክቶ የተጻፈው ይህ መጽሐፍ ስሕተትን አጕልቶ ከማሳየት ባሻገር፣ ለአንባቢያን መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አፈታትን ጥበብ ያስጨብጣል። እግዚአብሔር በቃሉ ያለውን በትክክል ለመረዳት በቂ ጥናት የማድረግን ባህል ያዳብራል። ስለሆነም የዋህ አማንያን በስሕተት ትምህርት እንዳይወሰዱ፣ በሐሰት ትምህርት የተወሰዱ ቃሉን በትክክል ተረድተው እንዲመለሱ፣ ሊጠቀሙበት ይገባል። በተጨማሪም በአገራችን ቋንቋ የተጻፉ መስል ድርሰቶች እጅግ አናሳ በሆኑበት ጊዜ የዚህ ጽሑፍ መገኘት ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎችና ለመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንዲሁም ለሁሉም አማኝ

ጥሩ የምሥራች ነው። እነዚህም ሁሉ የዚህ መግለጫ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ምኞቴና ጸሎቴ ነው።

ማሞ ገብረ መስቀል
የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት
እንዲሁም የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ መንበር

አቻና ተመሳሳይ ስምኙ ይዞ መነሣት ለውጤት ያበቃል፤ ውጤት ግን ውጤት ተብሎ ሊጠራ የሚችለው በሕያው ቃሉ መሠረትነት ላይ ጸንቶ ሲቆም ነው፤ ስለዚህ ከእውነቱ የነቀጥ ያህል የራቀ ትምህርት አጥፊ ነው፤ የጥፋቱም ልክ ተከታዮቹን ሁሉ ወደር ለሌለው ለእግዚአብሔር የመጨረሻ ቁጣ ማብቃት ነው።

ተስፋዬ ሮበሌም ሰዎች አንድም ከቁጣ ይተርፉ ዘንድ፣ አንድም የሐሰት ትምህርትን በእግዚአብሔር እውነት ለመተካት ሲል ይህንን መጽሐፍ ጽፎአል። ሐዋርያት ሳይሆኑ በሐዋርያነት ስም ስለተጠሩት ጉባኤያት፣ "የሚናገር እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር" (ሮሜ 12+6) በማለት ዕዳውን አቅልሎአል። የተቀረው፣ "የሚመለከተው ሁሉ" እያነበበው ይገረምበት፣ ይመከርበት፣ ይታረምበት ዘንድ በመጽሐፉ መጠቀም ነው።

ተስፋዬን እግዚአብሔር ለዐቃቤ እምነት ጠርቶታልና ይበረታበት ዘንድ ምክሬ ነው።

ስሜ ታደሰ (መጋቢ)
ቤዛ ባፐቲስት ቤተ ክርስቲያን

ይህ የተስፋዬ ሮበሌ መጽሐፍ፣ "የሐዋርያትን ቤተ ክርስቲያን" ትምህረት በግሩም ሁኔታ የሚፈትሽና መልስ የሚሰጥ ነው። ስለትምህርታቸውም፣ የስማ በለው ሳይሆን የቤተ ክርስቲያኒቷ መሪ የጻፉትን ትምህርቶች ቀጥታ በመጥቀስ ተገቢ መልስ ተሰጥቶበታል። የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ጸሐፊች የአብየተ ክርስቲያናትን አስተምህሮ በመቃወም ብዙ የዘበዘቡ ቢሆንም፣ ዝምታ ፍርሓት የመሰለበትን ሁኔታ የሚሰብር ሆኖ አግኝቼዋለሁ—ይህን መጽሐፍ።

ተስፋዬ መልስ የሚሰጥባቸው ትምህርቶችን ከዐውዱ አውጥቶ ማየት ግን ከባድ ነው ባይ ነኝ። አንባቢዎች ይህንን መጽሐፍ ሲያነቡ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ትኩረት የሚሰጡ ከሆነ፣ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ቤተ ክርስቲያኒቱ ቀድሞውኑ ከአስተምህሮተ ሥሉስ አሐዱ ውጪ በስሕተት መሠረት ላይ የቆመች ስለሆነ መሪዎቿ የሚጠቅሷቸው ጥቅሶች ወዲያው ስሕተተኛ ሆነዋል፤ ምክንያቱም ለሐሰተኛ መሠረት የቅዱስ ቃሉ ክፍለ ምንባቦችን ለድጋፍ በመጥቀስ ዋልታና ማገር ለማድረግ መሞከር መሠረቱን አይቀድሰውምና፣ አያድነውምና።

በርግጥ እነሱ የሚያነሷቸው ጥቅሶች የዋሉት በዚያ ስሑት መሠረት ማጉልበቻ ባይሆን ኖሮ፣ በጥሞና ሊታዩ የሚገባቸው ቁም ነገሮች በተገኙባቸው ነበር። በእኔ እምነት ሰይጣን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ቢጠቅስ ማንነቱ ቅዱስ አይሆንም። ይህም ብቻ ሳይሆን ጥቅሱ ራሱ በእሱ በመጠቀሱ ብቻ ስሕተት ወይም አሳች ወይም ትርጉሙን የሳተ ይሆናል። ነገር ግን ያው ጥቅስ በቅዱሳን ቢጠቀስ ለበረከት ይሆናል፣ ያስተምራል። ስለዚህም ነው ይህን መጽሐፍ የሚያነቡ ሁሉ ለሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ መሆኑን ብቻ ቢረዱ መልካም ነው የምለው።

የእነርሱን በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች እውነተኛ እምነት መስለው የቁጢላደሉትን መደላድል የሚንጥና የሚንድ መጽሐፍ ነው፤ ስሕተቱን ለማየት በሩ እነሆ ተከፍቶአል!

መጽሐፉ ሲያውቁ ለተሳሳቱ መመለሻ፣ ለተደነጋገረባቸው መጽኛ፤ ለሌሎችም ጥሩ የሚያነቃ በትር ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ያንብቡት፣ ያስነብቡት።

አፈወርቅ ኀይሉ
በኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ የነገረ መለኮት መምህር

ሰው እንዴት ከኀጢአቱ ይድናል? እንዴት የዘላለም ሕይወት ያገኛል? የሚለው ጥያቄ በጣም መሠረታዊ ጥያቄ ነው። ይህን ጥያቄ በማያወላዳ መንገድ መመለስ መቻል፣ የክርስቲያን ሁሉ ኀላፊነት ነው።

ተስፋዬ ሮበሌ በነገረ ድነት ላይ የተምታቱ፣ የተውገረገሩ፣ መስመር የሳቱ አመለካከቶችን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ አንጻር የተቸበት

ይህ መጽሐፍ፣ ጉዳዩን አጣርተን እንድንለይና ግልጽ አቋም እንዲኖረን የሚረዳ ሁነኛ አስተዋጽኦ ነው።

ንጉሤ ቡልቻ
ቃለ እግዚአብሔር አንባብያን ማኅበር

"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ሰዎች የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አላቸው። ለዚህም ድጋፍ ይሆናቸው ዘንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሷቸው ክፍሎች አሉ። ጥቅሶቹ ግን የተተረጎሙት ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት መንገድ ባለመከተልና ባለማወቅ ነው።

ወንድማችን ተስፋዬ ሮበሌ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" መሪዎች ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው በማለት ባነሷቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ፣ እጅግ በሚያረካ መንገድ ትክክለኛውን የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት መንገድ በመከተል "ለሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ተከታዮችም ሆነ ለሌላው ሰው በሚጠቅም መንገድ አቅርቦአል። እኔ ሳልሆን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይናገር ማለት ትልቅ ዐዋቂነት ነው። ስለዚህ ይህችን እጅግ ጠቃሚ የሆነች መጽሐፍ እውነትን ለማወቅ የሚሻ ሁሉ በእጃቸው አስገብተው እንዲያነቧት አበረታታለሁ።

ፍሬው ታምራት
የኢቫንጀሊካል የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት (ETC)
አካዳሚክ ዲንና የነገረ መለኮት መምህር

የማልስማማባቸው ድምዳሜዎች ቢኖሩበትም የሙግቱ የፍሰት ወጥነትና የይዘቱ ዐውዳዊነት እንዲሁም የርእስ ጉዳዩ አንገብጋቢነት ይህንን መጽሐፍ እንዳደንቅ ያስገድደኛል። ይህንን መጽሐፍ የሚያነብ ሰው ብዙ እንደሚያተርፍ ሳረጋግጥ እወዳለሁ።

እስጢፋኖስ ተስማ
የመካነ ኢየሱስ ሰሚናሪዮም
የነገረ መለኮትና የሥነ ምግባር መምህር

የስሕተት ትምህርት እውነት መስሎ የዋህና በቃሉ ያልጸኑትን ክርስቲያኖች እያማለቀ የሚወስድ ደራሽ ውሃ ነው። ይህ መጽሐፍ ደግሞ ከወንጌል እውነት ለሚያወጣው፣ "ውሃ ያድናችኋል" አስተምህሮ ማርከሻ ነው።

ነገረ መለኮትን በማስተማርም ሆነ የክርስትናን መሠረተ እምነት ከመናፍቃን በመጠበቅ፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተስፋዬ ሮበሌ ታላቅ ለውጥ ያመጣ ሰው ያለ አይመስለኝም። ይህ እነጋገሬ ምን ያህል እውነት እንደ ሆነ ለማረጋገጥ ይህን መጽሐፍ ማንበብ ብቻ እንኳ በቂ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ በፊት እንደ ጻፋቸው በርካታ መጻሕፍት ሁሉ ይህም መጽሐፍ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመማሪያ መጽሐፍነት እንደሚያገለግል እንዲሁም ለሰንበት ትምህርት ቤት ትልቅ ዕገዛ እንደሚያደርግ እምነቴ ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱሱ አስተምህሮ በተቃራኒው አንጻር የቆሙቱ ብቻ ሳይሆን፣ የቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና አገልጋዮች ሁሉ ከሙግቱ አካሄድ፣ ከነገረ መለኮት ጥልቀቱ እንዲሁም ከሥነ ጽሑፉ ውበት ብዙ የሚስንቁበት ሁነኛ መጽሐፍ ነው። ይነበብ!

ንዋይ ጸጋዬ
ኮልፌ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ

# ውሃውና ስሙ

## "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የድነት አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

ቅጽ 2

# DEDICATION

Mr. Robert M. Bowman Jr.,
who hugely influenced me
by his writings
more than anybody else.

# ACKNOWLEDGMENTS

There are many who have given both their encouragement and support to this work-of course, I take full responsibility for all that appears in this book, but I would also like to thank the following persons and institutions, all of whom contributed to making this book not only possible but actual.

I would like to give special thanks to Ato Amare Mesfin, Ato Menelik Asfaw, Ato Mamo Gebere Meskel, and Ato Negusse Bulcha. They have a great burden for apologetics and are good friends who have always shared my deep passion to defend and affirm the Historic Christian Faith. I am also grateful to them for critically reading the booklet manuscript prior to publication. Their proficiency in editing has greatly contributed to this book. As always, I am extremely thankful to Mr. Paul Carden, executive director for Center For Apologetics Research for his immeasurable support and for the supply of so many materials to my apologetic work.

I want to thank my friend and fellow worker Rev. Luke P. Wilson and his secretary, Barb Ray and other IRR staff and board members for their constant and concrete expressions of support, encouragement, and generosity. Without IRR's help, I never could have written this book. Finally, as always, I wish to earnestly thank my wife Samrawit for her genuine support for my apologetic work. I am grateful beyond words.

I would also like to thank Pastor Negusse Haile who shared me his former life as the pastor of "Jesus Only" Church for 17 years and how he came to the truth of our Lord Jesus Christ. Thank you for allowing me to include your life testimony to this book.

It's my pleasure to dedicate this book for Mr. Robert M. Bowman Jr., who has tremendous influence both in my life and ministry. You know how much influence the books have in our lives and ministry, those whom we've read and those at whose feet we have studied will transform our passions, power, and purpose. So when I consider your books that have changed me and helped me in my apologetic endeavor, I am speaking not only of the fingerprints of particular words, but of the very lives of the author as well. May God bless you richly for the expansion of His kingdom and the edification of His saints. Thank you, Rob.

It is my sincerest hope that this book will first glorify and please God, and, secondly, instruct and edify the people of God and innocent followers of the "Apostolic Church" of Ethiopia. May God be pleased to use this book to those ends, and may He richly bless you as you read the fruits of my apologetic labor.

# ምስጋና

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ወቅት ያበረታቱኝን፣ ረቂቁን በማንበብ ክበርካታ ስሕተት የታደጉኝን ወገኖች ማመስገን እወዳለሁ። ይህ እንዳለ ሆኖ በመጽሐፉ ላይ ስሕተት ቢገኝ፣ የስሕተቱ ሙሉ ተወቃሽ እኔው ጸሓፊው እንጂ እነዚህ ሰዎች አይደሉም— አስተያየታቸውን ሁሉ አላካተትሁምና። አቶ እማረ መስፍን፣ አቶ ምኒልክ አስፋው፣ አቶ ማሞ ገብረ መስቀል፣ አቶ ንጉሤ ቡልቻ።

ውድ ጊዜአቸውን መሥዋዕት በማድረግ የመጽሐፉን ረቂቅ በማንበብ አስተያየት የሰጡኝን ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካቸው። ከርእሰ ጉዳዩ ጋር በተገናኘ፣ በርካታ መጻሕፍትንና የጥናት ጽሑፎችን የላከልኝን ሚስተር ፖል ካርደንን (Mr. Paul Carden) እንዲሁም የአይ. አር. አር. ዳይሬክተር የሆነውን ቀሲስ ሉቃስ ዊልሰንን (Rev. Luke P. Wilson)፣ ሚስስ ባርብ ሬይን እንዲሁም አይ. አር. አር (IRR) ቦርድ ስላደረጉልኝ ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ።

ለዐሥራ ሰባት ዓመት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመጋቢነትና በተለያዩ የአስተዳደር ቦታዎች የነበረውን ታሪክ ያጋራኝን እንዲሁም ይህ ታሪክ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተት የፈቀደልኝን መጋቢ ንጉሤ ኀይሌን፣ እግዚአብሔር ይባርክህ ቀጣይ አገልግሎትህን እግዚአብሔር ይባርክ። ለሁሉም ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ።

የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነት በሕይወቴና በአገልግሎቴ ትልቅ ስፍራ ላላቸው ለሚስተር ሮበርት ቦመን ነው።

ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በማንቃት፣ ባለማወቅ በተሳሳተው ጎዳና ውስጥ ያሉትን፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አማንያንን ወደ ትክክለኛው ጎዳና በመመለስ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያመጣ ጸሎቴና ምኞቴ ነው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ተስፋዬ ሮበሌ
ወርኀ ሰኔ 1999 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# መግቢያ

"እውነት በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በማመን ብቻ፣ በእግዚብሔር ነጻ ስጦታ የሚገኝ የእምነት ችሮታ ነው" የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት "ክርስቲያን" በሚል ስያሜ ራሳቸውን የሚጠሩ አንዳንድ ክፍሎች በተለያየ መንገድ ያብራሩታል። የይሖዋ ምስክሮች፣ ድነት ለመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሙሉ ስሙሉ ከመገዛትና በሚያወጣቸውም ፕሮግራሞች ተካፋይ በመሆን የሚገኝ ሲሆን እንደ ሞርሞን አስተምህሮ ደግሞ፣ አንድ ሰው ድነት የሚያገኘው እጅ ተጭኖ ካተጸለየለት በኋላ ነው።

የዚህ መጽሐፍ ትኩረት የሆኑት፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ሰዎች ደግሞ፣ ድነት ለማግኘት በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ማመን ብቻ ሳይሆን፣ ትክክለኛ ነው በሚሉት የጥምቀት ቀመር ማለትም "በኢየሱስ ስም" በመጠመቅ በተጨማሪም ጥምቀቱ ተጠማቂውን በጥልቅ ውሃ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ በማስመጥ ካልተካሄደ ግለሰቡ ድነት እንደማያገኝ እንዲሁም የመዳን ምልክቱ "በልሳን" መናገር እንደ ሆነ ያስረዳሉ። በድርጅቱ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ አንድ ሰው ድነት ማግኘት በፍጹም አይችልም የሚል ጠንካራ አቋም አለው።

ይህ መጽሐፍ፣ ይህ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አስተምህሮ ከብሉያትና ከሐዲሳት አስተምህሮ ጋር እንደማይጣጣም በስፋት ይሞግታል። ይህ የሃይማኖት ድርጅት ከላይ የተዘረዘሩትን የድነት ትምህርቶች ለማስተማር የሚጠቅሳቸውን ክፍሎች አንድ በአንድ እየነቀሰ በማውጣት፣ "በርግጥ እነዚህ ምንባባት የድርጅቱን አስተምህሮ ያጸናሉ?" የሚለውን ጉዳይ ይሞግታል።

በርካታ ሰዎች ይህን መሰል መጽሐፍ ማንበብ ድፍረት የሌላቸው ቢሆን፣ አንዳንዶች ደግሞ ርእሰ ጉዳዩ ራሱ ስሜት አይሰጣቸውም። ለዚህ እንደ ምክንያት ከሚያቀርቧቸው መኻል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- "ኢየሱስን መውደድ እንጂ አስተምህሮ/ዶክትሪን ሁነኛ ጉዳይ አይደለም"

- "ምግባር ከንድፈ ሐሳብ ስለሚበልጥ፣ አንድ ሰው ምን እንዳመነ ሳይሆን ምን ዐይነት ምግባር አለው የሚለው ጉዳይ ዋነኛ ጉዳይ ነው"
- "በሌሎች ሰዎች ዶክተሪን ላይ መፍረድ ትክክል አይደለም!"
- "እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ!"
- "መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ይህ ዐይነቱ ትምህርት አይገባውም፤ አልገባ ካለህ ጸልይ እንጂ አትፍረድ!"
- "በእንዲህ ዐይነቱ ርእስ ጉዳዮች አስተማሪ አያስፈልግም የእግዚአብሔር መንፈስ ራሱ ይገልጽልናል!"

ይህን መሰል ጥያቄዎች ቃለ እግዚአብሔን መሠረት ያደረገና በሥነ አመክንዮ የተደገፈ ሁነኛ መልስ ማግኘት አለባቸው የሚል ጽኑ እምነት አለን:: ስለዚህም የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ በቅጽ አንድ መጽሐፉ ላይ፣ ለእነዚህና እነዚህን መሰል ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊና አመክንዮአዊ መልስ የሰጠ ስለሆነ፣ እነዚህ ጥያቄዎች የእኔም ጥያቄዎች ናቸው የሚሉ ሰዎች፣ የቅጽ አንድን መጽሐፍ እንዲያነቡ ከልብ ይበረታታሉ::

ይህ መጽሐፍ ትኩረት የሚያደርገው በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የድነት አስተምህሮ ላይ ብቻ ነው:: ድርጅቱ በትምህርተ ሥላሴን ጨምሮ በተለያዩ ርእስ ጉዳዮች ላይ ያለው አስተምህሮ በቅጽ አንድ መጽሐፍ ላይ በስፋት ስለቀረበ በድርጅቱ አስተምህሮ ላይ ጥናት ማካሄድ የሚፈልጉ ሰዎች፣ ቅጽ አንድ መጽሐፍንም ቢያነቡ ስለድርጅቱ ታሪካዊና ነገረ መለኮታዊ መሠረት የተሟላ መረጃና ዕውቀት ሊኖራቸው እንደሚችል እምነታችን ነው::

አንባቢያን፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን" የድነት አስተምህሮ በጠለለ መንገድ ማወቅ እንዲችሉ፣ በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል ላይ የድርጅቱን አንቀጸ ሃይማኖትና የድርጅቱን ጽሑፎች በቀጥታ በመጥቀስ ያላንዳች ማብራሪያ አቅርበናቸዋል:: በአስተምህሮው ላይ ሒስ መሰንዘር የሚጀመረው የድርጅቱ መሠረተ እምነት በቀጥታ ከቀረበ በኋላ ነው:: በመጨረሻም የድርጅቱ ሰዎች ቆም ብለው አስተምህሮአቸውን እንዲመረምሩ ሊያግዙ ይችላሉ ያልናቸውን ጥያቄዎች አቅርበናል:: መልካም ንባብ::

# ማውጫ


መቅድም

I. ድነት በ"ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አስተምህሮ

መግቢያ

1. ሰው ሁሉ ኀጢአተኛ ነው……………………………………2
2. የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት ወሳኝ ጉዳይ ነው ………………3
3. የውሃ ጥምቀት በጥልቅ ውሃ ካልተካሄደ ሰዎችን አያድንም……10
4. የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ካልተካሄደ ሰዎችን አያድንም……………………………………11
5. በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቀ ሰው ድነት አያገኝም፤ ምልክቱም ልሳን መናገር ነው……………………………………13

- ማጠቃለያ……………………………………13

II. "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የድነት ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

መግቢያ……………………………………15

1. የውሃ ጥምቀት ለድነት (ለኀጢአት ሥርየት) አስፈላጊ ነውን?
   - ማርቆስ 16÷16……………………………………19
   - የሐዋርያት ሥራ 2÷38……………………………………25
   - የሐዋርያት ሥራ 22÷16……………………………………29
   - 1ጴጥሮስ 3÷21……………………………………33
2. የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ነውን?
   - ዮሐንስ 3÷5……………………………………37
   - ሮሜ 6÷3-4……………………………………43
   - ቲቶ 3+5……………………………………48
   - ገላትያ 3÷27……………………………………49

- ኤፌሶን 5፥25-26 ........................................ 51
- ዕብራውያን 10፥22 ........................................ 53
- ቈላስይስ 2፥12 ........................................ 54
- 1ቆሮንቶስ 12፥13 ........................................ 56

3. በማጠናከሪያነት የሚጠቀሱ ሌሎች ክፍሎች
- ዮሐንስ 19፥34 ........................................ 58
- ማቴዎስ 28፥19-20 ........................................ 64
- ሐዋርያት ሥራ 8፥35-38 ........................................ 66
- ሐዋርያት ሥራ 10፥48 ........................................ 68
- ዕብራውያን 9፥19-20 ........................................ 70
- 1ዮሐንስ 5፥6 ........................................ 73
- ሉቃስ 7፥30 ........................................ 76
- ማጠቃለያ ........................................ 76

4. የውሃ ጥምቀት ውጤታማ የሚሆነው በጥልቅ ውሃ ሲካሄድ ብቻ ነውን? ........................................ 79
5. የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ መካሄድ አለበትን? 80
6. ልሳን መናገር የድነት ምልክት ነውን? ........................................ 93

III. *ቃለ እግዚአብሔር ስለ ድነት ምን ያስተምራል?* ........................................ 93
IV. *ጥያቄ ለሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማንያን* ........................................ 107
V. *ዐሥራ ሰባት ዓመት "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ባሪያ ነበርሁ—የመጋቢ ንጉሤ ኀይሌ የሕይወት ምስክርነት* ........................................ 119
VI. *ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography)* ........................................ 139


# ውሃውና ስሙ

## "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የድነት አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

### መግቢያ

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍት፣ መምህራንና አማንያን የሰው ልጅ ሁሉ በኀጢአት እንደ ወደቀ፤ ኀጢአት ባስከተለውም መዘዝ መንፈሳዊ ሞት እንደ ሞተ፤ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን የድነት መስፈርት አሟልቶ ራሱን ለማዳንም ሆነ ራሱን ለድነት ማዘጋጀት ፈጽሞ እንደማይችል ያስረዳሉ። እንዲሁም ጽድቅ በእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው ልጆች ኀጢአት የትኪ ሞት በመሞት ባስገኘው በኢየሱስ በማመን ብቻ እንደሚገኝ ያስገነዝባሉ። እንዲሁም ድነትን ለማግኘት ዳግም መወለድ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ይገልጻሉ። ይህ አቋማቸው ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነት ጋር የሚያመሳስላቸው ቢሆንም፣ ዳግም ልደት የሚገኘው የሚከተሉት አራት ቅድመ ሁኔዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፤ ይኸውም (1) እምነት፣ (2) ንስሓ፣ (3) የውሃ ጥምቀት፣ (4) በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የሚለው አስተምህሮአቸው ግን (በተለይ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ) ከቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ጋር ፍጹም የማይገጥም ነው።

እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ እምነት ሲባል እንዲያው ሥጋዊ የሆነ ዕውቀት ብቻ ሳይሆን፣ ምግባራዊ መስጠትንና መታመንን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ከተለወጠ ሕይወት ውስጥ የሚገኝ ፍሬ ነው፤ እንዲሁም ንስሓ ከኀጢአት ወደ ጽድቅ ሙሉ ለሙሉ መመለስ ነው ከሚለው የድርጅቱ አስተምህሮ ጋር የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚስማሙ ቢሆንም፣ 1) የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት ወሳኝ ጉዳይ ነው፤ 2) የውሃ ጥምቀት ኀጢአትን ያጥባል፤ 3) የውሃ ጥምቀት የታለመለትን ዐላማ (ማለትም ዳግም ልደት ማስገኘትንና ኀጢአትን ማጠብ) ከዳር ማድረስ የሚችለው፣ በጥልቅ ውሃ ማጥመቅ ሲቻል ብቻ ነው፤ እንዲሁም 4) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ሲሆን፣ አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቁ ሁነኛ ምልክት "በልሳን

መናገር” ነው የሚለው አስተምህሮአቸው ግን ከብሉያትና ከሐዲሳት ትምህርት ጋር አለመጣጣሙ ወይም ባይተዋር መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ዐበይት ከሚባሉትም ክርቲያናዊ አስተምህሮዎች ጋር በእጅጉ የሚጣረስ/የሚቃረን ነው።

ቅድሚያ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን የድነት አስተምህሮ የድርጅቱን ጽሑፎች በዋቢነት በማቅረብ በርእስ ጕዳዩ ላይ የሚሰጡትን ማብራሪያ ከተመለከትን በኋላ፣ ይህ ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ምን ያህል ይጣጣማል የሚለውን ጕዳይ በጥልቀት ለመፈተሽ እንሞክራለን። በመቀጠልም መጽሐፍ ቅዱስ ድነትን አስመልክቶ የሚያስተምረውን ትምህርት፣ የድርጅቱን የድነት አስተምህሮ ማረቅ/ማስተካከል በሚያስችል መልኩ ከቃኘን በኋላ፣ የድርጅቱን የአስተምህሮ ስሕተት አጕልተው የሚያሳዩ እንዲሁም ግራና ቀኙን ሳያገናዝቡ በየዋህነት የድርጅቱን መሠረተ እምነት የተቀበሉ ሰዎች ቆም ብለው አስተምህሮውን እንዲመረምሩ ሊረዷቸው የሚችሏቸውን ቍልፍ ጥያቄዎች እናቀርባለን።

# I. ድነት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ

## 1. ሰው ሁሉ ኀጢአተኛ ነው

“የመጀመሪያው ሰው ኀጢአትን የማያውቅ፣ ቅዱስ፣ ሙሉ፣ ፍጹም ሆኖ በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩንና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በንጹሕ ሲመላለስ መኖሩን እናምናለን (ዘፍጥረት 1፥27፤ 2፥7-8)። በኋላ ግን ሰው በገዛ ምኞቱ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ እንደ ወደቀ፣ ወደ ምድርም ፍዳ ከኀጢአት ጋር እንደ ተጣለ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ዘፍጥረት 2፥16-17፤ 3፥1-24)። ኀጢአትም ለሰው ሁሉ ተረፈ (ሮሜ 5፥12-21)”[2]።

---

[2] *የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች፣* አንቀጽ 5። እንዲሁም የሚከተሉትን የድርጅቱን መጻሕፍት ይመልከቱ (ሁሉም መጻሕፍት የተጻፉት በተክለ ማርያም ገዛኸኝ ነው)፦ *በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፊልጶ፣* ገጽ 12፣ 51-53፤ *ለድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አዲስ ልደት፣* ገጽ 12-15። *Bible Writers' Theology,* 103-106.



## 2. የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት ወሳኝ ጕዳይ ነው

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት ወሳኝ ነው ለሚለው ትምህርታቸው የሚያቀርቡት ማስረጃ የሚከተለው ነው።

“‘ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?’ ብሎ የፊልጵስዩስ ወኅኒ ቤት ዘበኛ ጳውሎስንና ሲላስን በጠየቀ ጊዜ፣ ‘በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ’ አላሉትምን? ሐሥ 16፥30። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ስለ ጥምቀት መቼ ተጠቀሰ? በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነንስ ሳንጠመቅ ብንቀር ልንድን እንችል የለም ወይ የሚሉ ተከራካሪዎች ጥቂቶች አይደሉም። የዚህ ጥያቄ መልስ በቍጥር 33-34 ላይ ይገኛል። እምነቱ ብቻ ሊያድነው እንደማይችል ስለሚያውቁ፣ በዚያች ሌሊት ጳውሎስና ሲላስ ይህንን ሰው ከነቤተሰቡ እንዳጠመቁት እናያለን”[3]።

“እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ስለመሰሉት ጥያቄዎች ግልጽ የሆነ መልስ ሲሰጥ፣ “ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም” ያላል ዮሐንስ 3፥5፤ ቲቶ 3፥5”[4]።

---

[3] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፣ *ለድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አዲስ ልደት፣* አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ገጽ 29። የዚህ ምዕራፍ ሐሳብ በአብዛኛው የተወሰደው ከዚህ መጽሐፍ ቢሆንም፣ ተመሳሳይ ሐሳቦችን ለማርጌ ማስታወሻ 2 ላይ የተዘረዘሩትን የድርጅቱን መጽሐፍ መመልከት ይቻላል። ምንም እንኳ ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ የድርጅቱን የእምነት አንቀጾች ጨምሮ ከ15 ያላነሱ መጻሕፍትን ቢጽፉም (በድርጅቱ የታተሙት በራሪ ጽሑፎች ራሳቸው፣ በአብዛኛው በቀጥታ የተወሰዱት ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ መጻሕፍት ላይ ነው። ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ የጻፉአቸውን መጻሕፍት ዝርዝር በዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር ይመለከቷል)፣ በጽሑፎቻቸው ውስጥ ሁሉ ግን የተደጋገሙ ሐሳቦችን መመልከት የተለመደ ነው። ምናልባትም “እነዚህን መጻሕፍት በሙሉ በአንድ መለስተኛ መጽሐፍ አጠቃሎ ማቅረብ ይቻላል” ቢባል፣ እብለትም ሆነ ግነት አይሆንም።

[4] ዝኒ ከማሁ፣ 30።

"ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን (ሊጠመቅ አይችልምና) ይፈረድበታል:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጥምቀት የማዳን ሥራ ሲመሰክር፣ ነገር ግን የመድኀኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን 1) ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና (በስሙ ጥምቀት)፣ 2) በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም" ይላል ቲቶ 3÷4-5"[5]::

"የመድኀኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነት ክርስቶስን (ሕይወትን) ሰጠን:: ክርስቶስ በመስቀል በመሞቱ ምክንያት ከጐኑ ውሃና ደም ፈስቀልን ዮሐንስ 19÷34:: ክርስቶስ በውሃው፣ በደሙና በመንፈሱ ሊያድነን መጣ 1ዮሐንስ 5÷6-8፣ ሕዝቅኤል 36÷25-27:: በአሪት ዘመን ሙሴ ከበግ ወይም ከፍየል የወጣውን ደም ለእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት ከተጠበቀው ውሃ ጋር በሂሶጵ በማደባለቅ በሕዝቡና በመጽሐፉ ላይ ይረጨው ነበር ዕብራውያን 9÷19-20:: ሙሴ ሲረጨው የነበረው የኪዳን ውሃና ደም ከክርስቶስ ጐን ስተገኘው ውሃና ደም ጥላ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ 'ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውሃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም ነበር፤ ይህም ውሃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል፤ የሰውነትን ዕድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጐ ኅሊና ልመና ነው እንጂ፤ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው' ይላል 1ጴጥሮስ 3÷20-21:: የቤተ ክርስቲያን መክፈቻዎች የተሰጠው ሐዋርያው ጴጥሮስ ጥምቀት በእምነት ስንቀበላት እንደምታድነን ሲመሰክር እኛ እንዴት ጥምቀት አታድንም ልንል እንደፍራለን?"[6]::

"ደሙና ውሃው ከጐኑ ሲወጡ በአንድነት እንጂ ተስያይተው ስላልወጡ በማዳን ሥራቸውም አይስያዩም 1ዮሐንስ 5÷6-7"[7]::

[5]ዝኒ ከማሁ፣ 30:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

[6] ዝኒ ከማሁ፣ 30-31:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

[7] ዝኒ ከማሁ፣ 76::



"ሙሴ የኩርማዎችንና የፍየሎችን ደም ከውሃ ጋር ቀላቅሎ ሲረጭ እንደ ነበር ሁሉ፣ ክርስቶስም የራሱን ደምና ውሃ በአንድ ላይ ከጐኑ በማመንጨት የመዳንን በር ከፍቶአል 1ዮሐንስ 5÷6-7፤ ዮሐንስ 19÷34"[8]::

"የአንዳንድ ሰዎች ጥያቄ 'ስወደደን ከኀጢአታችንም በደሙ ሳጠበን' ተብሎ ተጽፎአልና ደሙ ብቻ ነው የሚያጥበን፤ ውሃውም ሆነ በስሙ መጠመቅ ስኀጢአት ሥርየት እንዴት በአንድ ላይ ይሠራሉ? የሚል ነው፤ ይህን ዐይነት ጥያቄ የሚጠይቁ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል በሙላት የሌለባቸው ናቸው:: ቃሉ ግን ደሙ፣ ውሃው፣ ስሙና መንፈሱ ለማዳን በአንድ ላይ እንደሚጠሩ ይገልጻል ቲቶ 3÷4-5፤ ዮሐንስ 3÷5፤ ሐዋርያት ሥራ 3÷5፤ 2÷21:38፤ ዕብራውያን 10÷19-22፤ 1ዮሐንስ 5÷6-8:12"[9]::

"በዚህ በፍጻሜ ዘመን ያለው ትውልድ ደግሞ የዘላለም ሕይወት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በውሃ ተጠምቆ እንዳይድን አሻፈረኝ! የውሃ ጥምቀት አያድንም! በማለት የገዛ ራሱን ፍልስፍና ተከትሉ በመፋንን የእግዚአብሔርን መንገድ እንደ ሳተ የታመነ ነው:: በመስቀል ላይ የፈሰሰውን ውሃና ደም በስሙ አማካይነት በጥልቅ ውሃ ውስጥ በመጠመቅ እንድንቀበለው አዘዘን"[10]::

"መጽሐፍ ቅዱስ፣ 'ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል' ማርቆስ 16÷16:: እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ሰው ሁሉ ንስሓ እየገባ ለኀጢአት ሥርየት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጠመቅ ይድን ዘንድ ይገባዋል:: የሐዋርያት ሥራ 2÷38 የተሰበከለትን የመዳን ወንጌል ሰምቶ በእምነት የማይቀበል፤ አምኖም ተጸጽቶ ኀጢአቱን በመተው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቆ ከኀጢአቱ የማይታጠብና በመንፈስ ቅዱስ የማይታደስ ሰው ሁሉ፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት

[8] ዝኒ ከማሁ፣ 78::

[9] ዝኒ ከማሁ፣ 79::

[10] ዝኒ ከማሁ፣ 32::

የሰውም ዮሐንስ 3÷5፤ ቲቶ 3÷5፤ ሕዝቅኤል 44÷9"[11]:: "የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምሕረት በውሃ መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ እንጂ በሌላ ዘዴ እንደማንወርሰው በቲቶ 3÷4-5 ተገልጾአል:: በቸልተኝነትና በሰው ሠራሽ የመዳን መንገድ ተታልላችሁ እውነት በሚመስል የሞት መንገድ የምትጓዙ ሰዎች ትኖሩ ይሆን? ምሳሌ 16÷25:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ 'አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኀጢአትህም ታጠብ' እያለ ይጠራችኋል የሐዋርያት ሥራ 22÷16:: በገላትያ 3÷27 'በጥምቀት ክርስቶስን ለበሳችሁ ይላል'"[12]:: "በሮሜ '6÷3 ወይስ አታውቁምን? እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቅን በሞቱ እንደ ተጠመቅን' ይላል:: እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ባጭሩ ያለጥምቀት ድነት እንደማይገኝ ያስረዳሉ"[13]::

"እምነት፣ ንስሓ፣ ጥምቀት፣ መንፈስ ቅዱስ እነኝህ አራቱ ለድነታችን የተሰጡን የመዳን መንገዶች ስለሆኑ፣ በአንድነት በመውሰድ የምንድንባቸው እንጂ ለያይተን የምንድንባቸው ኀይሎች አይደሉም:: እንደ ሰው አስተያየት ገንጣጥለን ብንጠቀምባቸው የእግዚአብሔርን ፕላን የምናፈርስ መሆናችን ግልጽ ነው"[14]::

"በኦሪት ዘፀአት 30÷20-21፣ 'እንዳይሞቱ ይታጠቡበታል' ይላል:: ሊታጠቡበት የተፈቀደው የውሃ ዐይነትም በዘኍልቍ 19÷9 ተገልጦአል፤ ቃሉም እንዲህ ይላል፣ 'ርኩሰትን የሚያነጻ ውሃ ለእስራኤል ልጆች ማኅበር ይጠበቃል፤ ከኀጢአት ለማንጻት የሚሆን ነው' ይላል:: ለእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት በተለየ እንስራ የተጠበቀው ውሃ ኀጢአታቸውን ሊያስተሰርይ ከቻለ እንዴት ይልቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በጥምቀት የምንታጠብበት ውሃ ኀጢአታችንን ሊያስወግድ አይችልም? ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጐን የፈሰቀውስ ውሃና ደም

---

[11] ዝኒ ከማሁ፤ 33-34::
[12] ዝኒ ከማሁ፤ 34-35::
[13] ዝኒ ከማሁ፤ 36::
[14] ዝኒ ከማሁ፤ 37::



በጥምቀት በኢየሱስ ስም የምንጠመቅበትና የምንነጻበት ኀይል አይደለምን?"[15]::

"በብሉይ ኪዳን ዘመን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገፈ.ተው የመቅደስ አገልግሎት ተካፋዮች ሊሆኑ የሚመረጡ ሁሉ የልብና የሥጋ ግርዘት ከሁሉ በፊት ያስፈልጋቸው እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል:: ቃሉም፣ 'ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በእስራኤል ልጆች መካከል ካሉት ሁሉ በልቡና በሥጋው ያልተገረዘ እንግዳ ሁሉ ወደ መቅደሴ አይግባ' የሚል ነበር ሕዝቅኤል 44÷9:: የልብና የሥጋ ግርዘት ማለት ምን ማለት ነው? የልብ ግርዘት ማለት በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ማለት ሲሆን፣ የሥጋ ግርዘት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጠመቅ አሮጌው አዳም ተወግዶ ክርስቶስን የመልበስ ምሳሌ ነው ቲቶ 3÷5፤ ቈላ. 2÷11-13፤ 2ቆሮ. 5÷17፤ 1ቆሮ. 15÷45-50፤ ገላ. 3÷27"[16]::

"ከምድረ ግብፅ የወጡት እስራኤላውያን የኤርትራን ባሕር እስኪያልፉ ድረስ ፈርዖንና ተከታዮቹ አልለቀቁአቸውም ነበር:: እስራኤላውያን ወደ ፊት በመገሥገሥ ከፈርዖንና ከሠራዊቱ ለማምለጥ ያደረጉት ሙከራ ፍርሓትንና ጭንቀትን አበዛባቸው እንጂ ምንም ሊረዳቸው አልቻለም ነበር:: ነገር ግን በኤርትራ ባሕር ውስጥ በማለፍ በእግዚአብሔር ኀይል ፈርዖንንና ተከታዮቹን ካስጠሙአቸው በኋላ የፈርዖን አስፈሪነትና ጭቆና ዳግመኛ ሊከተላቸውና ሊያስፈራቸው አልቻለም 1ቆሮንቶስ 10÷1-3፤ ዘፀአት 14÷15 ተመልከት"[17]::

በብሉይ ኪዳን የጥምቀት "ምሳሌ ሆኖ የቆየው የዮርዳኖስ ወንዝ ነበር፤ በዕብራይስጥ ቋንቋ ዮርዳኖስ፣ 'ያራዳህ' ማለት፣ ወደ ታች መግባት ወይም መውረድ ማለት ነው:: ወንዝ ማለት ደግሞ ውሃ ማለት ስለሆነ የዮርዳኖስ ወንዝ ማለት ወደ ውሃ ውስጥ መግባት ማለት ነው:: ጥምቀት የተባለው ቃል በግሪክ ቋንቋ፣ 'ባፕቲዞ' መጥለቅ ወይም ወደ ውሃ ውስጥ መግባት ወይም በውሃ ውስጥ መነከር ከሚለው ቃል የተገኘ

---

[15] ዝኒ ከማሁ፤ 45::
[16] ዝኒ ከማሁ፤ 45-46::
[17] ዝኒ ከማሁ፤ 46::

ነው:: እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ወንዝ እንዴት እንደ ተጠቀመበት ከ2ነገሥት 5÷1-14 እንመልከት”[18]::

“ንዕማን የተባለው የሶሪያ ንጉሥ የሠራዊቱ አለቃ በጌታው ዘንድ ታላቅ ክቡር ሰው ነበር፤ ደግሞም ጽኑ ኀያል ነበር፤ ነገር ግን ለምጻም ነበረ:: የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች (እንባቢዎች) እንደሚያውቁት ሁሉ፣ ለምጽ የተወቀ የኀጢአት ምሳሌ ነው:: በለምጽ በሽታ የተወረበው ንዕማን በዮርዳኖስ ወንዝ ብቅ ጥልቅ ቢል ከለምጹ ታጥቦ እንደሚነጻ ወይም ከለምጹ እንደሚድን የእግዚአብሔር ሰው ስለነገረው በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ከለምጹ ሊነጻ ችሉአል”[19]::

“በብሉይ ኪዳን እንደምናገኘው ግርዘት ለአብርሃምና ለዘሩ ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነው:: እግዚአብሔርም፣ ‘የቍልፈቱን ሥጋ ያልተገረዘ ቈላፋ ሰው ሁሉ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ፤ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና’ አለ ዘፍጥረት 17÷1-14:: ስለዚህ እግዚአብሔር የአብርሃም ልጆች እንዲገረዙ አዘዛቸው፤ ካልተገረዙም የእርሱ ወገኖች እንዳልሆኑ አስታወቀ”[20]::

“እኛም በመንፈስ የአብርሃም ዘሮች ነን:: ይህንን የግርዘት ቃል ኪዳን እንዴት ልንቀበለው ይገባል? ሐዋርያው ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች በግልጽ እንደ ተናገረው፣ የአዲስ ኪዳን መንፈሳዊ ግርዘት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ነው ቈላ 2÷11-13...በቅዱስ ቃሉ እንደምናየው ሁሉ መንፈሳዊ ግርዘት (ማለት በኢየሱስ ስም ጥምቀት) ያልተቀበለች ነፍስ ሁሉ፣ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ፤ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና የሚል ነው:: ይህንን የግርዘት ትእዛዝ የሰጠው እግዚአብሔር እንጂ፣ ኢያሱ ወይም አብርሃም አልነበረም ዘፍ. 17÷1-14:: በቅድሚያ እንደ ተገለጠው ሁሉ ይህ የግርዘት ሥርዐት የተፈጸመው የዮርዳኖስን ወንዝ ከተሻገሩ በኋላ እንጂ በፊት አልነበረም ኢያሱ 3÷4-5 ተመልከት:: በአዲስ ኪዳን ዘመንም ሰው ሁሉ መንፈሳዊውን የዮርዳኖስ ወንዝ (በኢየሱስ ክርስቶስ

[18] ዝኒ ከማሁ፤ 50-51::

[19] ዝኒ ከማሁ፡ 51:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

[20] ዝኒ ከማሁ፤ 53-54::



ስም ተጠምቆ) ካልተሻገረ እግዚአብሔር ከማንኛውም ሰው ጋር የግርዘትን ቃል ኪዳን አይገባም”[21]::

“ከነዓን የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ እንደ ሆነች ከእግዚአብሔር ቃል ተምረናል:: የእስራኤላውያን በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ማለፍ በአዲስ ኪዳን ጥምቀት በኩል ወደ ሰያማዊት ኢየሩሳሌም (ከነዓን) የምንገባበት ምሳሌ ነበር:: እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ሳይረግጡ ድልድይ ሠርተው እንዲያልፉ አልተነገራቸውም:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ፕላን እጅግ ታላቅ ስለነበር ዮርዳኖስን ከፍሎ በውስጡ አሻገራቸው ኢያሱ 2÷5፤ ዘፀአት 14÷15-31 ተመልከት”[22]::

“በክርስቶስ ትምህርትና በሐዋርያት እንዲሁም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይህ ለኀጢአት ሥርየት በውሃ ውስጥ የማለፍ አስፈላጊነት በሚገባ የተገለጠ ስለሆነ፣ ማንም ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በጥልቅ ውሃ ለኀጢአቱ ሥርየት የመጠመቅን ሥርዐት ካልፈጸመ ወደ ሰማያዊት ከነዓን ሊገባ እንደማይችል መገንዘብ ይኖርበታል ዮሐንስ 3÷5”[23]::

“እጅግ ብዙ ሰዎች ከክርስቶስ ኢየሱስ ጐን ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ በእምነት ከጸነ እኛም ያለ ጥምቀት መዳን እንችላለን! የሚል ክርክር ለቤተ ክርስቲያን ያቀርባሉ:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ስለዚህ ክርክር የምትመልሰው መልስ፣ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ከበዓለ ኀምሳ ቀን በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት አልነበረም የሚል ነው:: ከበዓለ ኀምሳ ቀን በፊት ክርስቶስ፣ ‘ኀጢአትህ ተሰረየችልህ’ እያለ ይፈውስ ነበር:: ከበዓለ ኀምሳ ቀን ወዲህ ያለው ሕዝብ ሁሉ ግን ያለ ውሃ ጥምቀት አይድንም:: ከበዓለ ኀምሳ ቀን በፊት የነበረው የሃይማኖት ሥርዐት የኦሪትና የመጥምቁ ዮሐንስ ሥርዐት ስለነበር ቤተ ክርስቲያን ለምትመሠረትበት እውነተኛው የመዳን መንገድ ጥላ እንጂ በራሱ ፍጹምነት አልነበረውም”[24]::

[21] ዝኒ ከማሁ፤ 54-55:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

[22] ዝኒ ከማሁ፤ 55:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

[23] ዝኒ ከማሁ፤ 55-56::

[24] ዝኒ ከማሁ፤ 90-91::

"ከኢየሱስ ጋር ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ ያለ ጥምቀት ለምን ዳነ? የሚሉ ብዙ ናቸው:: ወንበዴውማ የዳነው የአዲስ ኪዳን ጥምቀት (ማለትም ከኢየሱስ ጐን በፈሰሰው ውሃና ደም በስሙ ለኀጢአት ሥርየት መጠመቅ) ከመጀመሩ በፊት በነበረው የንስሓ (የመንጻት) ሥርዐት ነው:: ጌታ ኢየሱስ፣ 'ኀጢአትህ ተሠረየችልህ'፣ 'ኀጢአትሽ ተሠረየችልሽ' እያለ ከኀጢአት ሲፈታቸው የነበረው ከመሞቱ በፊት ነበር:: ሞቶ ከተነሣ በኋላ ግን ሰው ከውሃና ከመንፈስ እንዲወለድ በደነገገው ሥርዐት እንጂ በቀደመው የመንጻት ሥርዐት መዳን አልተቻለም:: ስለዚህ ነው ብዙዎች የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እንደ ገና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተጠመቁት ሐዋርያት ሥራ 19÷1-6"[25]::

"እንግዲህ የወንጌል መልእክተኞች ሁሉ ስለ ስሙ፣ ስለ ደሙ፣ ስለ ውሃውና ስለመንፈሱ የማዳን አገልግሎት የተምታታ መልእክት በመስጠት ሕዝብን እንዳያወናብዱ ስብከት ከመጀመራቸው በፊት በእነዚህ የመዳን ጸጋዎች የሃይማኖታችን መሥራቾች የሆኑት ሐዋርያት እንዴት እንደ ተጠቀሙባቸው ከቃሉ መረዳት ይኖርባቸዋል ኤፌሶን 2÷20"[26]::

"የውሃ ጥምቀት እጅግ ተፈላጊ የሆነበት ዋናው ምክንያት ያለ ውሃ ጥምቀት ሰው ዳግም ተወልዶአል፣ ክርስቲያን ነው ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ነው ሊባል ስለማይችል ነው:: የቤተ ክርስቲያን አካልም ሊሆን አይችልም:: ያልተጠመቀ ሰው ሁሉ አረማዊ የሚባል ስም ይሰጠዋል"[27]::

## 3. የውሃ ጥምቀት በጥልቅ ውሃ ካልተካሄደ ሰዎችን አያድንም

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን የውሃ ጥምቀት በጥልቅ ውሃ ካልተካሄደ ሰዎችን አያድንም ለሚለው ትምህርታቸው የሚያቀርቡት ማስረጃ የሚከተለውን ይመስላል::

[25] *ጥምቀት ያድናል!* (በራሪ ጽሑፍ) በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

[26] እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?፡ 79::

[27] ዝኒ ከማሁ፡ 224::



"የውሃው ጥልቅ መሆን ለምን ይጠቅማል? ሰው ሁሉ ሰውነቱ የኀጢአት ለምጽ ስላለበት ሙሉ ሰውነቱን በሚያነጻ ውሃ መታጠብ ስለሚገባው ነው ዘኊልቊ 19÷9፤ ቈላስይስ 2÷11-12፤ ሐዋርያት ሥራ 8÷35-39፤ 22÷16፤ ሮሜ 6÷3-4፤ ዮሐንስ 3÷23፤ ማቴዎስ 3÷16"[28]:: "ልንገነዘበው የሚገባን ዋናው ነገር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስኀጢአት ሥርየት በጥልቅ ውሃ ውስጥ ስንጠመቅ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር መቀበራችንን ነው ሮሜ 6÷3-4:: ይህም በመስቀል ላይ በሞተልን ጊዜ በአፈሰሰልን ውሃና ደም ውስጥ በማለፍ ዘላለማዊውን የሞት ዕዳ ቀብረን በአዲስ ሕይወት ለመኖር አዲሱን አዳም ክርስቶስን መልበሳችንን ያስረዳል ዕብራውያን 6÷3-4፤ ሮሜ 6÷3-4"[29]::

## 4. የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ካልተካሄደ ሰዎችን አያድንም

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ካልተካሄደ ሰዎችን አያድንም ለሚለው ትምህርቱ የሚያቀርበው ማስረጃ የሚከተለው ነው::

"በማቴዎስ 28÷19 የተነገረው ቃል በነጠላ ቍጥር የተነገረ ስም ስለሆነ አንድን አምላክ ያመለክታል እንጂ ስለ ሦስት አይናገርም:: ሐዋርያትም በማስተዋል እንደ ተቀበሉትና እንደ ሠሩበት ከጥምቀት ሥርዐታቸው እንገነዘባለን"[30]:: "በማቴዎስ 28÷19 እንደ ተጻፈው አብ ማለት ስም አይደለም፤ ለአብ የመጠሪያ ስም ሊኖረው ይገባል:: ይኸውም የመጠሪያ ስሙ ኢየሱስ እንደ ሆነ ራእይ 3÷12፤ ዮሐንስ 5÷43፡ 17÷6:12፤ ማቴዎስ 1÷20-23፤ ዮሐንስ 14÷8-10 እንዲሁም ኢሳይያስ 9÷6 ይገልጻል:: ወልድ ማለት ደግሞ ስም አይደለም፡ የወልድም መጠሪያ ስሙ ኢየሱስ ነው:: ወልድ (ልጅ) ተብሎ ሊጠራና ሊቀደስ ስለማይገባው የግድ ስም ሊኖረው ይገባል:: እግዚአብሔር በሥጋ ከመገለጡ ወይም ከድንግል

[28] ዝኒ ከማሁ፡ 127::

[29] ዝኒ ከማሁ፡ 82::

[30] ዝኒ ከማሁ፡ 116::

ማርያም ከመወለዱ በፊት ሰዎችን ሊያድንበት ዐቅዶ በሰማያት ሰውሮ ያስቀመጠው የመለኮት (የአብ) ስም ኢየሱስ ነው:: መንፈስ ቅዱስም ከእግዚአብሔር ወይም ከኢየሱስ የሚፈስ የእግዚአብሔር ኀይል ነው:: ከቅዱስ አምላክ ስለሚወጣ መንፈስ ቅዱስ ይባላል፤ የመጠሪያ ስሙ ግን ኢየሱስ እንደ ሆነ በማቴዎስ 1÷20-21 እና 2ቆሮንቶስ 3÷17 ተገልጾአል . . . ኢየሱስ በሥጋ ሲወለድ ወልደ መንፈስ ቅዱስ አልተባለም፤ ነገር ግን ባባቱ ስም ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ፣ ጌታ መንፈስ ነውና ዮሐንስ 5÷43 ተመልከት"[31]:: "አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ እነዚህ ሦስት የእግዚአብሔር የክብር ስሞች የመጠሪያ ስሞቹ ቢሆኑ ኑሮ፣ ስም ተብሎ በነጠላ ቍጥር ከመጻፍ ይልቅ ስሞች ተብለው ሊጻፉ ይገባ ነበር:: ስም ተብሎ ስለተጻፈ ነጠላነትን ስለሚያሳይ ሐዋርያት ሳይሳሳቱ በዚህ በሦስት የክብር ስም የተጠራ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ በመንፈስ ቅዱስ ተረድተው ኀጢአትን በሚያስተሠርይ በአምላካችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጥምቀዋል:: እኛም በዚህ ስም እንድንጠመቅና እንድናጠምቅም በጥብቅ አዘዋል ኤፌሶን 4÷5፤ ቈላስይስ 3÷17፣ ገላትያ 1÷8-9 3÷27፤ ሐዋርያት ሥራ 2÷38-42 ተመልከት"[32]::

"ሐዋርያት ሥራ 2÷38 አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እየተባለ የሚጠራው ያው ራሱ አንድ አምላክ ሲሆን፣ ለሰው ልጆች በሦስት አገላለጽ መገለጹን ያሳያል:: ውሃ ሲረጋ በረዶ እንደሚሆን ሲፈላም እንፋሎት እንደሚሆን ዐይነት አባታችን እግዚአብሔር በረቂቅነትና በሚዳሰስ አካል ተገለጸ እንጂ አምላካችን አንድ የማዳን ስሙም አንድ ነው"[33]:: "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቀ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለማይገኝ፣ ሐዋርያትም ስላላጠመቁበትና አብና መንፈስ ቅዱስም ስለማይሞቱና ስለማይቀበሩ፣ ጥምቀት ደግሞ የሞትና የመቀበር ምሳሌ ስለሆነ፣ እኛም ሞቶ ከተነሣው ከክርስቶስ ጋር በንስሓ ሞተን፣ አሮጌውን ሰዋችን ከነዕዳ ጽሕፈቱ በኢየሱስ ስም ለማስገፈፍ በስሙ ጥምቀት ከእርሱ ጋር በእምነት ተቀበርን"[34]::

[31] ዝኒ ከማሁ፤ 117:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

[32] ዝኒ ከማሁ፤ 118::

[33] ዝኒ ከማሁ፤ 122::

[34] *የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች፤ አንቀጽ* 8::



## 5. በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቀ ሰው ድነት አያገኝም፤ ምልክቱም ልሳን መናገር ነው

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቀ ሰው ድነት አያገኝም፤ አንድ ሰው ድነት የማግኘቱ ምልክት በልሳን መናገሩ ነው ለሚለው ትምህርት የሚያቀርቡት ማስረጃ የሚከተለው ነው::

"የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምልክቱ የሕይወት ተሐድሶ ማግኘትና በልሳን ወይም በአዲስ ቋንቋ መናገር ነው:: መንፈስ ቅዱስ ሕይወትን የሚለውጥ ወይም የሚያድስ ጸጋ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ሕይወታችንን ማለትም መንፈሳችንን ስለሚያድነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በውሃ ቢጠመቅም በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቀ ሰው ሙሉ ደኅንነት አያገኝም ብለን እናምናለን ቲቶ 3÷4-8፤ ዮሐንስ 3÷5-6 ተመልከት"[35]:: "የመንፈስ ቅዱስና የውሃ ጥምቀቶች ለዳግም ልደታችን አስፈላጊዎች እንደ ሆኑ አጥብቀን ስለምናምን ማንኛውም ምዕመን ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ከተወለደ ከዘላለም ሞት ዕዳ መዳኑን እናረጋግጣለን ዮሐንስ 3÷1-6፤ ቲቶ 3÷4-8፤ ሐዋርያት ሥራ 8÷12-17፤ 19÷1-6፤ ሕዝቅኤል 36÷25-37"[36]::

## ማጠቃለያ

"ሰው ያለ ንስሓ ያለ ጥምቀትና ያለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት እንዴት ለመዳን ይችላል? ሐዋርያው ጴጥሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰበከላቸው ሦስት ሺህ ሰዎች በእጅ ማውጣትና በአፍ ምስክርነት አልዳኑም፤ በማቈላመጥና በማባበልም ወንጌል አልተሰበከላቸውም:: መጽሐፍ ቅዱስም ስለእነርሱ የመዳን ሁኔታ እንዲህ ብሎ ይመሰክራል፣ 'ቃሉን በሰሙ ጊዜ ልባቸው ታወከ፤ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት ወንድሞች ሆይ (አንድን ዘንድ) ምን እናድርግ?" አሏቸው'[37]::

[35] ዝኒ ከማሁ፤ አንቀጽ 9::

[36] ዝኒ ከማሁ፤ አንቀጽ 9::

[37] አድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?፤ 72:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

ቄስ ተከስ ማርያም ገዛኸኝ በኢየሱስ ስም በጥልቅ ውሃ መጠመቅ ለድነት ("ክርስቶስን ስመልበስ") ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ኢየሱስ ራሱ በአካለ ሥጋ ተገልጦ ያስረዳቸው ትምህረት መሆኑን በአንክሮ ያስገነዝባሉ:—

> በፖስታ ቤት በኩል በተላከልኝ ጽሑፍ ላይ፣ በኢየሱስ ስም ጥምቀት የሰው ሥርዐት ወይስ መለኮታዊ መልእከት...የሚለውን ርእስ ስመለከት አንብቤ ፊቴን አቅንቼ ወደ ፊት ስመለከት፣ ክርስቶስ ፊቴ ቆሞ ሰውነቴን በዚፕ የተዘጋ ልብስ እንደሚከፈት ከፍቶ ሰውነቴን ወደ ውስጡ አስገባና ራሴን በክርስቶስ ሰውነት ውስጥ ገብቼ አየሁት:: ራእዩ አብቅቶ ወደ ራሴ ስመለስ ከመደንገጤ ብዛት የተነሣ መንቀጥቀጥ ያዘኝ፤ የራእዩን ትርጉም ለማወቅ ፈልጌ ኢየሱስን ለመጠየቅ በፊቱ ተደፋሁ:: እርሱም:—"ያየኸው ራእይ ትርጉሙ በስሜ በጥልቅ ውሃ ውስጥ ገብቶ በመጠመቅ ያልለበስኝ ሁሉ ራቁቱን እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው" አለኝ:: ከዚያም "እነዚህን ጥቅሶች ተመልከትና ስጻግም ልደት በስሜ ተጠምቀህ ልበሰኝ" አለኝ:: ጥቅሶቹም እንደ ፊልም በአእምሮዬ ይታዩኝ ጀመሩ:— ዮሐ. 1÷12-13፤ 3÷3-6፤ ሐዋ. 2÷38፤ ቈላ. 2÷11-14፤ ሮሜ 6÷3-6፤ 8÷1:29-30፤ 2ቆሮ. 5÷1-5፤ ገላ. 3÷27:: ምስጢሩ ስለገባኝ እየተቁነጠነጥሁ ለባለቤቴ በስሜት መሰከርሁላት፤ እርሷ ግን ተቃወመችኝ፤ ነገር ግን ኢየሱስ ሊገልጥላት ስለፈቀደ፣ በጣም ታምማ በዐልጋዋ ላይ እያለች ከሥቃይዋ የተነሣ ስትወራጭ ድንገት ያችን አንብቤ የተለወጥሁባትን መጽሔት በእጇ ነካቻትና ከዚያ እንሥታ ማንበብ ጀመረች:: እያነበበች ሳለች ኢየሱስ በሽታዋን ይወስደውና ትፈወሳለች:: በሽታዋን ስታዳምጥ ምንም የለም:: ከዐልጋዋ ወርዳ ብትቆምም ምንም የበሽታ ስሜት የለም:: በደስታ እየዘለለች ጠበቀችን:: መፈወሷ አስገርሞኝ ሳመስግን ጌታ ኢየሱስ መጠመቅ እንዳለብን ተናገረን፤ ወዲያው ወደ ወንዝ መሄድ ስንጀምር በመንገድ አቁሞን ጽሑፉን ወደ ላኩልን ሰዎች ሄድን እንድንጠመቅ አዘዘንና ሄደን ተጠመቅን[38]::

[38] ተከስ ማርያም ገዛኸኝ፤ *ትምህርተ መለኮት፤* አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት 1996፤ ገጽ 34::



# II. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የድነት ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

## መግቢያ

ትክክልኛ የሙግት አካሄድ ወደ ትክክለኛ ድምዳሜ እንደሚያደርስ አሙን ነው:: ወደ ትክክለኛው ድምዳሜ በሚያደርስን መንገድ ካልሄድን ደግሞ የተሳሳተ የሙግት ድምዳሜ ላይ መድረሳችን አይቀሬ ነው (የተሳሳተ አካሄድ ተጠቅሞ ወደ ትክክለኛ ድምዳሜ መድረስ የሚቻለው በአጋጣሚ/"በአቦ ሰጥ" ብቻ ነዋ!):: ውይይታችን በአብዛኛው መሠረት የሚያደርገው መጽሐፍ ቅዱስን እስከ ሆነ ድረስ (ታሪክንና ሥነ አምክንዮን በተወሰነ ደረጃ እንጠቀማለን:: ትክክለኛው የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ዘዴ ራሱ ታሪክንና ሥነ አመክንዮን እንድንጠቀም የግድ ይላል)፣ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እናጥና/እንመርምር የሚለው ጉዳይ ለውይይታችን መሠረታዊ ነጥብ ነው::

"ድኅረ ዘመናዊ" በመባል የሚታወቀውን የአፈታት ጥበብ ጨምሮ፣ የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ አፈታት ዘዴዎችና ንድፈ ሐሳቦች መኖራቸው ቅቡል ቢሆንም፣ በዚህ መጽሐፍ የቀረቡት ትንተናዎች፣ ሒሶችና አስተያየቶች በሙሉ፣ "ቅዱሳት መጻሕፍት መተርጐም ያለባቸው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊና ሥነ ጽሑፋዊ (Historical, Grammatical, and Literary method—HGL) እውነታዎችን መሠረት ባደረገ መልኩ ብቻ ነው" የሚለውን መሠረታዊ የሥነ አፈታት መርሖ ታሳቢ ባደረገና መርሖቹን በተከተለ መንገድ ነው[39]:: ቅዱሳት መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን፣ ጥንታዊ ድርሳናትንም ሆነ ዘመናዊ ጽሑፎችን የምናጠናው ይህንኑ መርሖ በመከተል ነው:: ይህ ደግሞ በበርካታ የነገረ መለኮትና የቋንቋ ሊቃውንት ተቀባይነት ያለው የቅዱሳት መጻሕፍት አፈታት ጥበብ ነው::

በኢትዮጵያ የሚገኙትን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን የሚከተሉት የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት መንገድ የትኛው እንደ ሆነ

[39] Historical-Critical Method በመባልም ይታወቃል::

በግልጽ አስፍረዋል፡፡ ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ለመምህራኑ "በእካለ ሥጋ እየተገለጠ" በሚያሳያቸው "ራእይና" በሚናገራቸው "ንግግር" ላይ መሆኑን በሚከተለው መንገድ ገልጸዋል፡፡

> በፖስታ ቤት በኩል በተላከልኝ ጽሑፍ ላይ፣ በኢየሱስ ስም ጥምቀት የሰው ሥርዐት ወይስ መለኮታዊ መልእክት...የሚለውን ርእስ ስመለከት እንባቤ ፊቴን አቅንቼ ወደ ፊት ስመለከት፣ ክርስቶስ ፊቴ ቆሞ ሰውነቱን በዚፕ የተዘጋ ልብስ እንደሚከፈት ከፍቶ ሰውነቴን ወደ ውስጡ አስገባና ራሴን በክርስቶስ ሰውነት ውስጥ ገብቼ አየሁት፡፡ ራእዩ አብቅቶ ወደ ራሴ ስመለስ፣ ከመደንገጤ ብዛት የተነሣ መንቀጥቀጥ ያዘኝ፤ የራእዩን ትርጉም ለማወቅ ፈልጌ ኢየሱስን ለመጠየቅ በፊቱ ተደፋሁ፡፡ እርሱም:—"ያየኸው ራእይ ትርጉሙ በሰሜ በጥልቅ ውሃ ውስጥ ገብቶ በመጠመቅ ያልለበሰኝ ሁሉ ራቁቱን እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው" አለኝ፡፡ ከዚያም "እነዚህን ጥቀሶች ተመልከትና ለዳግም ልደት በሰሜ ተጠምቀህ ልበሰኝ" አለኝ፡፡ ጥቅሶቹም እንደ ፊልም በአእምሮዬ ይታዩኝ ጀመሩ:— ዮሐ. 1÷12-13፤ 3÷3-6፤ ሐዋ. 2÷38፤ ቈላ. 2÷11-14፤ ሮሜ 6÷3-6፤ 8÷1:29-30፤ 2ቆሮ. 5÷1-5፤ ገላ. 3÷27፡፡ ምስጢሩ ስለገባኝ እየተቁነጠነጥሁ ለባለቤቴ በስሜት መሰከርሁላት፥ እርሷ ግን ተቃወመችኝ፤ ነገር ግን ኢየሱስ ሊገልጥላት ስለፈቀደ፣ በጣም ታምማ በዐልጋዋ ላይ እያለች ከሥቃይዋ የተነሣ ስትወራጭ ድንገት ያችን እንባቤ የተለወጥሁባትን መጽሔት በእጇ ነካቻትና ከዚያ እንሥታ ማንበብ ጀመረች፡፡ እያነበበች ሳለች ኢየሱስ በሽታዋን ይወስደውና ትፈወሳለች፡፡ በሽታዋን ስታዳምጥ ምንም የለም፡፡ ከዐልጋዋ ወርዳ ብትቆምም ምንም የበሽታ ስሜት የለም፡፡ በደስታ እየዘለለች ጠበቀችን፡፡ መፈወሷ አስገርሞኝ ሳመሰግን ጌታ ኢየሱስ መጠመቅ እንዳለብን ተናገረን፤ ወዲያው ወደ ወንዝ መሄድ ስንጀምር በመንገድ አቁሞን ጽሑፉን ወደ ሳኩልን ሰዎች ሄድን እንድንጠመቅ አዘዘንና ሄደን ተጠመቅን[40]፡፡

ይህ ጉዳይ ቁስ ተክሌም ሆኑ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራንና እማኒያን፣ ትክክል ነው ብለው የተቀበሉት አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የተገኘ ሳይሆን፣ "በራእይ" የተገኘ ነው፡፡ ይህ ራእይና መገለጥ ትክክለኛ መሆኑን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? ምክንያቱም እርኩሳን መናፍስትም የብርሃን መላእክ በመምሰል እንደሚገለጡና ሰዎችን ከእግዚአብሔር እንደሚለዩ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል፡፡ ምናልባት የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂና የአስተምህሮ ቀራጺ፣ ያየሁት ራእይ ከእግዚአብሔር ለመሆኑ ማረጋገጫው "ጥቅሶቹ እንደ ፊልም በራእይ በአእምሮዬ ታይተውኛል፤ ቃለ እግዚአብሔርን ጠቅሶ ደግሞ ወደ ተሳሳተ ትምህርት መሄድ አይቻልም" የሚለውን ጉዳይ እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ሰይጣን ዲያብሎስ ለእኩይ ዐላማው ቃለ እግዚአብሔርን መጥቀስ እንደሚችል ይታወቃል (ለምሳሌ ማቴዎስ 4 ይመለከቷል)፡፡ ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ፣ ማናቸውም ዐይነት ትምህርቶችም ሆኑ መገለጦች መመዘን ያለባቸው የብሉያትና የሐዲሳትን ትክክለኛ ትምህርት ባገናዘበ መልኩ ብቻ ነው፡፡ ቃለ እግዚአብሔርን በትክክል መሠረት ያላደረገ ትምህርትም ሆነ መገለጥ ደግሞ ውጉዝ እጅግ ውጉዝ ነው (ገላትያ 1÷7-9)፡፡

ይህ የቁስ ተክሌ መገለጥም ከኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘ መገለጥ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው፣ አስተምህሮዎችና መገለጦች ሁሉ በሚመረመሩበት በቅዱሱ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ፣ ቁስ ተክለ ማርያም ይህንን አስተምህሮ ለማጽናት ራሱ ክርስቶስ አሳይቶኛል የሚሏቸውን ጥቅሶች አንድ በአንድ እየነቀሱ በማውጣት፣ ክፍሎቹን በቅርበት በመመርመር የሚወሰን ጉዳይ ይሆናል፡፡ በተሰሎንቄ ከተማ ከሚኖሩ ሰዎች ይልቅ በቤሪያ ከተማ የሚኖሩት ሰዎች "ልበ ሰፊዎች ነበሩ" (ሐዋርያት ሥራ 17÷11) የተባለበት ዐቢይ ምክንያት፣ የሐዋርያውን የጳውሎስ ትምህርቶች፣ ከብሉያት ጋር እያነጻጸሩ በመመርመራቸው መሆኑን ቃለ እግዚአብሔር ያስተምረናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ" ወይም "መንፈስን ሁሉ አትመኑ" ሲል በጥብቅ ማስጠንቀቁ፣ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን በሙሉ መመርመር እንዳለብን፣ የምንመረምረው ደግሞ በቃለ እግዚአብሔር መሆኑን አበክሮ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

መገለጦችን፣ ራእዮችን፣ ድንቃድንቆችን፣ ገድላገድሎችን፣ ድርሳኖችን፣ ተአምራትን ወዘተ እውነተኝነት የምንመረምረው በቃለ እግዚአብሔር ነው ስንል፣ ትክክለኛ የሆነውን የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ (HGL) መሠረት አድርገን መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በቤተ ክርስቲያን

[40] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ *ትምህርተ መለኮት፤* አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት 1996፤ ገጽ 34፡፡

ታሪክ ሁሉ ሲሠራበት የነበረና በሰፋት ተቀባይነት ያለው እንዲሁም ሳይንሳዊ የሆነው ይህ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ ተግባራዊ ባደረገ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት፣ ከፍተኛ የሆነ ጥረትም ሆነ ትዕግሥት ይፈልጋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን በቀላሉ አንብበን የክፍሉን መልእክት በቀላሉ ለማስተዋል አዳጋች ከሚያደርጉት ምክንያቶች መኻል አንዱ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ባሕርያት ባለቤት የመሆኑ ጉዳይ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እጅግ ጥንታዊ (ከ1200 ዓ.ቅ.ክ እስከ 100 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት የተጻፉ)፣ ከመሆናቸውም ባሻገር ጥንታውያን በሆኑ ማለትም በዕብራይስጥ፣ በአረማይስጥና በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉ ናቸው። ይህ ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ፣ እነዚህን ሰነዶች በትክክል ለመረዳት የእነዚህን ጽሑፎች ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊና ሥነ ጽሑፋዊ ይዘት እንዲሁም የመልእክቱ ጸሓፍያንም ሆኑ ቀዳማይ ተደራስያን ይኖሩበት የነበረውን ሰፍራ፣ በወቅቱ የነበረውን ባህል፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እንዲሁም መልከዐ ምድራዊ አቀማመጥ ምን እንደሚመስል በትክክል ማወቅ የግድ ይላል። እነዚህን ነገሮች በትክክል ያለማወቅ ምንባባቱን በጠለለ መንገድ እንዳናስተውላቸው እንቅፋት ይሆኑብናል። የመልእክቶቹ ጸሓፍያን ለቀዳማይ ተደራስያኖቻቸው ያስተላለፉትን መልእክት እንዲሁም ቀዳማይ ተደራስያኑ ከሰነዱ ያገኙትን ትምህርት በትክክል ነቅሶ ማውጣት የሚቻለው፣ የተጻፈበትን ዐውድና ቋንቋ በትክክል ማወቅ ሲቻል ብቻ ነው[41]።

እግዚአብሔር አምላክ "አስተማሪዎችን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ" (ኤፌሶን 4÷11፤ ሮሜ 12÷7፤ 1ቆሮንቶስ 12÷28፤ 13÷8) የሚሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ "ቅዱሳት መጻሕፍትን በሙሉ በቀላሉ አንብቦ መልእክታቸውን ለመረዳት ዕገዛ ያስፈልጋል" የሚሰውን ጉዳይ ታሳቢ ያደረገ ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮዎች ሁሉ፣ ማንኛውም

[41] የመልእክቱ ጸሐፊ ለቀዳማይ ተደራብያን ያስተላለፈው መልእክት ምን እንደ ሆነ ነቅሰን የምናወጣው "ሐቲት" (exegesis) በሚባለው ዘዴ ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ዛሬ ለእኛ ወይም ለእኔ ምን ትርጉም አለው? የተላለፈው መልእክት እኛ ወይም እኔ ካለሁበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዴት ሊዛመድ ይችላል? የሚለው ጉዳይ ደግሞ "ፍታቴ" (exposition) በመባል ይታወቃል። ይህ ጥንታዊ ሰነዶችን ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊና ሥነ ጽሑፋዊ ይዘታቸውን በጠበቀ መልኩ የምናብራራብት መንገድ እንዲሁም መልእክቱ እኛ ዛሬ ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዴት ይዛመዳል፣ መልእክቱን እንዴት እናስተምረዋለን ወይም እንሰብከዋለን የሚለውን ጉዳይ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ (hermeneutics) ይባላል።



ሰው በቀላሉ አንብቦ የሚረዳቸው ከሆኑ፣ የአስተማሪ ዕገዛ/ጥቅም እምኑ ላይ ነው?

ከዚህ በመቀጥል ሰፊ ቦታ ሰጥተን የምንነጋገረው የውሃ ጥምቀት ለድነት (ለኀጢአት ሥርየት) እንዲሁም ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጉዳይ ነውን? በሚሉት ርእስ ጉዳዮች ዙሪያ ሲሆን፣ የድርጅቱ መምህራን/ጸሓፍት (በዋነኝነት ተክለ ማርያም ገዛኸኝን፣ በማጠናከሪያነት አሜሪካውያኑን የድርጅቱ ጸሓፍት) ይህንን አስተምህሮ ለማዋቀር መሠረት ሆነውናል እንዲሁም እምሳክ በመገለጥ አሳይቶናል የሚሏቸውን ክፍሎች አንድ በአንድ እየነቀስን በማውጣት እንነጋገርባቸዋለን። ይህን የምናደርገው ታዲያ ከላይ ያስቀመጥነውን የሥነ አፈታት መርሖ መሠረት በማድረግ መሆኑን ልብ ይሏል።

## 1. የውሃ ጥምቀት ለድነት (ለኀጢአት ሥርየት) አስፈላጊ ነውን?

ማርቆስ 16÷16

"ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል"

"ὁ πιστεύσας καὶ βαπτισθεὶς σωθήσεται, ὁ δὲ ἀπιστήσας κατακριθήσεται"

ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው ለሚለው ትምህርታቸው አዘውትረው ከሚጠቅሷቸው ጥቅሶች መኻል ማርቆስ 16÷16 አንዱ ነው። ክፍሉን መሠረት በማድረግም ለድነት እምነት እንደሚያስፈልገው ሁሉ፣ የውሃ ጥምቀትም ድነት ለማግኘት ቅድመ ሁኔታ ነው ይላሉ። እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው።

አንደኛ፤ የአንድን ምንባብ ትርጉም/ትምህርት ከሚወስኑ ጉዳዮች መኻል አንዱ፣ ክፍሉ የሚገኝበትን ዐውድ በጥንቃቄ መመልከት ነው። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ የክፍሉን አጋማሽ አንብቦ መቆም ሳይሆን፣ ክፍሉን ሙሉ ለሙሉ ማንበብ የግድ ይሆናል። የክፍሉ አጋማሽ ክፍል፣ "ያላመነ ይፈረድበታል" ይላል እንጂ፣ "ያልተጠመቀ ይፈረድበታል"

አይልም። ፍርድ የሚጠብቀው ያልተጠመቀውን ሳይሆን፣ ያላመነውን ብቻ ነው። በአጠቃላይ ክፍሉ እምነት ከፍርድ ያድናል ይላል እንጂ፣ ጥምቀት ከፍርድ ያድናል አይልም። ሁለተኛ፤ ድነት በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በማመን ብቻ እንደሚገኝ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በስፋት ያስተምራሉ (ለምሳሌ ሮሜ 3፥20:26:28፤ 4፥1-5፥21፤ 8፥1:30-34፤ 10፥4:10፤ ገላትያ 2፥16፤ 3፥24)። ይህ በሆነበት ሁኔታ ጥምቀት የድነት ቅድመ ሁኔታ ነው ማለት ስሕተት ነው።

ሦስተኛ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ሳይጠመቁ ወይም ከመጠመቃቸው በፊት ድነት ያገኙ ወይም በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ወይም የተሞሉ ሰዎች እንዳሉ በግልጽ ይነግረናል (ሉቃስ 23፥39-43[42]፤ ሐዋርያት ሥራ 10፥44-48፤ 9፥17-18)። በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅም ሆነ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ደግሞ የዘላለም ሕይወት የማግኘት ምልክት እንደ ሆነ ቃለ

[42]ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መሥራች ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ በተደጋጋሚነት፣ ይህ ሰው የጸደቀው የውሃ ጥምቀት ለድነት በማያስፈልግበት በአሮጌው ኪዳን ነው ብለው ሲሞግቱ ይታያል። ይህ ትንተና የአዲስ ኪዳንን አስተምህሮ ያገናዘበ አይደለም፤ ምክንያቱም አዲሱ ኪዳን የሚጀምረው ከኢየሱስ ሞት በኋላ ነው (ለምሳሌ ዕብራውያን 9፥17 ይመለከቷል)፤ ኢየሱስ ደግሞ የሞተው አብረውት ከተሰቀሉት ወንበዴዎች በፊት ነው (ዮሐንስ 19፥32-33)። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከሞቱ በኋላ ድነት የሚገኘው በአሮጌው ኪዳን ነው ብሎ ማስተማር ስሕተት ነው። ከዚህ የምንማረው ትምህርት ከኢየሱስ ጋር የተሰቀለው ሰው በሐዲሱ ኪዳን ውበጥ እንጂ፣ በአሮጌው ኪዳን ውስጥ የነበረ ሰው ስላልነበረ፣ "በአሮጌው ኪዳን ውስጥ በለሆነ ነው ያለውሃ ጥምቀት መዳን የቻለው" የሚለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን አስተምህሮ ፍጹም ስሕተት ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ ይህ ሰው (ሉቃስ 23፥39-43) "ኢየሱስ በጦር በሚወጋበት ጊዜ ከጐኑ በፈሰሰው ውሃ ተጠምቋል" የሚልም ትምህርት አላቸው። ነገር ግን ውሃው ይህን ሰው በማጥመቅ የወጣ ነው የሚል ወይም ውሃው ግለሰቡን እንዳጠመቀው የሚገልጽ አንዳችም ቃል በመጽሐፍ ቅዱብ ውስጥ አልተጻፈም። ቄስ ተክለ ማርያም፣ "አንድ ሰው የውሃ ጥምቀት በሚወሰድበት ጊዜ በውሃው ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ካልተቀበረ ድነት አያገኝም" አያሉ በአንጻሩ ደግሞ፣ ግለሰቡ በውሃው ውስጥ ሳይጠመቅ በመረጨቱ ብቻ ድነት አግኝቶአል የሚለው ትምህርታቸው እርስ በርሱ የሚቃረን ነው (ውሃው በዚህ ሰው ላይ ተረጭቶአል እንዲሁም ግለሰቡን ለማጥመቅ ተብሉ ከኢየሱስ ጐን የፈሰሰ ውሃ ነው ብለን ብንገምት እንኳ ማለቴ ነው)። የዚህን አስተሳሰብ ከንቱነት ለመገንዘብ በዮሐንስ 19፥34 ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ በጥሞና ይመልከቱ።



እግዚአብሔር ያስተምራል (ሮሜ 8፥9፤ ኤፌሶን 1፥13፤ 1ዮሐንስ 3፥24)። አራተኛ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያድነውን የክርስቶስ ወንጌል ለመስበክ እንደ ተጠራ ሲገልጽ፣ ባለማጥመቁ ግን እግዚአብሔርን ያመሰግናል 1ቆሮንቶስ 1፥14-17። እንዲያውም ሐዋርያው፣ "ለማጥመቅ ክርስቶስ አላከኝምና ወንጌልን ልሰብክ እንጂ" ይላል። ጥምቀት የሚያድን ቢሆን ኖሮ ወንጌልን እንዲሰብክ በእግዚአብሔር እንደ ተላከው ሁሉ እንዲያጠምቅም ይላክ ነበር። ይህ አንዱ (ወንጌልን መስበክ) ለድነት ቅድመ ሁኔታ ሆኖ የመቅረቡን ያህል፣ ሌላው (የውሃ ጥምቀት) የድነት ቅድመ ሁኔታ ያለመሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ጉዳይ ነው።

አምስተኛ፤ በርካታ ሊቃውንት የማርቆስ ወንጌል የመጨረሻዎቹ ዐሥራ ሁለት ቊጥሮች (ማርቆስ 16፥9-20) የማርቆስ ወንጌል ክፍል አይደሉም የሚል አቋም አላቸው። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉ:— 1) እጅግ ጥንታዊና ተአማኒነት ያላቸው የግሪክ ቅጆች (ለምሳሌ ኮዴክስ ሳይናቲክስና ኮዴክስ ቫቲካነስ) ማርቆስ 16፥9-20 ያሉትን ክፍሎች አይጨምሩም[43]። ጥንታዊ ናቸው የሚባሉ ከ5,000 በላይ የግሪክ ቅጆች በእጃችን ላይ ያሉ ሲሆን፣ እነዚህ ቅጆች በአብዛኛው ማርቆስ 16፥9-20 ያለው ክፍል የላቸውም። ይህ ክፍል በአብዛኞቹ የኮፕቲክና የግእዝ (Ethiopic) ቅጆች ላይም አይገኝም። የሚጨምሩትም ቅጆች ቢሆኑ፣ በግርጌ ማስታወሻቸው ላይ ሌሎች ጥንታውያን የግሪክ ቅጆች እንደማይጨምሩት ይጠቁማሉ። 2) እጅግ ጥንታዊ የሆኑና ተአማኒነት አላቸው የሚባሉ የታሪክ መዛግብት እንዲሁም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንቀጸ ሃይማኖቶች፣ ማርቆስ 16፥9-20 ላይ ያለውን ክፍል ለትምህርታቸው ሲጠቅሱ አይስተዋልም። 3) ስመ ጥር የቤተ ክርስቲያን አበው፣ የማርቆስ ወንጌል የመጨረሻው ክፍል እንደ ጠፋ እንዲሁም በማርቆስ 16፥9-20 ያለው ክፍል የማርቆስ ወንጌል አካል እንዳልሆነ ገልጸዋል። ለምሳሌ አውሳብዮስና የሮም በማርቆስ 16፥9-20 ያለው ክፍል የበኩረ ጽሑፉ (የእናት ቋንቋው) አካል አይደለም የሚል አቋም ነበራቸው። የእስክንድርያው ቀለሜንጦስ፣ አርጌንስ፣ ቆጵርያኖስ፣

[43]አዲሱ መደበኛ ትርጒም፣ በግርጌ ጽሑፉ ላይ ያቀረበውን ማብራሪያ እንዲሁም የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1980 ዓ.ም ያሳተመው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም፣ በግርጌ ማስታወሻው ላይ ያሰፈረውን ማብራሪያ ይመለከቷል።

የእየሩሳሌሙ ቄርሎስ በማርቆስ 16÷9-20 ያለው ክፍል የማርቆስ ወንጌል ክፍል እይደለም ብለዋል:: 4) በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙት የነገረ መለኮት አስተምህሮዎች ከተቀሩት የማርቆስ ወንጌል ክፍሎች በእጅጉ የተለዩ ናቸው[44] (የአስተምህሮ ልዩነት ያለው ከማቆስ ወንጌል ብቻ ሳይሆን ከተቀሩትም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ነው):: 5) ሰባ ከመቶ (70%) በላይ በሚሆነው የማርቆስ 16+9-20 ክፍል ውስጥ የሚገኙት ቃላት፣ በተቀሩት የማርቆስ ወንጌል ክፍሎች ውስጥ አይገኙም:: የቃላት አመራረጡ ብቻ ሳይሆን፣ የዐረፍተ ነገር አሰካኩም ከተቀሩት የማርቆስ ወንጌል ክፍሎች በእጅጉ የተለየ ነው:: 6) እንደ ማርቆስ ወንጌል ትምህርት፣ ጌታ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ስደቀ መዛሙርት የመታየቱ ክልል እስከ ገሊላ የሚደርስ ሲሆን (ማርቆስ 14÷28፤ 16+7)፣ ከቍጥር 9-20 ባለው ክፍል ግን በኢየሩሳሌም የተገደበ ነው:: 7) ማቴዎስና ሉቃስ፣ ከማርቆስ 1÷1-16÷8 ክፍል ጋር የሚዛመዱ ተጓዳኝ ምንባባት

[44]ይህ ክፍል ከሌሎቹ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከራሱ ከማርቆስ ወንጌል ጋር የሚጋጩ በርካታ አስተምህሮቶችን ይዟአል:: ለምሳሌ ማርቆስ 16+12 ላይ ኢየሱስ፣ "በሌላ መልክ ተገለጠ" የሚለው ዐረፍተ ነገር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ መከራን በተቀበለበትና በሞተበት አካለ ሥጋ፣ ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ ከሚሉት የሐዲስ ኪዳን ምንባባት (ለምሳሌ:— 1ቆሮንቶስ 15+14-17፡ ሮሜ 10+9፤ ሉቃስ 24+39-40፤ ማቴዎስ 28+6፡ ማርቆስ 16+6፤ ዮሐንስ 2+19-22፡ 20+20፤ 21+12-15) ጋር በእጅጉ የሚቃረን ነው፤ ይህ ደግሞ ዐበይት ክርስቲያናዊ አስተምህሮ የሆነውን የትንሣኤ ሙታንን ትምህርት የሚያዛባ ነው ["የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የአካል ወይስ የመንፈስ?" በሚለው ርእስ ጕዳይ ላይ ስፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፡* (አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ራእይ አሳታሚ ድርጅት፤ 1991) ገጽ 92-104 ይመልከቷል]:: ማርቆስ 16+17 ለማመን ምልክቱ አጋንንትን ማውጣት፤ በአዲስ ልሳን መናገር፣ እባቦችን በእጅ መያዝ እንዲሁም የሚገድል መርዝ ጠጥቶ ያለመሞት የሚሉት ጕዳዮች ብዙ ያከራክራሉ:: አንዳንድ የድርጅቱ ታዋቂ ጸሐፍት ራሳቸው (ለምሳሌ:— David Bernard, C. A. Brewer, እንዲሁም P. D. Buford) በአዲስ ልሳን መናገርን ምልክት መሆኑን ከሙሉ ልባቸው ቢቀበሉትም፣ የተቀሩት ጕዳዮች ግን እንደ ምልክት ሊወሰዱ አይገባም የሚል አቋም አላቸው:: ይህ ደግሞ አንዱ ምልክት ሆኖ ከእርሱ ጋር የተዘረዘረው ሌላው፣ ምልክት እንዴት ሊሆን አልቻለም የሚለውን ጥያቄ ያስነሣል:: ጳውሎስ አማኞች ሁሉ በአዲስ ቋንቋ እንደማይናገሩ በግልጥ ማስተማሩን ግን ልብ ይሏል 1ቆሮንቶስ 12+10:30::



ያላቸው ሲሆን፣ 16÷9-20 ክፍል ግን ተጓዳኝ ምንባብ የለውም[45]:: 8) ከቍጥር 8 ወደ ቍጥር 9 የተደረገው የሐሳብ ሽግግር ድንገተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት ከሆነችው ሴት፣ ወደ ኢየሱስ የተደረገው የዐረፍተ ነገር ባለቤትነት ሽግግር ፍሰተ ሐሳቡን አደናቅፎአል:: 9) የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት የሆነችው መግደላዊት ማርያም ማንነት የቀረበው ገለጻ ከተጠናቀቀ በኋላ (ማርቆስ 15÷40:47፤ 16÷1) ስለ መግደላዊት ማርያም አዲስ ገለጻ ያቀርባል (ሉቃስ 8÷2):: 10) አብዛኞቹ ሊቃውንት (የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያንና የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት) ይህ ክፍል ተአማኒነት ያለው የማርቆስ ወንጌል ጽሑፍ ነው የሚል እምነት የላቸውም[46]::

ከእነዚህ መረጃዎች በመነሣት ምሁራን ወደ ሚከተሉት አራት ድምዳሜዎች ደርሰዋል:: ይኸውም 1) የማርቆስ ወንጌል የሚጠናቀቀው 16+8 ላይ ነው:: 2) የማርቆስ ወንጌል የመጨረሻው ክፍል (ማርቆስ

[45]ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ እጅግ በርካታ ተጓዳኝ ምንባባት ስላላቸው እንዲሁም ተመሳሳይ ዘገባ በተመሳሳይ መንገድ ስለሚያቀርቡ በነገረ መለኮቱ ዓለም ምስስል ወንጌላት (synoptic gospels) በመባል ይታወቃሉ::
[46]"ይህ ሁኔታ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ተአማኒነት በጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አያደርግምን?" የሚል ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል:: መገንዘብ ያለብን መሠረታዊው ቍም ነገር፣ በዚህ መልክ አከራካሪነት ያለው የሐዲስ ኪዳን ምንባብ ዮሐንስ 7÷53-8÷11 ብቻ ነው:: ዛሬ በእጃችን ላይ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች 97-99% ከመቶ በላይ ተአማኒነት አላቸው:: የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ *"የዳ ቪንቺ ኮድ— ድርሳነ ጠቢብ ወይስ ድርሳነ ባለቴት"* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ገጽ 39-44 ይመልከቷል:: በዚህ ረገድ ስፊ ጥናት ማካሄድ የሚፈልጉ ትጕሑ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የሚከተሉትን መጻሕፍት እንዲያነቡ ይበረታታሉ:— F. F. Bruce, *The New Testament Documents: Are They Reliable?* (Dowers Grove, Ill.: Inter Varsity Press, 1960). Kurt Aland and Barbara Aland, *The Text of the New Testament*, 2d ed. (Grand Rapids: Eerdmans, 1989). David A. Black, *New Testament Textual Criticism: A Concise Guide* (Grand Rapids: Baker, 1994). Craig L. Blomberg, *Making Sense of the New Testament: Three Crucial Questions* (Grand Rapids: Baker, 2004). Michael J. Wilkins and J. P. Moreland, eds., *Jesus Under Fire: Modern Scholarship Reinvents the Historical Jesus* (Grand Rapids: Zondervan, 1995).

16÷9-20) ጠፍቶአል። 3) ማርቆስ ወንጌሉን አጠናቆ ቢጽፍም ባልታወቀ ምክንያት የመጨረሻው ክፍል እንዲወገድ ተደርጓል። 4) ማርቆስ ጽሑፉን በተለያዩ ምክንያቶች ሳያጠናቅቀው ቀርቶ ይሆናል (ለምሳሌ ድንገተኛ ሞት)።

ለዘብተኛ አቋም የሌላቸው በርካታ የነገረ መለኮት ሊቃውንት፣ በቊጥር 4 ላይ የሰፈረውን ድምዳሜ የሚቀበሉ ቢሆንም፣ ይህንን ምንባብ በተመለከተ የተገኙት ማስረጃዎች፣ በማርቆስ ወንጌል 16÷9-20 ያለው ክፍል ሙሉ ለሙሉ ተአማኒ የሆነ የማርቆስ ወንጌል ክፍል ነው ማለት አያስችሉም። እነዚህን መረጃዎች ታሳቢ በማድረግም ነው በርካታ የማርቆስ ወንጌል አንድምታዎች/ትርጓሜዎች[47] ትንታኔአቸውን የሚያጠናቅቁት ማርቆስ 16÷8 ላይ ነው። በነገረ መለኮቱ ዓለም ያለው ስምምነት፣ እነዚህን ክፍሎች ከሌሎቹ የሐዲስና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በግልጥ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር በተስማማ መልኩ ብቻ ለማጠናከሪያነት መጥቀስ የሚቻል ሲሆን፣ ከዚህ ክፍል ተነሥቶ ነገረ መለኮት መቅረጽ በፍጹም ተገቢ ያለመሆኑን ነው። በየትኛውም ሚዛን በዚህ መልክ በሚያከራክሩ ክፍሎች ላይ መሠረተ እምነታችንን መመሥረት ተገቢ ሆኖ ሊገኝ አይችልም[48]።

[47] አንድምታ/ትርጓሜ/መክፈቻ/ማብራሪያ (commentary) የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (የተጻፉበትን ዘመን፣ መልክዐ ምድር፣ ታሪካዊና ነባራዊ ሁኔታ፣ የአናት ቋንቋውን በዋስው ወዘተ መሠረት ባደረገ መልኩ) ትርጕማቸውን የሚያብራሩ እንዲሁም ምንባቡቱ ሌሎች አማራጭ ትርጕሞች ያላቸው ከሆነ ደግሞ፣ እነዚህን አማራጭ ትርጕሞች የሚያስተዋውቁ መጻሕፍት አንድምታዎች ይባላሉ። ይህ ስያሜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የተለመደ ስያሜ ሲሆን፣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሰዎች ግን "መክፈቻ" የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። "አንድምታ" የሚለው ስያሜ፣ "አንድም እንደዚህ አንድም እንደዚያ" እየተባለ በምንባቡቱ ላይ የሚቀርቡትን አማራጭ ትንታኔዎች የሚየሳይ ሲሆን፣ "መክፈቻ" "ትርጓሜ"ና "ማብራሪያ" ግን፣ መጻሕፍቱ ምንባባቱን ያብራራሉ የሚለውን ጕዳይ ታሳቢ ያደረገ ስያሜ ነው።

[48] አብዛኛውን ጊዜ መናፍቃን ለአስተምህሮአቸው መሠረት የሚያደርጓቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስውርና ለመረዳት አስቸጋሪ በሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ላይ ነው። ለምሳሌ፦ 1ጴጥሮስ 3÷18-21 ያለው ክፍል እጅግ አወዛጋቢ እንዲሁም ለመረዳት አስቸጋሪ ከሚባሉት የሐዲስ ኪዳን ምንባባት መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀስ



## የሐዋርያት ሥራ 2÷38

### "ንስሓ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ"

"Μετανοήσατε, [φησίν,] καὶ βαπτισθήτω ἕκαστος ὑμῶν ἐπὶ τῷ ὀνόματι Ἰησοῦ Χριστοῦ εἰς ἄφεσιν τῶν ἁμαρτιῶν ὑμῶν"

ምናልባት ከየትኛውም ጥቅስ በበለጠ ሁኔታ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማንያንም ሆኑ ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ የውሃ ጥምቀት ለድነት ያስፈልጋል ለሚለው ትምህርት አዘውትረው የሚጠቅሱት ክፍል ነው። ነገር ግን የበኩረ ጽሑፉን የሰዋሰው አወቃቀር[49] እንዲሁም የሐዲስ ኪዳንን አስተምህሮ በትክክል የተረዳ ሰው፣ ጥምቀት የኀጢአት ሥርየት ያስገኛል ወደሚለው ድምዳሜ በፍጹም ሊደርስ አይችልም።

ይኸውም፦— "ንስሓ ግቡ" የሚለው ትእዛዛዊ አንቀጽ (imperative) (ግሪክ "ሜታኖኤሳቲ" "Μετανοήσατε" የብዙ ቊጥርን የሚያመለክት ሁለተኛ መደብ ነው) እንዲሁም፣ "ኀጢአታችሁ" ("የእናንተ ኀጢአት" ግሪክ "ሐማርቲዮን" "ἁμαρτιῶν") የብዙ ቊጥርን የሚያመለክት ሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ነው። ይህ ማለት "ንስሓ ግቡ" እና "ኀጢአ ታችሁ" ("የእናንተ ኀጢአት") ይሠረይ ዘንድ" ተያያዥ እንደ ሆኑ

ነው። የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሐፍት የውሃ ጥምቀት ያድናል ለማለት ቊጥር 21 ሲጠቅሱ፣ የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ ትንሣኤ ሙታን የአካል ሳይሆን የመንፈስ ነው ለማለት ቊጥር 18 ይጠቅሳሉ። ሞርሞኖች ደግሞ ቊጥር 19 መሠረት በማድረግ፣ "በሞቱ ዘመዶቻችን ስም የውሃ ጥምቀት ብንወስድ፣ የውሃ ጥምቀት የወሰድንላቸው ሙታን ዘመዶቻችን የንስሓ ዕድል ያገኛሉ" ይላሉ። ሐዋርያው ጴጥሮስ ጠንካራና ስውር ምንባባትን በመጠቀም እንግዳ የሆኑ ትምህርቶችን እንዳናስተምር አስጠንቅቆናል (2ጴጥሮስ 3÷15-17)። ይህ የሐዋርያው ጴጥሮስ ማስጠንቀቂያ አንዳንድ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለምንኖረው ለእኛ ብቻ ሳይሆን፣ በተመሳሳይ ዘመን ለኖሩት እንዲሁም የክርስቶስን አገልግሎት በቀጥታ ለተከተሉ ለሐዋርያቱ ራሳቸው አስቸጋሪ እንደ ነበር የሚያስገነዝብ ነው።

[49] "ቅዱሳት መጻሕፍት መተርጐም ያለባቸው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊና ሥነ ጽሑፋዊ (HGL-Historical, Grammatical, and Literary method) እውነታዎችን መሠረት ባደረገ መልኩ ብቻ ነው" የሚለውን መሠረታዊ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት መርሖ ልብ ይሏል።

የሚያመለክት ሲሆን፣ “ተጠመቁ” የሚለው ትእዛዛዊ አንቀጽ (ግሪክ “ባፕቲስቴቶ” “βαπτισθήτω”) ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቍጥርን የሚያመለክት ተገብሮ ግሥ (passive verb) እንዲሁም፣ “እያንዳንዳችሁ” (ግሪክ *“ሔካስቶስ ሁምን”* “ἕκαστος ὑμῶν”) ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቍጥር ናቸው:: ስለዚህ “ተጠመቁ” የሚለው ቃልና “እያንዳንዳችሁ” የሚለው ቃል አብረው የሚሄዱ ናቸው[50]::

ከዚህ የምንማረው ቍም ነገር፣ “የኀጢአት ሥርየት” የሚለው ቃል “ተጠመቁ” ከሚለው የትእዛዝ አንቀጽ ጋር አብሮ እንደማይሄድ ነው:: ስለዚህ የክፍሉ ትክክለኛ አተረጓጕም፣ “ንስሓ ግቡ ኀጢአታችሁ ይቅር እንዲባልላችሁ/እንዲሠረይላችሁ:: እያንዳንዳችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ” የሚለው ነው:: ይህ ደግሞ ዐረፍተ ነገሩ አንድ ሳይሆን ሁለት ዐረፍተ ነገር መሆኑን ያሳያል:: በረፍተ ነገሩ አንድ ሳይሆን ሁለት ከሆነ ደግሞ፣ ”ኀጢአታችሁ ይሠረይ ዘንድ” የሚለው ማሰሪያ አንቀጽ፣ ”ተጠመቁ” ወደሚለው ቃል ሊተሳሰፍ አይችልም:: ይህ ደግሞ የውሃ ጥምቀት ኀጢአትን ያስተሠርያል ለሚለው ትምህርት ድጋፍ እንደማይሆን የሚያሳይ ነው:: ስለዚህ ሰዋሰዋዊ አገባቡን መሠረት አድርገን ጥቅሱን እንተርጕመው ብንል የክፍሉ ትምህርት እንደሚከተለው ይሆናል፤ ”ንስሓ ግቡ ኀጢአታችሁ ይሠረይ ዘንድ:: እያንዳንዳችሁም በኢየሱስ ስም ተጠመቁ”:: ክፍሉ አንድ በረፍተ ነገር ሳይሆን ሁለት ዐረፍተ ነገር መሆኑ፣ የኀጢአት ሥርየት ከመጠመቅ ጋር የሚገናኝ እንዳልሆነ፣ አንዱ (ንስሓ መግባት) ቀዳሚ ሌላው (የውሃ ጥምቀት) ደግሞ ተከታይ፣ የመጀመሪያው የኀጢአት ሥርየት የሚያስገኝ ሁለተኛው ደግሞ ኀጢአቱ የተሠረየችለት ሰው የሚፈጽመው ሥርዐት እንደ ሆነ የሚገልጽ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ በ1954 የታተመው የአማርኛ ቅጅ፣ ”ዘንድ” ብሎ የተረጐመው ግሪኩ “ሔይስ” ”εἰς” የሚለውን ቃል ሲሆን፣ ቃሉ ምክንያትን የሚያሳይ ዐቢይ ሐረግ ነው (purpose clause):: ይህ ቃል ከተሳቢ ሙያ (accusative case) ጋር ተያይዞ ቢቀርብ አቅጣጫን

50 Stanley D. Toussaint, *Bible Knowledge Commentary*-New Testament, ed. Walvoord and Zuck, (Wheaton, IL.: Victor Books, 1983), 189-192.



የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን፣ “በዚህ ምክንያት”፣ “ከዚህ የተነሣ”፣ ”በዚህ መሠረት” ወዘተ የሚለውን ትርጕም ሊወክል ይችላል[51]:: ይህ ማለት፣ ”እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ” የሚለው ዐረፍተ ነገር፣ “ንስሓ ግቡ ኀጢአታችሁ ይሠረይ ዘንድ” በሚለው ዐረፍተ ነገር ላይ መሠረት እንደሚያደርግ የሚያሳይ ነው፤ አንዱ ቀዳሚ ሁለተኛው ደግሞ ተከታይ—እንደ ፈረስና (ንስሓ መግባት) እንደ ጋሪ (የውሃ ጥምቀት) ማለት ነው [“ሔይስ” ”εἰς” የሚለው የግሪክ ቃል በዚህ መልኩ የተተረጐመባቸው በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ፤ ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ማቴዎስ 3፥16፤ 12፥14፤ ማርቆስ 1፥4][52]:: ስለዚህ የክፍሉ አጠቃላይ ትምህርት፣ ንስሓ መግባት የኀጢአት ሥርየት እንደሚሰጥ እንዲሁም ንስሓ በመግባቱ የኀጢአት ሥርየት ያገኘ ሰው መጠመቅ እንዳለበት፣ አንዱ ቀዳሚ (ንስሓ መግባት) ሌላው ተከታይ (መጠመቅ) እንደ ሆነ የሚያስተምር እንጂ፣ ጥምቀት የኀጢአት ሥርየት እንደሚሰጥ የሚናገር ክፍል አይደለም::

ይህ ሰዋሰዋዊ ማስረጃ አጥጋቢ አይደለም ብሎ የሚያስብ ሰው እንኳ ቢኖር (አይደለም የሚል ሰው ሳለመሆኑ የግሪክ ሰዋሰው መሠረት ያደረገ ማስረጃ ማቅረብ እንደሚጠበቅበት መዘንጋት የለበትም)፣ ልብ ሊላቸው የሚገቡት ሌሎች መሠረታዊ ነጥቦችም አሉ፤ ይኸውም፣ (1) ”ለኀጢአት ሥርየት” የሚለው ሐረግ የመጥምቁ ዮሐንስን ጥምቀት ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል (ሉቃስ 3፥3፤ ማርቆስ 1፥4)፤ ነገር ግን ማንም ሰው አፉን ሞልቶ የዮሐንስ ጥምቀት የሰዎችን ኀጢአት ያጥባል/ያስተሠርያል አይልም (የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን ራሳቸው እንዲህ ዐይነቱ እምነት የላቸውም)፤ ምክንያቱም በመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት የሚጠመቁ ሰዎች፣ ለንስሓቸው ምልክት ይሆን ዘንድ፣ በውሃ እንደሚጠመቁ በግልጥ ስለሚገነዘብ ነው:: ጥምቀት የሰዎችን ኀጢአት ቢያጥብ ኖሮ፣ በመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁ ሰዎች

51 Walter Bauer, *A Greek-English Lexicon of the New Testament and Other Early Christian Literature,* trans. William F. Wilbur Gingrich, rev. F. Wilbur Gingrich and Fredrick W. Danker, 2d ed. (Chicago: University of Chicago Press, 1979), 228-30.

52 ዝኒ ከማሁ፥ 230::

ዳግም መጠመቅ አያስፈልጋቸውም ነበር (በመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁ ሰዎች ዳግም ተጠምቀዋል የሐዋርያት ሥራ 19፥1-6)። ይህ እውነት ከሆነ ከውሃ ጥምቀት ጋር ተያይዞ፣ "ኀጢአት ሥርየት" የሚለው ሐረግ፣ የውሃ ጥምቀት ኀጢአትን ያጥባል ወይም ለድነት አስፈላጊ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ሊደርስ አይችልም። ክርስቲያናዊው የውሃ ጥምቀት፣ አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመኑ ከኀጢአቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንደ ነጻ የሚያውጅበት ሜዳዊ/ውጫዊ ሥርዐት ነው። ከኀጢአት መንጻታችንን እንዲሁም ሐዲሱን ኪዳን መቀበላችንን የምናሳይበት መንፈሳዊ ሥርዐት ከኀጢአት የምንነጻበት ነው ማለት ስሕተት ነው። በጋብቻ የሚተሳሰሩ ጥንዶች በጋብቻ ኪዳን ውስጥ ወደውና ፈቅደው ለመግባታቸው ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ የጣት ቀለበት እንደኛው ወገን በሌላው ሰው ጣት ላይ ያኖራል። ቀለበቱ የጋብቻ ምልክት እንጂ ጋብቻ አይደለም። ልክ እንደዚሁ ሁሉ የውሃ ጥምቀት አንድ ሰው በአዲሱ ኪዳን ውስጥ መግባቱን፣ የኀጢአት ሥርየት ማግኘቱን ወዘተ የሚያውጅበት ትእምርት/ምልክት እንጂ ትእምርቱ/ምልክቱ ራሱ በአዲሱ ኪዳን ውስጥ ያስገባል፣ የኀጢአት ሥርየት ያስገኛል ብሎ ማስተማር ፍጹም ስሕተት ነው።

(2) በዚህ ስፍራ ልብ ልንለው የሚገባን ተጨማሪው ነጥብ፣ የመልእክቱ ጸሓፊ የሆነው ሉቃስም ሆነ የክፍሉ ተናጋሪ ጴጥሮስ፣ የኀጢአት ሥርየት የውሃ ጥምቀትን ሳይጨምር በስሙ በማመን ብቻ እንደሚገኝ ገልጸዋል (የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሉቃስ 24፥46-47፤ ሐዋርያት ሥራ 3፥19፤ 5፥31፤ 10፥43፤ 5፥31፤ 13፥38፤ 26፥18)።

(3) ሌላው ጥምቀት ለኀጢአት ሥርየት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚለው ሐሳብ፣ ለኀጢአት ሥርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ በቂ እንደ ሆነ ከሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ጋር የሚቃረን ነው (ዮሐንስ 3፥16:36፤ ሮሜ 4፥1-17፤ 11፥6፤ ሮሜ 3፥8-9፤ ኤፌሶን 2፥8-9 ወዘተ)።



## የሐዋርያት ሥራ 22፥16

**"አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኀጢአትህም ታጠብ"**

"Καὶ νῦν τί μέλλεις; ἀναστας βάπτισαι καὶ ἀπόλουσαι τὰς ἁμαρτίας σου ἐπικαλεσάμενος τὸ ὄνομα αὐτοῦ"

ይህን ክፍል በቅርበት ከመመርመራችን በፊት ልንጠይቀው የሚገባን፣ "ጳውሎስ ድነት ያገኘው በይሁዳ ቤት ነው ወይስ በደማስቆ መንገድ ላይ ነው" የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ነው። መረጃዎች ጳውሎስ ድነት ያገኘው በደማስቆ መንገድ ላይ እንደ ሆነ ይገልጻሉ:— 1) ወንጌል የተሰበከለት በሰው (በሐናንያ) ሳይሆን በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ገላትያ 1፥11-12)። 2) ራሱን ለክርስቶስ አሳልፎ የሰጠው በደማስቆ መንገድ ላይ ነው (ሐዋርያት ሥራ 22፥10)። 3) መንፈስ ቅዱስን የተሞላው የውሃ ጥምቀት ከመውሰዱ በፊት ነበር (ሐዋርያት ሥራ 9፥17-18)። እነዚህን መረጃዎች መሠረት ካደረግን ሐዋርያው ጳውሎስ ድነት ያገኘው የውሃ ጥምቀት ከመውሰዱ በፊት ነው ወደሚለው ድምዳሜ መድረሳችን አይቀሬ ይሆናል።

ቃለ እግዚአብሔር እርስ በርሱ የማይጣረስ ከሆነ የክፍሉን ትክክለኛ ትምህርት እንዴት ማግኘት እንችላለን? የሚለውን ጥያቄ በትክክል የሚመልሰው የክፍሉን ሰዋስው በቅርበት መመልከት ይሆናል። የክፍሉን ሰዋስው ወደ መመርመሩ ደግሞ እንዝለቅ:—

በክፍሉ ውስጥ ሁለት የትእዛዝ አንቀጾች አሉ። ይኸውም:—"ታጠብ" (ግሪክ "አፖሉሳይ" "ἀπόλουσαι") እና "ተጠመቅ" (ግሪክ "ባፕቲሳይ" "βάπτισαι")። እነዚህ ትእዛዛዊ ቃላት የተያያዙትም "እና" (ግሪክ "ካይ" "καὶ") በሚለው አያያዥ ቃል ሲሆን፣ "መታጠብ" ስሙን ከመጥራት ጋር የሚያያዝ በአንጻሩ፣ "መጠመቅ" ደግሞ "ተነሣ" ከሚለው ቃል ጋር የሚጣመር ነው። እዚህ የምንማረው ከኀጢአት መታጠብ ከጥምቀት ጋር የሚያያዝ ሳይሆን፣ ስሙን ከመጥራት ጋር የሚሄድ በአንጻሩ ደግሞ፣ መጠመቅ ከመነሣት ጋር አብሮ የሚጣመር እንደ ሆነ ነው (ሐዋርያት ሥራ 16፥31፤ ሮሜ 10፥9-10)። ክፍሉን በዚህ

መልክ ሰናስቀምጠው፣ "አሁንስ ስምን ትዘገያለህ? ተነሣና ተጠመቅ፤ ስሙን እየጠራህም ከኀጢአትህ ታጠብ"[53] የሚል ይሆናል (ሮሜ 10+13 "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና" እንደሚለው ማለት ነው)። ለዚህ ነው ትምህርተ ዘለቅ፣ ይህን የሰዋሰው አወቃቀር ታሳቢ ባደረገ መልኩ፣ "ጳውሎስ በእግዚአብሔር ጸጋ ከኀጢአት የመንጻቱን መንፈሳዊነት የገለጸው፣ ሜዳዊና ውጫዊ በሆነው የጥምቀት ምልክት ነው"[54] የሚሉት። ኤ. ቲ. ሮበርትሰን የተባሉት ስመ ጥር የግሪክ ቋንቋ ሊቅ፣ የክፍሉን ሰዋሰዋዊ ይዘት በትክክል የተረዳ ሰው የውሃ ጥምቀት የኀጢአት ሥርየት ያስገኛል ለሚለው ባዕድ ሐሳብ ይህን ክፍል በማስረጃነት መጥቀስ አይችልም የሚሉት[55]።

"ከኀጢአትህ ለመንጻት ተጠመቅ" ወይም "በመጠመቅ ኀጢአትህን ታጠብ" በሚል መንገድ የተተረጐሙ አንዳችም የአማርኛም ሆነ የእንግሊዝኛ ቅጆች የሉም። ከዚህ የምንማረው፣ ከኀጢአት መታጠብና መጠመቅ የተለያዩ ግብሮች መሆናቸውን እንዲሁም ከኀጢአት መታጠብ የሚገኘው የጌታን ስም በመጥራት ብቻ እንደ ሆነ የሚያስተምረን ነው። ነገር ግን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማንያን የውሃ ጥምቀት ኀጢአትን ያጥባል የሚል ቅድመ ግንዛቤ ስላደረባቸው፣ ነገሮችን ሁሉ በዚህ አስተምህሮ መነጽር በመመልከት ኪሳራ ውስጥ ይወድቃሉ።

በተጨማሪም ይህን ክፍል አስመልክቶ ልብ ልናደርገው የሚገባን ሌሎች በርካታ ነጥቦች አሉ:— አንደኛ፤ የውሃ ጥምቀት ለኀጢአት ሥርየት *ብቸኛ ጉዳይ* (sufficient cause) አይደለም፤ ምክንያቱም ጥምቀት ያለ እምነት ዋጋ የለውምና (ዕብራውያን 11+6)። ሁለተኛ፤ የውሃ ጥምቀት ለኀጢአት ሥርየት *አንገብጋቢ ጉዳይ አይደለም* (necessary cause) ምክንያቱም የኀጢአት ሥርየት ከውሃ ጥምቀት በፊት ሊገኝ እንደሚችል ቃለ እግዚአብሔር ያስተምራልና (ሐዋርያት ሥራ 2+41፤

[53] F.F. Bruce, *The Acts of the Apostles* (London: Tyndale, 1951), 403.

[54] F.F. Bruce, *Commentary on the Book of Acts* (Grand Rapids: Eerdmans, 1954), 442.

[55] AT. Robertson, *Word Pictures in the New Testament* (Broadman Press, 1933), Volume III, pp. 391-392.



8+12፤ 9+18፤ 10+47-48፤ 16+14-15:30-33፤ 18+8፤ ሉቃስ 23+39-43፤ ሮሜ 4+9-12፤ ቈላስይስ 2+11-14)። ከእነዚህ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች የውሃ ጥምቀት ለድነት ብቸኛ እንዲሁም አንገብጋቢ ጉዳይ እንዳልሆነ እንመለከታለን።

ሦስተኛ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ትእምርቶች/ምልክቶች ይጠቀማሉ። እነዚህ ትእምርቶችም አንድ የተወበነን ነገር ይወክላሉ፤ ለምሳሌ በጌታ ራት ወቅት የሚበላው ኅብስት የክርስቶስን ሞት ይወክላል (ዮሐንስ 6+51:56፤ ሉቃስ 22+19፤ 1ቆሮንቶስ 10+16)፤ ድነት የሚገኘው ግን በሚቈረሰው ኅብስት ሳይሆን፣ በጌታ ሞት ነው። የሚቈረሰው ኅብስት ግን ለኀጢአታችን የተቈረሰው የጌታ ሥጋ ትእምርት ነው። ስለዚህ ትእምርት ከሚወክለው መሠረታዊ ሐሳብ ጋር መደባለቅ (መጠናበር) የለበትም። የውሃ ጥምቀት ከኀጢአት ለመታጠባችን (ሐዋርያት ሥራ 22+16) እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ለመፍጠራችን፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ለመቀበራችን እንዲሁም በትንሣኤ ቀን ከሙታን ለመነሣታችን ትእምርት/ምልክት ነው (ሮሜ 6+1-7)። ነገር ግን የክርስቶስ ደም እንጂ ውሃ ከኀጢአት አያነጻንም (ዕብራውያን 9+13-14:12፤ 1ዮሐንስ 1+7፤ ራእይ 1+5፤ 7+14)[56]። አራተኛ፤ ከኀጢአት የነጻነው ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆናችን እንጂ በውሃ አይደለም (ቈላስይስ 2+11)። አምስተኛ፤ አማኞች ለሕግ፣ ሕጋዊ በሆነ መንገድ የሞቱት (ሮሜ 7+4) በመስቀል ላይ ከእርሱ ጋር አንድ በመሆናቸው/ኅብረት በመፍጠራቸው እንጂ፣ በውሃ ጥምቀት አይደለም። ስድስተኛ፤ አማኞች ከክርስቶስ ሞት ጋር ተቀበሩ እንጂ (ሮሜ 6+4)፣ በውሃ ጥምቀት አልተቀበሩም። ሰባተኛ፤ አማኞች ከሞት በመነሣት በሰማያዊ ስፍራ የተቀመጡት ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር አንድ በመሆናቸው/ኅብረት በመፍጠራቸው እንጂ (ኤፌሶን 2+4-6)፣ በውሃ ጥምቀት አይደለም።

ስምንተኛ፤ ጳውሎስ ድነትን ያገኘው በደማስቆ መንገድ ላይ እንጂ፣ ከሐናንያ ጋር በተገናኘበት በይሁዳ ቤት ውስጥ አይደለም። ምክንያቱም (1) በወንጌልን በቀጥታ የሰማው ከሰው/ከሐናንያ ሳይሆን ከራሱ ከክርስቶስ ነው (ገላትያ 1+11-12)። (2) ጳውሎስ ራሱን ለክርስቶስ አሳልፎ የሰጠው

[56] E. Calvin Beisner, *"Jesus Only" Churches* (Grand Rapids: Zondervan, 1998), 57.

በዚያው በደማስቆ መንገድ ላይ ነው (ሐዋርያት ሥራ 1+11-12)። (3) ጳውሎስ የውሃን ጥምቀት ከመውሰዱ በፊት መንፈስ ቅዱስ እንደ ሞላበት ከሐዋርያት ሥራ 9+17 ላይ እናነባለን። ከዚህ የምንማረው እውነት ጳውሎስ ወንጌልን በቀጥታ ከጌታ በመስማትና ወንጌልን በበማበት ቦታ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ በመቀበል የውሃ ጥምቀት ከመውሰዱ በፊት መንፈስ ቅዱስን መሞላቱን ነው።

ዘጠነኛ፤ የውሃ ጥምቀት የምሥራቹ ቃል አካል ላለመሆኑ ቢያንስ ሁለት ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ይኸውም (1) ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ የውሃ ጥምቀት የስብከተ ወንጌል ክፍል እንዳልሆነ በግልጥ ተናግሮአል፡—

> ከቀርስጳስና ከጋይዮስ በስተቀር ከእናንተ ማንንም ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ ስለዚህ በስሜ መጠመቁን የሚናገር ማንም የለም። እርግጥ የእስጢፋኖስን ቤተ ሰው አጥምቄአለሁ፤ ከእዚህ ሌላ ግን ማጥመቄ ትዝ አይለኝም። ክርስቶስ የላከኝ ወንጌልን እንድሰብክ እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም...(1ቆሮንቶስ 1+14-17ሀ)

ከዚህ ክፍል የምንማረው እውነት የውሃ ጥምቀት የድነት ወንጌል ክፍል እንዳልሆነ ነው። ወንጌል ግን፣ "ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኀይል ነው" (ሮሜ 1+16)። ምክንያቱም "በሞኝነት የሚያምኑትን ያድን ዘንድ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአል" (1ቆሮንቶስ 1+21ለ)። ይህ ወንጌልን ሰምቶ ማመን ብቻ ለድነት አስፈላጊው ጉዳይ እንደ ሆነ የሚያስረግጥ ነው። በእነዚህ ምንባብ ጳውሎስ የውሃ ጥምቀት የስብከተ ወንጌል አካል እንዳልሆነ ማስረዳቱ ሐዋርያው የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ እንዳልሆነ የሚያስገነዝብ ነው።

(1) በሐዋርያት ሥራ ላይ በግልጥ እንደምንመለከተው ጳውሎስ በክርስቶስ የተመረጠው "ስላየኸውና ስለ ሰማኸው ነገር በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆንዋለህና" (ሐዋርያት ሥራ 22+15) ተብሎ ነው። ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ የውሃ ጥምቀት የስብከተ ወንጌሉ ክፍል አድርጎ እንዳችም ቦታ አልሰበከም፤ እንዲያውም የውሃ ጥምቀትን የስብከተ ወንጌሉ ክፍል እንዳልሆነ በግልጥ ተናግሮአል (1ቆሮንቶስ 1+14-17ሀ)።



በአጠቃላይ ሐዋርያት ሥራ 22+16 ታሪካዊ እውነታን የሚተርክ ክፍል እንደ ሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ይኸውም ሐናንያ፣ ጳውሎስ እንዲጠመቅ ማዘዙና ጳውሎስም እንደ ተጠመቀ። ነገር ግን የክፍሉ ሰዋሰው ስሙን መጥራት/ማመን ድነት እንደሚያስገኝ (ሐዋርያት ሥራ 16÷31፤ ሮሜ 10+9-10) እንዲሁም ክርእስ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎች የውሃ ጥምቀት ኀጢአትን ያጥባል ወደሚለው ድምዳሜ በፍጹም ሊያደርሱን እንደማይችሉ የሚያስገነዝበን ነው። እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት የውሃ ጥምቀት የወንጌል ክፍል ካልሆነ፣ ሐዋርያት ሥራ 22+16 የውሃ ጥምቀት የድነት ቅደመ ሁኔታ ነው የሚል ትምህርት ሊኖረው አይችልም።

## 1ጴጥሮስ 3÷21

**"ይህም ውሃ አሁን የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ያድናችኋል፤ ይህም የሰውነትን ዕድፍ በማስወገድ ሳይሆን በንጹሕ ኀሊና በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ መማፀኛ ነው"**

"ὃ καὶ ὑμᾶς ἀντίτυπον νῦν σῴζει βαπτισμα, οὐ σαρκὸς ἀπόθεσις ῥύπου ἀλλὰ σὺειδησεως ἀγαθῆς ἐπερώτημα εἰς θεόν"

በዚህ ክፍል ውሃ የሚለው ቃል ጥምቀትን የሚያሳይ እንደ ሆነ ግልጽ ነው። እንግዲያው፣ "ውሃ አሁን የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ያድናችኋል" የሚለው ዐረፍተ ነገር ምን ማለት ነው? የሚያድነውስ ከምንድን ነው?

የሐዲስ ኪዳን መልእክቶች፣ "ታሪካዊና ወቅታዊ" ባሕርይ እንዳላቸው መገንዘብ ያስፈልጋል። ሁሉም መልእክቶች ማለት ይቻላል የተጻፉት በአንድ ታሪካዊ ወቅት ለነበሩ ሰዎችና በመካከላቸው ለተፈጠሩ ልዩ ልዩ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ነው። ለምሳሌ አንደኛ ቆሮንቶስን ብንወስድ፣ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እርስ በርስ መከፋፈል ነበር፤ ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ እንብላ ወይስ እንብላ የሚል ክርክር ነበር፤ የጋብቻ ጥያቄ ነበር፤ የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ችግር ነበር፤ የሙታን ትንሣኤ ክርክር ነበር። ለጢሞቴዎስ የተጻፉትን መልእክቶች ብንወስድ ደግሞ፣ ሐሰተኞች መምህራን ከአካባቢያቸው የለቃቀሙትን ትምህርት

ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመግባት፣ ብዙ ችግርና ምስቅልቅል ሁኔታዎችን ፈጥረው ነበር።

የሐዲስ ኪዳን መልእክቶች፣ "ታሪካዊና ወቅታዊ" ባሕርይ አላቸው የሚለው ጉዳይ ትክክለኛ የሆነው የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ አንዱ መርሖ ከሆነ፣ "ያድናችኋል" (ግሪክ "ሶድዜይ" "σῴζει") የሚለው ቃል መተንተን ያለበት ከዐውዱ አንጻር ብቻ ነው[57]። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ ውሃ ማለትም ጥምቀት ያድናችኋል የሚያድነው ጉዳይ መብራራት ያለበት ከዐውዱ አንጻር ብቻ ነው። በርግጥ ሐዋርያው ጴጥሮስ የውሃ ጥምቀት የዘላለም ሕይወት ያስገኛል እያለ ነው ወይ?

በክፍሉ ላይ ሐቲታዊ ምርመራ ከማካሄዳችን በፊት፣ የክፍሉን ታሪካዊ መቼት (setting) ማወቅ የክፍሉን ትምህርት በጠለለ መንገድ ለመመልከት ታላቅ ዕገዛ ስላለው፣ አካሄዳችን ታሪካዊ ቅኝቱን በወፍ በረር በመቃኘት እንጀምር።

የአንደኛ ጴጥሮስ ተደራስያን በትንሹ እስያ (በዛሬው ሰሜናዊ ቱርክ፤ ይኸውም በአምስቱ የሮማ ልሳነ ምድር፤ ማለትም በጳንጦስ፣ በገላትያ፣ በቀጰዶቅያ፣ በእስያና በቢታንያ) ተበትነው የሚገኙ ክርስቲያኖች ለመሆናቸው በ1ጴጥሮስ 1፥1 ላይ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል። በእነዚህ

---

[57] መጽሐፍ ቅዱስ "ሴት በመውለድ ትድናለች" (1ጢሞቴዎስ 2፥15) ሲል፣ ወላድ ሁሉ መንግሥተ ሰማይ ይገባል ወደሚለው ድምዳሜ ከደረስን፣ ከምንባቡ ትምህርት ጋር በእጅጉ ተቃርነናል። እንግዲያው "ትድናለች" (ግሪክ "ሶቴሰታይ" "σωθήσεται") የሚለው ቃል፣ መታየት ያለበት ከዐውዱ አንጻር ብቻ ነው። ጳውሎስ "ሴት በመውለድ ትድናለች" ሲል፣ ወላድ ሁሉ መንግሥተ ሰማይ ይገባል ለማለት ፈልጎ ነው የሚል አንዳችም ትንተና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ በአግራሞትነት ቀርቦ አላየንም፤ ሊቀርብም አይችልም፤ ምክንያቱም ድነት የኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛዊ ሥራ በማመን ብቻ በጸጋ እንደሚገኝ ከሚያስተምሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ጋር በቀጥታ ስለሚቃረን ነው። እንግዲያው "ትድናለች" ወይም "ያድናችኋል" የሚለው ቃል መታየት/መፈታት ያለበት፣ ዐውዱን ማዕከል ባደረገ መልክ ብቻ እንጂ፣ የዘላለም ሕይወትን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ አይደለም። በዚህ ረገድ ወንድም ምኒልክ አሰፋው "ቃለ ሕይወት" መጽሔት ቁጥር 27፤ 1995 ዓ.ም ገጽ 12 እና 19 ላይ ያቀረበውን ዐውዳዊ ትንተና ይመለከቷል።



ግዛቶች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ከአይሁድም ሆነ ከአሕዛብ (ከአረማውያን) ወገን የመጡ ክርስቲያኖች እንደ መሆናቸው መጠን (1፥14፤ 2፥10)፣ በአጸደ ሥጋ ሲኖሩ የክርስቶስ ወኪል (አምባሳደር) ሆነው መኖር እንደሚገባቸው፣ ይህ ዐይነቱን ሕይወት ለሚኖር ሰው ደግሞ ስደት አይቀሬ ጉዳይ መሆኑን ይገልጽላቸዋል። ነገር ግን በደታቸው እግዚአብሔርን እንደሚያከብር ተገንዝበው በቈራጥነት ስደቱን እንዲጋፈጡት ያበረታታቸዋል። በዚህ ዐይነቱም ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው ልጆች ሁሉ ፍንትው ብሉ እንደሚታይ ያሳውቃቸዋል (5፥12)።

ሐዋርያው በክርስቶስ ያገኙት አዲስ ልደት በስደትም ውስጥ እንኳ ሕያው እንደ ሆነ እንዲሁም ኢየሱስ ራሱ ክፉዎች ባመጡበት መከራ እስከ ሞት ድረስ መጽናቱን ያስታውሳል። ስለዚህ ክርስቲያኖች እርስ በርስ በመረዳዳት (ሕያው ድንጋይ በመሆን) ስደትን በቈራጥነት መጋፈጥ እንዳለባቸው ያስገነዝባል። ከቍጥር 13 ጀምረን የክፍሉን አንኳር መልእክት እንመልከት።

ቍጥር 13 እና 14፤ አብዛኛውን ጊዜ መልካም ነገር ማድረግ ለስደት ባይዳርግም እንኳ ስለጽድቅ መከራን ብትቀበሉ ግን "ብፁዓን ናችሁ" ይላቸዋል። በዚህ ዐውድ "ብፁዓን" (በግሪክ "ማካሪዎይ" "μακάριοι") የሚለው ቃል፣ በፈንጠዝያ የተሞሉ ማለት ሳይሆን፣ ለክርስቶስ መከራን ለመቀበል መልካም ዕድል የገጠማቸው ማለት ነው። ቍጥር 14 የሚደመደመው ኢሳይያስ 8፥12 በመጥቀስ ነው። ይህ የኢሳይያስ ክፍልም ሰዎች እግዚአብሔርን እንጂ ሰዎችን መፍራት እንደሌለባቸው የሚያስጠነቅቅ ምንባብ ነው።

ቍጥር 15 እና 16፤ አራት መሠረታዊ ነጥቦችን ያነሣል፤ ይኸውም 1) በመሠረተ እምነታቸው ላይ ሒስ የሚሰነዝሩ ሰዎች በሚያጋጥሟቸው ወቅት ምክንያታዊ ማስረጃዎችን በመጥቀስና በማጣቀስ የእስተሳሰባቸውን ከንቱነት መሞገት እንዳለባቸው እንጂ፣ ክፉን በክፉ መመለስ እንደሌለባቸው የሚያስረዳ፣ 2) ይህን የክርስትና መሠረተ እምነት

ማቀብ/መመከት[58] የክርስቲያን ሁሉ ኀላፊነት መሆኑን፣ 3) መሠረተ እምነታችንን ማቀብ የሚጠበቅብን በተገቢው መንገድ ይኸውም በትሕትናና በአክብሮት እንደ ሆነ፣ 4) መልካም ባሕርይ ኢፍትሓዊ ለሆነው ስደታቸውና ቅጣታቸው የሚሰጡት መለኮታዊ ምላሽ እንደ ሆነ ያስገነዝባል።

ቍጥር 17-18፤ ሐዋርያው መልካም ነገር በማድረጋቸው (1፥6፤ 2፥15፤ 4፥16:19) ምክንያት መሰደዳቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ ያሳስባቸዋል (2፥15፤ 4፥2:19)። ስለዚህ በሌሎች ላይ ክፉ ከማድረግ ይልቅ መከራን መቀበል ይሻላል (2፥14)። ቍጥር 18 ኢየሱስ ልንከተለው የሚገባንን ፈለግ ትቶልን እንደ ሄደ ይገልጻል። የእርሱ ከኀጢአት የራቀ ሕይወት ክፉዎች በእርሱ ላይ እንዲነሡ ቢያደርግም፣ ለዎችን ሳይፈራ ራሱን ለእግዚአብሔር ዐላማ በማስገዛት ለሰዎች ኀጢአት በመሞት ብዙዎችን አድኖአል።

የመጽሐፉ አጠቃላይ ትምህርትም ሆነ የክፍሉ ዐውድ የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል በስደት ውስጥ መጽናት አስፈላጊ ጕዳይ እንደ ሆነ የሚያስተምር ከሆነ፣ ቍጥር 21 ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ያድናችኋል ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ጥምቀት የሚያድነን ከምንድን ነው? በዚህ ስፍራ የውሃ ጥምቀት የተነጻጸረው በኖኅ ዘመን ከነበረው የጥፋት ውሃ ጋር ነው። በኖኅ ዘመን የነበረው የጥፋት ውሃ ኀጢአተኛውን ዓለም በማጥፋት ኖኅን በዙሪያው ከነበሩት ኀጢአተኞች ነጻ እንዳደረገው፣ ዛሬም ውሃ ማለት ጥምቀት የአሳዳጆቹን መጥፎ ኀሊና በማስወገድ ከስደት ያድናቸዋል። ይኸውም በወቅቱ ክርስቲያኖች በአደባባይ ይጠመቁ ስለነበር አሳዳጆቻቸው ክርስቲያን በመሆን የጽድቅ ሕይወት መኖር እንደ ጀመሩ ስለሚገነዘቡ፣ ቀድሞ የነበራቸውን እኩይ ባሕርይ ምክንያት በማድረግ እንዳያሳድዷቸው ያደርጋል። በዚህ ረገድ ጥምቀት "የበጎ ኀሊና ልመና ነው" (ቍጥር 16)። ስለዚህ ጥምቀት ያድናል፤ ነገር ግን ጥምቀት የሚያድነው ኀጢአት ካስከተለው ዘላለማዊ ጥፋት ሳይሆን ከመሰደድ ነው። ታሪካዊ ዳራውንና ዐውዳዊ ትርጕሙን የጠበቀው ትንተና ጥምቀት ከስደት ያድናችኋል የሚል ትምህርት ያለው ሆኖ

[58] "ዐቃቤ" ማለት ጠባቂ፣ ከላካይ፣ አገደ፣ አስከበረ ወዘተ ማለት ሲሆን፣ ዐቃቤ ክርስትና ማለት የክርስትናን መሠረተ እምነት ከአደጋ የሚከላከል፣ የሚጠብቅ የሚያስጠብቅ ማለት ነው።



ሳለ፣ ጥምቀት ከዘላለም ኵነኔ ያድናችኋል የሚል ትምህርት እሰው የሚለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊና መምህራን ትንተና ከዐውዱ ትምህርት ብቻ ሳይሆን፣ ከአጠቃላዩም የሐዲስ ኪዳን አስተምህሮ ጋር የሚቃረን ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ የውሃ ጥምቀት ከዘላለም ኵነኔ ያድናችኋል እያለ ከሆነ፣ ሳይጠመቁ ድነት ያገኙ ሰዎች ጕዳይ፣ እምነት ብቻ እንደሚያድን የሚያስተምሩት የሐዲስ ኪዳን ምንባባት፣ የውሃ ጥምቀት ሳይወስዱ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ወይም የተጠመቁ ሰዎች ጕዳይ ወዘተ እንዴት ይታይ ይሆን? በአጠቃላይ የውሃ ጥምቀት ከስደት የሚያድን የበጎ ኀሊና ልመና/መማጸኛ እንጂ፣ የድነት ቅድመ ሁኔታ አይደለም።

## 2. የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ነውን?

ዮሐንስ 3፥5

"እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ

በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም"

"Ἀμὴν ἀμὴν λέγω σοι, ἐὰν μή τις γεννηθῇ ἐξ ὕδατος καὶ

πνεύματος, οὐ δύναται εἰσελθεῖν εἰς τὴν βασιλείαν τοῦ

θεοῦ"

ከቋንቋ ባሕርይ የምንማረው እውነት፣ አንድ ቃል ከአንድ በላይ ትርጕም ሊወክል እንደሚችል፤ ነገር ግን የቃሉን አማራጭ ትርጕም የሚወስነው ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ወይም ዐውድ እንደ ሆነ ነው። ጥቂት አስረጆችን እንመልከት:—

"ሥጋ" የሚለው የአማርኛ ቃል በርካታ ትርጕሞችን ሊወክል ይችላል፤ የቃሉን አማራጭ ትርጕም የሚወስነውም ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ነው።

1. ምሳዬን የፍየል ሥጋ በላሁ። ማሞ ሥጋ ቤት አለው።
    - በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ሥጋ የሚለው ቃል፣ የእንስሳን ወይም የአእዋፍን ዐጥንት ሸፍኖ ከቈዳ በታች የሚገኘውን፣ ስብና ጡንቻ ቅልቅል ያለበትን ገላ የሚያመለክት ቃል ነው።
2. ቃል ሥጋ ሆነ።

  - ኢየሱስ ሰው ሆኖ ታየ ወይም ተገለጠ፣ የሰውን ባሕርይ ያዘ ማለት ነው።
3. ከበደ ሥጋዬ ነው።
  - ዘመዴ ነው ለማለት ተፈልጎ ነው።
4. በሆነው ባልሆነው የሰውን ሥጋ መብላት ትወዳለች።
  - ሐሜተኛ ነች፣ ስለ ሰው መጥፎ ነገር መናገር ያስደስታታል ማለት ነው።
5. ደብሪቱ "የእናቴን ሥጋ" ካስች አትመለስም።
  - መሐላ ነው፣ በእናቷ መማሏን የሚያመለከት።
6. ተመቸው መሰለኝ ሥጋ እየያዘ ነው።
  - እየወፈረ ነው ማለት ነው።
7. ይህ ሥጋዊ አመለካከት ነው።
  - ዓለማዊ የሆነ፣ መንፈሳዊነት የሌለበት ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር የሚቃረን አመለካከት ማለት ነው።
8. በዐጸደ ሥጋ እያለ የተናገረው ነው።
  - በሕይወት እያለ የተናገረው ንግግር ነው ማለት ነው።

በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች "ሥጋ" የሚለው ቃል የተለያየ ትርጕም ወክሎ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። ለምግብነት የሚያገለግል ሥጋ፣ ሰው መሆን፣ ዝምድና፣ ሐሜት፣ መሐላ፣ መወፈር፣ መንፈሳዊ ያልሆነ ምድራዊ አመለካከት፣ በዚህች ምድር በሕይወት መኖር ወዘተ ትርጕሞች አሉት።

"ሥጋ" (ግሪክ "ሳርክስ" "σαρξ") የሚለው ቃል በብሉያትና በሐዲሳት 130 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ልክ እንደዚሁ ሁሉ የተለያዩ ትርጕሞችን ወክሎአል። ይኸውም አካል/ገላ፣ ሰው መሆን፣ ምድራዊ፣ ሰብአዊ ተፈጥሮ፣ ዘር፣ ሰብአዊ መሰፈርት፣ ዐይነት/ባሕርይ፣ የሚበላ ሥጋ፣ ምድራዊ/ዓለማዊ አስተሳሰብ፣ ሰዎች፣ ቍሳዊ፣ ኀጢ አተኛ ባሕርይ፣ ለሚታዊ፣ ተራ፣ ውጫዊ፣ የዘር ሐረግ፣ አዳማዊ ባሕርይ፣ በሽታ፣ ጥመት፣ ይህች ዓለም ወዘተ። እነዚህን አማራጭ ትርጕሞች እምታቶ ማቅረብ ወደ ተሳሳተ ትምህርት/ድምዳሜ ይወስዳል። ለምሳሌ ዮሐንስ 1÷14፣ 1ቆሮንቶስ 3÷3 ጋር አንድ አድርገን ካየነው ("ሥጋ" የሚለውን ቃል በተመሳሳይ መልኩ ከፈታነው)፣ ኢየሱስ መንፈሳዊ ምስለት የሌለው ቅንአት፣ ክርክር፣ ተንኰል ወዘተ ያለበት ክፉ ሰው ወደሚለው የተሳሳተ ድምዳሜ ይወስደናል።



ልክ እንደዚሁ ሁሉ ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው በሐዲስ ኪዳን "ውሃ" (ግሪክ "ሁዶር" "ὕδωρ") የሚለው ቃል በርካታ ትርጕሞችን ወክሎ ሊያገለግል ይችላል። ነገር ግን የቃሉን ትርጕም የሚወስነው ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ወይም ዐውድ ነው። ጸሓፊውም ቃሉን የተጠቀመበት አማራጭ ሊሆኑ በሚችሉት ትርጕሞች በሙሉ ሳይሆን፣ አንድ ውስን ትርጕም ይዞ ነው። ይህ እውነት ከሆነ በዚህ ዐውድ ውስጥ "ውሃ" የሚለው ቃል ምን ትርጕም ይወክላል የሚለውን ወደ መመርመሩ እንዝለቅ።

በዚህ ዐውድ፣ "ውሃ" የሚለው ቃል ምን ትርጕም ይወክላል? በመልሱ ዙሪያ ሰዎች የተለያየ አስተያየት አላቸው።

1. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍያንን ጨምሮ አንዳንድ ሰዎች "ውሃ" (ግሪክ "ሁዳቶስ" "ὕδατος") የሚለው ቃል ክርስቲያናዊ ጥምቀትን ያመለክታል ባዮች ናቸው። በዮሐንስ 1÷33-34 እንዲሁም 3÷22፣ 4÷1 የኢየሱስን የጥምቀት አገልግሎት የሚናገር ስለሆነ "ውሃ" የሚለው ቃል ክርስቲያናዊ ጥምቀትን ያመለክታል ይላሉ።

   ይህ ትንተና ግን በርካታ መሠረታዊ ችግሮች አሉበት፤ ይኸውም የምንባቡ ዐውድ ይህን ትንተና የሚደግፍ አይደለም። ለምሳሌ ሀ) ቍጥር 8 ሙሉ ለሙሉ ትኩረት ያደረገው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ብቻ መሆኑ፤ ለ) ዳግም ልደት የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ሥራ መሆኑ እንዲሁም የእምነት ሥራ ብቻ መሆኑ "ውሃ" የሚለው ቃል ክርስቲያናዊ ጥምቀትን ያሳያል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርሰን አይደለም። እንደ ዐውዱ ትምህርት በምስጢራዊ ንፋስና በመንፈስ ቅዱስ ሉዓላዊ ሥራ መካከል ያለው ትዕምርታዊ ገለጻ (analogy) (ቍጥር 8) በመንፈስ መወለድ ከውሃ ጥምቀት ጋር ይያያዛል ብሎ ማሰብ ሲበዛ እንግዳ ትምህርት ነው።

   በዮሐንስ 1÷26:33 ላይ ውሃና መንፈስ የሚለው ቃል ጥምቀትንና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን የሚያመለክት መሆኑ

በዮሐንስ 3÷5 "ውሃ" ጥምቀትን ያመለክታል ብሎ ማሰብ ይቻላል የሚለው ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት፤ 1) ጥምቀትን የሚያሳይ ከሆነም ማሳየት ያለበት የመጥምቁ ዮሐንስን ጥምቀት ይኸውም ንስሓን እንጂ ክርስቲያናዊ ጥምቀትን ሊያመለክት አይችልም፤ ዮሐንስ 1+26:33 "ውሃ" የዮሐንስን ጥምቀት የሚያመለክት ነውና:: 2) በዮሐንስ 1+26:33 ላይ ውሃና ጥምቀት ሲነጻጸሩ የምንመለከት ሲሆን፣ በዮሐንስ 3÷5 ላይ ግን ውሃና መንፈስ እርስ በርሳቸው ሲያያዙ (ሲጣመሩ) እንመለከታለን:: ስለዚህ ዮሐንስ 3+5 ከዮሐንስ 1+26:33 ጋር አቈራኝቶ መመልከት ከዐውዳዊ ትርጕሙም ሆነ ከሰዋስው አወቃቀሩ ጋር የሚቃረን ነው::

2. አንዳንድ ሊቃውንት "ውሃ" (ግሪክ "ሁዳቶስ" "ὓδατος") የሚለው ቃል አካላዊ ልደትን/በሥጋ መወለድን ያሳያል ይላሉ[59]:: ኢየሱስ በቍጥር 5 ላይ የሚገኘውን ቃል (የምንወያይበትን ዐረፍተ ነገር) የተናገረው፣ ኒቆዲሞስ በቍጥር 4 ላይ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ይሆን ዘንድ ነው፣ "ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማሕፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው"፤ "ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል:— እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውሃ [ይኸውም ተፈጥሮአዊ በሆነው መንገድ ከእናቱ ማሕፀን] እና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም":: ኒቆዲሞስ "ዳግም" የሚለውን የኢየሱስ ቃል የተረዳው ለሁለተኛ ጊዜ ወደ እናት ማሕፀን መግባት አድርጎ ነበር፤ ነገር ግን ኢየሱስ "ዳግም" የሚለውን ቃል ያብራራው የመጀመሪያው ሥጋዊ ልደት ሁለተኛው ደግሞ መንፈሳዊ ልደት አድርጎ ነው:: በተጨማሪም ቍጥር 5 ላይ "ውሃና መንፈስ" የሚለውን ንጽጽር ቍጥር 6 ላይ

[59] ይህ ዐይነቱ አመለካከት ካላቸው ሊቃውንት መካከል የሚከተሉትን ይመለከቷል፤ Ben Witherington III, *NTS* 35, 1989, pp. 155-160. እንዲሁም Leon Morris, *JC* pp. 150-151.



ሥጋና መንፈስ ሲል መነጻጸሩ ውሃ የሚለው ቃል የሥጋ ልደትን የሚያሳይ ነው::

ቍጥር 6 ስለ ሁለት ልደት ይናገራል:: ይኸውም፣ ከሥጋና ከመንፈስ መወለድ፤ "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው":: "ውሃና መንፈስ" የሚለው ሐረግ ይህን ሁለት ልደት የሚያመለክት ነው:: አንዱ ተፈጥሮአዊ/ሥጋዊ ልደት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ልዕለ ተፈጥሮአዊ/መንፈሳዊ ልደት ነው:: ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት/የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት (ቍጥር 3 እና 5) በሥጋ መወለድ ብቻ ሳይሆን ለሁለተኛ ጊዜ በመንፈስ መወለድ ያስፈልጋል:: በዚህ ትንተና መሠረት "ውሃ" የሚለው ቃል እንድ ሕፃን ከእናቱ ማሕፀን ከመውጣቱ በፊት ከእናቲቱ ማሕፀን የሚፈሰውን የማሕፀን ውሃ (amniotic fluid) ለማመልከት ወይም የወንዱን የዘር ፈሳሽ (semen) ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ይህም አካላዊ/ሥጋዊ ልደትን ያመለክታል:: ውሃ የሚለው ቃል ልምሳሜን ወይም ሥጋዊ ልደትን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለባቸው በርካታ ጥንታዊ ጽሑፎች አሉ—ቃለ እግዚአብሔርን ጨምሮ (ለምሳሌ:— ምሳሌ 5+15-18፤ ማሕልየ 4+12-13)::

በአጠቃላይ ክፍሉ ስለ ውሃ ጥምቀት የሚናገር ሳይሆን፣ የመጀመሪያው ልደት ተፈጥሮአዊ በሆነው መንገድ ከሥጋ ወላጆቻችን የምንወለደው ልደት ሲሆን፣ ሁለተኛው ልደት ደግሞ ከሰማያዊው አባታችን ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የምንወለደው ልደት ነው::

3. አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ፣ "ውሃ" (ግሪክ "ሁዳቶስ" "ὓδατος") የሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስን ያሳያል ባይ ናቸው:: (ኢሳይያስ 12÷3፤ 35÷6፤ 44+3፤ 55+1፤ ኤርምያስ 2+13፤ ሕዝቅኤል 36÷25፤ ዘካርያስ 14÷8፤ ዮሐንስ 4+10፤ 7÷37-38፤ ራእይ 21÷6፤ እንዲሁም ሕዝቅኤል 47+1-5፤ ከራእይ 22+17 ጋር ያወዳድሩ):: ስለዚህ "ከውሃ መወለድ"

ማስት ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ ማለት ነው። "እና" (ግሪክ ካይ καὶ) የሚለው አያያዥ ቃል "ማለትም" ወይም "ወይም" ተብሎ መተርጐም ይችላል፤ ስለዚህ ሁለተኛው ሐረግ/ቃል የመጀመሪያውን ቃል ያብራራል ማለት ነው[60]። በተጨማሪም ውሃና መንፈስ እርስ በርሳቸው ሲያያዙ (ሲጣመሩ) እንመለከታለን። ስለዚህ ኢየሱስ ለማለት የፈለገው፣ "ሰው ከውሃ ማለትም ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" ነው።

ይህ ትንተና ከዮሐንስ 4፥10፤ 7፥37-38 ጋር የሚጣጣም ሲሆን፣ በእነዚህ ስፍራዎች መንፈስ ቅዱስ በዘላለም ሕይወት እንዲሁም በውሃ ተመስሏል። በተጨማሪም በቍጥር 8 ላይ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ብቸኛው መስፈርት ከመንፈስ መወለድ እንደ ሆነ መገለጹ ቍጥር 5 ስለ ውሃ ጥምቀት እንደማይናገር አመላካች ነው።

4. አንዳንድ ሊቃውንት "ውሃ" የሚለው ቃል ክርስቲያናዊ ጥምቀትን ሳይሆን፣ የመጥምቁ ዮሐንስን የንስሓ አገልግሎት የሚያመለክት ነው ባዮች ናቸው። ኢየሱስ ስለጥምቀት ያስተማረው ሞቶ ከተነሣ በኋላ ነው ማቴዎስ 28፥19። ስለዚህ ኒቆዲሞስ ውሃ የሚለውን ቃል እንደ ውሃ ጥምቀት ሊረዳው አይችልም፤ ነገር ግን "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" የሚለውን የመጥምቁ ዮሐንስን ጥምቀት ማለትም ንስሓን እንጂ። ኢየሱስና ኒቆዲሞስ ይህን ንግግር በሚናገሩበት ጊዜ የመጥምቁ ዮሐንስ የንስሓ ስብከትና ጥምቀት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነበር። የውሃ ጥምቀት ለዕብራውያን እጅግ አስፈሪ ነገር ነው፤ ምክንያቱም እርከኑስ ተደርገው የሚቈጠሩት አሕዛብ ወደ ዕብራውያን እምነት

---

[60] Walter Bauer, *A Greek-English Lexicon of the New Testament and Other Early Christian Literature,* trans. William F. Wilbur Gingrich, rev. F. Wilbur Gingrich and Fredrick W. Danker, 2d ed. (Chicago: University of Chicago Press, 1979), 393.



የሚለወጡበት ሂደት ነውና[61]። ይህም ለኒቆዲሞስ አስደንጋጭ ጒዳይ ነው፤ ኢየሱስ እያስ ያለው ከሕግ ውጪ ያሉ አሕዛብ ንስሓ እንደሚያስፈልጋቸው ልክ እንደዚያው አንተም የሕግ መምህሩ ንስሓ ያስፈልግሃል ነው።

በዚህ ክፍል ላይ የሚገኘው "ውሃ" ምን ያመለክታል የሚለው ጒዳይ እስካሁን ከተመለከትነውም በላይ በርካታ ትርጒሞች ያሉት ቢሆንም፣ "ክርስቲያናዊ ጥምቀትን የሚያሳይ ነው፤ ይህም ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጒዳይ ነው" የሚለው ትንተና በአማራጭነት ከቀረቡት/ከሚቀርቡ ትንተናዎች በሙሉ አሳማኝነቱ እጅግ ደካማ የመሆኑን ያህል ["ውሃ ክርስቲያናዊ ጥምቀትን ያመለክታል" የሚለው ትንተና ከክፍሉ የሰዋስው አወቃቀር፣ ከዐውዱ መሠረታዊ ትምህርት እንዲሁም ከሐዲስ ኪዳን ጠቅላላ ትምህርት ጋር በእጅጉ የሚጣረስ ነውና] "ውሃ" የሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ነው የሚለው ትንተና ከቀረቡት አማራጭ ትንተናዎች መካል ጠንካራውና ብዙ አሳማኝ ነጥቦችን የያዘ ነው። በአጠቃላይ ይህን ክፍል መሠረት በማድረግ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው የሚለው አስተምህሮ ከዐውዱ የሚገኙትን መረጃዎ በቅጡ ያላገናዘበ እንዲሁም የሐዲስ ኪዳንን አስተምህሮ በስፋት ያላመሳከረ ነው።

ሮሜ 6፥3-4

"ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንድንሆን የተጠመቅን፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ ተነሣ፣ እኛም እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንኖር በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል"

"ἢ ἀγνοεῖτε ὅτι, ὅσοι ἐβαπτίσθημεν εἰς Χριστὸν Ἰησοῦν, εἰς τὸν θάνατον αὐτοῦ ἐβαπτίσθημεν; συνετάφημεν οὖν αὐτῷ διὰ τοῦ βαπτίσματος εἰς τὸν θάνατον, ἵνα ὥσπερ ἠγέρθη Χριστὸς ἐκ᾽ εκρῶν διὰ τῆς δόξης τοῦ πατρός, οὕτως καὶ ἡμεῖς ἐν καιότητι ζωῆς περιπατήσωμεν."

---

[61] Merrill C. Tenney, *John The Gospel of Belief: An Analytic Study of the Text* (Grand Rapids: Eerdmans, 1948), 87.

"ልንገነዘበው የሚገባን ዋናው ነገር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለኀጢአት ሥርየት በጥልቅ ውሃ ውስጥ ስንጠመቅ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር መቀበራችንን ነው ሮሜ 6÷3-4:: ይህም በመስቀል ላይ በሞተልን ጊዜ በአፈሰሰልን ውሃና ደም ውስጥ በማለፍ ዘላለማዊውን የሞት ዕዳ ቀብረን በአዲስ ሕይወት ለመኖር አዲሱን አዳም ክርስቶስን መልበሳችንን ያስረዳል ዕብራውያን 6÷3-4፤ ሮሜ 6÷3-4"[62]::

ከላይ እንዳየነው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍት ከዚህ ክፍል በመነሣት የውሃ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርገን ቅድመ ሁኔታ እንደ ሆነ ይገልጻሉ:: ነገር ግን ክፍሉ ይህን ያስተምራልን? በጥራሽ ክፍሉ ይህ ዐይነቱ ትምህርት እንደ ሌለው በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል::

አንደኛ፤ የክፍሉ ሰዋስው ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ ያደርገናል የሚል ትርጉም የለውም:: በአማርኛው "ጋር" በእንግሊዝኛው "into" ተብሎ የተተረጐመው "εἰς" "ሔይስ" የሚለው የግሪክ ቃል፣ ዐውዳዊ ትርጉሙ "ውስጥ" የሚል አንዳችም ሐሳብ አይወክልም:: ስለዚህ ጥምቀት ከክርስቶስ "ጋር/ውስጥ" አንድ ያደርገናል የሚለው ሐሳብ ለዐውደ ምንባቡ ባዕድ የሆነ ሐሳብ ነው:: ሮበርትስን የተባሉት ስመ ጥር የግሪክ ቋንቋ ሊቅ ሮሜ 6÷3 በተመለከተ እንዲህ ይላሉ:—

> "በክርስቶስ ውስጥ መጠመቅ" የሚለው ትርጉም፣ ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ማድረግ የሚቻለው በውሃ ጥምቀት እንደ ሆነ እያስተማረ ነው የሚለው ባዕድ ሐሳብ የጳውሎስ ትምህርት አይደለም. . .ጥምቀት አንድ ሰው ከክርስቶስ ጋር ያለውን መንፈሳዊ ኅብረት የሚያውጅበት ሥርዐት ሲሆን፣ አንድ ሰው ከክርስቶስ ጋር መንፈሳዊ ኅብረት የሚጀምረውም ከጥምቀት በፊት ነው:: ገላትያ 3÷27 ላይ ጥምቀት ውጫዊ ልብስ ወይም መለዮ በማድረግ ነው የተመሰለው:: "በሞቱ ውስጥ"...ማለት ከሞቱ ጋር ኅብረት በማድረግ የሚለውን ትርጉም የሚወክል ነው እንደ ጳውሎስ ትንተና ይህም ኅብረት የተገለጸው በጥምቀት ምልክት ነው[63]::

ከዚህ የምንገነዘበው ሐቅ የግሪኩ ሰዋስው ጥምቀት በክርስቶስ ውስጥ እንድንገባ ወይም ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርገን ቅድመ ሁኔታ ነው የሚለው ሐሳብ ስሕተት መሆኑን ነው::

ሁለተኛ፤ ሐዋርያው ከዚህ ምዕራፍ አጋማሽ ጀምሮ ተምሳሌታዊ ገለጻዎችንና ትእምርቶችን በብዛት ይጠቀማል፤ ለምሳሌ የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ነው የሚሉ ሰዎች ራሳቸው በቍጥር 6 ላይ "አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን" የሚለውን ሐሳብ ተምሳሌታዊ/ትእምርታዊ በሆነ መልኩ እንጂ በቀጥታ ሊተረጕሙት አይችሉም:: ልክ እንደዚሁ ሁሉ ጥምቀት ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ ብቻ ነው ሊታይ የሚገባው:: ቍጥር 11 መታየት ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ ብቻ ነው:—

> እንደዚሁም ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ፣ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ:: (ቍጥር 11)

"ቍጠሩ" የሚለው ቃል የሚያስገነዝበን ለኀጢአት እንደ ሞትን ብቻ ሳይሆን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሕያዋን እንደ ሆንን ነው:: "ቍጠሩ" የሚለው ቃል በግልጽ እንደሚያመለክተው ክፍሉ ተምሳሌታዊ እንደ ሆነ የሚያሳየን ነው:: ከክርስቶስ ጋር ተሰቀላችሁ የሚለው ዐረፍተ ነገር ተምሳሌታዊ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ከክርስቶስ ጋር ተጠመቃችሁ የሚለውም ተምሳሌታዊ ነው (ቍጥር 3:4:6)::

ይህ የጥምቀት ተምሳሌታዊ ዘገባ አንድ ሰው ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል ምን እንደሚሆን የሚገልጽ ነው:: ይኸውም "ክርስቶስን በመልበሱ" "ዳግም እንደሚወለድ" ነው (እነዚህ ቃላት ራሳቸው ተምሳሌታዊ እንደ ሆኑ ልብ ይሏል):: ክርስትናን መቀበል

[62] እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?፤ 82::

[63]AT. Robertson, *Word Pictures*, Volume IV, ገጽ 361-362፡ እንዲሁም የሮበትስንን የግሪክ ሰዎስው መጽሐፍ ይመለከቷል, ገጽ 591, 593.

ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በጥሩ ሁኔታ የሚገልጸው የውሃ ጥምቀት ነው፤ ይኸውም ክርስትና ማለት ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር መሞት፣ መቀበርና መነሣት ማለት ነው። ነገር ግን የውሃ ጥምቀት በራሱ መሞት፣ መቀበርም ሆነ መነሣት ማለት አይደለም፤ ነገር ግን የመሞት፣ የመቀበርና የመነሣት ምሳሌ እንጂ። ሮበርትሰን እንደሚሉት፣ "ትእምርት/ተምሳሌት በራሱ እውነታው አይደለም፤ ነገር ግን እውነታው የሚገለጥበት ሥዕል ነው"[64]። ስለዚህ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆናችንን የሚያመለክት ሥዕላዊ ገለጻ ነው።

ሦስተኛ፤ ከሁለት የተለያዩ ምንባባት በግልጥ የምንማረው ነገር፣ የውሃ ጥምቀት ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ መሆናችንን የምናሳይበት ሥዕላዊ ገለጻ መሆኑን ነው። 1ቆሮንቶስ 10÷2-4 ሐዋርያው ጳውሎስ ስለእስራኤላውያን ወገኖቹ እንዲህ ይላል:—

> እነርሱ ሁሉ ከሙሴ ጋር ለመተባበር በደመናና በባሕር ተጠመቁ። ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ ምግብ በሉ፤ ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው መንፈሳዊ ዐለት ጠጥተዋልና፤ ያ፣ ዐለት ክርስቶስ ነበረ

(1ቆሮንቶስ 10÷2-4)

"ከሙሴ ጋር ለመተባበር በደመናና በባሕር ተጠመቁ" የሚለው ሐረግ እስራኤላውያን ከሙሴ ጋር አንድ መሆናቸውን (መተባበራቸውን) የሚያሳይ ተምሳሌታዊ ገለጻ ነው፤ ይኸውም:— "ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ ምግብ በሉ፤ ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ"።

ሮሜ 5÷12-6÷11 በጥንቃቄ የሚያነብ ሰው፣ የክፍሉ ዐቢይ ትምህርት ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለመሆንና በአንጻሩ ደግሞ፣ ከአዳም ጋር አንድ ስለመሆን እንደሚያትት በውል መገንዘብ ይችላል። ከአዳም ጋር አንድ ከመሆናችን የተነሣ ሞት በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ደረሰ (5÷12)፤ አዳም

[64]AT. Robertson, *Word Pictures in the New Testament* (Broadman Press, 1933), Volume I, ገጽ. 245; እንዲሁም AT. Robertson, *A Grammar of the Greek New Testament* (Broadman Press, 1934), ገጽ. 593 ይመለከቷል።



በመተላለፉ ምክንያት ብዙዎች ሞቱ (5÷15)። በእርሱ ላይ ከተላለፈው ፍርድ የተነሣ ሰዎች ሁሉ በኩነኔ ሥር ወደቁ (5÷16)፤ እርሱ እግዚአብሔርን ከማስቈጣቱ የተነሣ ሞት በሰዎች ልጆች ላይ ሁሉ ነገሠ (5÷17)፤ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በኪነ ጥበቡ ካልታደጋቸው በስተቀር (7÷25, 8÷1)፣ በአዳም መተላለፍ ሰዎች ሁሉ በፍርድ ሥር ናቸው (5÷18)፤ በእርሱ ያለመታዘዝ ሰዎች ሁሉ ኀጢአተኞች ሆኑ (5÷19)።

በሌላ መልኩ ደግሞ ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆናችን የተነሣ የዘላለም ሕይወት አገኘን (5÷14)። ነገር ግን ከአዳም ጋር አንድ ከመሆናችን የተነሣ ከደረሰብን መቅሠፍት ይልቅ ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆናችን ያገኘነው በረከት እጅግ ምጡቅ ነው (5÷15)። ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆናችን የተነሣ የእግዚአብሔር ጸጋ ተትረፈረፈልን (5÷15)። ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆናችን የተነሣ ጽድቅ ወደ እኛ መጣ (5÷16)። ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆናችን የተነሣ የተትረፈረፈ የሕይወት ጽድቅ አገኘን (5÷17)። ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆናችን የተነሣ የተትረፈረፈ የሕይወት ቅድስና አገኘን (5÷18)። ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆናችን የተነሣ የእርሱ መታዘዝ ለእኛ ተረፈ (5÷19)።

ሐዋርያው ጳውሎስ አዘውትሮ የውሃን ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ የመሆን ምልክት አድርጎ ይጠቀምበታል። በ1ቆሮንቶስ 10÷2 ላይ የውሃ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ የመሆን ምልክት ተደርጎ የቀረበው ትምህርት በሮሜ 6÷1-11 ፋፍቶና ዳብሮ እናገኘዋለን። ክርስቶስ ለኀጢአታችን እንደ ሞተ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ሲል ክርስቶስን ኀጢአት ስላደረገው (2ቆሮንቶስ 5÷21) የእኛን ኀጢአት ለመሸከም ለኀጢአት ሞተ (ሮሜ 6÷10)። ስለዚህ እኛ ራሳችንን ከእርሱ ጋር አንድ ካደረግን እኛም ከቀብሩ/ከሞቱና ከትንሣኤው ጋር አንድ ስንሆን (ቊጥር 3 እና 4) ለኀጢአት እንሞታለን (ሮሜ 6÷2)። ከስቅላቱ ጋር አንድ ስለሆንም (ቊጥር 6) ከእርሱ አዲስ ሕይወት ጋር በትንሣኤ አንድ እንሆናለን (ቊጥር 4-5)። ከእርሱም ጋር ሕያው ሆነን እንኖራለን (ቊጥር 8)። በእርሱ ላይ ሞት ደግሞ ጕልበት የለውምና (ቊጥር 9)። ሐዋርያው ይህን ሐሳብ በሚከተለው መልኩ ያጠቃልለዋል:—

> በሞተ ጊዜ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለኀጢአት ሞቶአል፤ ነገር ግን በሕይወት መኖርን ለእግዚአብሔር ይኖራል:: እንዲሁም ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ፣ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ (ቍጥር 10-11)

በሮሜ 5÷12-6÷11 ያለው ክፍል በአጠቃላይ ትኩረት የሚያደርገው፣ በቅድሚያ እኛ በተፈጥሮ ከአዳም ጋር ያለንን አንድነት በመቀጠልም ከኢየሱስ ጋር መንፈሳዊ በሆነ ዳግም ልደት ያለንን ጥምረት በማብራራቱ ላይ ነው (ዮሐንስ 3÷3-6):: ስለዚህ በ1ቆሮንቶስ 10÷2 እይታ ሮሜ 6 ያየነው ከሆነ፣ "ጥምቀት" አንድ የመሆን ምልክት እንደ ሆነ እንገነዘባለን:: ስለዚህ ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርገን የውሃ ጥምቀት አይደለም፤ የውሃ ጥምቀት አንድነታችንን የምናሳይበት ሚዳዊ/ውጫዊ ሥርዐት ነው:: በለዚህ የውሃ ጥምቀት ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር በእምነት አንድ መሆናችን ነው ድነት የሚያስገኝልን:: ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ማለትም ከእርሱ ጋር ለኀ ጢአት ሞተን ከእርሱ ጋር በትንሣኤ ሞትን ድል አድርገን መነሣት ነው:: ሮሜ 6÷3-4 የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጕዳይ ነው የሚል አንዳችም ትምህርት የለውም::

## ቲቶ 3÷5

### "ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን:: ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው"

ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝም ሆኑ አሜሪካውያኑ የድርጅቱ ጸሐፍት፣ ይህ ክፍል የውሃ ጥምቀት ዳግም ልደት እንደሚያስገኝ ያስተምራል ይበሉ እንጂ፣ በክፍሉ ውስጥ ጥምቀት የሚል ቃል አልተጠቀሰም:: በዕብራውያን 10÷22 ላይ በምናቀርበው ሐቲት እንደምናየው፣ ዳግም ልደት የምናገኘውም ሆነ ከእኩይ ኅሊና የምንነጻው የኢየሱስን ደም በእምነት በመረጨት ወይም በመታጠብ ብቻ ነው:: ራእይ 1÷5 ግልጽ እንደሚያደርገው ሰዎች ከኀጢአታቸው የሚነጹት በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንጂ በውሃ ጥምቀት አይደለም::



እንደ ክፍሉ ትምህርት "መታጠብ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ዳግም ልደትን እንጂ የውሃ ጥምቀትን አይደለም:: በአጠቃላይ ቲቶ 3÷5 ስለውሃ ጥምቀት የሚያስተምር ሳይሆን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በእምነት በመታጠብ ስለሚገኘው ዳግም ልደት ነው:: ምንም እንኳ የውሃ ጥምቀት የሕግ ሥራ ሳይሆን የጽድቅ ሥራ ቢሆንም፣ የውሃ ጥምቀት እኛ የምንተገብረው ጕዳይ እስከ ሆነ ድረስ ሥራ ነው:: ክፍሉ ራሱ ግልጽ እንደሚያደርገው፣ ድነት ያገኘነው እኛ ስላደረግነው እንዲሁም ስለምናደርገው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ ብቻ ነው:: የዳንነው በውሃ ጥምቀት እንዳልሆነ ሁሉ፣ ቲቶ 3÷5 የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጕዳይ ነው አይልም::

## ገላትያ 3÷27

### "ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና"

"ὅσοι γὰρ εἰς Χριστὸν ἐβαπτίσθητε, Χριστὸν ἐνεδύσασθε"

ይህ ክፍል ክርስቶስን "ስመልበስ" የውሃ ጥምቀት እንደሚያስፈልግ የሚናገር ስለሆነ፣ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጕዳይ እንደ ሆነ ይገልጻል የሚለው የቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝና የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ፍጹም የተሳሳተ ነው:: ለዚህ በርካታ ምክንያቶች አሉ:—

አንደኛ፤ ሐዋርያው "ጥምቀት" ከክርስቶስ ጋር "አንድ የሚያደርገን" ትእምርት (symbol) እንደ ሆነ ከላይ ባየናቸው ክፍሎች ውስጥ ተገልጾአል:: በዚህም ዐውድ ውስጥ ይኸው ቃል ተመሳሳይ ትርጕም ወክሉ እንደ ቀረበ እንመለከታለን፤ ይኸውም "ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆናችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁታል":: ከላይ እንደ ተመለከትነው እንዲሁም የክፍሉን ትምህርት በትክክል እንደሚገልጸው፣ ይህንንም ክፍል ተምሳሌታዊ ገለጻ አድርገን ለመውሰድ እንገደዳለን::

ሁለተኛ፤ "ስብሳችኋል" የሚለው የግሪክ ግስ መለዮውን የሚለብሰው ወታደር ዐይነት ትርጕም አለው:: ይህን ክፍል በተመለከተ ኤ.ቲ. ሮበርትሰን እንዲህ ይላሉ:—

> ይህ ግስ ልብስን ስመልበስ የምንጠቀምበት ግስ ነው (በቀጥታም ሆነ በተምሳሌታዊ ዘይቤው—ልክ እንደዚህ ስፍራ)። በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ በሌላም ስፍራ ይህ እውን ሆኖ እንመለከታለን (ሮሜ 13÷14፣ ቈላስይስ 3÷9፣ ኤፌሶን 4÷22-24፣ 6÷11፤ ሮሜ 6÷3-4)። በ1ተሰሎንቄ 5÷8 ጳውሎስ፣ "የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቊር እየለበስን" እንደሚለው ዐይነት ማለት ነው. . .እኛ በክርስቶስ በእምነት ጸድቀናል፤ የጸደቅነው በግርዘት ወይም በጥምቀት አይደለም. . . (ሮሜ 6÷4-6)[65]።

"ጥምቀት" የሚለው ቃል የውሃ ጥምቀትን ያሳያል ብንል እንኳ፣ ሐዋርያው በዚህ ቦታ የሚጠቀምበት ቋንቋ እንደሚያሳየው ትእምርትነቱ/ምልክትነቱ በውስጥ ለተካሄደው ነገር ውጫዊ ምልክት አድርጎ ነው። ስለዚህ ጥምቀት መንፈሳዊ ውጤት የሌለው፣ ነገር ግን መንፈሳዊ ትርጒም ያለው ሜዳዊ/ውጫዊ ክሥተት/ሥርዐት ነው።

ሦስተኛ፣ ሮሜ 6÷3 ላይ እንደ ተመለከትነው አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጆች (King James Version) "አንድ" የሚለውን ቃል "ውስጥ" ("into") ብለው ተርጒመውታል። ነገር ግን "εἰς" "ሔይስ" የሚለው የግሪክ ቃል፣ ዐውዳዊ ትርጒሙ "ውስጥ" የሚል አንዳችም ሐሳብ እንደማይወክል ሰዋሰዋዊ ሙግት አቅርበናል። ጥምቀት በራሱ በክርስቶስ "ውስጥ"/"ጋር" አንድ የሚያደርግ ሳይሆን፣ በእምነት አንድ መሆናችንን የምናሳይበት ውጫዊ ምልክት ነው።

አራተኛ፣ ድነት እንዳገኘን የምናውቀው መንፈስ ቅዱስን በመቀበላችን ነው። ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ ሁሉ ድነትን አግኝተዋል (ሮሜ 8÷1-16)። ሐዋርያው በገላትያ 3÷2-3 ላይ በግልጽ እንደሚናገረው ገላትያውያኑ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት በእምነት ነው። ስለዚህ ገላትያ 3÷27 የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጒዳይ ነው የሚል ከሆነ፣ ከቊጥር 2 እና 3 ጋር በቀጥታ ይቃረናል።

አምስተኛ፣ በቊጥር 6 ላይ ሐዋርያው፣ አብርሃም እግዚአብሔርን በማመኑ እንደ ጸደቀ ይገልጻል፤ ለመጽደቁም ብቸኛው ምክንያት

[65] A.T. Robertson, *Word Pictures*, Volume IV, ገጽ 298.



እምነቱ ነው። እንደ ዘፍጥረት 15÷6 ዘገባ የአብርሃም መጽደቅ ሜዳዊ/ውጫዊ የሆኑ ሥርዐቶች ማለትም ግርዘት እውን ከመሆኑ በፊት ነው። አብርሃም የጸደቀው እምነቱ እንዳጸደቀው በሥራ ከመረጋገጡ በፊት ነው (ሮሜ 8÷29-30፤ እንዲሁም ሮሜ 3÷1-5:28 ይመለከቷል)። የሐዲስ ኪዳኑ የውሃ ጥምቀት ልክ እንደ ብሉይ ኪዳኑ የግርዘት ሥርዐት ነው። ይህ እውነት ከሆነ ድነት ያገኘነው የውሃ ጥምቀት ከመውሰዳችን በፊት ነው ማለት ነው። የአብርሃም በእምነት መጽደቅ ከእኛ ጽድቅ ጋር አንድ ለመሆኑ ገላትያ 3÷28-29 ሐዋርያው በሮሜ 3-4 ባለው ክፍል ላይ በሰፋት ተገልጾአል።

ገላትያ 3÷27 ስለ ውሃ ጥምቀት የሚናገር አይደለም፤ ነገር ግን ልክ እንደ 1ቆሮንቶስ 12÷13 እንዲሁም ሮሜ 6÷3-4 በእምነት ስላገኘነውና ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለመሆናችን የሚገልጽ ትእምርት ነው (ዮሐንስ 1÷12-13)። ክፍሉ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጒዳይ እንደ ሆነ የሚያስተምር አይደለም። ስለ ጥምቀት የሚያስተምር ክፍል ነው እንኳ ብንል ጥምቀት መዳናችንን የሚያሳይ ሜዳዊ/ውጫዊ ሥርዐት ብቻ ነው። ሜዳዊ/ውጫዊ ሥርዐት ለውስጣዊው ለውጥ ተጽእኖ ቢኖረው ኖሮ ቆርኔሌዎስና ባልንጀሮቹ የውሃ ጥምቀት ከወሰዱ በኋላ ነበር መንፈስ ቅዱስ ሊሞላባቸው ይገባ የነበረው (ሐዋርያት ሥራ 10) ወይም አብርሃም ከተገረዘ በኋላ ነበር መጽደቅ የነበረበት (ዘፍጥረት 15)። በአጠቃላይ ገላትያ 3÷27 የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጒዳይ ነው የሚል ትምህርት የለውም።

## ኤፌሶን 5÷25-26

**"ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አጽንቶ እንዲቀድሳት ስለ እርሷ ራሱን አሳልፎ ሰጠ"**

በዚህ ስፍራ "በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አጽንቶ" የሚል ሐረግ እንጂ፣ ስለ ጥምቀት የሚናገር አንዳችም ነገር የለም። እስካሁን ለማየት እንደ ሞከርነው፣ "ውሃ" የሚለው ቃል ሁሉ የውሃ ጥምቀት ተብሎ ይተርጐም የሚለው የድርጅቱ የሥነ አፈታት አካሄድ የተሳሳተ መሆኑን አይተናል። በተለይ መታጠብን ወይም ዳግም ልደትን በሚያመለክቱ

ምንባባት/ዐውዶች ውስጥ። ከቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ የምንማረውም ትምህርት፣ አንድ ቃል መፈታት ያለበት (የቃሉ አማራጭ ትርጉም መወሰን ያለበት)፣ ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ወይም ዐውድ የሚያስተላልፈውን መልእክት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ብቻ ነው።

ክፍሉ ስለ ውሃ ጥምቀት የሚናገር ነው ካልን፥ ወደሚከተሉት ሁለት አስገራሚ ድምዳሜዎች መድረሳችን አይቀሬ ይሆናል፦ 1) ኢየሱስ ግለሰቦችን በተናጠል ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያንን በጅምላ አጥምቋል። 2) ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን በውሃ እንዳጠመቃት ባሉችም ሚስቶቻቸውን ማጥመቅ እንዳለባቸው የሚያሳስብ ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ትርጉም የለሽ ነው።

ክፍሉ "በውሃ መታጠብ" የሚለው ተምሳሌታዊ ገለጻ፣ ልክ እንደ ዮሐንስ 8፥31-32፣ "በቃሉ ማንጻትን" የሚያመለክት ነው።

> "ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ፣ እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ። እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ዐርነት ያወጣችኋል አላቸው"

የቃሉ ሁነኛ ተግባር ይኸው ነው። ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን "የሚያጥባት" ወደ ቃሉ በመምራት ነው። በመዝሙር 119፥9 ላይ በግልጥ እንደምንመለከተው አጠባውም ሆነ ማንጻቱ የሚካሄደው በቃሉ አማካይነት በሰዎች ልብ ውስጥ ነው፦

> "ጐልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው"

በዚህም ክፍል "ውሃ" የሚለው ቃል የውሃ ጥምቀትን የሚያመለክት አይደለም። የውሃ ጥምቀትም ኀጢአትን ያነጻል የሚለው ሐሳብም ከዐውደ ምንባቡ አንዳችም ድጋፍ የለውም። "በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አጽንቶ" የሚለው ሐረግ፣ ውስጣዊ መንጻትን የሚያመለክት ነው። ከዕብራውያን 9፥13-14 እንደምንመለከተው ሜዳዊ/ውጫዊ ሥርዐቶች



ልብን ከኀጢአት እንደማያነጹት ያስረዳል። በአጠቃላይ ኤፌሶን 5፥25-27 የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት ወሳኝ ነገር ነው አይልም።

## ዕብራውያን 10፥22

### "ከክፉ ኅሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን፣ ሰውነታችንንም በንጹሕ ውሃ ታጥበን፣ በእውነተኛ ልብና በሙሉ እምነት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ"

እንደሌሎቹ ሁሉ ይህም ክፍል የድርጅቱ ጸሐፍያን በተሳሳተ መንገድ የሚያብራሩት ምንባብ ነው። የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ነው የሚለውን አስተምህሮ ለማስደገፍ ቁስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ አዘውትረው የሚጠቅሱት ክፍል ነው። ክፍሉ የምንረጨው ልባችንን እንደ ሆነ እንዲሁም የምንነጻው ከክፉ ኅሊና እንደ ሆነ ያስተምራል። ይህ እውን ሊሆን የሚችለው ደግሞ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው (ዕብራውያን 9፥14፤ 1ጴጥሮስ 1፥2)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሥጋ ላይ የሚሆነውን ውጫዊ ቅድስና ማለትም ግርዘትን (ሮሜ 2፥28-29) ከውስጣዊ ቅድስና ማለትም ከልብ የሆነውን በጥንቃቄ ይለየዋል። እውነተኛ እስራኤላዊ እውነተኛ የአብርሃም ልጅ (ይኸውም እውነተኛ ክርስቲያን) እውነተኛ በሆነ የልብ ግርዘት እንደ ሆነ እንጂ፣ ውጫዊው በሆነ ግርዛት እንዳልሆነ፣ ይህም እውን የሚሆነው "በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመረጨት" (1ጴጥሮስ 1፥2) እንጂ በውሃ ጥምቀት አይደለም (1ጴጥሮስ 3፥21)።

የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ በግልጥ እንደሚያስረዳው ውጫዊ የሆነ አምልኮተ ሥርዐት አንዳችም የልብ ለውጥ አያመጣም (ዕብራውያን 9፥13-28)። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ ዕብራውያን 10፥22 ላይ በንጹሕ ውሃ ሰውነትን መታጠብ ውስጣዊ መንጻትን ያመጣል በፍጹም ሊል አይችልም፤ ይህ እርስ በርሱ የሚያቃረን ሐሳብ ነውና።

ይህ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም የመርጨት ሐሳብ የተቀዳው ከብሉይ ኪዳን ነው። የብሉይ ኪዳን አገልጋዮች የሚወክላቸውን እንስሳ ካቀረቡ በኋላ (ዘሌዋውያን 8፥22)፣ የእንስሳውን ደም በሕዝቡ ላይ ይረጩታል

(ዕብራውያን 9፥19፤ ዘፀአት 24፥8)። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር በግ በሆነው (ዘፍጥረት 22፥8) በመሲሑ ደም ታጥቦ ለሚነጻው ልብ ተምሳሌት ነው (ኢሳይያስ 53)። ነገር ግን "በውሃ መታጠብ" ግን ካህኑ ወደ መሠዊያ አገልግሎቱ ከመሄዱ በፊት ጽዱ ሆኖ ለመቅረብ የሚፈጽመው ሥርዐት ነው (ዕብራውያን 8፥6)። የመጀመሪያው (በደሙ መረጨት) ውስጣዊና መንፈሳዊ እንዲሁም "ልባዊ" ነው (ሮሜ 2፥28-29)፤ ሁለተኛው ግን በንጹሕ ውሃ (መታጠብ) ግን ውጫዊና ቍሳዊ እንዲሁም ሥጋዊ (ሮሜ 2፥28-29) ነው[66]።

ዕብራውያን 10፥22 በንጹሕ ውሃ ሰውነትን መታጠብ የሚለው ሐረግ የውሃ ጥምቀትን የሚያመለክት ቢሆንም፣ ይህ ጉዳይ የልብን መንጻት ሊያስከትል አይችልም። ስለዚህ የውሃ ጥምቀት የሰዎችን ልብ ከኀጢአት አያነጻም፤ ዳግም ልደትም አያመጣም፤ የድነትም ቅድመ ሁኔታ አይደለም። በአጠቃላይ ዕብራውያን 10፥22 የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚል ትምህርት የለውም።

## ቈላስይስ 2፥12

**"በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ፤ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፣ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ"**

ይህ ክፍል ሮሜ 6፥3-4፤ 1ቆሮንቶስ 12፥13 እንዲሁም ገላትያ 3፥27 ጋር ተመሳሳይ ሐሳብ ያለው ክፍል ነው። እነዚህ ክፍሎች የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው እንደማይሉ ሁሉ፣ ይህም ክፍል እንዲህ

---

[66]ይህን ምንባብ በተመለከተ በአማራጭነት የሚቀርቡ በርካታ ትንታኔዎች አሉ። እነዚህን ትንታኔዎች ለመመልከት የሚከተለውን እንድምታ ይመለከቷል:— Franz Delitzsch, *Commentary on the Epistle to the Hebrews* (T&T Clark, 1882), ቅጽ II, ገጽ 174-179። በርካታ ሊቃውንት፣ "ሰውነትን በንጹሕ ውሃ መታጠብ" የሚለውን ሐረግ የሚያመለክተው የውሃ ጥምቀትን እንደ ሆነ የሚስማሙ ቢሆንም እንኳ (አንዳንድ ሊቃውንት ይህ ሐረግ የውሃ ጥምቀትን አያሳይም የሚል አቋም አላቸው)፣ የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚለውን ሐሳብ አይቀበሉም። የውሃ ጥምቀት ውጫዊ ሥርዐት እንጂ በክርስቶስ ደም ለመረጨት በቅድመ ሁኔታነት የሚቀርብ አይደለም።



ዐይነቱ ትምህርት የለውም። ከቍጥር 10 እስከ 17 ያለው ክፍል አንድ ዐውድ ሆኖ ሳለ፣ ክፍሉ ከዐውዱ ተገንጥሎ ሲጠቀስ ይስተዋላል።

"በምትበሉት መብል ወይም በምትጠጡት መጠጥ ወይም በዓላትን በለማክበር ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለሰንበት እንዳችም በው አይፍረድባችሁ" ይላል። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለሚመጣው ነገር ጥላ ናቸው፤ አካሉ ደግሞ ክርስቶስ ነው።

ዐውዱ እንደሚያሳየን የሐዲስ ኪዳኑ የውሃ ጥምቀት የብሉይ ኪዳኑን ግርዘት የሚወክል ነው። በዚህም ቦታ እነዚህ ሁለት ነገሮች እርስ በርሳቸው ተነጻጽረዋል። በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያምን ሰው በእጅ ባልተደረገ ግርዘት ተገርዟል።

ጥምቀትና ግርዘት እርስ በርሳቸው መነጻጸራቸው ጥምቀት በሰው፣ "እጅ የሚካሄደውን ጥምቀት" ሳይሆን፣ ልክ እንደ ሮሜ 6፥3-4 ከክርስቶስ ጋር መሞትንና መነሣትን የሚያሳይ ሥዕላዊ ገለጻ ነው።

የአዲስ ኪዳኑ የውሃ ጥምቀት የብሉይ ኪዳኑን ግርዘት የሚተካ ከሆነ፣ ግርዘት በብሉይ ኪዳን ለድነት ወሳኝ ጉዳይ እንዳልሆነ ሁሉ፣ የውሃ ጥምቀትም ወሳኝ ሊሆን አይችልም። አብርሃም ከመገረዙ በፊት እንደ ጻደቀ ከቃለ እግዚአብሔር እንማራለንና (ዘፍጥረት 15፥6)። ሮሜ 2፥28-29 በግልጥ እንደሚነግረን ለድነት አስፈላጊው ጉዳይ በመንፈስ የልብ መገረዝ ነው እንጂ፣ በሥጋ የሚደረገው ግርዘት አይደለም። አንድን ሰው እውነተኛ አይሁዳዊ ወይም የአብርሃም ልጅ የሚያደርገውም መንፈሳዊ ግርዘት ነው።

የብሉይ ኪዳኑ ግርዘት የአዲስ ኪዳኑ የውሃ ጥምቀት ጋር አንድ ከሆነ፣ በብሉይ ኪዳን እውነተኛ አይሁዳዊ የሚያደርገው የሥጋ ግርዘት እንዳይደለ ሁሉ (የሥጋው ግርዘት አስፈላጊ ቢሆንም እንኳ)፣ የውሃም ጥምቀት አንድን ሰው እውነተኛ አማኝ/ክርስቲያን እንደማያደርገው ሮሜ 2፥28-29 ይገልጻል።

> በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፤ ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፤ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ

መገረዝ ነው እንጂ፣ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከበው አይደለም።

ሮሜ 6÷3-4፤ 1ቆሮንቶስ 12÷13 እንዲሁም ገላትያ 3÷27 ላይ በግልጽ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ በዚህም ክፍል ሐዋርያው "ጥምቀትን" የማንነት መገለጫ ሰርተፍኬት አድርጎ ነው የሚያቀርበው። ግርዘት አንድ ሰው አይሁዳዊ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ። በውሃ የምንጠመቀው መጠመቅ ውስጣዊውን ለውጥ የሚያሳይ ሜዳዊ/ውጫዊ ምልክት ነው። ሜዳዊው ሥርዐት የቤተ ክርስቲያን አባል እንደሚያደርገን ሁሉ፣ መንፈሳዊውም ጥምቀት የክርስቶስ አካል ያደርገናል።

ልክ እንደ ሮሜ 6÷3-4፤ 1ቆሮንቶስ 12÷13 እንዲሁም ገላትያ 3÷27 ሁሉ ቈላስይስ 2÷12 "ጥምቀት" የሚለው ቃል፣ በእጅ የማይከናወነውን መንፈሳዊ ጥምቀት የሚያሳይ ተምሳሌታዊ ገለጻ ነው። ይህም አንድን ሰው ከክርስቶስ ሞት፣ መቀበር እንዲሁም ትንሣኤ ጋር አንድ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህም በሰው እጅ የሚከናወን ጕዳይ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሆን ጕዳይ ነው። በአጠቃላይ ቈላስይስ 2÷12 የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጕዳይ ነው የሚል ትምህርት የለውም።

## 1ቆሮንቶስ 12÷13

**"አይሁድ ብንሆን፣ የግሪክ ሰዎች ብንሆን፣ ጨዋዎች ብንሆን እኛ ሁላችን ባንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል"**

ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝም ሆኑ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን፣ ይህ ክፍል የውሃ ጥምቀት የክርስቶስ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አካል ለመሆን መሠረታዊ ጕዳይ እንደ ሆነ ያስተምራል ባዮች ናቸው። ይህን ትምህርት ላለመቀበል በርካታ ምክንያቶች አሉ። ክፍሉ ስለ ውሃ ጥምቀት ያስተምራል ይባል እንጂ፣ ክፍሉ ስለ ውሃ ጥምቀት የሚያስተምር አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በውሃ መጠመቅ እንዳለ (ሐዋርያት ሥራ 10÷48)፣ በእሳት መጠመቅ እንዳለ (ማቴዎስ 3÷11)፣ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እንዳለ (ማቴዎስ 3÷11፤ ሐዋርያት



ሥራ 1÷5)፣ በኢየሱስ መጠመቅ እንዳለ (ሮሜ 6÷3-4) ያስተምራል። ስለዚህ ጥምቀት በተባለበት ቦታ ሁሉ ውሃን ታሳቢ ማድረግ ስሕተት ነው። ይህ ክፍል ስለውሃ ጥምቀት የሚናገር እንዳልሆነ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል:—

"የክርስቶስ አካል" የምንሆነው በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ እንደ ሆነ እሙን ነው፤ ነገር ግን ይህ እውን ሊሆን የሚችለው የውሃ ጥምቀት ስንወስድ ነው ወይም የውሃን ጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር አንድ ላይ ስንወስድ ድነት እናገኛለን የሚል ሐሳብ በዚህ ክፍል ውስጥ የለም።

አንደኛ፤ ሐዋርያው የክርስቶስ አካል ለመሆን በመንፈስ ተጠምቀናል ካለ በኋላ፣ አንዱን መንፈስ ጠጥተናል ይላል። ተጠምቀናል የሚለው ሐረግ የውሃ ጥምቀትን የሚያሳይ ከሆነ፣ በተመሳሳዩ መንገድ ጠጥተናል የሚለውም ውሃን ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ትርጕም የለሽ አነጋገር ነው። ሁለተኛውን ሐረግ በተምሳሌታዊ ዘይቤ ወስደን መንፈስ ቅዱስ ነው ካልን፣ በተመሳሳይ መንገድ የመጀመሪያውንም ሐረግ መንፈስ ቅዱስ ነው ማለት የግድ ይሆናል።

ሁለተኛ፤ የ1ቆሮንቶስ 12÷13 ዐውደ ምንባብ ተምሳሌታዊ ዘይቤን የተከተለ ነው። "አካል" የሚለው ቃል ራሱ፣ ክርስቶስን ያመኑ አማኒያን ያላቸውን ኅብረት በተምሳሌታዊ ዘይቤ የሚገልጽ ነው። ከቍጥር 7-11 ያለው ክፍል ቍሳዊ ሳይሆን፣ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የሚገልጽ ነው። ከቍጥር 12-31 ያለው ምንባብ ደግሞ ተምሳሌታዊ በሆነ ገለጻ ስለአንድነት የሚያስተምር ነው። ይህ ጕዳይ ቍጥር 13 ላይ "ጥምቀት" የሚለው ቃል በተምሳሌታዊ ገለጻ መንፈስ ቅዱስን እንደሚያመለክት የሚያሳይ ነው።

1ቆሮንቶስ 12÷13 ተምሳሌታዊ በሆነ ገለጻ ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን አንድነት የሚያመለክት ሲሆን፣ ይህም እውን የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መንፈሳዊ በሆነ መልኩ እንጂ ቍሳዊ በሆኑ ነገሮች አይደለም። ይህም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚወለዱትን ክርስቲያኖች ዳግም ልደት "አዲስ ፍጥረት" (2 ቆሮንቶስ 5÷17)

ያደርጋቸዋል:: በአጠቃላይ 1ቆሮንቶስ 12÷13 የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚል ትምህርት የለውም::

## 3. በማጠናከሪያነት የሚጠቀሱ ሌሎች ክፍሎች

### ዮሐንስ 19÷34

*"ነገር ግን ከጭፍሮቹ አንዱ ጐኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውሃ ወጣ"*

ይህን ክፍል በተመለከተ ቄስ ተከስ ማርያም ገዛኸኝ እንዲህ ይላሉ፣ "የመድኀኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነት ክርስቶስን (ሕይወትን) ሰጠን:: ክርስቶስ በመስቀል በመሞቱ ምክንያት ከጐኑ ውሃና ደም ፈሰቀልን ዮሐንስ 19÷34:: ክርስቶስ በውሃው፣ በደሙና በመንፈሱ ሊያድነን መጣ 1ዮሐንስ 5÷6-8...በአሪት ዘመን ሙሴ ከበግ ወይም ከፍየል የወጣውን ደም ለእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት ከተጠበቀው ውሃ ጋር በኢሶጵ በማደባለቅ በሕዝቡና በመጽሐፉ ላይ ይረጨው ነበር ዕብራውያን 9÷19-20:: ሙሴ ሲረጨው የነበረው የኪዳን ውሃና ደም ከክርስቶስ ጐን ለተገኘው ውሃና ደም ጥላ ነበር...ጥምቀት በእምነት በንቀበላት እንደምታድነን ሲመሰክር እኛ እንዴት ጥምቀት አታድንም ልንል እንደፍራለን?"[67]::

"ደሙና ውሃው ከጐኑ ሲወጡ በአንድነት እንጂ ተለያይተው ሰላልወጡ በማዳን ሥራቸውም አይለያዩም 1ዮሐንስ 5÷6-7"[68]::

"ሙሴ የኰርማዎችንና የፍየሎችን ደም ከውሃ ጋር ቀላቅሎ ሲረጭ እንደ ነበር ሁሉ፣ ክርስቶስም የራሱን ደምና ውሃ በአንድ ላይ ከጐኑ

[67] ተከለ ማርያም ገዛኸኝ፤ *እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አዲስ ልደት፤* አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ገጽ 30-31:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::
[68] ዝኒ ከማሁ፤ 76::



በማመንጨት የመዳንን በር ከፍቶአል 1ዮሐንስ 5÷6-7፤ ዮሐንስ 19÷34"[69]::

ተክለ ማርያም ገዛኸኝ ዮሐንስ 19÷34 ከውሃ ጥምቀት ጋር አያይዘው ማቅረባቸው ሲበዛ አግራሞትን የሚፈጥር ነው:: ይህ ዐይነቱ አመለካከት ሊከሠት የሚችለው በመጽሐፍ ቅዱስ "ውሃ" የሚለው ቃል በሙሉ፣ የውሃ ጥምቀትን ያሳያል ከሚለው የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲሁም አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚያስተምረው ትምህርት የሚወሰነው፣ ክፍሉ በሚገኝበት ዐውደ ምንባብ ሳይሆን፣ በድርጅቱ መምህራን ውሳኔ ነው ከሚለው መናፍቃዊ አስተሳሰብ የመነጨ ነው:: ይህ ከሥነ አፈታት መርሖ አንጻር ሲታይ፣ እጅግ የተሳሳተ አካሄድ ነው (ለምሳሌ በዮሐንስ 7÷37 "ውሃ" በማያጠራጥር መልኩ መንፈስ ቅዱስን እንደሚያመለክተው ሁሉ፣ አንድን ክፍል ከዐውዱ አላቄ/አፋቶ መተርጐምም አደገኛ የሆነ የሥነ አፈታት አካሄድ ነው):: የዮሐንስ 19÷34 ዐውዳዊና ታሪካዊ ዳራ በአለባ መልክ እንቃኝ:—

ሮማውያን በስቅላት እንዲሞት የፈረዱበት ሰው፣ ሕይወቱ እንዲያልፍ የሚፈለገው በመስቀል ላይ በለሆነ፣ ካልሞተ በበተቀር ከተሰቀለበት ዕንጨት ላይ እንዲወርድ አይደረግም:: ይህ ሁኔታ ደግሞ የተሰቀለው ሰው ለቀናት በመስቀል ላይ እንዲቆይ ሊያስገድድ ይችላል፤ እንዲያውም ሮማውያኑ ግለበቡ በመስቀሉ ላይ አካሉ በስብሶ ሥጋ በል አእዋፍ (ጥንብ አንሳ) ሬሳውን እንዲበላው ያደርጉ እንደ ነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ[70]:: ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች የተሰቀለውን ሰው ሬሳ በፍጥነት ከመስቀሉ ላይ ማንሣት ካስፈለገ፣ ወታደሮቹ የተሰቀለውን ሰው እግር (ጭን) በብረት መዶሻ ቀጥቅጠው ይሰብሩታል:: ለዚህም ሁለት ዐቢይ ምክንያቶች አሉ፣ አንደኛው ግለሰቡ ድንገት ሳይሞት በሥቃዩ ብዛት ብቻ ራሱን ስቶ ከሆነ፣ እግሩን በብረት መዶሻ በሚቀጠ ቀጥበት ጊዜ ነፍሱ ካልወጣች ሕይወት እንዳለው ፍንጭ ይሰጣል ከሚል አስተሳሰብ እንዲሁም ድንገት ሳይሞት ቀርቶ ከመስቀል ላይ እንዲወርድ

[69] ዝኒ ከማሁ፤ 78::
[70] Donald A. Carson. *The Gospel According to John*. (Grand Rapids: Eerdmans; Leicester: Inter-Varsity, 1991), 622.

ከተደረገ፣ እሽምቆ በሮም መንግሥት ላይ አደጋ ሊጥል ይችላል የሚለውን ፍራቻ ለማጥፋት ነው።

ሮማውያን ይህን መንገድ ይከተሉ እንጂ፣ የሙሴ ሕግ የሞት ቅጣት ተቀጥቶ የሞተ ሰው፣ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ሬሳው ከተሰቀለበት ዕንጨት ላይ ወርዶ እንዲቀበር ያዛል። ይህ እንዲሆን ያስፈለገበትም ምክንያት ሬሳው በዚህ መልኩ ሳይቀበር ካደረ፣ ምድሪቱን ያረክሳል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ዘዳግም 21÷22-23)[71]። በተጨማሪም ኢየሱስ የተሰቀለው በዕለተ ዐርብ ቢሆንም፣ ቅዳሜ የአይሁድ ሰንበት ስለሆነና በሰንበት ቀን ሬሳው በመስቀሉ ላይ እንዳይውል እይሁድ በመፈለጋቸው ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት የኢየሱስ አስከሬን ከመስቀል ላይ እንዲወርድ ጲላጦስን ለመኑ፣ "እይሁድ የተሰቀሉት ሰዎች ሬሳ ሰንበት ቀን በመስቀል ላይ እንዳይውል ስለፈለጉና ያም የተለየ ሰንበት ስለነበር፣ የተሰቀሉት ሰዎች ጭናቸው ተሰብሮ በድናቸው እንዲወርድ ጲላጦስን ለመኑት" (ቍጥር 31)።

ኢየሱስ ከስቅላቱ በፊት በደረሰበት ሥቃይ/ሕማም ክፉኛ ተጐድቶና ተዳክሞ ስለነበር፣ ከእርሱ ጋር ከተሰቀሉት ሰዎች በፊት እንደ ሞተ ቃለ እግዚአብሔር ያስረዳል (ዮሐንስ 19÷32-33)። ይህንን ጉዳይ በወል የተገነዘቡት የሮማውያኑ ወታደሮች፣ እግሩን (ጭኑን) በብረት መዶሻ ከመከትከት ይልቅ ጐኑን በጦር መውጋት መረጡ፣ "ከወታደሮቹ አንዱ የኢየሱስን ጐን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውሃ ፈሰሰ" (ቍጥር 34)። ይህ ሁኔታም ብሉያት መሲሑ በሚሰቀልበት ጊዜ፣ "ከዐጥንቱ አንድም አይሰበርም" (ቍጥር 36፤ ዘፀአት 12÷46፤ ዘኍልቍ 9÷12፤ መዝሙር 34÷20) የሚለው ትንቢታቸው እንዲፈጸም ምክንያት ሆነ።

የሕክምና ሰዎች ኢየሱስ የትኛው አካሉ ቢወጋ ነው ውሃና ደም ተቀላቅሎ ሊፈስ የቻለው በሚለው ጉዳይ ላይ (ማለትም ኢየሱስ በተወጋበት ቦታ ላይ) የተለያየ አስተያየት ቢኖራቸውም፣ ውሃ በመፍሰሱ ጉዳይ ላይ ግን፣ በዚህ መልክ ተሠቃይቶ ለሞተ በተለይም በመስቀል

71 ዝኒ ከማሁ።



ላይ ለተሰቀለ ማንኛውም ሰው ሊያጋጥም የሚችል ጉዳይ እንደ ሆነ ይስማማሉ[72]።

72 ዝኒ ከማሁ፤ 623 በዚህ ረገድ ሁለት ዋነኛ የሚባሉትን የሕክምና አስተያየቶች የሚከተለውን ምንጭ በመጥቀስ ጽፎአል። Pierre Barbet, *A Doctor at Calvary: the Passion of our Lord Jesus Christ as Described by a Surgeon* (Doubleday, 1953); W. D. Edwards, W. J. Gabel, F. E. Hosmer, Journal of the American Medical Association 255, 1986, pp. 1455-1463. ስበለጠ ማብራሪያ Donald A. Carson. *The Gospel According to John.* (Grand Rapids: Eerdmans; Leicester: Inter-Varsity, 1991), 622-29 ይመለከቷል። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ በዚህ ጉዳይ ላይ የቤቴል ቲቺንግ ጠቅላላ ሆስፒታል የሕክምና ዳይሬክተርና የቀዶ ጥገና ሐኪም የሆኑትን ዶክተር ምበግና ፍሥሐን አነጋግሮ ነበር፤ ዶክተር ምስግና የሰጡት መልስ ዶክተር ባርቤት በጽሑፋቸው ካሰፈሩትና ፕሮፌሰር ካርሰን በመጽሐፋቸው ከጠቀሱት አስተያየት የተለየ አይደለም። የዶክተር ምስግና ፍሥሐ አስተያየት በአጭሩ እንደሚከተለው ነው:ጀ "አንድ ሰው ጐኑ በጦር በሚወጋበት ጊዜ ደምና ውሃ መፍሰሱ፣ በሕክምናው ዓለም የሚታወቀው በግለሰቡ አካል ውስጥ ፈሶ የተጠራቀመ ደም መኖሩን ነው። ይህ ደም ሊጠራቀም የሚችለው ደግሞ ደሙ የሚታቈርበት ቦታ ሲገኝ ነው። ሳንባችን የመተንፈስ ሥርዐቱን ለማከናወን በጐንና በደረታችን ውስጥ በዙሪያው እንደ ቀረጢት ያለ (pleural cavity ወይም pleura) የተባለ ክፍል አለው። ይህ ደግሞ በጉዳት ጊዜ ደም ለማጠራቀም አመቺ ስፍራ ነው። የግራና የቀኙ pleural cavity እያንዳንዱ ከሁለት ሊትር በላይ ደም የማቈር ብቃት አለው። ብዛት ያለው ደም በዚህ ስፍራ ሊከማች በዝቅተኛ ስፍራ ያለው የመርጋትና ከላይ የዘንጋዳ ውሃ የመሰለ ፈሳሽ (serum) የመትፋት ባሕርይ ይኖረዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለና በሞተ ጊዜ ወታደሩ ጐኑን በጦር መውጋቱና በተወጋበት ቀዳዳ ደምና ውሃ መፍሰሱ ተገልጾአል። ይህ እንደ አንድ መለኮታዊ ተአምር ባይሆን፣ እንደ ተፈጥሮአዊ ክሥተት (natural phenomena) መታየት ይኖርበታል። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ከመስቀሉ በፊት ክፉኛ እንደ ተገረፈና እንደተደበደበ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ጀርባው ተገርፎአል፤ ይህ ደግሞ የጎለኛውን የሳንባችንን ክፍል ያጠቃልላል። ከባድ መስቀል ተሸክሞ ደፋ ቀና እያለ ዐተሰት እንዲወጣ ተደርጎአል። ብዙ ጊዜ ወድቆ እንደ ተነሣ የሚያመለክቱ አመላካች ነገሮችም አሉ። በደረቱም አካባቢ ጉዳቶቹ እንደደረሱበት መገመት አያዳግትም። በመጨረሻም ለሰዓታት በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎአል። ስለዚህ በኢየሱስ ሞት ጊዜ በደረቱ ውስጥ ደም መድማቱ አስደናቂ ጉዳይ ሊሆን አይችልም። በጦር በሚወጋ ጊዜ ደምና ውሃ መፍሰሱ የተፈጥሮ ሂደት እንጂ ተአምራት ሊሆን እንደማይችል ማንም የሕክምና ባለሙያ ሊገነዘበው የሚችል ጉዳይ ነው። በአጠቃላይ ከኢየሱስ ጐን ውሃ

ዮሐንስ ከኢየሱስ አካል ደምና ውሃ ፈሰሰ የሚለውን ጉዳይ ለምን ዘገበ የሚለው ለተነሣንበት የውይይት ርእስ፣ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው:: ትምህርተ ዘለቅ ለዚህ ጉዳይ ሁለት ዐበይት ታሪካዊና ነገረ መለኮታዊ መልስ እንዳለ ያስረዳሉ፤ ይኸውም 1) የኢየሱስ ዐጥንት ሳይሰበር የቀረበትን ዋነኛ ምክንያት ለማሳወቅ ነው:: አይሁድ የኢየሱስን መሲሕነት ለመቀበል ፈቃደኛ ባይሆኑም እንኳ፣ አሟሟቱ ብሉያት ስለ መሲሑ ከሚናገሩት እውነት ጋር አንድ መሆኑን ለማሳሰብ እንዲሁም፣ 2) ኢየሱስ ፍጹም ሰው መሆኑን ለማስረገጥ ነው:: ሐዋርያው ዮሐንስ መልእክቱን በሚጽፍበት ወቅት፣ ዶሲትዝም በመባል የሚታወቀው ኑፋቄ እየሉ የወጣበት ወቅት ነበር (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሉች ይመለከቷል 1ዮሐንስ 2÷22፤ 4÷1-4፤ 5÷6-9):: ዶሲቲስቶች ደግሞ ኢየሱስ ፍጹም ሰው ነው የሚለውን ጉዳይ አይቀበሉም[73]:: እንደ ዶሲቲስቶች አስተምህሮ ኢየሱስ፣ "ሰው ይምሰል እንጂ ሰው አልነበረም":: ኢየሱስ ሰው የሚመስል ነገር ግን ሰው ያልነበረ ስለነበር፣ በመስቀል ላይ ሞተ የሚለው ጉዳይ በዶሲቲስቶች እምነት ስሕተት ነው:: "በወቅቱ የነበሩት ዕብራውያንም ሆኑ ግሪካውያን ደግሞ የሰው አካል ውሃና ደም ያዘለ ነው የሚል እምነት ነበራቸው"[74]:: ይህን የዶሲቲስቶች አቋም ፉርሽ ለማድረግ ከኢየሱስ አካል ውሃና ደም ፈሰሰ የሚለውን ጉዳይ መዘገብ ዋነኛ ጉዳይ ነው:: ለዚህም ነበር ዮሐንስ በሞቱ ወቅት ደምና ውሃ ፈሰሰ የሚለውን ጉዳይ የጠቀሰው[75]:: በእጠቃላይ ክፍሉ ኢየሱስ ፍጹም ሰው እንደ ሆነ፣ ለሰው ልጆች ኀጢአት እንደ ሞተ እንዲሁም አሟሟቱ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መሲሑ

---

መፍሰሱ ኢየሱስ ከፉኛ መሠቃየቱን እንዲሁም መሞቱን የሚያመለክት ነው:: በሰውነታችን ውስጥ በተለይም ከላይ በጠቀስኋቸው ቦታዎች ይህ የሚሆንበት አንዳንዴም ግለሰቡ በሕይወት እያለ ይህ ዐይነቱ ችግር ከተፈጠረ፣ ውሃውን ከሰውነቱ የምንቀዳበት ጊዜ አለ"::

[73] ራሱ ዶሲቲዝም የሚለው ስያሜያቸው የተወሰደው፣ "ዶኪዮ" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፣ ትርጕሙም "ይመስላል" ማለት ነው::

[74] ዝኒ ከማሁ፤ 624::

[75] ሊቃውንት፣ እስልምና ስለክርስቶስ አሟሟት መረጃውን የወሰደው፣ ከዶሲቲስቶች ምንጭ ነው የሚሉትም ከዚህ የተነሣ ነው:: ቍርዓን ሱራ 4÷156 ላይ አይሁዶች ኢየሱስን፣ "አልገደሉትም፡ አልሰቀሉትምም፡ ነገር ግን የገደሉትና የሰቀሉት መሰላቸው" ይላል::



የሚያስተምሩትን ትምህርት የሚያሟላ እንደ ሆነ የሚያስገነዝብ ነው:: በአጭር አነጋገር ኢየሱስ መሞቱን የሚያመለክት አካላዊ ምልክት ነው (ደም በሰው አካል ውስጥ የሚረጋው ግለሰቡ ሲሞት ብቻ ነው:: ደም ሕያው በሆነ ሰው ውስጥ ሊረጋ አይችልም:: የሚረጋ ከሆነ ግን፣ በአካል ውስጥ የፈሰሰው ደም ከፍተኛ ከሆነ ነው:: በኢየሱስ አካል ውስጥ ውሃ መጠራቀሙ ደሙ መርጋቱን የሚያመለክት ነው፤ ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ኢየሱስ ሲሞት ብቻ ነው[76])::

ከኢየሱስ ጐን ደምና ውሃ ፈሰሰ የሚለው ዐረፍተ ነገር ታሪካዊና ዐውዳዊ ፋይዳው ይህ ሆኖ ሳለ፣ "ከጌታ ጐን የፈሰሰው ውሃ ጥምቀትን ያሳያል፤ ይህ የኢየሱስ ደም ከኀጢአት እንደሚያነጻው ሁሉ፣ ጥምቀትም ከኀጢአት ያነጻል" የሚለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ፣ ለክፍሉ ታሪካዊ መቼትም ሆነ ዐውድ እጅግ ባይተዋር ነው:: ይህ የቄስ ተክለ ማርያም ጉዳይ አንድ የቆየ ታሪክ ያስታውሰኛል:: አንድ የአእምሮ በሽታኛ የሆነ ሰው፣ ሐኪሙን፣

- "ዶክተር እኔ እኮ ሞቻለሁ" ይለዋል ዶክተሩም፣
- "በፍጹም አልሞትህም፣ ምክንያቱም ትበላለህ፣ ትጠጣለህ፣ ትንቀሳቀሳለህ"
- "አይ ዶክተር የእናንተ ሳይንስ ባይደርስበት እንጂ ሙታንም ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይንቀሳቀሳሉ"
- ዶክተሩ በሽተኛው እንዳልሞተ ለማስረዳት የሚያመጣቸውን ማስረጃዎች ሁሉ በሽተኛው፣ "የእናንተ ሳይንስ ስላልደረሰበት እንጂ ሙታንም እንደዚያ ያደርጋሉ" እያለ ይመልሳል::
- በመጨረሻም ዶክተሩ፣ "ለመሆኑ ሙታን፣ ደማቸው በደም ሥራቸው ውስጥ ይዘዋወራል ብለህ ታስባለህ" ሲል በሽተኛውን ይጠይቀዋል::
- በሽተኛውም ምንም ሳያቅማማ፣ "በፍጹም ሙታን ደማቸው የረጋ ስለሆነ በደም ሥራቸው ውስጥ የደም ዝውውር የለም" ሲል በልበ ሙሉነት ይመልሳል::

---

[76] ከዶክተር ምስግና ፍሥሓ ጋር ከተደረገ ቃለ ምልልስ የተወሰደ::

- ዶክተሩ፣ "በጣም ጥሩ እጅህን አቀብለኝ" በማለት፣ የበሽተኛውን ጣት በመርፌ ይወጋዋል:: ከበሽተኛውም ጣት ደም መንጠባጠብ ይጀምራል::
- በሽተኛውም እጅግ በመደነቅ፣ "ወይ ጉድ! ለካስ ሙታንም ደም ይፈሳቸዋል" አለ ይባላል::

ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ውሃ" የሚለውን ቃል ሁሉ፣ የውሃ ጥምቀትን ያሳያል የሚል ጽኑ እምነት ስላደረባቸው፣ እንደ አእምሮ በሽተኛው ማስረጃዎችን ሁሉ ከቀድሞ አቋማቸው አንጻር ብቻ የመመልከት፣ መረጃዎቹ ምን ያመላክታሉ የሚለውን ጉዳይ ያለማገናዘብ ችግር አለባቸው:: መረጃዎችን መሠረት ባደረገ መንገድ አመለካከትን መቅረጽ ወይም አቋምን ማስተካከል ትምህርትን ከሚፈልግ ሰብአዊ ፍጥር የሚጠበቅ ጉዳይ ነው (ግለሰቡ ካላበደ ወይም በአጋንንት ልቡናው ካልታወረ በስተቀር):: ይህ ባይሆን ኖሮ ይህን ክፍል የእንግዳ ትምህርታቸው ማጠናከሪያ አድርገው ባልተመለከቱት ነበር:: እስካሁን የተመለከትነው ትንተና እንኳ ስሕተት ነው ቢባል፣ በዮሐንስ ወንጌል ውሃ የሚለው ቃል የውሃ ጥምቀትን ከማሳየት ይልቅ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳይባቸው በርካታ ሁኔታዎች ነበሩ (ለምሳሌ ዮሐንስ 3÷5፤ 7÷37-39):: ነገር ግን ውሃ የሚለው ቃል ጥምቀትን ያሳያል ከሚለው አቋም ይልቅ የተሻሉ አማራጮች እያሉ፣ የውሃ ጥምቀት ብቸኛ አማራጭ ተደርጎ መቅረቡ አስገራሚ ጉዳይ ነው::

## ማቴዎስ 28÷19-20

"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ"

ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ ለሐዋርያቱ የሰጠው ትእዛዝ ሲሆን፣ በዚህ ሂደት ውስጥ ጥምቀት ሁነኛ ስፍራ ተሰጥቶት ይገኛል:: በሌላ አገላለጽ የውሃ ጥምቀት ደቀ መዛሙርት የማድረግ አንዱ ክፍል ነው:: ነገር ግን ክፍሉ የውሃ ጥምቀት ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ነው አይልም:: ደቀ መዛሙርት



በማድረጉ ሂደት ውስጥ፣ "ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው" የሚል ትእዛዝ እናገኛለን:: የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው ብለን የምናስብ ከሆነ ግን፣ እንደ ክፍሉ ትምህርት የኢየሱስን ትእዛዝ ሁሉ መጠበቅ ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ የግድ ይሆናል፤ የማንጠመቅ ከሆነም ድነት አናገኝም ወደሚለው ድምዳሜ ይወስደናል::

ይህ ዐይነቱ ድምዳሜ ግን ከሐዲስ ኪዳን አስተምህሮ ጋር በእጅጉ ይቃረናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች ከኀጢአት እንዲርቁ የሚያበረታታ ቢሆንም፣ አንድም ክርስቲያን ኀጢአት የለብኝም ማለት እንደማይችል ግን በግልጥ ይናገራል (ለምሳሌ 1ዮሐንስ 1÷7-2÷2 ይመለከቷል):: እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ንስሓን የሰጠው የሰው ልጆችን ድካም ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ነው:: ክርስቲያኖች የጌታን ትእዛዝ ሁሉ ካልጠበቁ ድነት አያገኙም እንደማንለው ሁሉ፣ ካልተጠመቁ ድነት አያገኙም እንዴት ማለት እንችላለን?

በውጭ የሚገኙ አንዳንድ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሐፍትም ሆኑ ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፣ ከዚህ በተቃረነ መንገድ የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ "ውስጥ" የምንገባበት ሂደት ነው ይላሉ[77]:: ይህ ትንተና ሪቫይዝድ ቨርዥን (Revised Version) የተባለውን የእንግሊዝኛ ቅጅ መሠረት ያደረገ ነው:: ይህም "በ-----ስም" ("in the name of" ግሪክ "εἰς τὸ ὃ ὄνομα") ከሚለው ቃል በመነሣት ነው:: በአማርኛችን "በ" ብለን የተረጐምነውን የግሪክ መስተዋድድ (ግሪክ "εἰς") ሪቫይዝድ ቨርዥን "ውስጥ" ("in") ብሎ መተርጐሙ የድርጅቱን ጸሐፍት ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል:: የሚገርመው ግን ከሪቫይዝድ ቨርዥን በስተቀር አንድም የእንግሊዝኛ ቅጅ፣ ክፍሉን በዚህ መንገድ የተረጐመው የለም[78]:: በእንግሊዝኛ ተናጋሪው ዓለም በቀዳማይነት የሚጠቀሱትና ስመ ጥር የሆኑት የግሪክ ቋንቋ ሊቅ ኤ.ቲ. ሮበርትሰን በግሪክ "ሄይስ" (ግሪክ "εἰς") የሚለውን መስተዋድድ ሪቫይዝድ ቨርዥን

---

[77] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ *እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል፤* ገጽ 85::

[78] ለምሳሌ *Authorized Version (King James), Phillips Modern English Translation,* the *New English Bible,* the *Jerusalem Bible,* the *New International Version,* the *Today's English Version.*

"ውስጥ" ("in") ብሎ መተርጐሙ ስሕተት መሆኑን ገልጸዋል[79]:: ለምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል 10÷41-42 ባለው ክፍል ውስጥ "ሄይስ" (ግሪክ "εἰς") የሚለውን መስተዋድድ በዚህ መልኩ እንተርጐመው ብንል አንዳችም ትርጕም ሊኖረው አይችልም:: በአጠቃላይ ይህ ክፍል የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው የሚለውን ጕዳይ የሚያስተምር አይደለም::

## ሐዋርያት ሥራ 8÷35-38

"ፊልጶስ አፉን ከፈተ፤ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት:: በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውሃ ደረሱ፤ ጃንደረባውም:— እነሆ ውሃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው አለው:: ፊልጶስም በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው:: መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ:: ሠረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፤ ፊልጶስና ጀንደረባው ሁለቱም ወደ ውሃ ወረዱ፤ አጠመቀውም"

ክፍሉ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው የሚል አንዳችም ሐሳብ ባይኖረውም እንኳ፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው የሚለውን አስተምህሮአቸውን ለማጽናት አብዝተው የሚጠቅሱት ክፍል ነው:: ኢትዮጵያዊው ጀንደረባ የእግዚአብሔርን ቃል በማ፤ ቃሉንም ተማረ፤ ንስሓ ገባ፤ አመነ፤ በመጨረሻም የውሃ ጥምቀት በመውሰድ ሂደቱን ሙሉ አደረገ:: ከዚህ ሂደት የምንማረው ነገር፣ ክርስቶስን በምንሰብክበት ጊዜ ሁሉ የውሃ ጥምቀትንም መስበክ እንዳለብን ሲሆን፣ ይህም ለድነት አስፈላጊ ጕዳይ እንደ ሆነ አበክሮ ያስገነዝባል ይላሉ::

ነገር ግን ይህ ትንተና ፊልጶስ ለኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ስለጥምቀት ነግሮታል የሚለውን ጕዳይ ታሳቢ ያደረገ ነው:: ይህ ደግሞ የክፍሉን ዐውድ ያገናዘበ አይደለም:: ክፍሉ ፊልጶስ ስለውሃ ጥምቀት ለጀንደረባው እንደ ነገረው የሚገልጽ አንዳችም ጠቋሚ ነገር የለም:: ቍጥር 27 ላይ

[79] AT. Robertson, *Word Pictures in the New Testament* (Broadman Press, 1933), Volume I, p. 245; እንዲሁም የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል AT. Robertson, *A Grammar of the Greek New Testament* (Broadman Press, 1934), p. 593.



ኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ለአምልኮ ነው:: ይህም፣ ይህ ሰው ቢሆን ቢሆን የይሁዲን ሃይማኖት ተቀብሎ የነበረ አልያም ለይሁዲ እምነት ባይተዋር ያልነበረ ሰው መሆኑን የሚያሳየን ጕዳይ ነው:: አረማውያን በሙሉ የይሁዲን ሃይማኖት ሲቀበሉ ይጠመቃሉ[80]:: ግለሰቡም ይህን ስለተገነዘበ ነው ፊልጶስ ስለ ውሃ ጥምቀት ሳይነግረው ውሃ በሚያይበት ጊዜ ለፊልጶስ፣ "እነሆ እዚህ ውሃ አለ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ነገር ምንድን ነው" ያለው (ቍጥር 36፤ 1980 ትርጕም):: ስለዚህ ፊልጶስ የድነትን ወንጌል በሚናገርበት ጊዜ የውሃ ጥምቀትንም አያይዞ ሰብኳል የሚለው ድምዳሜ አሳማኝ አይደለም::

ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጀንደረባ ባገኘው ጊዜ ያነብ የነበረው ኢሳይያስ 53÷7-8 ያለውን ክፍል ቢሆንም፣ ከሐዋርያት ሥራ 8÷28 የምንማረው ቍም ነገር (ከሰዋሰው አወቃቀሩ)[81] ኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ከፊልጶስ ጋር ከመገናኘቱ በፊትም ሆነ ከተገናኘ በኋላ፣ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ እንደ ነበረ የሚያስገነዝበን ነው:: ከዚህም ጀንደረባው ኢሳይያስ 52÷15 እንዳነበበ መገመት እንችላለን:: ይህ ክፍል ደግሞ አይሁዶች አሕዛብ/አረማውያን የይሁዲ እምነትን ተቀብለው የውሃ ጥምቀት በሚወስዱበት ጊዜ አይሁድ አዝወትረው የሚጠቅሱት ክፍል ነው:: እነዚህ መረጃዎች የሚያሳዩን ፊልጶስ ለኢትዮጵያዊው ጀንደረባ የውሃን ጥምቀት አስቀድሞ እንዳልነገረው የሚያስገነዝቡን ናቸው::
ፊልጶስ ኢየሱስን በሰበከበት ወቅት የውሃ ጥምቀትን ለድኅነት አስፈላጊ ነው ብሎ እንዳልሰበከ፣ ከሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት መገንዘብ እንችላለን 1ቆሮንቶስ 1÷17:: ጳውሎስ የውሃ ጥምቀትን ከወንጌል መልእክት ነጥሎ የሚመለከት ከሆነ ፊልጶስ ግን የውሃ ጥምቀት የድነት ምክንያት አድርጎ ይመለከታል ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው፤ ምክንያቱም

[80] Reference: James Hastings, editor, "Baptism," *A Dictionary of the Bible* (Charles Scribner's Sons, 1905); Gerhard Kittel, editor, *Theological Dictionary of the New Testament* (Wm. B. Eerdman's Publishing Company, 1976); Everett F. Harrison, editor, *Baker's Dictionary of Theology* (Baker Book House, 1975).

[81] "ያነብ ነበር"—ግሪክ "ἀνεγίνωσκεν"—የሚለው የግሪክ ቃል—imperfect ነው—"he was reading":: ይህም ከፊልጶስ ጋር ከመገናኘቱም በፊት ያነብ እንደ ነበረና ከተገናኘም በኋላ ማንበቡን እንደ ቀጠለ የሚያሳይ ነው::

ቃለ እግዚአብሔር እርስ በርሱ አይቃረንምና:: በአጠቃላይ ፊልጶስ የውሃ ጥምቀትን የወንጌል ትምህርት አድርጎ ሊያስተምረው እንደሚችል እሙን ቢሆንም፣ የድነት ምክንያት አድርጎ እንደማይመለከተው ግን ቅቡል ነው:: በዚህ ክፍል እየተመለከትነው ያለነው ፊልጶስ ስለውሃ ጥምቀት ከመናገሩ በፊት ኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ራሱ ካለው ተሞክሮ ስለ ውሃ ጥምቀት ሊናገር እንደሚችል፣ ፊልጶስም የውሃ ጥምቀትን የድነት አንዱ ክፍል አድርጎ እንዳላቀረበ የሚያሳየን ጉዳይ ነው::

እነዚህን ሁሉ መረጃዎች መሠረት ካደረግን ሐዋርያት ሥራ 8÷35-38 ያለው ክፍል የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርስን እንደማይችል እሙን ነው:: ፊልጶስ የውሃ ጥምቀትን ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ አድርጎ አቅርቦታል ለማለት ግልጽ የሆነ መረጃ የለም ብቻ ሳይሆን፣ አንዳችም መረጃ የለም ወደሚለው ድምዳሜ እንደርሳለን:: በአጠቃላይ የሐዋርያት ሥራ 8÷35-38 የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚል አንዳችም ትምህርት የለውም::

## ሐዋርያት ሥራ 10÷48

### "በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው"

### "προσέταξεν δέ αὐτοὺς ἐν τῷ ὀνόματι Ἰησοῦ Χριστου"

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማንያንም ሆኑ መምህራን፣ የውሃ ጥምቀት ለዳግም ልደት አስፈላጊ ነው ለሚለው ግንዛቤአቸው እንደ ማጠናከሪያ/ማስረጃ አድርገው ከሚጠቀሙባቸው ክፍሎች መካከል ይህ አንዱ ነው:: ነገር ግን ወደዚህ ድምዳሜ የሚያደርስ አንዳችም ነጥብ በዚህ ክፍል ውስጥ አይገኝም:: የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የውሃ ጥምቀትን ችላ ማለት ስሕተት/ኀጢአት ነው የሚል ጽኑ እምነት አላቸው:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ይህ ጉዳይ ከኀጢአትም ዐልፎ የተጠማቂውን የዘላለም ዕጣ ፈንታ ይወስነዋል የሚለው አስተምህሮአቸው ግን አንዳችም የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ የለውም:: ምክንያቱም ድነት የኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛዊ ሥራ በማመን ብቻ በጸጋ እንደሚገኝ ቃለ እግዚአብሔር በማያሻማ መንገድ ይናገራልና ነው::

ይህ ክፍል ሰዎችን እንድናጠምቅ ማዘዙ ቅቡል ነው:: ነገር ግን የውሃ ጥምቀት ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ነው የሚል አንዳችም ትምህርት



የለውም:: ኀጢአት እንዳናደርግ ታዘናል፤ ነገር ግን ኀጢአት በማድረጋችን የዘላለም ሕይወት አናገኝም ማለት ግን ስሕተት ነው 1ዮሐንስ 2÷1:: ስለዚህ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ የጌታን ትእዛዝ ሳያከብሩ እንኳ ድኅነት እንደሚገኝ መገንዘብ ይቻላል—መጽደቅና መቀደስ እጅግ የተለያዩ ሐሳቦች ናቸውና[82]::

አትስረቅ፣ አትዋሽ ወዘተ ከሚሉት ትእዛዛት ይህን ትእዛዝ የሚለየው ጉዳይ ምንድን ነው? እነዚህን ትእዛዛት መጻረር ሥርየት ካለው፣ የውሃ ጥምቀት ግን ሥርየት የለውም ለማለት የሚያበቃን አጥጋቢ ምክንያት በዚህ ምንባብ ውስጥ ይገኛልን? ከቃለ እግዚአብሔር በግልጥ የምንማረው ቊም ነገር ድነት የማናገኝበት ኀጢአት ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ አለመቀበል ብቻ ነው (ዮሐንስ 8÷24፤ ማርቆስ 16÷16ለ፤ ሐዋርያት ሥራ 16÷31):: በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ለኀጢአት ሁሉ ይቅርታን የሚያስገኝ ታዛዥነት ነው (ቈላስይስ 1÷14፤ 1ዮሐንስ 1÷7-2÷2):: በእውነተኛው ክርስቶስ ላይ እውነተኛ እምነት ካለን፣ ከዘላለም ኵነኔ ወደ ዘላለም ሕይወት ተሸጋግረናል—ጸድቀናል (ሮሜ 3÷1-5: 23-28):: መጽደቅ ደግሞ ለድነት ብቸኛውና ዋነኛው ማረጋገጫ ነው (ሮሜ 8÷29-30):: በአጠቃላይ የሐዋርያት ሥራ 10÷48 ክርስቲያኖች እንዲጠመቁ መታዘዛቸውን ያስተምራል:: ነገር ግን የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊው ጉዳይ ነው አይልም::
ይህ ክፍል የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው የሚል ትምህርት የለውም ለማለት የሚያበቁን ሌሎችም ምክንያቶች በዚሁ ክፍል ውስጥ

---

[82] "መጽደቅ" እና "መቀደስ" የሚሉት ቃላት ሁለት የተለያየ ሐሳብ የሚወክሉ የነገረ መለኮት ቃላት ናቸው:: አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ በመቀበሉ ብቻ፣ ከዘላለም ኵነኔ ስላመለጠ "ጸድቋል"፤ "መቀደስ" ግን ሁለት ገጽ አለው፤ አንደኛው አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ በማመኑ የሚቀደሰውን ቅድስና የሚያመለክት ሲሆን (ይህ በእንግሊዝኛ positional sanctification በመባል ይጠራል፤ 1ቆሮንቶስ 1÷2፤ ሮሜ 1÷7)፤ በሌላ መልኩ ደግሞ በዕለት ተዕለት ኑሮው የሚቀደሰው ቅድስና አለ (ይህ ደግሞ ongoing sanctification ይባላል፤ ዘሌዋውያን 11÷44፤ ያዕቆብ 1÷15-16፤ 1ዮሐንስ 3÷3):: ብዙውን ጊዜ ሰዎች መጽደቅና መቀደስ የሚባሉት ቃላት የወከሏቸውን ትርጕሞች እርስ በርስ ሲያቀላቅሉ ይስተዋላል::

አሉ። ጴጥሮስ ይህን ክፍል የሚናገረው ለቆርኔሌዎስና ከእርሱ ጋር ለነበሩት ሰዎች ነው።

> እነዚህ እንደኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ፣ እንዳይጠመቁ ውሃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማነው? አለ። (ቊጥር 47)

ጴጥሮስ፣ "እነዚህ ሰዎች ልክ እንደኛው መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል" የሚለው አነጋገሩ "ልክ እንደነጴጥሮስ" እነዚህ ሰዎችም ድነት እንዳገኙ እምነት እንዳደረበት የሚገልጽ ነው። ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር ያሉት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እንደ ተቀበሉ ቆርኔሌዎስና ከእርሱ ጋር ያሉት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸው ድኅነት ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥ ነው። ቃለ እግዚአብሐር መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉ ሰዎች ድኅነት እንዳላቸው/ይመስክራል ሮሜ 8÷9-16።
የእግዚአብሔርን መንፈስ የተቀበሉ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። "ከመንፈስ ተወልደዋል"፤ "ዳግም ተዋልደዋል"፤ ለሚጠብቃቸው ርስት ዋስትና ተቀብለዋል (ሮሜ 8÷1:11፤ 2ቆሮንቶስ 1÷22: 5÷5፤ ኤፌሶን 1÷14)። ከዚህ የምንማረው ቊም ነገር ቆርኔሌዎስና ባልንጀሮቹ፣ ጴጥሮስ የውሃ ጥምቀት እንዲጠመቁ ከማዘዙ በፊት መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸው ድነት ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥ ነው። በአጠቃላይ የሐዋርያት ሥራ 10÷48 የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚል ትምህርት የለውም።

## ዕብራውያን 9÷19-20

"ሙሴ እያንዳንዱን የሕግ ትእዛዝ ለሕዝቡ ሁሉ ከተናገረ በኋላ የጥጆችን
ደም ከውሃ፣ ከቀይ የበግ ጠጕርና ከሂሶጵ ጋር ወስዶ፣ በመጽሐፉና
በሕዝቡ ላይ ረጨው፤ እንዲህም አለ፤ 'እንድትጠብቁት እግዚአብሔር
ያዘዛችሁ የኪዳኑ ደም ይህ ነው'"

ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ ይህን ክፍል መሠረት በማድረግ፣ "በኦሪት ዘመን ሙሴ ከበግ ወይም ከፍየል የወጣውን ደም ለእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት ከተጠበቀው ውሃ ጋር በሂሶጵ በማደባለቅ በሕዝቡና በመጽሐፉ ይረጨው ነበር ዕብራውያን 9÷19-20...ጥምቀት በእምነት ስንቀበላት



እንደምታድነን ሲመሰክር እኛ እንዴት ጥምቀት አታድንም ልንል እንደፍራለን?"[83] ይላሉ።

ይህ ትንተና ብሉያትንና ሐዲሳትን እንዲሁም የክፍሉን ዐውድ በቅጡ ያገናዘበ አይደለም። አንደኛ፤ ኀጢአትን የሚያስተሠርየው ደም ብቻ ነው የተባለበት ዋነኛ ምክንያት የእንስሳ ሁሉ ሕይወት በደም ውስጥ ስለሆነ፣ ደም ፈሰሰ ማለት ደግሞ ሕይወት ተከፈለ ማለት ስለሆነ ነው፣ "የፍጡር ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ በመሠዊያ ላይ ለሕይወታችሁ ማስተሥረያ እንዲሆን ደሙን ሰጥቻችኋለሁ፤ ለሰውም ሕይወት ሥርየት የሚያስገኘው ደም ነው" (ዘሌዋውያን 17÷11) ስለሚል እንዲሁም "ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም" (ዕብራውያን 9÷22)። በብሉይ ኪዳን የእንስሳ ደም እንዳይበላ የተከለከለበትም ዋነኛ ምክንያት ደም ለኀጢአት ሥርየት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ በመሆኑ ነው (ዘሌዋውያን 17)። ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት በግልጽ የሚያስተምሩን የኀጢአት ማስተሠረያ ደም ብቻ እንጂ ውሃ እንዳልሆነ ነው። አሮጌው ኪዳን በደም (በእንስሳ ደም) ላይ መሠረት እንዳደረገ ሁሉ አዲሱም ኪዳን ደምን (የኢየሱስ ክርስቶስን ደም) መሠረት ያደረገ ነው።

ሁለተኛ፤ የዕብራውያን ጸሓፊ 9÷19-20 ያለውን ክፍል የወሰደው ከዘፀአት 24÷4-8፤ ዘሌዋውያን 14÷4-5፤ እንዲሁም ዘኊልቊ 19÷18[84] ላይ ነው። በእነዚህ ክፍሎች ደግሞ ደሙ ብቻ እንጂ ከደሙ ጋር የተቀላቀለው ውሃ ስኀጢአት ሥርየት እንዳገለገለ አይናገሩም። እንዲያውም ውሃ ለኀጢአት ሥርየት አገለገለ የሚል እንዳችም የብሉይ ኪዳን ክፍል የለም[85]። ዕብራውያን 9÷19-20 መሠረት በማድረግ ብቻ ውሃው ከደሙ

[83] ዝኒ. ከማሁ፤ 30-31። በቅንፍ ያለውን ይጨምራል።
[84] በዚህ ክፍል ውሃው በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚገኙትን ዕቃዎች እንዲሁም ሬሳ/አስከሬን የነካውን ሰው ለማጽዳት እንጂ የኀጢአት ሥርየት ለማስገኘት አይደለም። ክፍሉ ሥርዐተ አምልኮ ለማካሄድ በደረግ ያለበትን ጽዱነት የሚያሳይ አካላዊ የመንጻት ሥርዐትን አመላካች እንጂ፣ ኀጢአት ሥርየትን የሚያሳይ አይደለም። የመንጻት ሥርዐት መሥዋዕት ማቅረብንና መታጠብን ያካትታል።
[85] ዘፀአት 30÷20-21፤ ዘኊልቊ 19÷9:13 አካላዊ መንጻትን የሚያሳይ ነው። በሕጉ የተደነገገውን ይህን ሥርዐት ተግባራዊ ያለማድረግ ደግሞ ኀጢአት ነው። ይህ እውነት

ጋር በመቀላቀሉ ብቻ ሥርየት ያስገኛል ከተባለ፣ ከደሙ ጋር የተቀላቀለው ውሃ ብቻ ሳይሆን ቀይ የበግ ጠጕርና ሂሶጵ[86] ጭምር በመሆኑ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለኀጢአት ሥርየት አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው ሊባል ነውን? ቀይ የበግ ጠጕርና ሂሶጵ ለኀጢአት ሥርየት አስፈላጊ ጉዳዮች አይደሉም ከተባለ ደግሞ፣ አብሯቸው የተጠቀሰው ውሃ ለኀጢአት ሥርየት አስፈላጊ ነው የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ እነዚህ ነገሮች ምን ትርጕም ይወክላሉ የሚለውን ጕዳይ ከብሉያት ጋር እያመሳከረ ያጣናል እንጂ፣ ከደም ጋር በመቀባቀላቸው ብቻ የኀጢአት ሥርየት ያስገኛሉ ማለት ክፍሉ ያልተናገረውን ነገር እንደ መሻታችን ማናገር እንዲሁም ከክፍሉ ትምህርት ጋር መቃረን ነው:: ሦስተኛ፤ የዕብራውያን መልእክት በሙሉ እንዲሁም እየተወያየንበት የሚገኘው ክፍል (ምዕራፍ 9) የኀጢአት ሥርየት በደም ብቻ እንሚገኝ እንዲሁም በክርስቶስ ሞት ብቻ ከኀጢ አት ነጻ መውጣት እንደሚቻል ይገልጻል (በተለይ ቍጥር 11-28 ይመለከቷል)::

አራተኛ፤ በርካታ የብሉይ ሊቃውንት በዚህ ክፍል "ውሃ" የሚለው ቃል ካህኑ ወደ መሠዊያ አገልግሎቱ ሕዝቡም ወደ መቅደሱ ከመምጣቱ በፊት ጽዱ ሆኖ በአምላኩ ፊት ለመቅረብ የሚፈጽመውን የአምልኮ ሥርዐት የሚያሳይ ሊሆን ይችላል የሚል አመለካከት አላቸው (ዕብራውያን 8÷6):: የመጀመሪያው (በደሙ መረጨት) ውስጣዊና መንፈሳዊ እንዲሁም "ልባዊ" ነው (ሮሜ 2÷28-29)፤ ሁለተኛው ግን በንጹሕ ውሃ (መታጠብ) ግን ውጫዊና ቍሳዊ (ሮሜ 2÷28-29) ነው::

አምስተኛ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ውሃ" የሚለው ቃል ሁሉ፣ የውሃ ጥምቀትን የሚያመለክት ነው የሚለው አስተሳሰብ፣ የአንድን ቃል ትርጕም የሚወስነው ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ወይም ዐውድ ነው፤ በዚህ ዐይነቱም ሁኔታ ውስጥ አንድ ቃል ከአንድ በላይ ትርጕም ሊወክል ይችላል የሚለውን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚፈቱበትን

ሆኖ ሳለ ውሃ ለኀጢአት ሥርየት ሕዝቡን ወክሎ ይቀርባል ወይም የድነት ቅድመ ሁኔታ ነው የሚል እንዳችም የብሉይ ኪዳን ክፍል የለም::

[86] በብሉይ ኪዳን በሥርዐቱ መሠረት ለሚደረገው መንጻት ሰዎችንም ሆነ የመቅደሱን ዕቃዎች ለመርጨት የሚያገለግል የተክል ዐይነት ነው::



መሠረታዊ ሕግ የሚጻረር ነው[87]:: ቄስ ተክለ ማርያም በዚህ ክፍል "ውሃ" የሚለው ቃል የውሃ ጥምቀትን የሚወክል ለመሆኑ ምን ማስረጃ አላቸው? በቃለ እግዚአብሔር "ውሃ" የሚለው ቃል ሁሉ የውሃ ጥምቀትን የሚያመለክት ነው የሚለው አስተሳሰብ መሠረቱ ምንድን ነው?

## 1ዮሐንስ 5÷6

"በውሃና በደም የመጣው ይህ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱ በውሃና በደም እንጂ በውሃ ብቻ አልመጣም:: የሚመሰክረውም መንፈስ ነው፤ መንፈስ እውነት ነውና"

ቄስ ተክለ ማርያም ይህን ክፍል በተመለከተ እንዲህ ይላሉ፣ "ክርስቶስ በውሃው፣ በደሙና በመንፈሱ ሊያድነን መጣ 1ዮሐንስ 5÷6-8፤ ሕዝቅኤል 36÷25-27"[88]:: "ደሙና ውሃው ከጐኑ ሲወጡ በአንድነት እንጂ ተለያይተው ስላልወጡ በማዳን ሥራቸውም አይለያዩም 1ዮሐንስ 5÷6-7"[89]:: "ሙሴ የኰርማዎችንና የፍየሎችን ደም ከውሃ ጋር ቀላቅሎ ሲረጭ እንደ ነበር ሁሉ፣ ክርስቶስም የራሱን ደምና ውሃ በአንድ ላይ

[87] ለምሳሌ በዚሁ መጽሐፍ ዕብራውያን 10÷22 ብንመለከት፣ "ውሃ" የሚለው ቃል ካህኑ በክህነት አገልግሎቱ ወቅት ጽዱ ሆኖ ለመቅረብ አካሉን የሚታጠብበትን ውሃ የሚያመለክት እንጂ፣ የውሃ ጥምቀትን የሚያሳይ አይደለም:: ይህ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም የመርጨት ሐሳብ የተቀዳው ከብሉይ ኪዳን ነው:: የብሉይ ኪዳን አገልጋዮች የሚወክላቸውን እንስሳ ካቀረቡ በኋላ (ዘሌዋውያን 8÷22)፣ የእንስሳውን ደም በሕዝቡ ላይ ይረጩታል (ዕብራውያን 9÷19፤ ዘፀአት 24÷8):: ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር በግ በሆነው (ዘፍጥረት 22÷8) በመሲሑ ደም ታጥቦ ለሚነጻው ልብ ተምሳሌት ነው (ኢሳይያስ 53):: ነገር ግን "በውሃ መታጠብ" (ዕብራውያን 10÷22) ካህኑ ወደ መሠዊያ አገልግሎቱ ከመሄዱ በፊት ጽዱ ሆኖ ለመቅረብ የሚፈጽመው ሥርዐት ነው (ዕብራውያን 8÷6):: የመጀመሪያው (በደሙ መረጨት) ውስጣዊና መንፈሳዊ እንዲሁም "ልባዊ" ነው (ሮሜ 2÷28-29)፤ ሁለተኛው ግን በንጹሕ ውሃ (መታጠብ) ግን ውጫዊና ቍሳዊ (ሮሜ 2÷28-29) ነው::

[88] ዝኒ ከማሁ፤ 30-31:: በቅንፍ ያለውን ይጨምራል::

[89] ዝኒ ከማሁ፤ 76::

ከጉኑ በማመንጨት የመጻንን በር ከፍቶአል 1ዮሐንስ 5፥6-7፤ ዮሐንስ 19፥34"[90]። "በዚህ በፍጻሜ ዘመን ያለው ትውልድ ደግሞ የዘላለም ሕይወት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በውሃ ተጠምቆ እንዳይድን አሻፈረኝ! የውሃ ጥምቀት አያድንም! በማለት የገዛ ራሱን ፍልስፍና ተከትሎ በመፋነን የእግዚአብሔርን መንገድ እንደ ሳተ የታመነ ነው። በመስቀል ላይ የፈሰሰውን ውሃና ደም በስሙ አማካይነት በጥልቅ ውሃ ውስጥ በመጠመቅ እንድንቀበለው አዘዘን"[91]።

ቄስ ተክለ ማርያም እንዲህ ይበሉ እንጂ፣ የሐዲስ ኪዳን ትምህርተ ዘለቅ ክፍሉን በተመለከተ የሚሰጡት ዐውዳዊና ታሪካዊ ትንተና ከዚህ ፍጹም የተለየ ነው።

"ውሃና ደም" የሚለው ሐረግ ምን ትርጉም ይወክላል በሚለው ጉዳይ ሦስት ታላላቅ አመለካከቶች ያሉ ሲሆን፣ ስመ ጥር በሚባሉ በርካታ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት ተቀባይነት ያለው እንዲሁም ከክፍሉ ታሪካዊና ዐውዳዊ ትርጉም ጋር ተጣጥሞ የሚሄደው አመለካከት፣ በመጀመሪያ በትልቁ የቤተ ክርስቲያን አባት በተርቱሊያን የቀረበው ትንተና ነው[92]። በዚህ ትንተና መሠረት "'ውሃ' የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት የሚያመለክት ሲሆን፣ በዚህም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዲሁም ለሥራው እንደ ተሾመና ኀይልን እንደ ተቀበለ ያስረገጠበት ሲሆን፣ 'ደሙ' ደግሞ ኀላፊነቱን/ሥራውን ያጠናቀቀበትን ሞቱን ያመለክታል"[93]። "ውሃ" እና "ደም" በዚህ ስፍራ መጠቀሳቸው፣ የኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት በጥምቀት ተጀምሮ በሞቱ ስለተፈጸመ ነው። እንደ ጆን ስቶት ያሉ ስመ ጥር የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት፣ ይህ ትንተና ታሪካዊ ዳራውን በግምት ውስጥ ያስገባ እንደ ሆነ ይገልጻሉ[94]። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ሔሬኔዎስ በወቅቱ የነበረውን

[90] ዝኒ ከማሁ፣ 78።

[91] ዝኒ ከማሁ፣ 32።

[92] John R.W. Stott, *The Letters of John* (Grand Rapids: Eerdmans; Leicester: Inter-Varsity, 1964), 179.

[93] ዝኒ ከማሁ።

[94] ዝኒ ከማሁ፣ 180።



የሲሬንቱስንና የተከታዮቹን ኑፋቄ እንደ ገለጸው፣ እነዚህ ሰዎች "ኢየሱስ" እና "ክርስቶስ" የሚሉትን ለያይተዋቸዋል። በትምህርታቸው መሠረት ኢየሱስ ከዮሴፍና ከማርያም ጋብቻ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ የተወለደ ሰው ብቻ ሲሆንም እንኳ፣ በጥምቀቱ ወቅት ክርስቶስነት የወረደበት ሲሆን፣ ስቅላቱ በፊት ክርስቶስነት ተለይቶት ሄዷል ይላሉ። በዚህ የኑፋቄ ትምህርት መሠረት፣ "ኢየሱስ" እና "ክርስቶስ" ኅብረት የፈጠሩት በጥምቀቱ ወቅት ሲሆን፣ የተለያዩት ደግሞ ከመስቀሉ በፊት ነው። ስለዚህ በመስቀል ላይ የሞተው ሰው ብቻ የሆነው ኢየሱስ ነው በማለት እነዚህ መናፍቃን ያስተምሩ ነበር። በዚህ መልእክት ውስጥ ዮሐንስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እምላክም ሰውም እንደ ሆነ በእጽንዖት ይናገራል (ለምሳሌ 1፥1-4፤ 4፥2፤ 5፥5 ይመለከቷል)። ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም እንደ መጣ፣ እንደ ተጠመቀና እንደ ሞተም ጽፎአል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የነበረው በጥምቀቱ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ በሞቱም ጊዜ ነበር (ቍጥር 6)። ኢየሱስ ሰው ብቻ ሆኖ ቢሞት ኖሮ ደግሞ፣ የሰዎችን ኀጢአት ማስተሰረይ አይችልም ነበር (2፥2፤ 4፥10)።

ክፍሉ፣ ኢየሱስ በውሃ ብቻ አልመጣም ይላል እንጂ፣ "ውሃ የሚለው ቃል ጥምቀትን የሚያመለክት ነው፤ ይህም ጥምቀት ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ነው" የሚል ሐሳብ የለውም። ነገር ግን ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ በመጽሐፍ ቅዱስ "ውሃ" የሚለው ቃል ሁሉ፣ የውሃ ጥምቀትን የሚያመለክት ነው በሚል የተሳሳተና መረጃ አልባ በሆነ መቅድመ ልባዊ/ቅድመ ግንዛቤ ቃለ እግዚአብሔርን መተንተን ስለጀመሩ በክፍሉ ውስጥ ያልተጠቀሱትን ሐሳቦች ከቶ በማንበብ ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ መሄድ ግድ ሆኖባቸዋል። የአንደኛ ዮሐንስ መልእክት የተጻፈበትን ዐላማ፣ የተጻፈበትን ታሪካዊ መቼት እንዲሁም የክፍሉን ዐውዳዊ ትርጉም በትክክል የተገነዘበ እንዲሁም እነዚህ ሁኔታዎች ቃለ እግዚአብሔርን ለመተርጐም መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው የሚል ማንኛውም ሰው፣ ከእንዲህ ዐይነቱ ስሕተት እንደሚጠበቅ እሙን ነው። በአጠቃላይ ይህ ክፍል የውሃ ጥምቀት ለድነት ቅድመ ሁኔታ ነው የሚል ትምህርት የለውም።

## ሉቃስ 7፥30

"ፈሪሳውያንና ሕግ ዐዋቂዎች ግን በእርሱ ስላልተጠመቁ፣ የእግዚአብሔርን ምክር ከራሳቸው ጣሉ"

ክፍሉ ስለመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት እንጂ ስለ ክርስቲያናዊ ጥምቀት የሚናገር አይደለም (የክፍሉን ዐውድ ይመለከቷል)። ስለዚህ ክፍሉ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚለውን ትምህርት የሚመለከት አይደለም። ከሐዋርያት ሥራ 18፥24-19፥7 የምንማረው የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት በአሁኑ ዘመን ተቀባይነት እንደሌለው ነው። በአጠቃላይ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው በሚል ሰው ይህን ክፍል በማስረጃነት ማቅረቡ ስሕተት ነው።

## ማጠቃለያ

ምንም እንኳ ያለመጠመቅ የክርስቶስን ትእዛዝ ያለመፈጸም በመሆኑ ኀጢአት ቢሆንም[95]፣ ያለመጠመቅ ከድነት አያጉድልም (ቆርኔሌዎስና ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች የውሃ ጥምቀት ከመውሰዳቸው በፊት ድነት አግኝተዋል—ሐዋርያት ሥራ 10፥47-48—ከጌታ ጋር የተሰቀለውም ሰው የውሃ ጥምቀት ከመውሰዱ በፊት ነው ድነት ያገኘው—ሉቃስ 23፥39-43—ሐዋርያው ጳውሎስ የውሃ ጥምቀት ከመውሰዱ በፊት ድነት አግኝቶአል—ሐዋርያት ሥራ 9፥17)።

የውሃን ጥምቀት አስፈላጊ የሚያደርጉት ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ። እነርሱም 1) የውሃ ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ ያዘዘው አስፈላጊ ሥርዐት ነው ማቴዎስ 28፥19 ይህን አምላካዊ ትእዛዝ መጻረር ደግሞ

[95]አትስረቅ፣ አትዋሽ ወዘተ የሚሉትን ትእዛዛት መጻረር ኀጢአት ነው። እነዚህን ትእዛዛት መተላለፍ ሥርየት ካለው፣ የውሃ ጥምቀት ግን ሥርየት የለውም ለማለት የሚያበቃን አጥጋቢ ምክንያት የለም። ከቃለ እግዚአብሔር በግልጥ የምንማረው ቀኍም ነገር ድነት የማናገኝበት ኀጢአት ወይም ሥርየት የሌለው ኀጢአት ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ አለመቀበል ብቻ ነው (ዮሐንስ 8፥24፤ ማርቆስ 16፥16ለ፤ ሐዋርያት ሥራ 16፥31)። ታላላቅ የሚባሉት ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን ሥርዐቶች የጌታ ራትና የውሃ ጥምቀት እንደ ሆኑ ልብ ይሏል።



ኀጢአት ነው። 2) የውሃ ጥምቀት ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ኪዳናዊ ግንኙነት የሚያመለክት ማኅተም/ምልክት ስለሆነ እጅግ አስፈላጊ ሥርዐት ነው። 3) አማኙ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልጥበት/የሚያውጅበት ሥርዐት ነው (በጌታ ራት ላይ ተካፋይ እንደ መሆን)።

የውሃ ጥምቀት ይህ ዐይነት ታላቅ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም፣ ቃለ እግዚአብሔር የውሃ ጥምቀት ለድነት ወይም ለዳግም ልደት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚል አንዳችም ትምህርት የለውም። መጠመቅ ሲቻል ያለመጠመቅ ኀጢአት ቢሆንም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት እንደሚያነጻ ሁሉ ለዚህም ኀጢአት ይቅርታ አለ (ቈላስይስ 1፥14፤ 1ዮሐንስ 1፥7)። መጽሐፍ ቅዱስ ሥርየት የሌለው ኀጢአት መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ብቻ ነው ይላል (ማቴዎስ 12፥31-32 እንደ ክፍሉ ትምህርት መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ማለት (ቢያንስ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ትንታኔ)፣ የኢየሱስ ክርስቶስን የድነት አገልግሎት ያለመቀበል ወይም የኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ ያለመቀበል ማለት ነው)።

የፊልጵስዩስ እስር ቤት ዘበኛ፣ "እድን ዘንድ ምን ላድርግ" ሲል ጳውሎስና ሲላስን በጠየቃቸው ጊዜ፣ የሰጡት አጭርና ቀጥተኛ መልስ፣ "በጌታ በኢየሱስ እመን፤ አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ አሉት" (ሐዋርያት ሥራ 16፥31-32)[96]። ድነት ያገኘነው በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ ብቻ ነው። ይኸውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን በመቀበላችን። ድነት ለማግኘት ከማመን ውጪ ልናደርገው የምንችለው ወይም የሚገባን አንዳችም ነገር የለም "በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ

[96]ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፣ "ጳውሎስና ሲላስ ይህን ሰው በእኩለ ሌሊት አቻኩለው ያጠመቁት እምነት ብቻ እንደማያድን ነገር ግን የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ መሆኑን ስለተገነዘቡ ነው" ቢሉም፣ ግለሰቡ "እድን ዘንድ ምን ላድርግ" ብሎ በጠየቀ ጊዜ የተሰጠው መልስ፣ "እመን" የሚል እንጂ ተጠመቅ የሚል አይደለም። ነገር ግን ያመነ ሰው መጠመቅ ስላለበት አጥምቀውታል። "አቻኩለው" ያጠመቁት የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ስለሆነ ነው የሚል ሐሳብ በምንባቡ ላይ አልተጠቀሰም።

አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም" (ኤፌሶን 2፥8-9)። ስለዚህ፣ "ማንም ሰው ሕግን በመፈጸም ሳይሆን፣ በእምነት እንደሚጸድቅ እናረጋግጣለን" (ሮሜ 3፥28)። እውነተኛ እምነት መልካምን ሥራ ፍሬው ያደረገ ነው (ያዕቆብ 2፥19)፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ድነት የሰጠን በማመናችን እንጂ በመልካም ሥራችን አይደለም። ቃለ እግዚአብሔር ሰው በማመን ብቻ ድነት እንደሚያገኝ በሰፋት ይናገራል (ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ምንባባት ይመልከቱ ዮሐንስ 3፥16፤ ሮሜ 1፥16-17፤ 3፥20-28፤ 4፥1-8:13-16:23:25፤ 5፥1፤ 6፥23፤ 8፥30፤ ገላትያ 2፥16:21፤ 3፥2-3:10-24፤ ኤፌሶን 2፥8-10፤ ቲቶ 3፥5-7፤ 1ጴጥሮስ 1፥2-9)። በእምነት በጸጋ አማካይነት ድነት አግኝተናል፤ የሕግን ሥራ በመፈጸም ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ጸድቀናል (ሮሜ 1፥16-17፤ 1ጴጥሮስ 1፥9)።

ከዚህ ጥናት በግልጥ የምንገነዘበው ጉዳይ፣ የውሃ ጥምቀት ለድነት እንዲሁም ለዳግም ልደት አስፈላጊ ነው የሚለው ትምህርት "ልዩ ወንጌል" (ገላትያ 1፥8-9) እንደ ሆነ ነው። የውሃ ጥምቀት ለድነት ያስፈልጋል የሚሉ ሰዎችም ከወንጌሉ ትምህርት በመራቅ በራሳቸው የጽድቅ ሥራ ላይ ታምነዋል፤ ይህ ደግሞ ስሕተት ነው (ቲቶ 3፥5)፤ አስተምህሮአቸው ቃለ እግዚአብሔር ስለድነት ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር በቀጥታ ይቃረናልና። ድነት የብሉይ ኪዳን ሥርዐትን በመጠበቅ ወይም በሌላ መንገድ ይገኛል ሲሉ፣ እንደ ነበሩት ሰዎች ሁሉ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚሉም ሰዎች ተመሳሳይ የሆነን ስሕተት እየደገሙ ነው (ሮሜ 8፥1-4፤ ገላትያ 3)። የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው የሚሉ ሰዎች ሁሉ "የተረገሙ ናቸው" ማለት ግን እንዳልሆነ ልብ ይሏል (ገላትያ 1፥8-9)። ከስሕተታቸው ተመልሰው አንድ ሰው በእምነት በጸጋ አማካይነት ይድናል ለሚሉ ሁሉ (ዮሐንስ 10፥27-29፤ 1ጴጥሮስ 1፥4-9) እግዚአብሔር ምሕረት አለው።



## 4. የውሃ ጥምቀት ውጤታማ የሚሆነው በጥልቅ ውሃ ሲካሄድ ብቻ ነውን?

በኢትዮጵያ፣ ከሉተራን/ከመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በስተቀር፣ ሁሉም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት (በኢትዮጵያ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ከታቀፉ አብያተ ክርስቲያናት) የሚያጠምቁት በጥልቅ ውሃ ውስጥ በማስመጥ ነው። የውሃ ጥምቀት፣ ለዳግም መወለድም ሆነ ኀጢአትን ለማጠብ አስፈላጊ ጉዳይ እስካልሆነ ድረስ፣ ድነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዴት እናጥምቅ የሚለው ጉዳይ አስፈላጊ አይደለም። ልክ እንደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ፣ እነዚህም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የውሃ ጥምቀትን በጥልቅ ውሃ ውስጥ ተጠማቂውን በማስመጥ ማካሄድ አለበት ይበሉ እንጂ፣ የውሃ ጥምቀት ለድነትም ሆነ ኀጢአትን ለማጠብ አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚል አንዳችም ትምህርት ስለሌላቸው እንዴት እናጥምቅ የሚለው ጉዳይ አወዛጋቢ አይደለም።

ይህ እንዳለ ሆኖ "ጥምቀት" (በግሪኩ "βαπτιζω") በሚለው ቃል ላይ የተካሄዱ በርካታ ታሪካዊና ነገረ መለኮታዊ ጥናቶች፣ የውሃ ጥምቀት ተጠማቂውን በጥልቅ ውሃ ውስጥ በማስመጥ ብቻ መካሄድ አለበት የሚለውን ጉዳይ አይደግፉም[97]።

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከጻፉአቸው ጽሑፎች የምንማረውም ይህንኑ እውነት ነው። ለምሳሌ ዲዳኬ (ትምህርተ ሐዋርያት) በመባል የሚታወቀው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮና የአስተምህሮ መጽሐፍ፣ "ጥምቀትን በተመለከተ ማጥመቅ የሚገባን እንደሚከተለው ነው፤ የሚከተሉትን ነጥቦች ሁሉ በአደባባይ አስተምር ከዚያም በሚፈስ ውሃ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ

[97] ለምሳሌ "ጥምቀት" በሚለው ቃል ላይ ብቻ የሚያጠነጥነውንና ከ1,300 ገጽ በላይ ያለውን የጀምስ ዳልን አራት ቅጽ መጻሕፍት በናሙናነት መመልከት ይቻላል። James W. Dale, *Christic and Patristic Baptism: An Inquiry into the Meaning of the Word as Determined by the Usage of the Holy Scriptures and Patristic Writers.* 1874. Reprint. Phillipsburg, (N.J.: Presbyterian & Reformed; Wauconda, Ill.: Bolchazy-Carducci; and Toney, Ala.: Loewe Belfort Projects, 1995).

ቅዱስ ስም አጥምቅ፤ ፈሳሽ ውሃ ከሌለ፣ በሌላ መንገድ አጥምቅ፤ ቀዝቃዛ ውሃ ከሌለ በሞቀ ውሃ አጥምቅ፤ ይህ ሁሉ ከሌለም በተጠማቂው ራስ ላይ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሦስት ጊዜ ውሃ አፍስስ"[98]:: በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኖረው ካርታጎ/ቅርጣግና (Carthage) ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቆጵርያኖስ (Cyprian) የውሃ ጥምቀት በማስመጥ ወይስ በተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ በመርጨት መካሄድ አለበት የሚለውን ጉዳይ ሲጠየቅ እንዲህ ሲል ነበር የመለሰው፣ "የውሃ ጥምቀትን በተመለከተ እንዴት ሳጥምቅ የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ አይደለም...በመርጨትም ማጥመቅ ይቻላል...ይህን ማድረጋቸው አጥማቂውም ሆነ ተጠማቂው አልተሳሳቱም"[99]::

በምን መልክ እናጥምቅ የሚለው ጉዳይ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ሊያከራክር ይችላል፤ ነገር ግን የውሃ ጥምቀት ለድነት ወሳኝ ጉዳይ እስካልሆነ ደረስ፣ እንዴት እናጥምቅ የሚሰውም ጉዳይ ወሳኝ ርእስ ጉዳይ ሊሆን በፍጹም አይችልም[100]::

## 5. የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ መካሄድ አለበትን?

ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ እንደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" (ማቴዎስ 28÷19) ሳይሆን፣ በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደምንመለከተው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው:: እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ ለዚህ አራት ዐበይት ምክንያቶች አሉ:: አንደኛው፤ ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ፣ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የሚለው ስም የኢየሱስ ስም መሆኑን በማወቃቸው፣

[98] *Didache,* 7:1-3; Lightfoot and Harmer, *Apostolic Fathers,* 232.

[99] Cyprian, Epistle LXXV.12, in *ANF,* 5:401.

[100] የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ የውሃ ጥምቀት በጥልቅ ውሃ ውስጥ ተጠማቂውን በማስመጥ ቢካሄድ የሚመርጥ ቢሆንም፣ የውሃ ጥምቀት በተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ በመርጨትም ሆነ በማፍሰስ ቢካሄድ ትክክል አይደለም የሚል አቋም የለውም::



ከበዓለ ኀምሳ ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርት ያጠመቁት በኢየሱስ ስም ነው[101]:: ሁለተኛ፤ በማቴዎስ 28÷19 ላይ፣ "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" የሚለው የጥምቀት ቀመር በተጸውዖ (በመጠሪያ ስም) ሳይሆን በማዕረግ ስም ስለቀረበ በጥምቀት ቀመርነት ሊያገለግል አይችልም:: እንዲሁም በክፍሉ ላይ "ስም" የሚለው ቃል፣ የነጠላ ቍጥርን እንጂ የብዙ ቍጥርን አለማሳየቱ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የሚለው "የማዕረግ ስም" የኢየሱስን ስም እንደሚያሳይ የሚያስገነዝብ ነው:: ሦስተኛ፤ አብ በሥጋ ከመገለጡ ወይም ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት ሰዎችን ሊያድንበት ዐቅዶ በሰማያት ሰውሮ ያስቀመጠው የመለኮት (የአብ) ስም ኢየሱስ ስለሆነ፣ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ መጠመቅ አለባቸው:: አራተኛ፤ ሰዎች "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" (ማቴዎስ 28÷19) ሊጠመቁ የምናይበት አንዳችም ስፍራ የለም::

ሰዎች "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ብቻ መጠመቅ አለባቸው ይህም ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ነው የሚለው የድርጅቱ ትምህርት ስሕተት ነው:: ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉ:: *አንደኛ፤* ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው የውሃ ጥምቀት ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ካልሆነ፣ በማን ስም

[101] ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት፣ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የበላይ ጠባቂ ከሆኑት ከቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝና ከቤተ ክርስቲያኒቱ የኮሌጅ ፕሬዝደንት ከቄስ አየለ ላቀው ጋር ታኅሣሥ 24 ቀን 1999 ዓ.ም በቄስ ተክለ ማርያም ቢሮ ባካሄደው ውይይት፣ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ "ማቴዎስ 28÷19 ካቶሊኮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጨመሩት ክፍል ነው፤ ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር ሐዋርያት ሥራ 2÷38 ነው" የሚል አስተያየት በጥተዋል:: ቤተ ክርስቲያን ምሥራቅና ምዕራብ (ካቶሊክና ኦርቶዶክስ) ተብላ ለሁለት የተከፈለችው 1054 ዓ.ም ላይ ሆኖ ሳለ፣ "የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጨመረችው" የሚለው ሐሳብ፣ ታሪክን መሠረት ያደረገ አይደለም:: እጅግ ጥንታዊና ተአማኒነት አላቸው የሚባሉትን የግሪክ ቅጆች (1054 ዓ.ም በፊት የተጻፉ) እንዲሁም ጥንታዊ ድርሳናት *በሙሉ* ማቴዎስ 28÷19 ማካተታቸው ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ ይህ ክፍል የማቴዎስ ወንጌል ክፍል አይደለም ያለ ወይም መሆኑን ለማስተባበል የሞከረ *አንዳችም* ሰው የለም:: ክፍሉን በተመለከተ አንዳችም ምንባባዊ አማራጭ (textual variants) ያስመቅረቡንም ከግሪክ ቅጆች ላይ በመመልከት የሐያስያኑን ባዶ ትችት መገንዘብ ይቻላል::

እናጥምቅ የሚለው ጉዳይ ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ሊሆን አይችልም። ሁለተኛ፤ ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" ካልሆነ፣ በማንስ ስም ሊሆን ይችላል? ምክንያቱም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ወጥነት ያለውና እንደ ቀመር ልንጠቀምበት የምንችለው ለንጻችም የጥምቀት ቀመር የለም። በሐዋርያት ሥራ 2፥38 ላይ፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም [ἐπί τῷ ὀνόματι Ἰησοῦ Χριστου]" ሲል፣ በሐዋርያት ሥራ 8፥16 እና 19፥5፣ "በጌታ በኢየሱስ ስም [εἰς τὸ ο῎νομα τοῦ κυρίου Ἰησοῦ]"፣ በሐዋርያት ሥራ 10፥48፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ἐν τῷ ὀνόματι Ἰησοῦ Χριστου" ይላል። በሐዋርያት ሥራ 10፥48፣ ደግሞ፣ "ስሙን እየጠራህ [ἐπικαλεσάμενος τὸ ὄνομα αὐτοῦ" ] ይላል። በእነዚህ ምንባባት ውስጥ የመስተዋድድ ልዩነት ብቻ ሳይሆን፣ መሠረታዊ የሆኑ ቃላት ልዩነትም አለ፤ እንግዲያው ቀመሩ የሚያድን ከሆነ፣ በየትኛው ቀመር እናጥምቅ? "በኢየሱስ ስም" እና "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" የሚለው ጉዳይ በተለይ በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ዕይታ ሲታይ፣ ከፍተኛ ለውጥ አለው። "ኢየሱስ" ማለት የአብ (የአምላክ) ሰብአዊ አካል ሲሆን፣ "ጌታ" ደግሞ መለኮት ነው። "ጌታ ኢየሱስ" የሚለው ስያሜ አብና ወልድን የሚያሳይ ሲሆን (በአንድ ሰብዕና)፣ "ኢየሱስ" የሚለው ግን ሰባዊ ተፈጥሮን ብቻ ያሳያል። ይህ እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ትክክለኛው ቀመር የቱ ነው?[102]

ሦስተኛ፤ ከታሪክ መጻሕፍት ቀኖናዊ ሕግጋትን/አስተምህሮዎችን ለማውጣት መሞከር ከቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ ጋር በጽኑ የሚቃረን ነው። የታሪክ መጻሕፍት ምን እንደ ተካሄደ የሚነግሩን ምንባባት እንጂ ምን መሆን እንዳለበት የሚያስተምሩን መጻሕፍት አይደሉምና። የሐዋርያት ሥራ፣ ሉቃስ ለቴዎፍሎስ የጻፈለት ታሪካዊ ዘገባ ነው (ሐዋርያት ሥራ 1፥1)። ይህም ሉቃስ፣ ለቴዎፍሎስ የሐዋርያቱን ገድልና የመጀመሪያዪቱን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲያውቅ የጻፈለት ጽሑፍ እንጂ፣ ነገረ መለኮት ሊያስተምረው ያዘጋጀለት ድርሳን አይደለም። ከቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ

---

[102] ትክክለኛውን የጥምቀት ቀመር የቱ ነው በሚለው ጉዳይ ላይ በውጪው ዓለም የሚገኙ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አባላትን ከፋኛ የሚያወዛግብ ጉዳይ ነው።



ከምንማራቸው ሕግጋት መኻል አንዱ ሕግ፣ የታሪክ መጻሕፍት (መስተጋብአዊ ምንባባት)[103] መብራራት ያለባቸው ምንጩታዊ ምንባባት (አስተምህሮአዊ ምንባባት)[104] ከሚያስተምሩት ትምህርት አንጻር ብቻ ነው የሚለው ሕግ ነው። ለምሳሌ "ጻድቅ ሲጣል ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም" የሚለውን የዳዊት አነጋገር ዘመን የማይሽረው እውነታ ነው (በየትኛውም ዘመን የሚኖሩ ጻድቃን ሊያውቁትና ሊከተሉት የሚገባ መርሕ ነው) ካልን፣ ክርስቲያን አይርበውም፣ አይጠማውም፣ ችግር አይደርስበትም ወዘተ ወደሚለው ድምዳሜ ("የብልጽግና ወንጌል" "prosperity gospel") ልንሄድ የግድ ይሆናል። "አላየሁም" ያለው ዳዊት ነው፤ እኛ ግን አይተናል፤ አያየንም ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር አንዳንድ ክርስቲያኖችን የተትረፈረፈ ምድራዊ ንዋይ አይሰጣቸውም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ይህን ክፍል ለሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ የሚያገለግል የምጣኔ ሀብት መርሐ ነው ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው (ከዳዊት የንግሥና ዘመን በኋላ እንኳ እጅግ አሠቃቂ የሆነ ራብ በምድረ እስራኤል በተደጋጋሚነት ተከሥቶ እንደ ነበር የሚዘነጋ አይደለም—ለምሳሌ የሰማርያን ራብ ልብ ይሏል። የእምነት ምዕራፍ በመባል የሚታወቀው ዕብራውያን 11 በዚህ ረገድ ጥሩ ትምህርት አለውና ይነበብ)። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን መሠረት በማድረግ (ለምሳሌ ምዕራፍ 2 እና 4) መንፈስ ቅዱስ በሚወርድበት ጊዜ ሁሉ ስፍራው ይናወጣል፣ እንደሚነጥቅ ዐውሎ ንፋስ ከሰማይ ድምፅ ይመጣል፣ እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ይታያሉ ወዘተ ብሎ ማስተማር ስሕተት ነው። በዚያ ታሪካዊ ወቅት እንዲያ ሆኗል ማለት፣ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን በሚሞላ ጊዜና ቦታ ሁሉ ይህ ዐይነቱ ታሪክ ይከሠታል ማለት አይደለም።

በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራንና ጸሓፍት ዘንድ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብን በተመለከተ ያለው ችግር እጅግ የጠለቀ ነው። ይህም ጉዳይ ነው ድርጅቱ በበርካታ አስተምህሮዎቹ ወደ ተሳሳተ የአስተምህሮ ድምዳሜ ሲዳርጋቸው የሚታየው። ይህን መሠረታዊ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ ሕግ በተመለከተ ክራምተን

---

[103] inductive

[104] deductive

የተባሉ የነገረ መለኮት ምሁር የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብን በተመለከተ በጻፉት መጽሐፍ ላይ እንዲህ ብለዋል:—

> ምንጩታዊ ምንባባት ነገረ መለኮታዊ እውነታዎችን የሚያስተምሩ ናቸው:: ለምሳሌ ወንጌላት ስለክርስቶስ ሕይወት የሚያስተምሩን ሲሆን፣ የሐዲስ ኪዳን መልእክቶች ደግሞ ኢየሱስ ያስተማረው ትምህርትና የሠራው ሥራ ለእኛ ያለው ፋይዳ ምን እንደ ሆነ የሚያብራሩልን መጻሕፍት ናቸው:: በባሕርያቸውም ምንጩታዊ ናቸው:: በሌላ መልኩ ደግሞ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚናገር መጽሐፍ ነው:: የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዐቢይ ዐላማ፣ አስተምህሮአዊ እውነታዎችን ማስተማር ሳይሆን፣ የሐዋርያቱን ገድልና በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መዘከር ነው::
>
> ይህ ማለት ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የምንማረው ትምህርት የለም ማለት አይደለም:: ነገር ግን የዚህን መጽሐፍ ትምህርት መመልከት ያለብን ከአስተምህሮአዊ መጻሕፍት ከሚያስተምሩት ትምህርት አንጻር ነው:: የታሪክ መጻሕፍትን ዋቢ በማድረግ አስተምህሮ መመሥረት በፍጹም የለብንም/አይቻልም[105]::

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን የደርጅቱን አስተምህሮ ያዋቀሩት ይህን መሠረታዊ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ በመጻረር ነው:: መሠረታዊ የሚባለው የድነት አስተምህሮቸው በሙሉ (ቢያንስ በአብዛኛው) የተዋቀረው ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው:: በማቴዎስ 28፥19 ላይ የሚገኘው የጥምቀት ቀመር የተሰጠው፣ ሐዋርያት ወንጌልን ይዘው ወደ አሕዛብ እንዲሄዱ ትእዛዝ በተሰጠበት ጊዜ ነው:: ይህ ደግሞ የማቴዎስ 28+19 ክፍል መመሪያ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው::

አራተኛ፤ በማቴዎስ 28፥19 ላይ የሚገኘውን ክፍል ማብራራት ያለብን ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አንጻር ነው፤ ይኸውም "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" የሚለው የጥምቀት ቀመር በሐዋርያት ሥራ

[105] W. Gary Crampton, *Biblical Hermeneutics* (Lakeland: Whitefield Press, 1986), 27.



መጽሐፍ፣ "በኢየሱስ ስም" ተብሎ መቅረቡ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" በመባል የሚጠራው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን የሚያመለክት ነው የሚለው የድርጅቱ ትንተና ከላይ ያየነውን የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ የሚጻረር ብቻ ሳይሆን፣ ምንጩታዊ ምንባባት መብራራት ያለባቸው ከመስተጋብአዊ ምንባባት አንጻር ነው የሚለውን ሕግ ገልብጦ የሚያነብ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ/ኢ-ሐቲታዊ አካሄድ ነው:: የማቴዎስ ወንጌል ሐዋርያት ሥራን ማብራራት ሲኖርበት የሐዋርያት ሥራ ማቴዎስን አብራርቶታልና:: ይህ የሥነ አፈታት አካሄድ ስሕተት ለመሆኑ ሰዋስዋዊ ማስረጃ እናቅርብ፤ እንዲሁም ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ ያቀረቡት የሰዋስው ማስረጃ ስሕተት መሆኑን እንመልከት:: በማቴዎስ 28፥19 ላይ የምንመለከተው የሰዋስው አወቃቀር "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የተለያዩ (distinct) አካላት (persons) መሆናቸውን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው:: አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከሚለው ስም ፊት የሚገኙት ውስን መስተአምሮች (definite articles) አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: እንደ እንግሊዝኛው ሰዋስው ሁሉ የግሪኩ ሰዋስው በስሞች ፊት የተወሰነ መስተአምር ኖሮ፣ ስሞቹ አንድ ዐይነት ሙያ (case) ካላቸው፣ ስሞቹ የተለያየን አካል ይወክላሉ:: ነገሩን ግልጽ ለማድረግ አንድ የእንግሊዝኛ ዐረፍተ ነገር በዋቢነት እናቅርብ፤ The black and the white dogs ስንል ጥቁርና ነጭ ቀለም ያላቸው ሁለት የተለያዩ ውሾች ማለታችን ሲሆን፣ The black and white dog ካልን ግን ጥቁርና ነጭ ቀለም ያለው አንድ ውሻ ማለታችን ነው:: ልዩነቱን ያመጣው በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ላይ ነጭ በሚለው ቅጽል ፊት የነበረው የተወሰነ መስተአምር በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያለመገኘቱ ነው:: ልክ እንደዚሁ ሁሉ በግሪኩም አብ (ግሪክ "ፓትሮስ" "πατρὸς")፣ ወልድ (ግሪክ "ሁዮ" "υἱοῦ") እና መንፈስ ቅዱስ (ግሪክ "ሐግዮ ኑማቶስ" "ἁγίου πνεύματος") ከሚሉት ስሞች ፊት የተወሰነ መስተአምር አለ (ዘርፍ ሙያ የተወሰነ መስተአምር):: ይህም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን በግልጥ የሚያሳይ ነው ("in the name of <u>the</u> Father and of <u>the</u> Son and of <u>the</u> Holy Spirit"— "βαπτίζοντες αὐτοὺς εἰς τὸ ὄνομα τοῦ πατρὸς καὶ τοῦ υἱοῦ καὶ τοῦ ἁγίου πνεύματος")::

ቄበ ተክለ ማርያም ገዛኸኝም ሆኑ በውጭ የሚኖሩ የድርጅቱ ጸሐፍት፣ "አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ እነዚህ ሦስቱ የእግዚአብሔር ስሞች የመጠሪያ ስሞቹ ቢሆኑ ኖሮ፣ ስም ተብሎ በነጠላ ቍጥር ከመጻፍ ይልቅ፣ ስሞች ተብለው ሊጻፉ ይገባ ነበር" ይላሉ:: ነገር ግን "ስም" (name) ሳይሆን "ስሞች" (names) መባል አለበት የሚለው የየትኛው ቋንቋ ሰዋሰው ነው? በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛም ሆነ በግሪክ ቋንቋ ሰዋሰው "ስም" (name) የሚለው ነጠላ ቃል የብዙ ሰዎችን ስም ወክሎ ሊገባ ይችላል:: "ይህን ስጦታ በእኔና በባለቤቴ ስም አሰጣለሁ" ይባላል እንጂ "በእኔና በባለቤቴ ስሞች አሰጣለሁ" አይባልም፤ ይህ አማርኛ ነው የግሪኩም ሰዋሰው ይህንኑ የሰዋሰው አካሄድ የተከተለ ነው:: አንዳንድ አብረጆችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመልከት፤ "ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ባረካቸውም:: ስማቸውንም (name) በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው" (ዘፍጥረት 5÷2):: ወንድና ሴት ሆነው የተፈጠሩት አዳምና ሔዋን ሁለት የተለያዩ አካላት ሆነው ሳለ "ስም" (name) የሚለው ነጠላ ቃል ወክሎአቸው እናገኛለን:: "በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን (name) እናበጠራው አሉ" (ዘፍጥረት 11÷4):: የባቢሎንን ግንብ የሠሩት ሰዎች ብዙ ሆነው ሳለ፣ "ስማችንን" እንጂ "ስሞቻችንን" የሚለውን ቃል አልተጠቀሙም:: "ከእነርሱም በኋላ የምትወልዳቸው ልጆች ለአንተ ይሁኑ፤ በርስታቸውም በወንድሞቻቸው ስም (name) ይጠሩ" (ዘፍጥረት 48÷6) ይላል እንጂ በወንድሞቻቸው "ስሞች" አይልም:: "ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ፤ ስሜም (name) የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅም ስም (name) በእነርሱ ይጠራ" (ዘፍጥረት 48÷16):: አብርሃምና ይስሐቅ አባትና ልጅ ሆነው ባለ፣ "ስሞች" የሚለው የብዙ ቍጥር ሳይሆን፣ "ስም" የሚለው ነጠላ ቃል ተክቷቸው ሲገባ እንመለከታለን:: በአጠቃላይ ከግሪኩም ሆነ ከአማርኛው ሰዋሰው የምንማረው እውነት "ስም" የሚለው ቃል የበርካታ ሰዎችን ስም ወክሎ ሊገባ ስለሚችል፣ "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም (name)" መባሉ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ የማዕረግ ስም ነው የሚለው ትንተና ከግሪኩ የሰዋሰው ሕግጋት ጋር ክፉኛ የሚጋጭ ነው::



አምስተኛ፤ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በኢየሱስ ስም የተጠመቁት ሁሉ፣ በሥጋ ከአይሁድ ወገን የሆኑ ወይም የይሁዲን ሃይማኖት የተቀበሉ ሰዎች ናቸው:: 1) አይሁዶች (ሐዋርያት ሥራ 2÷5፤ 22÷16፤ 18÷1-8):: 2) ሳምራውያን (ሐዋርያት ሥራ 8÷5:12:16 ሳምራውያን ቅልቅል አይሁድ መሆናቸውን ልብ ይሏል):: 3) በትውልድ አሕዛብ የነበሩ ነገር ግን የይሁዲን እምነት የተቀበሉ (ሐዋርያት ሥራ 10÷12:22:48):: 4) የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት (ሐዋርያት ሥራ 19÷1-5 የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት አይሁድ እንደ ሆኑ ልብ ይሏል:: የመጥምቁ ዮሐንስ ተልእኮ "አብርሃም አባታችን" ለሚሉ ለአይሁድ እንጂ አሕዛብ አልነበረም፤ ለምሳሌ ማቴዎስ 3÷5:7:8:9):: በአዲስ ኪዳን ምንባባት በአብዛኛው "አሕዛብ" (nations) የሚለው ቃል ተያይዞ የቀረበው ከእስራኤል/ከአይሁድ ነገድ ውጪ ያሉትን ሕዝቦች ለማመልከት ነው (ለምሳሌ ከሐዋርያት ሥራ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሐዋርያት ሥራ 4÷25፤ 7÷45፤ 13÷19፤ 14÷16፤ 18÷1-8) :: "አሕዛብ" (nations) የሚለው ቃል ቤተ እስራኤልን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለበት ስፍራ የለም:: ከዚህ መረጃዎች የምንመለከተው እውነት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተጠመቁት ከቤተ እስራኤል ወገን የሆኑ ብቻ ናቸው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የማቴዎስ 28÷19 ትእዛዝ የሰጠው ደግሞ፣ "ለአሕዛብ" ነው:: ስለዚህ የማቴዎስ 28÷19 ትእዛዝ በዋነኝነት የተሰጠው ለቤተ እስራኤል ሳይሆን "ለአሕዛብ" ነው:: በብሉይ ኪዳን ቤተ እስራኤሎች የጥምቀትን ሥርዐት ይወስዱ ነበር:: በዘመነ ሥጋዌ/በመሲሑ ዘመን ግን እስራኤላውያን መሲሑን እንፈልግም አሉ:: እንግዲያው መሲሑን ሲቀበሉ በመሲሑ ስም መጠመቃቸው የግድ ይሆናል::

ስድስተኛ፤ አንዳንድ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት በተራ ቍጥር አምስት ላይ የቀረበውን ትንተና አይቀበሉም:: ለዚህም ዋነኛ ምክንያታቸው በምንም መልኩ የታሪክ (የሐዋርያት ሥራን) መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ነገረ መለኮት መመሥረት አንችልም የሚለው ነጥብ ነው:: እነዚህ ምሁራን "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ" ለሚለው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዘገባ የሚሰጡት ትንታኔ እንደሚከተለው ነው:: "በ. . .ስም" የሚለው ሐረግ በቃለ እግዚአብሔር የተለመደ ነው:: ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያት ቃሉን በተለያየ ትርጒም

ተጠቅመውበት ይገኛል። የዚህን ሐረግ ትርጒም የሚወስነው ሐረጉ የሚገኝበት ዐውድ፣ የዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የስዋስው አገባብ፣ የጸሓፊው ቀዳማይ ዐላማ ወዘተ እንደ ሆነ ግን ልብ ይሏል። በአብዛኛው፣ "በ. . .ስም" የሚለው ሐረግ "በ. . .ሥልጣን" የሚለውን ትርጒም ይወክላል። ለምሳሌ ዳዊት ጎልያድን ለመግጠም ሲወጣ፣ "በተገዳደርከው በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ" 1ሳሙኤል 17፥45 ሲለው እንመለከታለን። ይህ ማለት ደግሞ የእግዚአብሔርን ሥልጣን ተተግኜ እገጥምሃለሁ ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "በአባቴ ስም" መጣሁ ሲል (ዮሐንስ 5፥43)፣ "በአባቴ ሥልጣን" መጣሁ ማለቱ ነው። በማቴዎስ 18፥20 ላይ ኢየሱስ፣ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" ሲል፣ "ጥንታዊ በሚባሉት በፓፒረስ ጽሑፎች 'በስሜ' ማለት 'እኔን የበላይ ባደረገ መልኩ' ወይም 'በእኔ ንብረትነት'"[106] ማለት እንደ ሆነ ምሁራን ያስገነዝባሉ። በማቴዎስ 28፥19 ላይም "ስም" የሚለው ቃል በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ "በኢየሱስ ስም" የሚለው ሐረግ በኢየሱስ ሥልጣን ማለት ሲሆን፣ በዚህ ሥልጣን መጠመቅ ማለት ደግሞ ኢየሱስ ባስተማረው የጥምቀት ቀመር መጠመቅ ማለት ነው። የጥምቀቱ ቀመር መጠሪያ፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጥምቀት" ይባል እንጂ፣ በውስጡ አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን የሚያካትት ነው። ጳውሎስ በኤፌሶን ያገኛቸውን ደቀ መዛሙርት ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲነግራቸው "መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንኳ አልሰማንም" ሲሉት፣ ያለመስማታቸው ነገር ቢያስደንቀው እንግዲያው በማን ስም ተጠመቃችሁ አላቸው፤ እነርሱም በዮሐንስ ጥምቀት አሉት (ሐዋርያት ሥራ 19፥1-7)። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን አልሰማንም ላሉት ሰዎች፣ እንዴት አልሰማችሁም እንግዲያው "በማን ስም ተጠመቃችሁ" የሚለው አነጋገሩ፣ የጌታ የኢየሱስ ስም ጥምቀት መንፈስ ቅዱስን የሚያካትት እንደ ሆነ የሚያስገነዝብ ነው። "የዮሐንስ ጥምቀት" ሲባል አንድ ሰው በዮሐንስ ስም ተጠመቀ ማለት እንዳልሆነ ሁሉ፣ "በጌታ በኢየሱስ ስም" ማለትም፣ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠመቀ ማለት አይደለም።

[106] H. L. Ellison, "Mathew," in *The International bible Commentary, with the New International Version*, ed. F. F. Bruce (Grand Rapids: Zondervan, 1986), 1140.



ለባተኛ፤ ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን እንሥቶ እስከ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ (የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ቈርቋሪዎች እስከ ተነሡበት ዘመን ድረስ) በታሪክ የሚታወቅ አንድም ሰው ወይም እንቅስቃሴ የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ስም ብቻ ነው የሚል ትምህርት አስተምሮም ሆነ፣ በዚህ የጥምቀት ቀመር ሰዎችን አጥምቆ የሚያውቅ ሰው ነበር የሚል ትምህርት ታሪክ አያስተምረንም። ከጉባኤ ኒቂያ በፊት ያነበሩትን የታሪክ መዛግብትን እንኳ ብንመለከት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታጠምቅ የነበረው፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደ ሆነ ማየት እንችላለን።

በዚህ ረገድ አንዳንድ የታሪክ ማስረጃዎችን እንመልከት። ትምህርተ ሐዋርያት (ዲዳኬ)[107] በመባል የሚታወቀውና 90 ዓ.ም እስከ 120 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት እንደ ተጻፈ የሚገመተው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የአስተምህሮና ሥርዐተ አምልኮ መጽሐፍ፣ የጥምቀት ቀመርን በተመለከተ እንዲህ ይላል፣ "ጥምቀትን በተመለከተ ማጥመቅ የሚገባን እንደሚከተለው ነው፤ የሚከተሉትን ነጥቦች ሁሉ በአደባባይ አስተምር ከዚያም በሚፈስ ውሃ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቅ፤ ፈሳሽ ውሃ ከሌለ፣ በሌላ መንገድ አጥምቅ፤ ቀዝቃዛ ውሃ ከሌለ በሞቀ ውሃ አጥምቅ፤ ይህ ሁሉ ከሌለም በተጠማቂው ራስ ላይ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሦስት ጊዜ ውሃ አፍስስ"[108]።

[107] "ዲዳኬ" በግሪክ ቋንቋ ትምህርት ማለት ሲሆን፣ በዚህ ስያሜ የሚታወቀው ጥንታዊ ሰነድ፣ "ትምህርተ ሐዋርያት" በመባልም ይጠራል። ዲዳኬ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነቷን የምታስተምርበት የአስተምህሮ መጽሐፍ ሲሆን፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮ በምታካሂድበት ጊዜ ሁሉ ይነበብ የነበረ መጽሐፍ ነው። ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያም ሆነ አርጌንስ ዲዳኬ የቅዱሳት መጻሕፍት አካል ነው ይበሉ እንጂ፣ ቀኖናዊ መጽሐፍ ነው የሚለው ጒዳይ ዓለም ዐቀፋዊ ስውቅና ስላላገኘ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሊካተት አልቻለም። ነገር ግን እንደ እትናቴዎስ ያሉ ስመ ጥር የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣ ዲዳኬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢነበብ ሰዎችን ያንጻል የሚል አቋም ነበራቸው። በዚህ ስፍራ መገንዘብ ያለብን መሠረታዊው ነጥብ፣ የጥንቷ (90 ዓ.ም እስከ 120 ዓ.ም) ቤተ ክርስቲያን ምን ዐይነት መሠረተ እምነት ነበራት የሚለውን ጒዳይ ጥርት ባለመልክ የሚነግረን ዲዳኬ መሆኑን ነው።

[108] Didache, 7.1-4, ed. Cyril C. Richardson, *Early Christian Fathers* (New York: Macmillan, 1975), 174.

በ100 ዓ.ም ተወልዶ 165 ዓ.ም እንደ ሞተ የሚገመተውና የሰማዕትነትን ክብር የተቀዳጀው ዮስጦስ ሰማዕት (Justin Martyr)፣ በማን ስም እናጥምቅ የሚለውን ጉዳይ በተመለከተ እንዲህ ይላል፣ "በውሃ የምናጠምቀው የሁሉ አባትና ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር አብ ስም፣ በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው"[109]:: በ115 ዓ.ም ተወልዶ 190 ዓ.ም የሞተው እንዲሁም የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ከነበረው ከፖሊቃርጶስ ቃለ እግዚአብሔርን የተማረውና የልዮን ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የነበረው ሔሬኔዎስ (Irenaeus)፣ በማን ስም እናጥምቅ የሚለውን ጉዳይ አስመልክቶ እንዲህ ይላል፣ "ስንጢአት ሥርየት ጥምቀታችንን የምንቀበለው በእግዚአብሔር አብ ስም፣ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው፣ ትስብእት በሆነው፣ በሞተው፣ ዳግም በተነሣው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲሁም በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው"[110]::

በ160 ዓ.ም ተወልዶ በ215 ዓ.ም የሞተው በቃቤ እምነት ጠርጡሊያኖስ (Tertullian)፣ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንድናጠምቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ እንደ ተሰጠን ይገልጣል፣ "ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ከአባቱ ዘንድ የተሰጠውን ተስፋ እንደሚልክላቸው ቃል ገብቶላቸዋል፤ በመጨረሻም በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ እንጂ አካል በሌለው አምላክ እንዲያጠምቁ አላዘዛቸውም፡ ወደ ውሃውም መጥለቅ ያለብን አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ሦስት ጊዜ ነው፤ ይኸውም በሦስቱ አካላት ነው፤ በእያንዳንዱም ጊዜ የሦስቱን ስም መጥራት ይኖርብናል"[111]::

[109] Justin Martyr, *The First Apology*, 61, ed. Alexander Roberts and James Donaldson, *The Ante-Nicene Fathers*, vol. 1 (New York: Charles Scribner's Sons, 1899).

[110] J. N. D. Kelly, *Early Christian Doctrines* (San Francisco: Harper Collins, 1978), 90.

[111] Tertullian, *Against Praxeas*, 26, ed. Alexander Roberts and James Donaldson, *The Ante-Nicene Fathers*, vol. 3 (New York: Charles Scribner's Sons, 1899).



በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኖረው የካርታጎ/የቅርጣግና (Carthage) ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቆጵርያኖስ (Cyprian)፣ የውሃ ጥምቀትን በተመለከተ እንዲህ ብሏል፣ "'እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲጠመቁ አስተምሯቸው' የሚለው እነጋገሩ፣ ሥላሴን አመላካች ነው፤ አሕዛብ መጠመቅ ያለባቸው ሥርዐተ ጥምቀት ምን እንደ ሆነ የሚያስተምር[112] . . .ክርስቶስ ራሱ አረማውያን ሙሉዕና ኅቡር በሆነው በሥላሴ እንዲጠመቁ አዟል[113]":: በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እንዳለብን የሚያስተምሩ እጅግ በርካታ የታሪክ መዛግብትን ማጣቀስ የሚቻል ቢሆንም፣ ይህን በናሙናነት ካቀረብን በቂ ነው::

ታላቁ የነገረ መለኮት ሊቅ አውግስጢኖስ (Augustine)፣ በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ፣ "መናፍቃን አያጠምቁም፤ ካጠመቁም በሥላሴ ስም አያጠምቁም"[114] ሲል ጽፎአል::

ይህ እንዳለ ሆኖ አንዳንድ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍት፣ የታሪክ መዛግብትን በማላከር የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን "በኢየሱስ ስም" ታጠምቅ ነበር እንዲሁም በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ ስሕተት ነው የሚል ሙግት ለማቅረብ ሞክረዋል[115]:: "እነዚህ ጸሓፍት በዋቢነት ከጠቀሷቸው 47 ማጣቀሻዎች ውስጥ 10ሩ በግልጥ 3ቱ በአብዛኛው አንዳችም ቀመር አልተጠቀሙም:: ከእነዚህም [47 ማጣቀሻዎች] ውስጥ 13ቱ በግልጥ 4ቱ በአብዛኛው ሥላሴያዊ ቀመር ተጠቅመዋል:: በተጨማሪም [ከ47 ማጣቀሻዎች ውስጥ] 11ዱ በግልጥ 4ቱ በአብዛኛው አንዳችም ቀመር አልተጠቀሙም፤ ከዚህ ውስጥ [ከ47 ማጣቀሻዎች ውስጥ] 4ቱ በግልጥ 3ቱ በአብዛኛው በኢየሱስ ክርስቶስ

[112] ዝኒ. ከማሁ፤ ቅጽ 5::

[113] ዝኒ. ከማሁ::

[114] Besiner, 72 ከ Augustine, *On Baptism, Against the Donatists*, vi.25, compare iii. 14-15; in *NPNF*, 1, 4:442, 491. ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[115] E. Calvin Beisner, *"Jesus Only" Churches*, ገጽ 61 ከBernard, *Oneness and Trinity*, ch 8, እንዲሁም Weisser, *Baptism*, *passim*. ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

ስም ማጥመቅ እንደሚገባ ገልጸዋል:: ነገር ግን መገንዘብ የሚገባን መሠረታዊው ነጥብ በኢየሱስ ስም አጥምቁ የሚሉት ሰነዶች እግዚአብሔር አብ ሐሰተኛ እምላክ ነው የሚሉ በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት የኖስቲክ ማርሴዮናይት ሰነዶች ሲሆኑ፣ ከዚህም ውስጥ ሁለቱ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አሪዮሳውያንና በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተነሥተው የነበሩ የፖላንድ ወንድማማች በመባል የሚታወቁ ክፍሎች ናቸው፤ ታዲያ ሁሉቱም ምንጮች የኢየሱስን አምላክነት የማይቀበሉ ሰዎች ያዘጋጇቸው ሰነዶች ናቸው:: 3ቱ በአብዛኛው የተባሉት ደግሞ በዐሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡና ምናልባት የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚክዱ እንዲሁም በዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡ፣ ትምህርተ ሥላሴን የማይቀበሉ ምናልባትም የራሳቸው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሐፍት ናቸው"[116]::

"እነዚህ ጸሓፍት [በርናርድና ዊሰር] በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ከተጻፉ መዛግብት ከጠቀሷቸው 23 ጥቅሶች መካከል ሦስቱ ብቻ በኢየሱስ ስም ጥምቀትን የሚደግፉ ሲሆን፣ እነዚህም አንዱ የማርስዮናይት ሁለቱ ደግሞ የአርዮሳውያን ሰነዶች ናቸው:: ከዚህ ውስጥ 2ቱ በግልጥ 6ቱ ደግሞ በአብዛኛው ከሁለት አንዱን ቀመር የሚደግፉ ናቸው:: 6ቱ በግልጥ 4ቱ ደግሞ በአብዛኛው ሥላሴያዊውን ቀመር የሚደግፉ ሲሆን፣ 6ቱ በግልጥ 2ቱ ደግሞ በአብዛኛው አንዳቸውንም ቀመር ትክክል ነው የሚል አቋም የላቸውም"[117]::

ከዚህ መረጃ በግልጥ መመልከት የሚቻለው፣ ለታሪክ ማስረጃነት ይጠቅሙናል ብለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሓፍት ከጠቀሷቸው ጥንታዊ የታሪክ ሰነዶች መካካል፣ ሦስቱ ብቻ በኢየሱስ ስም እንድናጠምቅ የሚያዙ ናቸው:: እነዚህ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የሚክዱ መናፍቃን ያዘጋጇቸው ጽሑፎች እንጂ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን

[116] ድምሩ ከ47 በላይ ነው:: ይህ የሆነበት ምክንያት "በአብዛኛው" የሚለው ከአንድ በላይ አቋም ሊወክል ይችላልና ነው:: E. Calvin Beisner, *"Jesus Only" Churches*, 61 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም::
[117] ዝኒ ከማሁ::



መሠረተ እምነትን የሚገልጡ ወይም ስመ ጥር በሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተጻፉ አይደሉም::

## 6. ልሳን መናገር የድነት ምልክት ነውን?

መጽሐፍ ቅዱስ ልሳን መናገር የድነት ምልክት ነው የሚል እንጻች ትምህርት የለውም:: በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቃቸው ምልክቱ ልሳን መናገር ነው የሚለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እስተምህሮ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ አይደለም::

ቀድሞ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበረ ሰው፣ የድርጅቱን አስተምህሮ ተቀብለው፣ ትክክለኛ እንዲሁም ለድነት ወሳኝ ነው በሚባለው የጥምቀት ቀመር ተጠምቀው ልሳን የማይናገሩ በርካታ ሰዎች እንዳሉ ይገልጻል:: ለዚህ ዐይነቱ ጉዳይ የድርጅቱ መምህራን የሚሰጡት መልስ፣ "ያልተናዘዛችሁት ኀጢአት ስላለ ነው" ወይም "እምነት ስለሌላችሁ ነው" ወዘተ ሲሆን፣ እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ ውስጥ የገቡ ሰዎች ለረጅም ጊዜ ተከታታይ ጾምና ጸሎት በመያዝ፣ ኀጢአታቸውን በመናዘዝ እንዲሁም ድነት እንዲያገኙ (በልሳን እንዲናገሩ) እግዚአብሔርን እንደሚለምኑ ይገልጻል:: እንዲያም ሆኖ በርካታ ሰዎች ያሰቡት ሲሞላላቸው እንደማይታይ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ተስፋ መቍረጥ ውስጥ እንደሚወድቁ ይገልጻል—እግዚአብሔር ድነት ስለከለከላቸው የድነት ምልክት የሆነው ልሳን እውን ሊሆን አልቻለምና ከፍተኛ ተስፋ መቍረጥ እንዲሁም ሐዘን ውስጥ መውደቅ እንዴት ይነስ![118]:: በድርጅቱ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚለጠው ለፍራ ከከንፈር ያለፈ አይደለም!

ታዋቂ የድርጅቱ ጸሓፊ ይህን ጉዳይ በተመለከተ፣ "መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በቂ ጊዜ በመስጠት ንስሓ መግባትና ራስን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠት ያስፈልጋል"[119] ባይ ነው:: እንዲያውም ይህ

[118] Gregory A. Boyd, *Oneness Pentecostals and the Trinity* (Grand Rapids, MI.: Baker, 1992), 221.
[119] David Bernard, *The New Birth* (Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1984), 216.

ሰው፣ "ይህ እውን እንዲሆን ስረጅም ጊዜ ጥረት ማድረግ ወይም ተደጋጋሚ ሙከራ ማካሄድ ዋጋ የለውም:: መንፈስ ቅዱስን የማይቀበሉ ሰዎች አንድም እምነት ስለሌላቸው አልያም ኀጢአታቸውን ሙሉ ስሙሉ ስላልተናዘዙ ወይም ደግሞ የሕይወታቸውን እያንዳንዱ ክፍል ስእግዚአብሔር ስላላስገዙ ነው"[120] የሚል ትምህርትም አለው:: እንዴት አሳዛኝ ጉዳይ ነው እግዚአብሔር እድነኝ ተብሎ በጾም በጸሎት ቢጠየቅ አላድንም የሚልበት ሁኔታ/

ሉቃስ 11÷13 እንዲሁም ሐዋርያት ሥራ 2÷39 በልሳን መናገር የድነት ምልክት ነው የሚል ትምህርት የላቸውም:: በማርቆስ 16÷17 ላይ ስለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወይም ሙላት የሚናገር አንዳችም ሐረግ ወይም ቃል የለም:: ስለዚህ በልሳናት መናገር የድነት ምልክት ነው የሚለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በዚህ ክፍል አንዳችም ድጋፍ የለውም:: ማርቆስ 16÷17 ደቀ መዛሙርት ሁሉ በልሳናት ይናገራሉ የሚል ትምህርት አለው የምንል ከሆነ፣ መርዛማ እባብን መያዝ፣ የሚገድል መርዝ ጠጥቶ ያለመሞት፣ በበሽተኞች ሁሉ ላይ እጅ ጭኖ መፈወስ የደቀ መዛሙርትነት ምልክት ነው ማለት የግድ ይሆናል:: ይህ ደግሞ እንደ ዴቭድ በርናርድ ያሉ ታዋቂ የድርጅቱ ጸሓፍያን ራሳቸው የሚስማሙበት ጉዳይ አይደለም (ማርቆስ 16÷9-20 ያለው ክፍል ነገረ መለኮትን ለማዋቀር አንዳችም ስገዛ እንደሌለው ከላይ ያየነውን ሐሳብ ልብ ይሏል)::

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምንባባት በተናጠልም ሆነ በኅብረት ስመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ምልክቱ ልሳን መናገር ነው የሚል ትምህርት የላቸውም:: ስምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 2÷1-4 ባለው ክፍል ደቀ መዛሙርት በልሳን ከመናገራቸው በፊት በዮሐንስ 20÷22-23 ባለው ክፍል ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር (ከሰባት ሳምንት በፊት)፤ ነገር ግን ልሳን ሲናገሩ አንመለከትም:: ምንም እንኳ በሚከተሉት አምስት ክፍሎች ሰዎች በልሳን ስለ መናገራቸው ቢዘገብም (በሐዋርያት ሥራ 2÷1-4፤ 8÷8:12-18፤ 10÷44-48፤ 19÷1-7፤ 19÷17) በልሳን መናገር የድነት ምልክት ነው ወደሚለው ድምዳሜ መድረስ አይቻልም:: ምክንያቱም 1) መጽሐፍ ቅዱስ ልሳን መናገር የድነት

[120] ዝኒ ከማሁ::



ምልክት ነው ስለማይል:: 2) እንደ ሐዋርያት ሥራ ያሉ የታሪክ መጻሕፍት የታሪክ ዘገባ የሚያቀርቡ መጻሕፍት እንጂ (የሆነውን ነገር የሚገልጹ እንጂ) መሆን ያለበትን ነገር የሚያስተምሩን የአስተምህሮ መጻሕፍት አይደሉም (ከላይ ስለመስተጋብአዊ ምንባባትና ስለምንጩታዊ ምንባባት የቀረበውን ትምህርት ልብ ይሏል)::

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሰዎች ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በተቀበሉበትም ጊዜ ሆነ ወይም በመንፈስ ቅዱስ በሚሞሉበት ወቅት በልሳናት ስለመናገራቸው አልተዘገበም (በሐዋርያት ሥራ 2÷37-41፤ 4÷31፤ 6÷3-6፤ 7÷55፤ 11÷24፤ 13÷52):: በሦስት ክፍሎች ሰዎች መንፈስ ቅዱስ በተሞሉበት ወይም በተጠመቁበት ጊዜ በልሳን መናገራቸው በግልጽ የተጠቀሰ ሲሆን (በሐዋርያት ሥራ 2÷1-4፤ 10÷44-48፤ 19÷1-7)፣ ሐዋርያት ሥራ 8÷8:12-18 እንዲሁም 19÷17 ላይ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉበት ወቅት በልሳን ስለመናገራቸው ግልጽ የሆነ ማስረጃ አንመለከትም::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ ወይም እንደ ተጠመቁ የተነገረላቸው የእግዚአብሔር ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ወይም ጥምቀት በተቀበሉበት ወቅት በልሳናት ስለመናገራቸው የተነገረ አንዳችም ነገር የለም:: ስምሳሌ የኢየሱስ እናት ማርያም (ሉቃስ 1÷35)፣ ኤልሳቤጥ (ሉቃስ 1÷41)፣ ዘካርያስ (ሉቃስ 1÷67)፣ መጥምቁ ዮሐንስ (ሉቃስ 1÷15)፣ ስምዖን (ሉቃስ 2÷25-27)፣ ኢየሱስ (ማቴዎስ 3÷16 እንዲሁም ማርቆስ 1÷10፤ ሉቃስ 3÷22-23 እንዲሁም ዮሐንስ 1÷32፤ ሉቃስ 4÷1:14:18፤ ሐዋርያት ሥራ 10÷38፤ ከኢሳይያስ 11÷1-2፤ 42÷1-4፤ 61÷1-3 ጋር ያነጻጽሩ)::

በርካታ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን፣ መንፈስ ቅዱስን በተሞሉበት ጊዜ በልሳን እንደ ተናገሩ የሚገልጽ አንዳችም ክፍል ያለመኖሩ በልሳናት መናገር የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወይም ጥምቀት ምልክት ነው የሚለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ስሕተት እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው (ዘፀአት 31÷3-5፤ ዘኍልቍ 11÷17:25:26፤ 24÷2-3፤ መሳፍንት 3÷10፤ 6÷34፤ 11÷29፤ 13÷25፤ 14÷6:19፤ 15÷14፤ 1ሳሙኤል 11÷6፤

10÷5-6፤ 16÷14፤ 19÷23-24፤ 19÷20፤ 16÷13፤ 2ሳሙኤል 23÷1-2፤ 1ዜና 12÷18፤ 2ዜና 20÷14-15፤ 24÷20፤ ሚክያስ 3÷8)[121]።

በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ከ40 በሚበልጡ ምንባባት ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተጠመቁ ወይም እንደ ተሞሉ የሚናገር ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከላይ በተመለከትናቸው በሦስት ምንባባት ብቻ ነው ሰዎች መንፈስ ቅዱስ በተሞሉበት ወይም በተጠመቁበት ጊዜ በልሳናት እንደ ተናገሩ የሚገልጹት። ከዚህ የምንማረው ነገር በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ወይም ለመጠመቅ እንዲሁም ድነት ለማግኘት ምልክቱ በልሳኖች መናገር ነው የሚለው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ስሕተት መሆኑን የሚገልጽ ነው።

በልሳን መናገር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላታቸው ወይም ለመጠ መቃቸው ምልክት ሆኖ የታየበት ሁኔታ አለ (ሐዋርያት ሥራ 10÷46) ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የሚጠመቁ ወይም የሚሞሉ ሰዎች ሁሉ በልሳን ይናገራሉ ማለት ስሕተት ነው (ተመሳሳይ ሥነ አመክንዮ በመጠ ቀም "ሰዎች አጥቢ እንስሳት ናቸው፤ አጥቢ እንስሳት ሁሉ ደግሞ ሰዎች ናቸው" ማለት ስሕተት ነው)።

121 በዘመነ ብሉይ መንፈስ ቅዱስ በተወሰኑ ሰዎች ማለትም በነገሥታት፣ በነቢያትና በካህናት ውስጥ ብቻ ሲያድር፣ በዘመነ ሐዲስ ደግሞ በሕዝበ ክርስቲያኑ ውስጥ ሁሉ ያድራል፤ ይህም ነው በሁለቱ ኪዳኖች መካከል ያለው የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ልዩነት።



# III. ቃለ እግዚአብሔር ስለ ድነት ምን ያስተምራል?

ከአዳም ኀጢአት የተነሣ የሰው ልጅ ሁሉ በኀጢአት ወድቋል፤ ኀጢአት ባስከተለውም መዘዝ መንፈሳዊ ሞት ሞቶአል። የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን የድነት መስፈርት አሟልቶ ራሱን ለማዳንም ሆነ ራሱን ለድነት ማዘጋጀት ፈጽሞ አይችልም (ሮሜ 5÷12-19፤ መዝሙር 49-7-9)። ጽድቅ በእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው ልጆች ኀጢአት የትኪ ሞት በሞተው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ የሚገኝ የአምላክ ነጻ ስጦታ ነው (ሮሜ 3÷28፤ 4÷4-5)። ስለዚህም ድነትን ለማግኘት ዳግም መወለድ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል (ዮሐንስ 3÷3:5-7)።

ኀጢአተኛ ከሆነው የሰው ልጅ ችሎታና ሥራ ውጪ፣ ድነት በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ጸጋ ብቻ የሚገኝ ስጦታ ነው (ሮሜ 9÷15-21)። ይህ እውን ሊሆን የሚችለውም፣ "ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን፣ ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ዳግመኛ ስለተወለድን" (1ጴጥሮስ 1÷23 ጸሓፊው እንደ ተረጐመው፤ እንዲሁም ያዕቆብ 1÷18፤ ይመሰክሯል) እንዲሁም "እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት የሥጋችንን ምኞች እያረካን፣ መንገዱንም እየተከተልን በመካከላቸው እንኖር ነበር፤ እንደ ሌሎቹም የቍጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን በምሕረቱ ባለ ጸጋ የሆነ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ፣ በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ፣ በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፤ የዳናችሁት በጸጋ ነው" (ኤፌሶን 2÷3-5 እንዲሁም ዮሐንስ 3÷8:3-8፤ 1ጴጥሮስ 1÷3፤ ዮሐንስ 5÷21፤ 6÷44-45:65 ይመሰክሯል)።

ዳግም ልደት የእግዚአብሔርን ጥሪ እውን ያደርገዋል። "ይህም ከተጠ ራንበት እምነት የሚቀድም ጉዳይ በመሆኑ (ዮሐንስ 1÷12-13[122]፤ 3÷3:5፤ 5÷24፤ 1ዮሐንስ 5÷1)፣ በእምነት ላይ መሠረት ያደረገ አይደለም። "በዚህም አምላካዊ ሥራ ኀጢአተኛው ሰው ለአዲስ ሕይወት ዳግም

122 "ሥልጣን" የሚለው የሕግ ቃል የማደጎ ልጅነታችንን የሚገልጽ ሲሆን፣ ከእግዚአብሔር ተወለዱ የሚለው ሐረግ ደግሞ፣ ዳግም ልደትን የሚያሳይ ነው። E. Calvin Beisner, ገጽ 65።

ተወልዷል፤ የልቡም እርኩሰት ተወግዷል ወይም ነጽቶአል (ሕዝቅኤል 36÷25-26፤ ዮሐንስ 3÷5፤ ቲቶ 3÷5)፤ ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በእምነት "ማየትና" "መግባት" ችሏል (ዮሐንስ 3÷3:5)። ኢየሱስ መሲሕ (1ዮሐንስ 5÷1) መሆኑን ማመን ችሏል (ዮሐንስ 1÷12-13)፤ ሌሎችን በተለይም ሌሎች ክርስቲያኖችን መውደድ ችሏል (1ዮሐንስ 4÷7፤ 5÷1)፤ ኀጢአተኛ ሕይወትን በመተው ጽድቅን ማድረግ ችሏል (1ዮሐንስ 3÷9፤ 5÷18)"[123]።

እምነትና ንስሓ አዲስ ልደትን የሚከተል ጉዳይ ነው። "'እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰማ (ግሪክ "አክዎውን" "ἀκούων" የአሁን ጊዜን ያመለክታል)፣ በላከኝም የሚያምን (ግሪክ "ፒስትዎን" "πιστεύων" የአሁን ጊዜን ያመለክታል)፣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ (ግሪክ "ሜታቤቢኬን" "μεταβέβηκεν" የተከናወነ ድርጊትን ያመለክታል)፣ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም (ግሪክ "ኤርኬታይ" "ἔρχεται" የአሁን ጊዜን ያመለክታል)'" (ዮሐንስ 5÷24)። ከዚህ የምንማረው ዳግም ልደት ("ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ")፣ ቃሉን ከመስማትና ከማመን እንደሚቀድም ነው[124]። የሐዋርያው ጴጥሮስ አድማጮች፣ "ልባቸው ከተነካ" በኋላ ነው፣ "'ወንድሞች ሆይ፤ ታዲያ ምን እናድርግ?'" ያሏቸው (ሐዋርያት ሥራ 2÷37-38)፤ ይህ የሚያመለክተው ንስሓ ከመግባታቸው በፊት እግዚአብሔር በልባቸው ይሠራ እንደ ነበረ ነው[125]። በአጠቃላይ እምነትና ንስሓ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው (መዝሙር 80÷3:7:19፤ ኤርምያስ 31÷18፤ ሰቆቃው ኤርምያስ 5÷21፤ ሐዋርያት ሥራ 5÷31፤ 11÷18፤ 13÷46-48፤ 18÷27፤ ፊልጵስዩስ 1÷29፤ 2ጢሞቴዎስ 2÷25)[126]።

እምነት ጽድቅን ያስከትላል ይህ ደግሞ ቅድስናን/ለእግዚአብሔር መለየትን፣ የማደጎ ልጅነትን፣ በዕለት ተዕለት ኑሮ መቀደስን/በቅድስና

---

[123] ዝኒ ከማሁ።

[124] ዝኒ ከማሁ።

[125] ዝኒ ከማሁ።

[126] ዝኒ ከማሁ።



ማደግን፣ እስከ መጨረሻው በቅድስና መጽናትን እንዲሁም መከበርን ያስገኛል (ሮሜ 8÷28-39 በተለይ ቍጥር 29-30 ያለውን ክፍል ይመለከቷል)። ጽድቅ በእምነት እንጂ በሥራ የሚገኝ ጉዳይ አይደለም (ሮሜ 3÷21-30፤ 4÷3-5)። የሰዎችን የኀጢአት ዕዳ የከፈለው እግዚአብሔር ራሱ ነው (ሮሜ 4÷4-8)። የአማኞች ሕጋዊ ኀጢአት የተከፈለው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባከናወነው የትኪ ሞት አማካይነት ነው (ማቴዎስ 20÷28፤ 1ጢሞቴዎስ 2÷6፤ ቲቶ 2÷14፤ 1ጴጥሮስ 1÷18-19)። ክርስቶስ ለኀጢአት የከፈለው ዋጋ አማኞች ከፍርድ እንዲያመልጡ ምክንያቱ ሆነ (ሮሜ 5÷12-19)። በዚህም ምክንያት አማኞች በእግዚአብሔር ፊት ኢንዳችም የኀጢአት ዕዳ የለባቸውም (ሮሜ 6÷23፤ 8÷1-4)። ስለዚህ አማኞች ከክርስቶስ ጋር ኅብረት በመፍጠራቸው በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ተቀባይነትን አግኝተዋል (ኤፌሶን 1÷3-8፤ 2÷1-10:13:18)።

አማኞች የእግዚአብሔር ከመሆናቸው የተነሣ፣ ከሚጠፋው ዓለም ለእግዚአብሔር ተለይተዋል (ሐዋርያት ሥራ 26÷18፤ ፊልጵስዩስ 1÷1፤ ቈላስይስ 1÷2)፣ ከዚህም የተነሣ "ቅዱሳን" ይባላሉ። አማኞች የእግዚአብሔር የማደጎ ልጆች ስለሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር ወራሾች ናቸው (ዮሐንስ 1÷12-13፤ ሮሜ 8÷14-17፤ ገላትያ 4÷4-5፤ ኤፌሶን 1÷4-5:13-14)። አማኞች በዕለታዊ ኑሮአቸው የሚቀደሱት በራሳቸው ጥረት/ዐቅም ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት በሕይወታቸው ውስጥ ከሚሠራው ሥራ የተነሣ ነው (ዮሐንስ 17÷17፤ ሮሜ 6-7፤ 8÷13፤ 12÷2፤ 2ቆሮንቶስ 3÷18፤ 7÷1፤ ኤፌሶን 4÷11-16፤ ፊልጵስዩስ 2÷12-13፤ ቈላስይስ 3÷5፤ 1ተሰሎንቄ 5÷23፤ 1ጴጥሮስ 2÷2)።

አማኞች ወደ ጌታ እስከሚሄዱ ወይም ጌታ ዳግም እስከሚመጣ ድረስ በቅድስና ጸንተው የሚቆሙት ባላቸው የእምነት ጽናትና በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ለመቀደስ/ለእግዚአብሔር ለመለየት ባላቸው ፍላጎት የተነሣ ነው፤ ይህም እውን ሊሆን የሚችለው ከእግዚአብሔር የጥበቃ ታላቅነት የተነሣ ነው (መዝሙር 37÷23-24፤ 73-1-2:23፤ ዮሐንስ 6÷37-40፤ 10÷28-29፤ ሮሜ 5÷8-10፤ 8÷30-39፤ 1ቆሮንቶስ 1÷8-9፤ 3÷15፤ ፊልጵስዩስ 1÷6፤ ዕብራውያን 7÷25፤ 1ጴጥሮስ 1÷5)።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት እስከ መጨረሻው የሚጸና ብቻ እንደሚድን ይገልጻሉ (ማቴዎስ 24÷13፣ ዮሐንስ 8÷31፣ 15÷6፣ 1ቆሮንቶስ 15÷1-2፣ ቈላይስይ 1÷22-23፣ ዕብራውያን 3÷6:14፣ 10÷36:39):: እነዚህ ምንባባት እምነት እንዳላቸው የሚያውጁ ነገር ግን ዳግም ያልተወለዱ ከዚህም የተነሣ ክርስቶስን በትክክል የማያውቁትን ሰዎች የሚያመለክቱ ናቸው:: ከእግዚአብሔር ዳግም የተወለዱ እምነትም የተለገሳቸውን ሰዎች እስከ መጨረሻው የመጽናታቸው ጉዳይ ግን በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ የተመሠረተ ነው (ሮሜ 8÷23-39)::

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ከእምነታቸው የሚያፈገፍጉ ሰዎች ጥፋት እንደሚጠብቃቸው ይገልጻሉ (ሮሜ 14÷15፣ 1ቆሮንቶስ 8÷11፣ ዕብራውያን 3÷6:14):: ከእምነታቸው የሚያፈገፍጉ እንደሚጠፉ እሙን ቢሆንም፣ እግዚአብሔር እያስጠነቀቀ ያለው፣ እርሱ የጠራቸውን፣ ዳግም የተወለዱትን እንዲሁም የጸደቁ አማኞች ከእምነታቸው ያፈገፍጋሉ እያለ አይደለም (ሮሜ 8÷29-30)::

አንጻንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በእምነት ያሉ ሰዎች ሊወድቁ እንደሚችሉ ይገልጻል (ማቴዎስ 24÷10:12፣ 1ጢሞቴዎስ 1÷19፣ 4÷1፣ 2ጢሞቴዎስ 4÷10፣ ዕብራውያን 6÷4-6፣ 2ጴጥሮስ 2÷20-22):: ይህ የሆነበት መሠረታዊ ምክንያት ጊዜያዊ የሆነ እምነት በመኖሩ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዘሪው የተናገረው ምሳሌ ይህንኑ ጉዳይ የሚያጸና ነው፣ "አንዳንዱ ዘር ዐፈሩ ስስ በሆነ፣ ድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ፤ ዐፈሩ ስስ ስለሆነም ፈጥኖ በቀለ:: ነገር ግን ፀሓይ ሲመታው ጠወለገ፤ ሥር ባለመስደዱም ደረቀ...በድንጋያማ መሬት ላይ የተዘራው፣ ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ በደስታ የሚቀበለውን ሰው ይመስላል:: ነገር ግን ሥር መስደድ ባለመቻሉ ብዙ አይቈይም፤ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት ሲመጣ ወዲያውኑ ይሰናከላል" (ማቴዎስ 13÷5-6:20-21፣ ማርቆስ 4÷5-6:16-17):: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ዐይነቶቹ ሰዎች ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ይገልጻል፣ "ከእኛ መካከል ወጡ፤ ይሁን እንጂ ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገን ቢሆኑማ ኖሮ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር:: ነበር ግን ሁሉም ከእኛ ወገን እንዳልነበሩ ይታወቅ ዘንድ ከእኛ ተለዩ" (1ዮሐንስ 2÷19):: እነዚህ የማስጠንቀቂያ ምንባባት፣ "እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኀይል ተጠብቃችኋል" (1ጴጥሮስ



1÷5፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሮሜ 8÷38-39፤ 2ጢሞቴዎስ 1÷12፤ 1ዮሐንስ 2÷3፤ 3÷14፤ 4÷13፤ 5÷13) የሚለውን አማኞች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን ትምክህት የሚሸረሽር አይደለም:: ዳግም የተወለዱ፣ ንስሓ የገቡ፣ በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ሁሉ በመጨረሻ ታላቅ ክብር ይጠብቃቸዋል (ሮሜ 8÷17-23:29-30፤ 9÷22-23፤ 1ቆሮንቶስ 15÷51-57፤ 2ቆሮንቶስ 4÷17፤ 5÷8፤ ኤፌሶን 5÷25-27 ፊልጵስዩስ 1÷21-23፤ 3÷21፤ 2ተሰሎንቄ 2÷14፤ ዕብራውያን 12÷23፤ ራእይ 14÷13)::

ሮሜ 8÷28-30 "የድነት ወርቃማው ሰንሰለት" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ አማኞች በመጨረሻ የሚጠብቃቸው ክብር እውን የሚሆነው በእግዚአብሔር ጸጋና ኀይል ነው፣ "እግዚአብሔርን፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን:: እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኵር እንዲሆን ነው:: አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው":: ምንም እንኳ አማኞች "የራሳቸውን መዳን ፈጽሙ" (ፊልጵስዩስ 2÷12) ቢባሉም፣ ቃለ እግዚአብሔር፣ "እንደ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና" (ፊልጵስዩስ 2÷13 እንዲሁም ሮሜ 8÷28 ይመለከቷል) ይላል:: በእኛ ውስጥ ከሚሠራው ሥራው የተነሣም ለክብሩ ምስጋና እንሆናለን (ኤፌሶን 1÷12):: እግዚአብሔር አማኞችን የጠራበት ዐላማ አማኞች የልጁን መልክ እስኪመስሉ ድረስ (ሮሜ 8÷29) ቅዱሳን እንዲሆኑ (ኤፌሶን 1÷4) ነው:: የእግዚአብሔር ጥሪም የእግዚአብሔርን ቅድመ ምርጫ/ምዳቤ መሠረት ያደረገ ነው (ሮሜ 8÷30):: የእግዚአብሔር ቅድመ ምዳቤ፣ ቅድመ እይታውን መሠረት ያደረገ ነው:: የእግዚአብሔር ቅድመ እይታው ደግሞ በግለሰቡ ማንነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ በራሱ በግለሰቡ በራሱ ላይ መሠረት ያደረገ ነው (እነርሱን ዐወቃቸው እንጂ ስለእነርሱ አይደለም):: ዕውቀቱም አእምሮአዊ ሳይሆን ኪዳናዊ ነው፤ ክርስቶስ የራሱ የሆኑትን እንደሚያውቀው በአንጻሩ ደግሞ የእርሱ ያልሆኑትን እንደማያውቃቸው ማለት ነው (ማቴዎስ 7÷23):: ስለዚህ "አስቀድሞ የወደዳቸውን" የሚለው ቃል ኪዳናዊና የፍቅር ግንኙነትን የሚያሳይ

ነው:: አስቀድሞ ያወቃቸውን (የወደዳቸውን) የክርስቶስን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖአል፤ ስለዚህ ከወሰናቸው መካከል አንድም ከድነት የሚጐድል የለም (ሮሜ 8÷29):: አስቀድሞ የወሰናቸውን (ይኸውም አስቀድሞ ያወቃቸውን) ጠራቸው፤ ስለዚህ ከወሰናቸው መካከል አንድም ከድነት የሚጐድል የለም (ሮሜ 8÷30):: ከዚህ ዕውቀት የተነሣም አማኞች የተባረከ ተስፋ አላቸው፤ ከዚህም ተስፋ አንዳችም ነገር አያጐድላቸውም፣

> ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን ይችላል? ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንዴት በልግስና አይሰጠን? እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ ታዲያ የሚኰንን ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል:: ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ራብ ወይስ ዕራቍትነት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ? ይህም 'ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን፤ እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን' ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው:: ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን:: ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ መላእክትም ይሁኑ አጋንንት፣ ያለውም ይሁን የሚመጣው ወይም ማንኛውም ኀይል፣ ከፍታም ይሁን ጥልቀት ወይም የትኛውም ፍጥረት፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም (ሮሜ 8÷31-39)::

በዚህ የድነት ሂደት ውስጥ የውሃ ጥምቀት የድነት ምልክትና ማኅተም ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ንብረት መሆናችንን የሚያረጋግጥ ውጫዊ ትእምርት ነው:: የእግዚአብሔር ንብረት መሆናችን እውን ሊሆን የሚችለው ደግሞ፣ አማኞች በእምነት ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ሲኖራቸውና እርሱም ከኀጢአታቸው ሲያነጻቸው ብቻ ነው:: መጠመቅ እየቻሉ አለመጠመቅ ስሕተት ቢሆንም፣ ጥምቀት ከዘላለም ኵነኔ አያስመልጥም:: እንዴት አድርገን እናጥምቅ የሚለው ጉዳይ ግን እንደ ሁኔታው የሚታይ ሲሆን ቀመሩ ግን ሥላሴ ነው::

የውሃ ጥምቀት አማኞች ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያላቸውን አንድነት የሚያመለክት ምልክትና ማኅተም ነው:: የጥምቀት ቀመር በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው ሲባል (ማቴዎስ



28÷19)፣ አማኞች ከሥላሴ አካላት ጋር ኪዳናዊ ትስስር አላቸው ማለት ነው:: ቃለ እግዚአብሔር፣ "እነርሱ ሁሉ ከሙሴ ጋር ለመተባበር በደመናና በባሕር ተጠመቁ" (1ቆሮንቶስ 10÷2) ወይም "በጳውሎስ ስም ተጠምቃችኋልን?" (1ቆሮንቶስ 1÷13) ሲል፣ ተጠማቂው ከሚጠመቅበት ስም ጋር ያለውን ኪዳናዊ ግንኙነት አመላካች ነው[127]:: ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ በሚከተሉት ክፍሎች በግልጥ የምንማረው ነገር፣ የውሃ ጥምቀት ተጠማቂው ከክርስቶስ ሞት፣ ቀብርና ትንሣኤ ጋር ኅብረት ማድረጉን የሚያሳይ ነው (ሮሜ 6÷3-6፤ 1ቆሮንቶስ 12÷13፤ ገላትያ 3÷27:28፤ 5÷8፤ ቈላስይስ 2÷11:12)[128]:: አጠቃላይ የውሃ ጥምቀት ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ኪዳናዊ ትስስር የሚያመለክት ምልክት ነው:: ሰዎች በኢየሱስ ስም ብቻ መጠመቅ አለባቸው የሚለው አስተምህሮ ስሕተት ከሚሆንባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ይህ የጥምቀት ቀመር ትምህርተ ሥላሴን መቃወሙ ነው:: በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቃችን ግን፣ ለሦስቱም አካላት መስጠታችንን እንዲሁም ከሦስቱም አካላት ጋር ኪዳናዊ ኅብረት ማድረጋችንን የሚያሳይ ነው::

የውሃ ጥምቀት አማኞች ከኀጢአት መንጻታቸውን የሚያመለክት ምልክት እንዲሁም ማኅተም ነው:: ቃለ እግዚአብሔር አንድም ቦታ የውሃ ጥምቀት ከኀጢአት ያነጻል ወይም ለዳግም ልደት ወሳኝ ጉዳይ ነው አይልም:: ነገር ግን የውሃ ጥምቀት ከኀጢአት ለመንጻታችን እንዲሁም ዳግም ለመወለዳችን ምልክት ወይም ማኅተም ነው የሚሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጸሐፍያን ጥምቀት ራሱ ከኀጢአት ያነጻል፣ ለዳግም ልደትም ወሳኝ ጉዳይ ነው ብለው ያብራሯቸዋል (ዮሐንስ 3÷5፤ ቲቶ 3÷5፤ 1ቆሮንቶስ 6÷11)፤ ይህ ስሕተት ነው:: ምልክቱን፣ ምልክቱ ከሚወክለው ቍም ነገር ጋር አቀላቅለዋልና::

[127] John Murray, *Christian Baptism* (Phillipsburg, N.J.: Presbyterian and Reformed, 1980), 3.
[128] ዝኒ ከማሁ::

የአዲስ ኪዳን የውሃ ጥምቀት የብሉይ ኪዳኑን ግርዘት የሚተካ ነው (ቈላስይስ 2÷11-12)[129]። የግርዘት ሥርዐት የአሮጌው ኪዳን (የብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመጽደቁ፣ ይቅር ለመባሉ፣ ዳግም ለመወለዱ በአጠቃላይ ለድነቱ) ምልክት ነው (ሮሜ 4÷8-12)። አካላዊ ግርዘት አንድን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረው አያግዘውም (ሮሜ 2÷28-29)። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲያደርግ የተጠራ ሰው፣ ከእግዚአብሔር ጋር የኪዳን ግንኙነት እንዳደረገ በግርዘት ሥርዐት ምልክት ወይም ማኅተም ያደርጋል (ሮሜ 4÷11)[130]። ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ የውሃ ጥምቀትም የአዲሱ ኪዳን (የሐዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመጽደቁ፣ ይቅር ለመባሉ፣ ዳግም ለመወለዱ በአጠቃላይ ለድነቱ) ምልክት ነው (ሮሜ 6÷1-5፤ ገላትያ 3÷27፤ 1ጴጥሮስ 3÷21)። ክርስቲያኖች ክርስቶስ ለኀጢአት ከሞተው ሞት ጋር አንድ መሆናቸውን/መተባበራቸውን (ሮሜ 6÷10-11)፣ ከሞቱ ጋር መሞታቸውን (ሮሜ 6÷3-4)፣ በድል አድራጊና በአዲስ ሕይወት በትንሣኤው መነሣታቸውን የሚያሳዩበት ሥርዐት/ምልክት ነው (ሮሜ 6÷4-5)። የውሃ ጥምቀት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲፈጠር የሚረዳ ሳይሆን፣ ኅብረት የፈጠረ ሰው ኅብረት ማድረጉን የሚያሳይበት ሥርዐት/ምልክት ነው (ሮሜ 2÷28-29 ጠንቋዩ ሲሞን የውሃ ጥምቀትን ቢወስድም የውሃ ጥምቀት መውሰዱ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲያደርግ አልረዳውም —ሐዋርያት ሥራ 8÷10-24—ሮሜ 9 ከቍጥር 13 ጀምሮ በግልጥ እንደምንመለከተው ሚዳዊ/ውጫዊ ሥርዐት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲያደርጉ ዕገዛ ሊያደርግላቸው እንደማይችል በግልጽ ይናገራል)። አንድ ሰው እምነት ከሌለው የውሃ ጥምቀት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ እንደማይረዳው ሁሉ፣ የጸደቀ፣ የኀጢአት ይቅርታ ያገኘ፣ ዳግም የተወለደ ሰው ግን እንዲጠመቅ ታዞአል (ሐዋርያት ሥራ 10÷48)። ጥምቀቱ

[129] አሮጌው ኪዳን ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን የቀፈ ቢሆንም እንኳ፣ ግርዘቱ የሚመለከታቸው ግን ወንዶቹን ብቻ ነው። ምልክቱ በአካላቸው ላይ በሰሌለ የኪዳኑ አባላት አይደሉም ማለት ግን በፍጹም አይቻልም።

[130] ግርዘት ከድነት እንደማያጐድለው ሁሉ (ሮሜ 4+10)፣ የውሃ ጥምቀትም ከድነት ሲያጐድል ወይም ለድነት ሊያበቃ አይችልም።



ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የኪዳን ግንኙነት የሚያመለክት ሰንደቅ ነውና (ሮሜ 4÷11፤ 6÷3-11፤ ገላትያ 3÷27)።

የዮሐንስ ጥምቀት ሰዎች ንስሓ ለመግባታቸውና የኀጢአት ይቅርታ ለማግኘታቸው ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ (ማቴዎስ 3÷6፤ ማርቆስ 1÷4፤ ሉቃስ 3÷3)፣ ክርስቲያናዊውም ጥምቀት ሰዎች ከኀጢአት ለመንጻታቸው ምልክት ነው (ሐዋርያት ሥራ 2÷38፤ 22÷16)። በአጠቃላይ የውሃ ጥምቀት በክርስቶስ ደም ተረጭተን ከኀጢአት መንጻታችንን የሚያመለክት ምልክት ነው።

የውሃ ጥምቀት ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በእምነት አንድ መሆናችንን እንዲሁም ከኀጢአት መንጻታችንን የምናሳይበት ሥርዐት/ምልክት ነው (ዮሐንስ 3÷18፤ ዕብራውያን 11÷6)። ስለዚህ አንድ አማኝ የውሃ ጥምቀት ያለመውሰዱ ኵነኔ አይሆንበትም፣ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ፣ አሁኑኑ ተፈርዶበታል" (ዮሐንስ 3÷18)። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐንስ 3÷16)።

የውሃ ጥምቀት በመርጨት፣ በማፍሰስ ወይስ በማስመጥ ይካሄድ የሚለው ጉዳይ መሠረታዊ ርእስ ጉዳይ አይደለም። "ጥምቀት" (ግሪክ "ባፕቲዞ" "βαπτιζω" ወይም "ባፕቲዝማ" "βαπτισμα") የሚለው ቃል ሦስቱንም (የተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ ውሃ ማፍሰስ ወይም መርጨት ወይም ደግሞ በውሃ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ማስመጥ) መንገዶች ሊያመለክት ይችላል። የውሃ ጥምቀት በተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ (በአብዛኛው እጅን መታጠብ) ውሃን ማፍሰስ ሊያመለክት ይችላል (ማቴዎስ 15÷2፤ ማርቆስ 7÷2-5፤ ሉቃስ 11÷38)። ጥንታዊ የሚባሉ የዕብራውያን ምንጮች እንደሚያስረዱት የብሉይ ኪዳኑ ጥምቀት በእጅ ላይ ውሃን ማፍሰስ እንጂ፣ እጅን ውሃ በያዘው ሳሕን ውስጥ መንከርን

አያመለክትም[131]:: በርካታ የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶች መርጨትን (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ዕብራውያን 9÷13:19:21) ማጥመቅ ብለው ይጠሩታል (ዕብራውያን 9÷10 እንደ NIV ሁሉ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ግሪኩ ጥምቀት "ባፕቲዞ" "βαπτιζω" የሚለውን መንጻት ብሎ ተርጉሞታል):: ጥምቀት የሚለው ቃል በተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ ማፍሰስንና መርጨትን እንደሚያመለክተው ሁሉ፣ ማስመጥንም ያመለክታል (ለምሳሌ የሚከተለውን ክፍል ይመለከታል 2ነገሥት 5÷14):: የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በመርጨት፣ በማፍሰስም ሆነ በማስመጥ ታጠምቅ እንደ ነበር በርካታ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ[132]:: ትክክለኛውም የጥምቀት ቀመር "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" (ማቴዎስ 28÷19) ማጥመቅ ነው:: ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉ፤ ከእነዚህ ምክንያቶች ውስጥ 1) የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወትና አስተምህሮ ከያዘው የማቴዎስ ወንጌል ላይ ስለሚገኝ፣ 2) ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው የመጨረሻ ትእዛዝ ስለሆነ፣ 3) ለጥምቀት ቀመርነት እንዲሁም ለማስታወስ እንዲያገለግል ሲባል በግጥም/በዜማ መልክ መቅረቡ[133]:: 4) የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታጠምቅ የነበረው በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነበር[134]:: 5) ስመ ጥር የቤተ ክርስቲያን አባቶች በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ እንዳለብን አስተምረዋል (ለምሳሌ ዮስጦስ ሰማዕት፣ ሔሬኔዎስ፣ ጠርጡ ሊያኖስ፣ ቆጵርያኖስ፣ አጉስጢ

[131] ዝኒ. ከማሁ፤ 12-14 ከAlfred Edersheim, *The Life and Times of Jesus The Messiah*, 3d ed. (Grand Rapids: Eerdmans, 1971), 2:10-12 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[132] *Didache*, 7:1-3; Lightfoot and Harmer, *Apostolic Fathers*, 232. በዚህ ረገድ ከላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክንና ዲዳኬ/ትምህርተ ሐዋርያትን በመጥቀስ የቀረቡትን ክፍሎች ይመለከቷል::

[133] E. Calvin Beisner, *God in Three Persons: The Doctrine of the Trinity in the New Testament and the Nicene Creed* (Bachelor's thesis, University of Southern California, 1978), 34 n. 7.

[134] ከላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክንና ዲዳኬ/ትምህርተ ሐዋርያትን በመጥቀስ የቀረቡትን ክፍሎች ይመለከቷል::



ኖስ)[135]:: 6) በርካታ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍያን፣ ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደ ሆነ መስክረዋል፣ (ለምሳሌ ሶዞመን (Sozomen) የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ፣ "ሐዋርያዊው ትውፊት እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ በጥንቃቄ ሲተላለፍ መጥቶአል እንደ አዲስ ግኝት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ አጥምቁ የሚሉት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡት አሪዮሳውያን ናቸው"[136] ሲል ጽፎአል:: በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሶቅራጥስ የተባለው ሌላው የታሪክ ጸሐፊ ሶዞመን ከሚለው ሐሳብ ጋር እንደሚስማማ ጽፎአል[137])::

## IV. ጥያቄ ለሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማንያን

አንድ ግለሰብ አባል የሆኑበት የሃይማኖት ድርጅት እጅግ አደገኛ የሆነ አስተምህሮ ቢያራምድ፣ የዚህ አደገኛ ትምህርት ቀዳማይ ሰለባ ደግሞ ግለሰቡና እንደ ግለሰቡ ያሉ የድርጅቱ ምዕመናን ቢሆኑ እንዲያውም እንደ ግለሰቡ ያሉ የድርጅቱ የዋህ አባላት የድርጅቱን ትምህርት ለማስፋፋት ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውን ከዚህም ዐልፎ ተርፎ ሕይወታቸውን ለዚህ አስተምህሮ ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉ፣ እርስዎ ደግሞ እነዚህ ሰዎች አባል የሆኑበት የሃይማኖት ድርጅት የተሳሳተ ትምህርት እንደሚያስተምር ጠንቅቀው ቢያውቁ፣ ለእንደዚህ ዐይነቶቹ የዋህ የድርጅቱ አባላት መሳሳታቸውን በይፋ አይነግሩምን?

በትልቅ ደስታ ያለውን እውነት አፍረጥርጠው እንደሚነግሯቸው እሙን ነው::

በታላቅ አክብሮት የምንልጽልዎት ጉዳይ፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን፣ ድርጅታቸው የተሳሳተ ትምህርት እንደሚያስተምር፣ ይህም

[135] ከላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክንና ዲዳኬ/ትምህርተ ሐዋርያትን በመጥቀስ የቀረቡትን ክፍሎች ይመለከቷል::

[136] Beisner, 72 ከ Sozomen, *Ecclesiastical History*, vi.26; in *NPNF*, 2, 2:363 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[137] ዝኒ. ከማሁ ከ Socrates, *Ecclesiastical History*, vi.25; in *NPNF*, 2, 2:135 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

ትምህርት ስለ እግዚአብሔርም ሆነ ስለ ድነት ቃለ እግዚአብሔር ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር ከፋኛ የሚቃረን እንደ ሆነ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ እችላለሁ። እነዚህ ማስረጃዎች ሁሉ ደግሞ ቃለ እግዚአብሔርንና ቃለ እግዚአብሔርን ብቻ መሠረት ያደረጉ ናቸው የሚል እምነት አለኝ። እኔ የማቀርባቸው ማስረጃዎች ትክክለኛ አይደሉም የሚሉ ከሆነ ግን፣ እርስዎ ማስረጃዎን ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት ባደረገ ሁኔታ የሚያቀርቡ ከሆነ፣ ልቀበላቸው ሙሉ ፈቃደኛ ነኝ። በዚህ የውይይት ዐላማም ሆነ ቅድመ ሁኔታ የምንስማማ ከሆነ፣ ቀጥዬ የማቀርባቸውን ጥያቄዎች በጥንቃቄ እንዲመረምሯቸው በታላቅ አክብሮት እጠይቅዎታለሁ። ጥያቄዎቹ የተውጣጡት ይህ መጽሐፍ ካቀረበው የሙግት ነጥቦች ላይ ስለሆነ፣ ጥያቄውን በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ የሚፈልጉ ከሆነ መጽሐፉን በጥሞና ያንብቡት።

1. እጅግ በርካታ መረጃዎች የማርቆስ ወንጌል የመጨረሻዎቹ ዐሥራ ሁለት ቁጥሮች (ማርቆስ 16+9-20) የማርቆስ ወንጌል ክፍል እንዳልሆኑ ያስረዳሉ፤ በተጨማሪም የምዕራቧም ሆነች የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትና ስዘብተኛ አቋም ያላቸው የነገረ መለኮት ሊቃውንት ይህ ክፍል የማርቆስ ወንጌል ክፍል ነው የሚል እምነት የላቸውም። በተጨማሪም በኢትዮጵያ የሚገኙት የኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር እንዲሁም የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ባሳተሟቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች (አዲሱ መደበኛ ትርጒም እንዲሁም 1980 ዓ.ም ትርጒም) ይህንኑ ሐቅ በግርጌ ማስታወሻዎቻቸው ላይ አስፍረዋል። ታዲያ በዚህ መልኩ በዓለም አብያተ ክርስቲያናትና በሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነት የሌለውን ክፍል በመጥቀስ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው ብሎ ማስተማር ተገቢ ነውን? እንዲያውም የክፍሉ ሁለተኛ እጋማሽ ፍርድ የሚጠብቀው የማያምነውን እንጂ ያልተጠመቀውን ነው አይልም። እርስዎ ይህንን ጒዳይ እንዴት ይመለከቱታል (በተጨማሪ በማርቆስ ወንጌል 16÷16 የቀረበውን ማብራሪያ ይመለከቷል)።

2. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መሥራችና የበላይ ጠባቂ ቄስ ተከለ ማርያም ገዛኸኝ፣ የውሃ ጥምቀት ለድነት እንዲሁም ለዳግም ልደት ወሳኝ ነው በሚል ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሷቸው ክፍሎች ዐውዳዊ ትርጒማቸውም ሆነ ስዋስዋዊ መልእክታቸው ወደዚህ



ድምዳሜ የሚያደርሱ አይደሉም (ከዚህ በላይ በዝርዝር የቀረቡትን ክፍሎች በጥሞና ይመልከቷቸው)። ቃለ እግዚአብሔርን ማብራራት ያለብን ዐውዳዊና ሰዋስዋዊ ትርጒሙን በተከተለ መንገድ ከሆነ፣ የድርጅቱ መምህራን ይህን መሠረታዊ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥበብ ለምን ያፋልሳሉ?

3. በመጽሐፍ ቅዱስ ሳይጠመቁ ወይም ከመጠመቃቸው በፊት ድነት ያገኙ (በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ/የተሞሉ) ሰዎች እንዳሉ በግልጽ ይነግረናል (ሉቃስ 23+39-43፤ ሐዋርያት ሥራ 10÷44-48፤ 9÷17-18)። ድነት ሳያገኙ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅም ሆነ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አይቻልም (ሮሜ 8÷9፤ ኤፌሶን 1÷13፤ 1ዮሐንስ 3÷24)። ይህ መረጃ እውነት ከሆነ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን፣ የውሃ ጥምቀት ለድነት እንዲሁም ለዳግም ልደት ወሳኝ ጒዳይ ነው እንዴት ይላሉ?

4. ቄስ ተከለ ማርያም ገዛኸኝ ከኢየሱስ ጋር የተሰቀለው ወንበዴ (ሉቃስ 23+39-43) የጸደቀው የውሃ ጥምቀት ለድነት በማያስፈልግበት በአሮጌው ኪዳን ነው ብለው ሲሞግቱ ይታያል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ ኪዳን የሚጀምረው ከኢየሱስ ሞት በኋላ እንደ ሆነ (ለምሳሌ ዕብራውያን 9÷17 ይመለከቷል) በተጨማሪም ኢየሱስ የሞተው ደግሞ አብረውት ከተሰቀሉት ወንበዴዎች በፊት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል (ዮሐንስ 19÷32-33)። ታዲያ ቄስ ተከለ ማርያም ገዛኸኝ ከኢየሱስ ሞት በኋላ ድነት የሚገኘው በአሮጌው ኪዳን ነው ብሎ ማስተማራቸው ስሕተት አይሆንምን?

5. አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቄስ ተከለ ማርያም ገዛኸኝ ይህ ሰው (ሉቃስ 23+39-43) ኢየሱስ በጦር በሚወጋበት ጊዜ ከጐኑ በፈሰሰው ውሃ ተጠ ምቋል የሚል ትምህርት አላቸው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ሰው ከኢየሱስ ጐን በፈሰሰው ውሃ ተጠመቀ የሚል ትምህርት አያስተምርም (ዮሐንስ 19+34)። እንዲያውም ከጐኑ የፈሰሰው ውሃ ኢየሱስ መሞቱን የሚያመለክት እንጂ ጥምቀትን የሚወክል እንዳልሆነ የሕክምና ሰዎች እንዲሁም የክፍሉ ዐውድ ያስረዳል (ለተጨማሪ በዮሐንስ 19+34 የቀረበውን ማብራሪያ ይመለከቷል)።

መጽሐፍ ቅዱስ "ከኢየሱስ ጉን የፈሰሰው ውሃ ይህን ወንጀለኛ ሰው ለማጥመቅ ነው" የሚል እንዳችም ትምህርት በማያስተምርበት ሁኔታ እንዲሁም የክፍሉ ትምህርት ስለኢየሱስ ሞት የሚተርክ እንጂ ስለውሃ ጥምቀት የሚናገር እንዳልሆነ በግልጽ እየታየ፣ ይህን ክፍል በዚህ መልኩ በማብራራት ከጌታ ጉን የፈሰሰው ውሃ ጥምቀትን የሚያሳይ ነው ይህም ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ነው ማለታቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያላስተማረውን ነገር ማስተማር አይሆንምን?

**6.** ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያድነውን የክርስቶስ ወንጌል ለመስበክ እንደ ተጠራ ሲገልጽ፣ ባለማጥመቁ ግን እግዚአብሔርን ያመሰግናል 1ቆሮንቶስ 1፥14-17:: እንዲያውም ሐዋርያው፣ "ለማጥመቅ ክርስቶስ አላከኝምና ወንጌልን ልሰብክ እንጂ" ይላል:: ጥምቀት የሚያድን ቢሆን ኖሮ ወንጌልን እንዲሰብክ በእግዚአብሔር እንደ ተላከው ሁሉ እንዲያጠምቅም ይላክ ነበር:: ወንጌልን መስበክ ለድነት ቅድመ ሁኔታ ሆኖ የመቅረቡን ያህል፣ የውሃ ጥምቀት የድነት ቅድመ ሁኔታ ሆኖ ያለመቅረቡን ያሳያል:: ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በተጻረረ መልኩ፣ ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝም ሆኑ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን የውሃ ጥምቀት ለድነት ውሳኝ ጉዳይ ነው እንዴት ይላሉ?

**7.** "ለኀጢአት ሥርየት" የሚለው ሐረግ የመጥምቁ ዮሐንስን ጥምቀት ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል (ሉቃስ 3፥3፤ ማርቆስ 1፥4)፤ ነገር ግን ማንም ሰው አፉን ሞልቶ የዮሐንስ ጥምቀት የሰዎችን ኀጢአት ያጥባል/ያስተሠርያል አይልም (የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን ራሳቸው እንዲህ ዐይነቱ እምነት እንደሌላቸው ግልጽ ነው)፤ ምክንያቱም በመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት የሚጠመቁ ሰዎች፣ ለንስሓቸው ምልክት ይሆን ዘንድ፣ በውሃ እንደሚጠመቁ ስለሚገነዘቡ ነው:: ከልብ ንስሓ በመግባታቸው እንጂ በመጠመቃቸው አይደለም የኀጢአት ሥርየት ያገኙት፤ የኀጢአት ሥርየት ለማግኘታቸው ምልክት ይሆን ዘንድ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ተጠምቀዋል:: ይህ እውነት ከሆነ ከክርስቲያናዊው የውሃ ጥመቀት ጋር በተያያዘ መልኩ፣ "ለኀጢአት ሥርየት" የሚለው ሐረግ (ሐዋርያት ሥራ 2፥38፤ 22፥16)፣ የውሃ ጥምቀት ኀጢአትን ያጥባል ወይም



ለድነት አስፈላጊ ነው ወደሚለው ድምዳሜ እንዴት ሊያደርስ ይችላል?

**8.** በርካታ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ለኀጢአት ሥርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ በቂ እንደ ሆነ በግልጽ ያስተምራሉ (እባክዎን የሚከተሉትን ክፍሎች በጥሞና ይመልከቷቸው ዮሐንስ 1፥12-13፤ 3፥15:16:18:36፤ 5፥24፤ 6፥35:40:47፤ 7፥38-39፤ 11፥25-26፤ 20፥31፤ ሐዋርያት ሥራ 2፥21፤ 10፥43፤ 11፥17፤ 13፥38-39፤ 15፥11፤ 16፥31፤ 20፥21፤ ሮሜ 1፥16፤ 3፥22:26:28:30፤ 5፥1፤ 10፥9:11:13፤ 1ቆሮንቶስ 15፥1-2፤ ገላትያ 2፥16፤ 3፥2-9:14:24:26፤ ኤፌሶን 2፥8-9፤ 2ተሰሎንቄ 2፥10:12፤ 1ጢሞቴዎስ 4፥10፤ 2ጢ ሞቴዎስ 3፥15፤ ቲቶ 3፥8፤ 1ዮሐንስ 5፥1:11-13):: በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ የውሃ ጥምቀት ለድነት ወይም ለዳግም ልደት ቅደመ ሁኔታ ተደርጎ አልቀረበም:: ይህ እውነት ከሆነ፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን፣ ሰዎች ካልተጠመቁ ድነት አያገኙም ወይም ዳግም ሊወለዱ አይችሉም ለምን ይላሉ?

**9.** ቅዱሳት መጻሕፍት ትእምርቶች/ምልክቶች ይጠቀማሉ:: እነዚህ ትእምርቶችም እንድ የተወሰነን ነገር ይወክላሉ፤ ለምሳሌ በጌታ ራት ወቅት የሚበላው ኅብስት የክርስቶስን ሞት ይወክላል (ዮሐንስ 6፥51:56፤ ሉቃስ 22፥19፤ 1ቆሮንቶስ 10፥16)፤ ነገር ድነት የሚያስገኘው ግን የሚቈረሰው ኅብስት ሳይሆን፣ የጌታ ሞት ነው:: የሚቈረሰው ኅብስት ግን ለኀጢ አታችን ለተቈረሰው የጌታ ሥጋ ትእምርት ነው:: ስለዚህ ትእምርት ከሚወክለው መሠረታዊ ሐሳብ ጋር መደባለቅ የለበትም:: የውሃ ጥምቀት ከኀጢአት ለመታጠባችን (ሐዋርያት ሥራ 22፥16) እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ለመፍጠራችን፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ለመቀበራችን እንዲሁም በትንሣኤ ቀን ከሙታን ለመነሣታችን ትእምርት ነው (ሮሜ 6፥1-7):: ይህ በሆነበት ሁኔታ የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው ብሎ ማስተማር ስሕተት አይደለምን?

**10.** የሐዲስ ኪዳኑ የውሃ ጥምቀት የብሉይ ኪዳኑን ግርዘት የሚተካ እንደ ሆነም ቃለ እግዚአብሔ በግልጽ ያስተምራል (ቈላስይስ 2፥11-12):: ግርዘት በብሉይ ኪዳን ለድነት ወሳኝ ጉዳይ እንዳልሆነ ሁሉ፣

የውሃ ጥምቀትም ወሳኝ ሊሆን አይችልም። አብርሃም ከመገረዙ በፊት እንደ ጻደቀ ከቃለ እግዚአብሔር እንማራለንና (ዘፍጥረት 15÷6)። ሮሜ 2÷28-29 በግልጥ እንደሚነግረን ለድነት አስፈላጊው ጉዳይ በመንፈስ የልብ መገረዝ ነው እንጂ፣ በሥጋ የሚደረገው ግርዘት አይደለም። አንድን ሰው እውነተኛ አይሁዳዊ ወይም የአብርሃም ልጅ የሚያደርገውም መንፈሳዊ ግርዘት ነው። ነገር ግን የክርስቶስ ደም እንጂ ውሃ ከኀጢ አት አያነጻንም (ዕብራውያን 9+13-14:12፤ 1ዮሐንስ 1+7፤ ራእይ 1+5፤ 7+14)። በጋብቻ የሚተሳሰሩ ጥንዶች በጋብቻ ኪዳን ውስጥ ወደውና ፈቅደው ለመግባታቸው ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ የጣት ቀለበት አንደኛው ወገን በሌላው ሰው ጣት ላይ ያኖራል። ቀለበቱ የጋብቻ ምልክት እንጂ ጋብቻ አይደለም። ልክ እንደዚሁ ሁሉ የውሃ ጥምቀት አንድ ሰው በአዲሱ ኪዳን ውስጥ መግባቱን፣ የኀጢአት ሥርየት ማግኘቱን ወዘተ የሚያውጅበት ትእምርት/ምልክት እንጂ ትእምርቱ ራሱ በአዲሱ ኪዳን ውስጥ ያስገባል የኀጢአት ሥርየት ያስገኛል ብሎ ማስተማር ፍጹም ስሕተት ነው።

**11.** የውሃ ጥምቀት ለኀጢአት ሥርየት ብቸኛ ጉዳይ (sufficient cause) አይደለም ምክንያቱም ጥምቀት ያለእምነት ዋጋ የለውምና (ማርቆስ 16+16፤ ዕብራውያን 11+6)። የውሃ ጥምቀት ለኀጢአት ሥርየት አንገብጋቢ ጉዳይ አይደለም (necessary cause) ምክንያቱም የኀጢአት ሥርየት ከውሃ ጥምቀት በፊት ሊገኝ እንደሚችል ቃለ እግዚአብሔር ያስተምራልና (ሐዋርያት ሥራ 2+41፤ 8+12፤ 9+18፤ 10+47-48፤ 16+14-15:30-33፤ 18+8፤ ሉቃስ 23+39-43፤ ሮሜ 4+9-12፤ ቈላስይስ 2+11-14)። ከእነዚህ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች በመነሣት የውሃ ጥምቀት ለድነት ብቸኛ እንዲሁም አንገብጋቢ ጉዳይ አይደለም ብንል ስሕተቱ እምኑ ላይ ነው?

**12.** የሐዲስ ኪዳን የውሃ ጥምቀት የብሉይ ኪዳኑን ግርዘት የሚተካ ነው (ቈላስይስ 2+11-12)። የግርዘት ሥርዐት የአሮጌው ኪዳን (የብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመጽደቁ፣ ይቅር ለመባሉ፣ ዳግም ለመወለዱ በአጠቃላይ ለድነቱ) ምልክት ነው (ሮሜ 4+8-12)። አካላዊ ግርዘት አንድን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት



እንዲኖረው አያግዘውም (ሮሜ 2+28-29)። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲያደርግ የተጠራ ሰው፣ ከእግዚአብሔር ጋር የኪዳን ግንኙነት እንዳደረገ በግርዘት ሥርዐት ምልክት ወይም ማኅተም ያደርጋል (ሮሜ 4+11)። ግርዘት በብሉይ ኪዳን ለድነት ወሳኝ ጉዳይ እንዳልሆነ ሁሉ፣ የውሃ ጥምቀትም ወሳኝ ሊሆን አይችልም። አብርሃም ከመገረዙ በፊት እንደ ጸደቀ ከቃለ እግዚአብሔር እንማራለንና (ዘፍጥረት 15+6)። ሮሜ 2+28-29 በግልጥ እንደሚነግረን ለድነት አስፈላጊው ጉዳይ በመንፈስ የልብ መገረዝ ነው እንጂ፣ በሥጋ የሚደረገው ግርዘት አይደለም። አንድን ሰው እውነተኛ አይሁዳዊ ወይም የአብርሃም ልጅ የሚያደርገውም መንፈሳዊ ግርዘት ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጥምቀት ያድናል ማለት ግርዘት ያድናል እንደ ማለት አይደለምን? ይህ ደግሞ በጳውሎስ መልእክቶች በተለይ በሮሜ መጽሐፍ ክፉኛ የተወገዘ ሐሳብ አይደለምን?

**13.** የፊልጵስዩስ እስር ቤት ዘበኛ፣ "እድን ዘንድ ምን ላድርግ" ሲል ጳውሎስና ሲላስን በጠየቃቸው ጊዜ፣ የሰጡት አጭርና ቀጥተኛ መልስ፣ "በጌታ በኢየሱስ እመን፤ አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ" የሚል ነበር (ሐዋርያት ሥራ 16+31-32)። ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ ጳውሎስና ሲላስ ይህን ሰው በእኩለ ሌሊት አቻኩለው ያጠመቁት እምነት ብቻ እንደማያድን ነገር ግን የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ መሆኑን ስለተገነዘቡ ነው ቢሉም፣ ግለሰቡ "እድን ዘንድ ምን ላድርግ" ብሎ በጠየቀ ጊዜ የተሰጠው መልስ፣ "እመን" የሚል እንጂ ተጠመቅ የሚል አይደለም። ነገር ግን ያመነ ሰው መጠመቅ ስላለበት አጥምቀውታል። "አቻኩለው" ያጠመቁት የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ስለሆነ ነው የሚል ሐሳብ በምንባቡ ላይ አልተጠቀሰም። "እንዳቻኩሉትም" የሚገልጽ ሐሳብ በክፍሉ ላይ አልተጠቀሰም። የውሃ ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ቢሆን ኖሮ፣ "እድን ዘንድ ምን ላድርግ" ላለው ሰው እነጳውሎስ "እመን" ብቻ ሳይሆን ተጠመቅም ይሉት ነበር። ይህ እውነት ከሆነ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሰው ካልተጠመቀ ድነት አያገኝም ለምን ይላሉ?

**14.** ቄስ ተከለ ማርያም ገዛኸኝ ማቴዎስ 28+19 ላይ "ስም" የሚለው ነጠላ ቃል አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ስሞች መሆናቸውን ያመለክታል ይላሉ። እንዲያውም ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ ሐዋርያቱ በኢየሱስ ስም ማጥመቃቸው አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ራሱ ኢየሱስ መሆኑን ያሳያል ይላሉ። ከግሪክ ቋንቋ ሰዋሰው አንጻር ሲታይ ግን ይህ ትንተና ስሕተት ነው (በማቴዎስ ወንጌል 28+19 ላይ የቀረበውን ማብራሪያ ይመለከቷል)። የቄስ ተከለ ማርያም የመጽሐፍ ቅዱስ ትንተና የበኩረ ጽሑፉን ሰዋሰው የሚጻረር መሆን አለበት? መጻረር ከሌለበት ቄስ ተከለ ማርያም ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር በኢየሱስ ስም ነው ማለታቸው ትክክል ነውን?

**15.** የውሃ ጥምቀት በመርጨት፣ በማፍሰስ ወይስ በማስመጥ ይካሄድ የሚለው ጉዳይ መሠረታዊ ርእስ ጉዳይ አይደለም። "ጥምቀት" (ግሪክ "ባፕቲዞ" "βαπτιζω" ወይም "ባፕቲዝማ" "βαπτισμα") የሚለው ቃል ሦስቱንም (የተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ ውሃ ማፍሰስ ወይም መርጨት ወይም ደግሞ በውሃ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ማስመጥ) መንገዶች ሊያመለክት ይችላል። የውሃ ጥምቀት በተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ (በአብዛኛው እጅን መታጠብ) ውሃን ማፍሰስ ሲያመለክት ይችላል (ማቴዎስ 15+2፤ ማርቆስ 7+2-5፤ ሉቃስ 11+38)። ጥንታዊ የሚባሉ የዕብራውያን ምንጮች እንደሚያስረዱት የብሉይ ኪዳኑ ጥምቀት በእጅ ላይ ውሃን ማፍሰስ እንጂ፣ እጅን ውሃ በያዘው ሳሕን ውስጥ መንከርን አያመለክትም። በርካታ የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶች መርጨትን (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ዕብራውያን 9+13:19:21) ማጥመቅ ብለው ይጠሩታል (ዕብራውያን 9+10 እንደ NIV ሁሉ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ግሪኩ ጥምቀት "ባፕቲዞ" "βαπτιζω" የሚለውን መንጻት ብሎ ተርጉሞታል)። ጥምቀት የሚለው ቃል በተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ ማፍሰስንና መርጨትን እንደሚያመለክተው ሁሉ፣ ማስመጥንም ያመለክታል (ለምሳሌ የሚከተለውን ክፍል ይመለከቷል 2ነገሥት 5+14)። "ጥምቀት" (በግሪኩ "βαπτιζω") በሚለው ቃል ላይ የተካሄዱ በርካታ ታሪካዊ፣ ቋንቋዊና ነገረ መለኮታዊ ጥናቶች፣ የውሃ ጥምቀት ተጠማቂውን በጥልቅ ውሃ ውስጥ በማስመጥ ብቻ



መካሄድ አለበት የሚለውን ጉዳይ አይደግፉም[138]። ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ከጻፉአቸው ጽሑፎች የምንማረውም ይህንኑ እውነት ነው። ይህ እውነት ከሆነ ቄስ ተከለ ማርያም አንድ ሰው በጥልቅ ውሃ ውስጥ በማስመጥ ካልተጠመቀ በቀር ድነት አያገኝም ለምን ይላሉ? መጠመቅ ለድነት አስፈላጊ ጉዳይ ካልሆነ፣ በማስመጥ ወይስ በማፍሰስ ወይስ ደግሞ በመርጨት የሚለው ጉዳይ እንዴት አንገብጋቢ ጉዳይ ሊሆን ይችላል?

**16.** ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" ካልሆነ፣ በማንስ ስም ሊሆን ይችላል? ምክንያቱም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ወጥነት ያለውና እንደ ቀመር ልንጠቀምበት የምንችለው አንዳችም የጥምቀት ቀመር የለም። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 2+38 ላይ፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም [ἐπί τῷ ὀνόματι Ἰησοῦ Χριστου]" ሲል፣ በሐዋርያት ሥራ 8+16 እና 19+5፣ "በጌታ በኢየሱስ ስም [εἰς τὸ ὄνομα τοῦ κυρίου Ἰησοῦ]"፣ በሐዋርያት ሥራ 10+48፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ἐν τῷ ὀνόματι Ἰησοῦ Χριστου" ይላል። በሐዋርያት ሥራ 10+48፣ ደግሞ፣ "ስሙን እየጠራህ [ἐπικαλεσάμενος τὸ ὄνομα αὐτοῦ" ] ይላል። በእነዚህ ምንባባት ውስጥ የመስተዋድድ ልዩነት ብቻ ሳይሆን፣ መሠረታዊ የሆኑ ቃላት ልዩነትም አለ፤ እንግዲያው ቀመሩ የሚያድን ከሆነ በየትኛው ቀመር እናጥምቅ/እንጠመቅ? "በኢየሱስ ስም" እና "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" የሚለው ጉዳይ በተለይ በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ዕይታ ሲታይ፣ ከፍተኛ ለውጥ አለው። "ኢየሱስ" ማለት የአብ (የእግዚአብሔር) ሰብአዊ አካል ሲሆን፣ "ጌታ" ደግሞ መለኮት ነው። "ጌታ ኢየሱስ" የሚለው ስያሜ አብና ወልድን የሚያሳይ ሲሆን (በአንድ ሰብዕና)፣ "ኢየሱስ" የሚለው ግን

---

138 ለምሳሌ "ጥምቀት" በሚለው ቃል ላይ ብቻ የሚያጠነጥነውንና ከ1,300 ገጽ በላይ ያለውን የጀምስ ዳልን አራት ቅጽ መጻሕፍት በናሙናነት መመልከት ይቻላል። James W. Dale, *Christic and Patristic Baptism: An Inquiry into the Meaning of the Word as Determined by the Usage of the Holy Scriptures and Patristic Writers.* 1874. Reprint. Phillipsburg, (N.J.: Presbyterian & Reformed; Wauconda, Ill.: Bolchazy-Carducci; and Toney, Ala.: Loewe Belfort Projects, 1995).

ሰባዊ ተፈጥሮን ብቻ ያሳያል። ይህ እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ትክክለኛው ቀመር የቱ ነው?

**17.** ከታሪክ መጻሕፍት ቀኖናዊ ሕግጋትን/አስተምህሮዎችን ለማውጣት መሞከር ከቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ ጋር በጽኑ የሚቃረን ነው። የታሪክ መጻሕፍት ምን እንደ ተካሄደ የሚነግሩን ምንባባት እንጂ ምን መሆን እንዳለበት የሚያስተምሩን መጻሕፍት አይደሉምና። የሐዋርያት ሥራ፣ ሉቃስ ለቴዎፍሎስ የጻፈለት ታሪካዊ ዘገባ ነው (ሐዋርያት ሥራ 1፥1)። ይህም ሉቃስ፣ ለቴዎፍሎስ የሐዋርያቱን ገድልና የመጀመሪያዪቱን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲያውቅ የጻፈለት ጽሑፍ እንጂ፣ ነገረ መለኮት ሊያስተምረው ያዘጋጀለት ድርሳን አይደለም። ከቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ ከምንባራቸው ሕግጋት መኻል አንዱ ሕግ፣ የታሪክ መጻሕፍት (መስተጋብአዊ ምንባባት) መብራራት ያለባቸው ምንጪታዊ ምንባባት (አስተምህሮአዊ ምንባባት) ከሚያስተምሩት ትምህርት አንጻር ብቻ ነው የሚለው ሕግ ነው። ይህ እውነት ከሆነ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራንና ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት መንገድን በትክክል ሳይረዱ ለማስተማርና ለመጻፍ መነሣታቸው የተሳሳቱ ትምህርቶችን እንዲያስተምሩ የሚያደርጓቸው አይመስሉትም?

**18.** በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በኢየሱስ ስም የተጠመቁት ሁሉ፣ በሥጋ ከአይሁድ ወገን የሆኑ ወይም የይሁዲን ሃይማኖት የተቀበሉ ሰዎች ብቻ ከሆኑ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ያለው ለአሕዛብ ማለትም ከአይሁድ ነገድ ውጪ ላሉ ሰዎች ከሆነ፣ በሥጋም ሆነ በሃይማኖት አይሁዳዊ ያልሆኑ ሰዎችን በኢየሱስ ስም ማጥመቅ ትክክል ነው? እንዲያውም በዚህ ስም ካልተጠመቃችሁ ድነት አታገኙም ማለት ስሕተት አይደለምን?

**19.** ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አንሥቶ እስከ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ (የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ቈርቋሪዎች እስከ ተነሡበት ዘመን ድረስ) በታሪክ የሚታወቅ አንድም ሰው ወይም እንቅስቃሴ የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ ስም ብቻ



ነው የሚል ትምህርት አስተምሮም ሆነ፣ በዚህ የጥምቀት ቀመር ሰዎችን አጥምቆ እንደማያውቅ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስተምረናል። ከጉባኤ ኒቂያ በፊት የነበሩትን የታሪክ መዛግብትን እንኳ ብንመለከት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታጠምቅ የነበረው፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደ ሆነ ማየት እንችላለን። በታሪክ በማይታወቅ እንዲሁም በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተጀመረ የጥምቀት ቀመር ተጠመቁ ይህም የጥምቀት ቀመር ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ነው ብሎ ማስተማር ኑፋቄ አይደለምን? በእነዚህ ዘመናትስ ሰዎች ድነት ሳያገኙ ቀርተው ነበር ማለት ነው? በእነዚህ ዘመናት እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክር ትቶ ነበር ማለት ነው?

**20.** ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፣ "ትምህርተ መለኮት" በሚል ርእስ በ1996 ዓ.ም ባዘጋጁት መጽሐፍ፣ በጥልቅ ውሃ በኢየሱስ ስም ከመጠመቃቸው በፊት፣ ክርስቶስን ከአምስት ጊዜ ባላይ በአካለ ሥጋ እንዳዩት እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልሳን ይናገሩ እንደ ነበር በስፋት ያስረዳሉ[139]። በተመሳሳይ መንገድ በጥልቅ ውሃ በኢየሱስ ስም ከመጠመቃቸው በፊት "መለኮታዊ ኀይል" የተባለውን መጽሐፋቸውን፣ ራሱ እግዚአብሔር እጃቸውን ይዞ በአንድ ጀንበር እንዳጻፉቸው እንዲሁም በጽሑፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ (በዚያች ሌሊት) ራሳቸውን እንኳ ያውቁ እንዳልነበረ ይመሰክራሉ[140]። እንደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በጥልቅ ውሃ መጠመቅ ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ከሆነ፣ ቄስ ተክለ ማርያም ይህ ሁሉ ታሪክ በሕይወታቸው የተከናወነው ድነት ከማግኘታቸው በፊት ነው ማለት ነው። ያልዳነ ሰው እንዴት በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላ ይችላል? (በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅም ሆነ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የዘላለምን ሕይወት የማግኘት ምልክት እንደ ሆነ ግን ልብ ይሏል ሮሜ 8፥9፤ ኤፌሶን 1፥13፤ 1ዮሐንስ 3፥24) ድነት ያላገኘ ሰው በልሳናት የመናገር ስጦታ

[139] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ *ትምህርተ መለኮት፤* አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት 1996፤ ገጽ 31-34።

[140] ለዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ቃለ መጠይቅ አድርጉላቸው በነበረ ጊዜ የተናገሩት ንግግር ነው፤ ንግግሩ በካሴት ተቀርጾአል።

እንዴት ሊሰጠው ይችላል? (እንዲያውም እንደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በልሳን መናገር የድነት ምልክት ነው)[141] የክርስቶስ አካል እንዴት መሆን ይችላል? እንዴትስ እግዚአብሔር ገንዘቡ ያላደረገውን በው (ዳግም ያልተወለደውን) እጁን ይዞ ስለራሱ ማንነት የሚገልጽ መጽሐፍ ሊያጽፈው ይችላል?[142]

[141] በሐዲስ ኪዳን ትምህርት ስልሳናት መናገር የድነት ምልክት ሳይሆንም እንኳ፣ ድነት ሳያገኙ በልሳን መናገር ይቻላል ማለት ግን በፍጹም ስሕተት ነው (የ x አባላት ሁሉ Y ውስጥ አሉ ማለት፣ የ Y አባላት ሁሉ x ውስጥ አሉ ማለት አይደለም:: ውሻ ሁሉ እንስሳ ነው ነገር ግን እንስሳ ሁሉ ውሻ አይደለም)::

[142] የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ናቸው የሚባሉት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ራሳቸው በዚህ መንገድ እንዳልተጻፉ ልብ ይሏል (ነገረ መለኮት ስለ ቀኖና እንዲሁም እስትንፋሰ መለኮት የሚያበተምረውን ትምህርት ይመለከቷል)::





# ዐሥራ ሰባት ዓመት
## "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"
## ባሪያ ነበርሁ
### የመጋቢ ንጉሤ ኀይሌ የሕይወት ምስክርነት[1]

### *ወደ እንቅስቃሴው መግባት*

በዚያን ጊዜ እንቅስቃሴው፣ "የተባበሩት ጵንጤቈስጣውያን" በመባል ነበር የሚጠራው:: "የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ስያሜ የመጣው ኋላ ነው:: ከዚህ ድርጅት ጋር የነበረኝ ግንኙነት የጀመረው ድንገት ነው ማለት ይቻላል:: ወደ ጌታ የመጣሁት 1963 ዓ.ም ላይ ነው:: አንድ ቀን ከጓደኛዬ ወደ አንድ ሰፍራ ይዞኝ ሄደ:: ይህ ሰው ከእኔ ቀደም ብሎ ጌታን የሚያቅ ሰው ስለነበር፣ እንደ መንፈሳዊ አባት እንዲሁም እንደ ታላቅ ወንድም የምመለከተው ሰው ነበር:: ከቄስ ተክሌ ጋር ረዘም ያለ ውይይት አደረጉ (በዚያን ጊዜ ቄስ ተክሌ፣ ቄስ ሳይሆን ወንጌላዊ ነበር):: ውይይታቸው ረዥም ሰዓት የፈጀ ነበር:: እኔ ግን በሚወያዩበት ርእሰ ጉዳይ ላይ ምንም ዐይነት ዕውቀት አልነበረኝም:: ከዚያ በፊትም ከቄስ ተክሌ ጋር ተገናኝተን አናውቅም:: ከውይይታቸው ዐልፎ ዐልፎ የተረዳሁት ግን፣ ውይይታቸው በትምህርተ ሥላሴ ዙሪያ የሚያጠነጥን እንደ ነበር ነው:: ይህ፣ እኔ ጌታን አግኝቼ ወይም ደግሞ ጌታ እኔን አግኝቶኝ ሕይወቴ በእግዚአብሔር ፍቅር እየተቀጣጠለ ያለበት ወቅት ነበር ነው:: በወቅቱ በነበርሁበት አካባቢ

[1] ይህ ጥር 30 ቀን 1996 ዓ.ም ከመጋቢ ንጉሤ ኀይሌ ጋር፣ በመጋቢነት ከሚያገለግሉበት ንፋስ ስልክ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ጊቢ ከሚገኘው ቢሮአቸው ውስጥ የተደረገ ቃለ መጠይቅ ነው::

በክርስትናዬ ምክንያት ስደት አጋጥሞኝ ከሥራም ሁሉ የተባረርሁበት ሁኔታ ነበር። ቢሆንም በእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅር ውስጥ የነበርሁበት ወቅት ስለነበር ችግሩ በዙም አልተሰማኝም፤ አላሳሰበኝምም። በመጨረሻ ባልንጀራዬ የነበረው ሰውና ወንጌላዊ ተክሌ በአንድ ሐሳብ ተስማሙ። ሊያጠምቀውም ወደ አንድ ወንዝ ይዞት ሄደ፤ አጠመቀውም።

ባልንጀራዬ በኢየሱስ ስም ተጠምቆ ሲመለስ፣ አንተስ ለምን አትጠመቅም የሚል ጥያቄ ቀረበልኝ። እኔ ስለጥምቀት የማቀው አንዳች ነገር የለም። ጥምቀት ራሱ ይኑር አይኑር እንዲሁም መጠመቅ አስፈላጊ ጉዳይ ይሁን የማያስፈልግ ጉዳይ አንዳች የማውቀው ነገር አልነበረም። በአንጻሩ ግን ለጓደኛዬ ትልቅ ከበሬታ ስለነበረኝ፣ የእግዚብሔርም ቃል ዕውቀት በሙላት አለው ብዬ የምገምተው ሰው ስለነበር፣ እርሱ ያደረገው ነገር ሁሉ ጥሩ ነው በሚል አስተሳሰብ፣ ተጠመቅ የሚለውን ግብዣ ተቀበልሁ፤ ቄስ ተክሌም አጠመቀኝ።

ችግር ውስጥ እንደ ገባሁ የተረዳሁት ግን በነጋታው ነበር። አንዳንድ ሰዎች የጓደኛዬንና የእኔን ስም በመጥራት፣ "አንሊ ጂሰስ (Only Jesus) ሆነዋል፤ ሥላሴን ክደዋል"፤ የሚል ወሬ በስፋት ይወራ ጀመር። ቢሆንም ግን በቀጥታ መጥቶ ያነጋገረኝ ሰው አልነበረም። ይህ ሁሉ ታሪክ የተፈጸመው ታዲያ በነጌሌ ቦረና ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ፣ ለሥራ ከሄድሁበት ከነጌሌ ቦረና ወደ አዲስ አበባ መጣሁኝ። አዲስ አበባ ስመጣ የት አካባቢ ላይ እነርሱ የአምልኮ ስፍራ እንዳላቸው ተነግሮኝ ስለነበርና የአዲስ አበባም ልጅ ስለነበርሁ፣ የሚያመልኩበትን አካባቢ አፈላልጎ ለመድረስ አላስቸገረኝም። ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ አገኘኋቸሁ። ከጥምቀቱ በኋላም እንኳ በትምህርቱ ላይ የጠለቀ ዕውቀት አልነበረኝም። በድርጅቱም ውስጥ ፍላጎት ኖሮኝ "እኔ አንሊ ጂሰስ ነኝ" በሚል ዐይነት መልክ የተመላለስሁበት ሁኔታ አልነበረም። የአምልኮ ፕሮግራማቸውንም እካፈል ጀመር። በተጨማሪ በወቅቱ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን፣ በአዲስ አባባ ናዝሬት ትምህት ቤት አካባቢ ስለነበር፣ እዚያም አዘውትሬ እሄድ ነበር። አብዛቹ የምሄደው፣ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ነው ማለት ይቻላል። በተለይ ደግሞ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ክፍል ስለነበራት፣ እኔ ደግሞ ቤቴ ውስጥ መጸለይ ስለማይመቸኝ፣ በየቀኑ ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አልለይም ነበር። በአብዛኛውን ጊዜ፣ በቀን ውስጥ የተወሰነ ሰዓት በጸሎት አሳልፋለሁ። እዚም እዚያም ማለትም ሙሉ ወንጌልም ሆነ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እያጣቀስሁ ለተወሰነ ጊዜ ቆየሁ።



ተክሌ ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን የወጣበት ዘመን ስለነበር፣ የእርሱ ጉዳይ በአብዛኞቹ የሙሉ ወንጌል ሰዎች ዘንድ የመነጋገሪያ ርእስ ሆኖ ነበር። "እንዲ እኮ ነው የሚለው"፤ "አይደለም እንደዚያ ነው የሚለው" ይባል ነበር። ነገር ግን የልዩነቱ ነጥብ ለእኔ ብዙም ግልጽ አልነበረም። ምክንያቱም ስለ ትምህርተ መለኮት የማውቀው አንዳች ነገር አልነበረም። እንዲያው ጌታ አዳኝ መሆኑን ተረድቼ የመጣሁ ሰው ብቻ ነኝ። ስለዚህ ሰዎች የሚሉት የትምህርተ መለኮት ጣጣ የማይገባኝ ርእስ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ስሜት የሚሰጠኝም ጉዳይ አልነበረም። ነገር ግን ትምህርቱ የመነጋገሪያ ርእስ የመሆኑ ጉዳይ፣ ቀስ በቀስ ነገሩ ምንድን ነው ብዬ እንድጠይቅ፣ ጉዳዩንም እንድመረምር ፍላጎት እያሳደረብኝ መጣ።

በጊዜው ሚስተር ዊንድል የሚባሉ "የተባበሩት ጴንጤቈስጣውያን"[2] ሚስዮናዊ ከነቤተሰቦቻቸው አዲስ አባባ ሲጃራ ፋብሪካ አካባቢ ይኖሩ ነበር። አንዳንድ ጽሑፎችን እንዲሰጡኝ ጠየቅኋቸው፤ በነበረችኝ ትንሽ የእንግሊዝኛ ችሎታ ዕየታገዝሁ የሰጡኝን መጽሐፍ እያነበብሁ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያስቀመጧቸውን ጥቅሶች እያመሳከርሁ፣ ጉዳዩን ማጥናት ጀመርሁ። በተቃራኒው ግን የሥላሴ አስተምህሮ ምን ይመስላል የሚለውን ጥናት እንዳካሂድ የሚገፋፋኝም ሆነ፣ በርእስ ጉዳዩ ላይ ጽሑፎችን የሚያቀብለኝ ሰው አልነበረም። ስለዚህ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ያለአንዳች ከልካይ የእነርሱን ትምህርት ብቻ ማስገባት ጀመርሁ። ቀስ በቀስም ከእነርሱ ጋር ያለኝ ኅብረት እየጠነከረ መጣ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ በወንጌል አገልግሎት እንዳገለግል ተጋበዝሁ። እኔም ደግሞ በልቤ ወንጌልን የማገልገል ትልቅ ሸክም ስለነበር፣ ያንን ጥሪ በደስታ በመቀበል ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ ወንድም ጋር በመሆን ሰላሌ በሚገኝ አንድ ገጠር ውስጥ የድርጅቱን አስተምህሮ መስበክ ጀመርሁ። እንግዲህ በዚህ መልክ ነው ከድርጅቱ ጋር በመቀላቀል የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ ሠራተኛ የሆንሁት።

[2] በአሜሪካን አገር የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነት የሚከተሉ በርካታ ቤተ እምነቶች ቢኖሩም እንኳ፣ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሚስዮናዊ የላከው የተባበሩት ጴንጤ ቈስጣውያን (United Pentecostal Church International) የተባለው ቤተ እምነት ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም (UPCI) በኢትዮጵያ ከሚገኘው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ጋር አብሮ ይሠራ ነበር። ለበለጠ ማብራሪያ፣ የዚህን መጽሐፍ የመጀመሪያ ቅጽ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ዳራ" የሚለውን ክፍል ይመለከቷል።

## የእንቅስቃሴው አገልጋይ መሆን

አገልጋይ ከሆንሁ በኋላ ትምህርቱን ለሌሎች በስፋት ለማበረዳት እንዲሁም ለመስበክ አስተምህሮአቸውን በትጋት ማጥናት ነበረብኝ። በዚህ ሂደት ውስጥ ቀስ በቀስ ትምህርቱን በወል እየተገነዘብሁ መጣሁ። በዚህ ጊዜ መተሐራና ወላይታ አካባቢ ለማገልገል የሄድሁባቸው ሁኔታዎች ነበሩ። በ1964 ዓ.ም ወላይታ አካባቢ ለአንድ ሳምንት ታስሬ ኋላ በዋስ ተለቅቄአለሁ። የመታሰሬ ዋነኛ ምክንያት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ በመሆኔ ብቻ ሳይሆን፣ ሙሉ ወንጌሎችን ጨምሮ የጵንጤቈስጤ አማንያን በሙሉ በወቅቱ ከፍተኛ ስደት በለነበረባቸው እንዲሁም ሰባክያኑ እየታደኑ ይታሰሩ ስለነበር ነው። የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በወቅቱ ትታወቅ የነበረው፣ "የተባበሩት ጴንጤ ቈስጣውያን" በሚለው ስም በለነበር፣ የመበደዱ ምክንያት ይኸው ነው። በዋስ ከተለቀቅሁ በኋላ፣ ፍርድ ቤት ሦስት ወር ፈረደብኝ፤ ነገር ግን እስራቱ በገንዘብ ስለተቀየረልኝ ገንዘብ ከፍዬ ልለቀቅ ቻልሁ።

## በእንቅስቃሴው ውስጥ የተፈጠረ እሰጣገባ

በ1964/65 ዓ.ም ላይ ተከለ ማርያም ሌላ አዲስ ትምህርት ጀምሮ ነበር። ትምህርቱ የእሳት ጥምቀት የሚባል ሲሆን፣ ትምህርቱ ከምን ምንጭ እንደ መጣ ማንም አያውቅም። ኋላ ኋላ ግን ፍራንክሊን ሆል ከሚባለው ሐሰተኛ አስተማሪ የተገኘ ትምህርት መሆኑን ተረዳሁ። ከዚህ የተነሣ በጊዜው ከነበሩት ሚስዮናውያን ጋር ችግር ተፈጠረ። እነርሱም ይህ የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት አይደለም ስለዚህ ተው አሉት። እርሱ ግን አሻፈረኝ በማለቱ ምክንያት ከሚስዮናውያኑ ጋር ተጋጨ። ቄስ ተክሌ በወቅቱ ያገለግል የነበረው በአዋሳ ነበር። በወቅቱ ያገለግሉ የነበሩት የድርጅቱ ሚስዮናውያን በመንግሥት ታውቀውና ተመዝግበው የገቡ በለነበር፣ የድርጅቱ ጸሎት ቤቶች ሁሉ ዕውቅና ነበራቸው። ነገር ግን ቄስ ተክሌ በአዲሱ ትምህርት ምክንያት ከድርጅቱ ተወግዞ ሳለ፣ ሚስዮናውያኑ በድርጅቱ ጸሎት ቤቶች ሁሉ ቄስ ተክሌ እንዳይሰብክ ዐገዱ። ቄስ ተክሌ ዕገዳውን አሻፈረኝ በማለቱ ምክንያት ሚስዮናውያኑ ጉዳዩን በወቅቱ ለነበሩት የአዋሳ ፖሊስ አዛዥ (ጀነራል ቀልቤሳ ይመስሉኛል) አመለከቱ። በዚህ ምክንያት ቄስ ተክሌና ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች ብዙ ተደበደቡ፤ ይሰብኩ የነበሩበት ቤተ ክርስቲያንም እንዲዘጋ ተደረገ።



ቄስ ተክሌ አልመለስም በማለቱ ምክንያት ተወገዘ፤ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ኅብረት ተወግዞ ተለየ። ነገሮች በዚህ መልኩ በመሄድ ላይ እንዳሉ፣ በ1966 ዓ.ም ደርግ መጣ። ደርግ የሚስዮናውያኑን ፈቃድ በመሰረዝ ሚስዮናውያኑ በፍጥነት አገር ለቀው እንዲሄዱ አስቸኳይ ትእዛዝ አወጣ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሚስዮናውያኑ በጊዜው ለነበርነው ሰዎች ኀላፊነቱን ሰጥተው ሄዱ። ቄስ ተክሌ በዚህ ሁኔታ ወስጥ ለሦስት ዓመት ታግዶ ቢቆይም፣ በወቅቱ ከነበርነው ሰዎች ሁሉ በፊት በእምነቱ አንጋፋ ስለሆነ፣ ከእኛ ለምን ይለያል በሚል ትምህርቱን በማስተካከል ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲያደርግ ግብዣ አቀረብንለት። ነገሩን እንዲሸመግሉም ሽማግሌዎችን ላክን። ከድርጹሩም በኋላ ቄስ ተክሌ (ያን ጊዜ ወንጌላዊ ነበር) ዳግም ከድርጅቱ ጋር ኅብረት ማድረግ ጀመረ።

በወቅቱ ሚስዮናውያኑ ኀላፊነቱን ሙሉ ለሙሉ የሰጡት፣ ለቄስ አማረ ዋቅቶላ ነበር። እኔ ደግሞ የቄስ አማረ ሁለተኛ ሰው ሆኜ እሠራ ነበር። ነገር ግን ቄስ ተክሌ በዕድሜም ሆነ በድርጅቱ አንጋፋ ስለነበር፣ የቤተ እምነቱ የበላይ ተጠሪ እንዲሆን ስለተስማማን ቦታው እንዲሰጠው ተደረገ። ቄስ አማረ (በዚያን ጊዜ ወንጌላዊ ነበር) የቄስ ተክሌ ምክትል ሆኖ የአዲስ አበባ ዋና ተጠሪ በሚሆን ጊዜ፣ እኔ ደግሞ የቄስ አማረ ምክትል ሆኜ እንድሠራ ተወሰነ። በዚያን ዘመን የነገረው የቤተ ክርስቲያኒቱ እንቅስቃሴ፣ በአዲስ አበባ፣ በወላይታ፣ በከንባታና በናዝሬት የተወሰነ ነበር። በወቅቱ ድርጅቱ ከእነዚህ ቦታዎች ውጪ አልተስፋፋም ነበር።

ውሎ ሳያድር ቄስ ተክሌ ሌላ አዲስ ትምህርት ጀመረ፤ ይኸውም "እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?" በሚለው መጽሐፉ ውስጥ በተወሰነ ደረጃ የጠቀሳት ትምህርት ነች፤ ይኸውም "አዳም ሲፈጠር መንፈስ ቅዱስ ነበረው" የሚል ትምህርት ነው። ይህን ትምህርት ከቀድሞ ከተወገዘበት ከፍራንክሊን ሆል ትምህርት ጋር በማቀናጀት ማስተማር ጀመረ። እኛም ማለትም ቄስ አማረ ዋቅቶላ፣ ቄስ ወርቁ ገ/ማርያም፣ ቄስ አሸናፊ፣ ቄስ ወልደ ጊዮርጊስ ሲሳይ፣ አቶ ሰሎሞን ሉዳሞና[3] እኔ (አቶ ሰሎሞን ሉዳሞ በስተቀር በዚያን ጊዜ እነዚህ ሁሉ

---

[3] በአሁኑ ወቅት ከመጋቢ ንጉሤ ኀይሌ በስተቀር እነዚህ ሰዎች በሙሉ በከፍተኛ የኀላፊነት ቦታ በድርጅቱ ውስጥ በመሥራት ላይ የሚገኙ ናቸው። ሰሎሞን ሉዳሞ ከቄስ ተክሌ ኅበረት ውጪ ከዓለም ዐቀፉ ቢሮ ጋር የሚሠራ ቢሆንም እንኳ፣ በማያዊ

ወንጌላውያን ነበሩ) አዳም ሲፈጠር መንፈስ ቅዱስ ነበረው የሚል ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ ስለማይገኝ፣ ትምህርቱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ባዕድ ነው በሚል፣ ዳግም ከቄስ ተክሌ ጋር የነገረ መለኮት አንጃ ግራንጃ ተፈጠረ። ቄስ ተክሌ ደግሞ ይህን ትምህርት ደጋግሞ ከማስተማርም በላይ በበራሪ ጽሑፍ አወጣ። ቀድሞ ትቼዋለሁ ያለውን የፍራንክሊን ሆልን ትምህርት ውስጥ ለውስጥ ማስተማርም ቀጠለ። ኋላ ግን የተሰጠውን ድርጅቱን የመምራት ኀላፊነት በመጠቀም፣ በኬንያ የሚገኘው የድርጅቱ ዋና ኀላፊና የሚስዮናውያን ተወካይ ለሆኑት ለሚስተር ሔሪስ፣ "አገልግሎቴን እየተቃወሙ ናቸው" በማለት የተለያየ ደብዳቤ ይጽፍብን ጀመር።

በዚህ ምክንያት በኬንያ የነበረው የሚስዮናውያን ተወካይ ሚስተር ሔሪስ ከኬንያ ወደ አዲስ አበባ መልእክተኛ በመላክ በጉዳዩ ላይ ስብሰባ እንዲካሄድ ተደረገ። በመጀመሪያው ቀን ስብሰባ ላይ ሁኔታዎች ጥሩ ስላልነበሩ፣ ለጊዜው ስብሰባው ከጸሎት ቤቱ ውጪ ቄስ ተክለ ማርያም ቤት እንዲካሄድ ተደረገ። እርሱ ይህ በሚሆንበት ጊዜ በደንብ ተዘጋጅቶ ነበር። በተለይ ከወላይታና ከከንባታ አካባቢ እርሱ ወንጌላውያን ያላቸውን ሰዎች ለድጋፍ በብዛት አሰባስቦ ነበር። ከላይ እንደ ጠቀስሁት እኛ ግን ስድስት ብቻ ነበርን። እኛም ቀድሞ ያስተምረው የነበረውንና ሚስዮናውያኑም ሆኑ እኛ ያወገዝነውን ትምህርት እንዳልተወ ገለጽን። በመጨረሻም ሚስዮናዊው ቄስ ተክሌ ደብዳቤውን በሚጽፍበት ውቅት፣ ደብዳቤውን እነርሱ ዘንድ ከመላኩ በፊት ለእኛ ማሳየት እንደ ነበረበት እንዲሁም የተወገዘበትን የቀድሞ ትምህርት ማስተማሩ በሕተት እንደ ሆነ ይፋ አደረገ። ቄስ ተክሌ በዚህ መልኩ በመወገዙ ምክንያት ደጋፊዎቹና እርሱ በበብሰባው ቦታ ከፍተኛ የሆነ ሁከት ፈጠሩ፤ በልሳን እየተናገሩ "እናንተ ሰይጣኖች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውጡ" ብለው አዋከቡን፤ ቤቱም በከፍተኛ ሁከት ተሞላ። እኛም ቤቱን ጥለን ወጣን።

ችግሩ እርሱ ዘንድ እንጂ እኛ ዘንድ እንዳልሆነ ታውቋል። ነገር ግን ምንም እንኳ እኛ እውነተኞች ሆነን ብንገኝም እኛ ከወጣን በኋላ፣ ከዩናይትድ ፔንቲኮስታል (United Pentecostal Church) ኅብረት እንድንለይ በድምፅ ብልጫ ተበየነብን። የሚበዮን ድርጅቱን ስናነጋግር

---

ሥጋ ከሚባለው ከቄስ ተክሌ ትምህርት በበተቀር የድርጅቱን አስተምህሮ ሙሉ በሙሉ ይቀበላል።



ቄስ ተክሌ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ስለሚያውቅ ለእኛ እርሱ ያስፈልገናል ነገር ግን እናንተ ትክክል መሆናችሁን ደርሰንበታል ወደሚል ድምዳሜ ተደረሰ። እኛም "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በሚል ስያሜ መንቀሳቀስ ጀመርን። በዚህ ምክንያት ቄስ ተክሌ "የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን" በሚል ስያሜ፣ እኛ (ማለትም ቄስ ወርቁ ገብረ ማርያም፣ ቄስ አሸናፊ፣ ቄስ ወልደ ጊዮርጊስ ሲሳይ፣ ቄስ አማረ ዋቅቶላ፣ አቶ ሰሎሞን ሉዳሞ[4] እንዲሁም እኔ) ደግሞ፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በሚል ስያሜ ለሁለት ተከፈልን።

## የእግዚአብሔር ምሪት

በዚህ መልኩ ጥቂት ዓመታት አብረን ከተጓዝን በኋላ፣ የቄስ ተክሌ ወገን ቄስ አሸናፊን ያዘ። እርሱ ደግሞ ከእኛ ጋር የነበሩ ጥቂት አማንያንን በመያዝ፣ ከእኛ በመገንጠል ከቄስ ተክሌ ኅብረት ጋር ተቀላቀለ። በዚህ መልኩ የእኛ ኅብረት እየተመናመነ መጣ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ የቄስ ተክሌ ወገን፣ ቄስ ወርቁንና ቄስ ወልደ ጊዮርጊስን ያዘ። እነዚህም ሰዎች የተወሰኑ ሰዎችን ይዘው ከቄስ ተክሌ ኅበረት ጋር ተቀላቀሉ። በዚህ ሁኔታ እኔና ቄስ አማረ እንዲሁም ጥቂት ሰዎች ብቻ ቀረን። ሁኔታው ከዐቅማችን በላይ ስለሆነብን፣ ቄስ አማረ ሌላ ሥራ ፈልጎ ተቀጠረ፤ እኔም ሥራ ፈልጌ ገባሁ።

በእግዚአብሔር አመራር በዚህ ሂደት ውስጥ ነው እንግዲህ እኔ አሁን ወዳለሁበት ደረጃ ልመጣ የቻልሁት። ለጥቂት ጊዜ አፍሪካ አንድነት ድርጅት ውስጥ የካፍቴሪያ አስተዳዳሪ ሆኜ እሠራ ስለነበር፣ ወርልድ ቪዥን ደግሞ በወቅቱ የፋሲሊቲ አስተዳደር ይፈልጉ ስለነበር፣ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ያገኘሁትን ሰርተፍኬት በመጠቀም ወርልድ ቪዥን ተቀጠርሁ።

ከዩናይትድ ፔንቲኮስታል ወይም ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምሮ ጋር መለያየት የጀመርሁት በዚህ ታሪካዊ ቦታና በዚህ ታሪካዊ ወቅት

---

[4] ሰሎሞን ሉዳሞ የቄበ ተክሌን ሰማያዊ ሥጋ የሚለውን ትምህርት በመቃወም በርካታ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያናትን" ከጉኑ በማሰለፍ ከዩናይትድ ፔንቲኮስታል ጋር የሚሠራ ሰው ነው።

ነው። እኔ ወርልድ ቪዥን የተቀጠርሁት በቀድሞው የትምህርተ መለኮት አቋሜ ነው። የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ትክክልኛ ነው የሚል ጽኑ እምነትም ነበረኝ። ስለዚህ ነገሮች እስከሚስተካከሉ ጊዜ ድረስ እዚህ እሠራለሁ ነገሮች ሲመቻቹ ግን ተመልሼ ወደ አገልግሎቴ እገባለሁ የሚል አቋም ነበረኝ። በአጠቃላይ እሠራ የነበረው ለመኖር የሚያስፈልገኝን ነገር ለማግኘት ብቻ ነበር።

ወርልድ ቪዥን ክርስቲያናዊ ድርጅት ስለሆነ፣ በነበርሁበት ፕሮጀክት በየቀኑ የጧት አምልኮ ፕሮግራም እንዲሁም በየሳምንቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የሰንበት አምልኮ እንዲሁም የማለዳ የጸሎት አለ። በዚያ ስፍራ የነበሩ ክርስቲያኖች የነበራቸው ሕይወት እጅግ በጣም የሚማርክ፣ ፈሪሓ እግዚአብሔር ያላቸው፣ እግዚአብሔርን ከልብ የሚወዱ፣ በአጠ ቃላይ የእኔን ሕይወት በአያሌው የሚማርክ ነበር። የእነዚህ ሰዎች አስደናቂ ሕይወት ከፍተኛ ጥያቄ እየፈጠረብኝ መጣ። አሁን እነዚህ ሰዎች ድነት የላቸውም ማለት ነው? ካልዳኑ መንፈስ ቅዱስ እንዴት ሊሞሉ ቻሉ? ይህ ዐይነቱን ማራኪ ሕይወትስ እንዴት ሊኖራቸው ይችላል? ይህ ዐይነቱ ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ከሆነ ደግሞ ድነት ሳያገኙ ይህ እውን ሊሆን እንዴት ይችላል? በውኑ እነዚህን ሰዎች በኢየሱስ ስም ታልተጠመቃችሁ ድነት አላገኛችሁም ማለት ተገቢ ነው? የሚለው ጉዳይ ልቤንና አእምሮዬን ወጥሮ ያዘው። እነዚህ ሰዎች ከነበሯቸው ጽሑፎች ያላቸውን ያህል፣ እኔም ማንበብ የምችለውን ያህል ሰጥተውኛል፤ ነገር ግን መሥሪያ ቤቱ በወቅቱ የዳበረ ቤተ መጻሕፍት አልነበረውም። በወቅቱ የነበሩት አብዛኞቹ ጽሑፎች በራሪ ወረቀቶች እንዲሁም መለስተኛ ጥራዝ ያላቸው መጻሕፍት ብቻ ነበሩ። በወቅቱ ያላቸውን፣ እኔም የምፈልገውን ያህል መረጃ ሰጥተውኛል።

በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በነበርሁበት ጊዜ፣ "የሥላሴ ስም ጥምቀት የተጀመረው ከአንድ መቶ ዓመተ ምሕረት ማለትም ሐዋርያው ዮሐንስ ከሞተ በኋላ ነው፤ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀት በኢየሱስ ስም እንጂ በሥላሴ ስም አልነበረም፤ የሥላሴ ስም ጥምቀት የተጀመረው ከዚያ በኋላ ነው" የሚል ትምህርት ነበር። ለዚህ አስተሳሰብ በማስረጃነት የሚያቀርበውም የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2፣ 8፣ 10፣ 19፣ 21፣ ላይ የምናገኘው የጥምቀት ቀመር በኢየሱስ ስም ነው። በሐዋርያቱ እግር ሥር ከተማሩት ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው ራሳቸው፣ ሥርዐተ



ጥምቀት ያካሂዱ የነበረው በኢየሱስ ስም ጥምቀት ነበር ባዮች ናቸው። ከዚህ በኋላ ግን የሥላሴ ስም ጥምቀት ቦታውን ያዘ ይባላል። በ1905 ዓ.ም አካባቢ በአሜሪካን አገር በአዙሳ በተጀመረው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ወቅት፣ "እግዚአብሔር ለአንድ ሰው በኢየሱስ ስም ጥምቀት ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር እንደ ሆነ ገለጸለት፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዳግም በኢየሱስ ስም ማጥመቅ ተጀመረ" የሚል ትምህርት አላቸው። ይህ ጉዳይ ጥያቄ ፈጠረብኝ፣ ይኸውም ከሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ፣ ቢያንስ ለአንድ ሺህ ስምንት መቶ ዓመት፣ ሰዎች በኢየሱስ ስም ካልተጠመቁ በዚህ ጊዜ ሰዎች ድነት አያገኙም ነበር ማለት ነው? በእነዚህ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ዓመታት ክርስቶስ አልተሰበከም ነበር ማለት ነው? በዚህ ወቅት እግዚአብሔር ራሱን ያለምስክር ተቶ ነበር ማለት ነው? በአጠቃላይ በእነዚህ ዘመናት ምን እየተካሄደ ነበር? እኔ እንኳ እስከ ማውቀው ድረስ በእነዚህ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ዓመታት ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ስደቶች በተለያዩ ቦታዎች ተከሥተው እንደ ነበር፣ በርካታ ሰማዕታት ለእምነታቸውም ሆነ ለወንጌል የሕይወት መሥዋዕት እንደ ከፈሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም የተስፋፋችበት ዘመን እንደ ነበር ዐውቃለሁ። በምንም ሚዛን ቢታይ ወንጌል አልተሰበከም፣ ሰዎች ድነት አላገኙም ማለት በፍጹም አይቻልም። ታዲያ በእነዚህ ዘመናት የነበሩ ሰዎች እግዚአብሔር አያውቃቸውም ነበር ማለት ነው? ለክርስቶስ ሰማዕት የሆኑ ሰዎች ሁሉ ደማቸው የፈሰሰው በከንቱ ነበር ማለት ነው? የሚለው ጉዳይ ትልቅ ጥያቄ በውስጤ ፈጠረ። ምክንያቱም ይህ ዐይነቱ አካሄድ የክርስቶስን ተልእኮ መና የሚያስቀር ነውና። ጌታ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱችሁ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ሲል፣ በእነዚህ ዓመታት ይህ እውን አልሆነም ነበር ማለት አይቻልም። እግዚአብሔር በእነዚህ ዘመናት የነበሩ ሰዎች እንዲጠፉ በይኖባቸው ነበር ማለት የሚቻል አይደለም።

በዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ውስጥ አንድ ነገር ፍንትው ብሎ ታየኝ፤ ይኸውም በስሕተት ውስጥ መሆኔ። ይህ ጉዳይ ሲገለጥልኝ ያማረርሁት እግዚአብሔርን ነው። ምክንያቱም ቀደም ብዬ እንዳልሁት ወደዚህ እንቅስቃሴ የገባሁት ሃይማኖቶችን በማወዳደር በራሴ ውሳኔ አይደለም። ዝም ብዬ ያለ ዕውቀት ነው የገባሁት። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱ ውሸት ውስጥ እንድገባ ለምን ፈቀደ? በተጨማሪም ከላይ እንደ

ገለጽሁት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተፈጠረው እስጣ ገባ ስድስታችን[5] በአንድ ወገን ሌሎቹ ደግሞ በሌላ ወገን በነበርንበት ሂደት ውስጥ፣ ያጋጠሙኝ ሁኔታዎች ቀላል አልነበሩም። ባለትዳር ነኝ፤ ልጆች አሉኝ፤ የነበረው ቤተ ክርስቲያን በጣም ደካማ ስለነበር ኑሮአችን ከእጅ ወደ አፍ የሚባል ብቻ ሳይሆን ምንም ሊባልለት እስከማይችል ድረስ፣ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ነው ያሳለፍነው። እኔ፣ ልጆቼና ባለቤቴ የምንበሳው ምግብ የምንለብሰው ልብስ፣ የምንጫማው ጫማ እስከምናጣ ድረስ ከፍተኛ በሆነ ጉስቁልና ውስጥ ነው የገባነው። በእኛ መረዳት ይህን ሁሉ ዋጋ የከፈልነው ስለወንጌልና ስለክርስቶስ ብለን ነው። ነገር ግን ይህ ሁሉ ነገር በሕይወታችን ውስጥ ዐልፎ ነገሮቹ ሁሉ ባዶ ሆነው መገኘታቸው  እጅግ በጣም አሳዘነኝ። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ እኔ ወደ እንቅስቃሴው የገባሁት የሃያዎቹ የዕድሜዬ ክልል ውስጥ ነው። በእነዚህ ረጅም ዓመታት "ሀ" ብዬ ፊደል በመቍጠር ትምህርት ብጀምር እንኳ፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ገብቼ ትምህርቴን የማጠናቅቅበት ጊዜ ነው። እነዚህ 17 ዓመታት በከንቱ መቃጠላቸው እጅግ በጣም አሳዘነኝ። ምክንያቱም ወደዚያ እንቅስቃሴ ያስገባኝ ተክለ ማርያም አይደለም፤ ጓደኞቼም አይደለም። ስለዚህ የችግሩ ተወቃሽ ማንም አይደለም። በዚህ ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ ከፉኛ ተማረርሁ። ነገር ግን እነዚህን ሁኔታዎች በመመልከት በግትርነት በቀድሞው አቋሜ መቀጠል አለብኝ የሚለውን ጉዳይ ውስጤ በፍጹም ሊቀበለው አልቻለም። ልቤ ተይዞአል፤ ተማርኳል።

## *ከእውነት ጋር መገናኘት*

ስለሥላሴ ባላውቅም እንኳ በዘመኔ ሁሉ የሥላሴን ትምህርት ስቃወም፤ ሰዎችን ከዚህ አስተምህሮ ሳፈናቅል ነው የቆየሁት። በወቅቱ ብቸኛ አማራጭ ነው ብዬ ያሰብሁት፣ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት በመቅረብ እግዚአብሔር ራሱ እውነቱን እንዲገልጽልኝ መጠየቅ ነበር። ይህን አቋም ወስጄ ያላንዳች የሥላሴም ሆነ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያናት አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሴን ለማንበብ ወሰንሁ። በሥላሴአውያንም ሆነ "በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አተያይ ሳይሆን፣ ቃሉን ሌጣውን በማጥናት እኔ የማገኘውን መረዳት ለመውሰድ ራሴን አሳመንሁ።

[5] እንቅስቃሴውን የምንመራው ስድስታችን እንሁን እንጂ፣ የእኛን አካሄድ/አስተምህሮ የሚደግፉ በርካታ ሰዎች ከእኛ ጋር አብረው ነበሩ።



ጥናቴን የጀመርሁት የዮሐንስን ወንጌልና የዮሐንስን መልእክቶች በማጥናት ነበር። የማታ ማታ አንድ ነገር ለውስጤ ሰላም ሰጠው። ይኸውም ሥላሴ የሚለው ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ።

ምናልባት ያን ጊዜ ስለሥለሴ አብራራ ቢሉኝ ላላብራራ እችላለሁ። ነገሬ ግን ይህ የሥላሴ አስተምህሮ እንደኛ ለልቤ ሰላም ሰጥቶታል፣ ሁለተኛ "በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ውስጥ በነበርሁበት ጊዜ የድርጅቱን አስተምህሮ ጥንቅቄ ዐውቀዋለሁ የሚል የራሴ የሆነ መረዳት ቢኖረኝም፣ የሚፈታተኑኝ ልረዳቸው የሚያስቸግሩኝ፣ የሚያውኩኝ ክፍሎች ነበሩ። በተለይ ሦስት ክፍሎች፤ አንደኛው ዮሐንስ ወንጌል 14 ላይ ያለው ክፍል፣ "ስፈራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ ወደ አባቴ እሄዳለሁ"፣ የሚሰው ሐሳብ ላይ፣ ተናጋሪው የሚናገረው አባቴ እያለ ነው፤ እኔ ደግሞ አብም ወልድም እርሱ ራሱ ነው ስል ነው የከረምሁት፤ አብ ነው ያልሁት ኢየሱስ አባቴ ብሎ ሲናገር እርሱ ራሱ ተመልሶ እንዴት አብ ሊሆን ይችላል? ይህ ጉዳይ ወልድ ከአብ የተለየ ማንነት ያለው ነው ወደሚለው ድምዳሜ እንዳልደርስ፣ በወቅቱ የነበርሁበት ትምህርት ሥላሴን እንድቀበል ዐይኔን ሸብቦ አስሮት ስለነበር፣ ነገሩን እናንቄ ማለፍ ነው የምመርጠው። 21ኛው ቍጥር ላይ ደግሞ፤ "የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ…ወደ እርሱ እንመጣለን፣ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን" የሚለው ክፍል፣ ኢየሱስ በብዙ ቍጥር ነው ስለእርሱና ስለአባቱ የሚናገረው። ምዕራፍ 17 ላይ ስለእርሱና ስለአባቱ "እኛ" እያለ የሚናገረው ንግግር ምንም ዐይነት ማስረጃ ላገኝላቸው የማልችላቸው ክፍሎች ነበሩ። የሚገርመው ይህ ጥያቄ የእኔ ብቻ ሳይሆን፣ የባለቤቴ ጥያቄም መሆኑ ነው። ብዙ ጊዜ ይህን ጥያቄ ስትጠይቀኝ፣ እኔም ራሴ ጥያቄ የፈጠረብኝ ክፍል ነው ከማለት ይልቅ፣ ብዙ ጊዜ የምሰጠው መልስ፣ "ዝም ብለሽ መጽሐፍ ቅዱስሽን አጥኚ" የሚል ነበር። በእነዚህ ክፍሎች ላይ እኔ ራሴ ጥያቄ እንዳለኝ ገልጬላት አላውቅም። ይህ የሆነበት ምክንያት "ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ጋር የነበረን ኅብረት በብዙ አሸንፎን ስለነበር ይህ ዐይነቱ ሁኔታ ከመንገዳችን እንድንመለስ አላደረገንም ነበር። ይህም ለረጅም ጊዜ ጥያቄ ሆኖ የኖረ ጉዳይ ስለነበር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ብሎ ማመኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን በግልጥ መረዳት ቻልሁ። አንሊ ጂስስ በነበርሁበት ጊዜ እንደምለው አብም ወልድም መንፈስ ቅዱስም ኢየሱስ

ነው ብዬ ቀጣጥዬ እንደማወራው ትምህርተ ሥላሴን ማብራራት ባልችልም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያየ ማንነት እንደ ነበራቸው ግን መረዳት ቻልሁ።

የዮሐንስ ወንጌልንና የዮሐንስን መልእክቶች አንብቤ እንደጨረስሁ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተንበርክኬ ጸለይሁ። በመጀመሪያ ውስጤ ስላልለመደው ፈርቶታል፤ በጸሎቴም ፈራ ተባ ብያለሁ። ነገር ግን ደጋግሜ በጸልይ በውስጤ ትልቅ ደስታና ሐሴት ነው የፈሰሰው። ብዙ ጊዜ ለሰዎች ተናግሬአለሁ። በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ ሰዎች ምስክርነት ስጥ ሲሉኝ፣ ስለሥላሴ ለመረዳት ለእኔና ለእናንተ አንድ አይደለም፤ እኔ የሥላሴን እውነት በተቀበልሁበት ዕለት፣ እግዚአብሔር በውስጤ በመንፈሱ ያስቀመጠው ትልቅ ደስታና ሐሴት እናንተ እንደኔ ስላልነበራችሁ ልትረዱኝ አትችሉም፤ ስለዚህ ይህ እውነት በቃሌ ከማስረዳው ይልቅ በውስጤ እውነት ነው የሚለውን ነገር እነግራቸዋለሁ። በዚያን ቀን መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ያደረገው ነገር ትልቅ ማረጋገጫ ሆኖልኛል ብዬ የተናገርሁባቸው ሁኔታዎች አሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ምን ጊዜም ከልቤ የማይደመሰስ ትልቅ ደስታና ሐሴት ነው በልቤ አስቀምጦ ያለፈው።

## *መሠረተ እምነታችንን እንወቅ*

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ዐልፌ ከዓመታት በኋላ፣ አንዳንድ ሰዎች ከአንሊ ጂሰስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ፣ የምናግራቸው የራሴን የግል ምስክርነት ነው። በምን ሁኔታ ውስጥ ዐልፌ ወደዚህ ደረጃ እንደ ደረስሁ እተርክላቸዋለሁ። ያለፍሁባቸውን ጉዳናዎች ሁሉ አስቃኛቸዋለሁ። ከትምህርተ መለኮት ውይይቱ ይልቅ ይህ የብዙዎችን ሕይወት ሲነካ አይቻለሁ። ምክንያቱም ሰዎች የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት የሚቀበሉበት ምክንያት፣ ሰዎች ትምህርተ ሥላሴን መረዳት ስለሚቸግራቸው፣ ርእስ ጉዳዩንም ጊዜ ሰጥቶ ለማጥናት ፍላጎት ስለሌላቸው ነው። በርካታ የሥላሴ አማንያንም በአስተምህሮው ላይ የጠለቀ መረዳት ስለሌላቸው፣ ከአንሊ ጂሰስ የሚመጡትን ሰዎች ማነጋገር አይችሉም[6]።

[6] ስለ ትምህርተ ሥላሴ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የዚህን መጽሐፍ የመጀመሪያ ቅጽ እንዲሁም የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ "የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት" በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መለስተኛ መጽሐፍ ይመስከቷል።



አንድ የማስታውሰው ታሪክ አለ። በአሁኑ ጊዜ ጥሩ ወዳጄ የሆነ የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ነው። አንዲት የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ልጅ ጉረቤቷ የነበሩ አንዲት እናት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንድትጠመቅ ነግረዋት ከእኔ ጋር ያገናኟታል። እኔም ጥምቀት በኢየሱስ ስም ብቻ መካሄድ እንዳለበት፣ በኢየሱስ ስም ያልተጠመቀም ሰው ድነት እንደማያገኝ ነገርኋት። ነገሩን ብትቀበለውም እንኳ፣ ቀድሞ የነበረውን የሥላሴ እምነቷን ጥላ ወደዚህ እምነት ለመምጣት ተቸገረች። ከዚህ የተነሣ ወደሚከተለው አቋም ላይ ደረሰች፣ "የእኔን ቤተ ክርስቲያን ስመ ጥር ወንጌላዊ አጠራለሁ፤ አንተና እርሱ በርእሱ ጉዳዩ ላይ ትነጋገራላችሁ፤ ከሁለታችሁ ያሸነፈው ወገን ይወስደኛል" አለች። እኔም ጉዳዩን በደስታ ተቀበልሁት። ያም ወንድም ተጠርቶ መጣ፤ በጊዜው የታወቀ ወንጌላዊ ነው፤ እኔም በርቀት የማውቀው ሰው ነበር። እኔ በጉዳዩ ላይ ተዘጋጅቼ፣ እንዳያመልጥ አድርጌ ለመያዝ እንዲመቸኝ በጣም ትሑት ሆኜ ተቀበልሁት። ጸሎት እንዲጸልይም ቅድሚያውን ለእርሱ ሰጠሁት። እርሱም ወይይቱን በጸሎት ጀመረ። አሁን ወግ ባለው መንገድ ውይይታችንን ለማካሄድ እኔ ንግግሬን ስጨርስ እርሱ ይናገራል፤ እርሱ ሲጨርስ ደግሞ እኔ እናገራለሁ፣ ይህ ሁኔታ ትርምስ እንዳይኖር እንዲሁም ሰዎች ጉዳዩን በትክክል እንዲረዱ ያደርጋቸዋል ወደሚለው መግባባት ላይ ደረስን። ብዙ እየተነጋገርን መጣን፤ ነገር ግን ግለሰቡ የሥላሴ አማኝ ይሁን እንጂ፣ በሥላሴ ትምህርት ላይ ጥልቀት ያለው ዕውቀት ስላልነበረው፣ እኔ ደግሞ አለኝ በምለው በቀድሞ ትምህርት ላይ ጥሩ መረዳት ስለነበረኝ፣ ቀስ እያልሁ እያደበላለቅሁበት መጣሁና በመጨረሻም ይህ ስመ ጥር ወንጌላዊ ትምህርቱ ጠፋበት። እርሱ መልስ እያጠረው ሲመጣ፣ እኔ ደግሞ የልብ ልብ እየተሰማኝ፣ "ዐዋቂ ነህ" የሚል ብርታት እያገኘው መጣሁ። በአሸናፊነት ስሜት ተሞላሁኝ። ከዚህ የተነሣ ከበፊቱ ይልቅ እጅግ ትሑት ሆንሁኝ። በመጨረሻ እርሱ መልስ እያጠረውና ዐውቀዋለሁ የሚለው ትምህርት እየተደበላለቀበት ሲመጣ ቀጥ ቀጥ ይለው ጀመር፣ ተናደደ፣ ተነሥቼ እሄዳለሁ አለ። እኔ ድግሞ በፍጹም ይህ መሆን የለበትም ውይይታችንን በጸሎት ስለጀመርን በጸሎት መጨረስ ይኖርብናል አልሁት። ነገር ግን ለመቆየት ፍጹም ፈቃደኛ ስላልሆነ ተነሥቶ ሄደ። ልጅቷን ትቷቶ መሄዱን ግን አልተገነዘበውም ነበር።

በሥላሴ ትምህርት ላይ አብዛኞቹ የሥላሴ አማንያን ራሳቸው አጥጋቢ የሆነ መረዳት አላቸው ማለት አያስደፍርም። በርካታ አገልጋዮች፣

ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን ሰዎች ራሳቸው ከማነጋገር ይልቅ ወደ እኔ የሚልኩበት ዐቢይ ምክንያቱም የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ያለማወቃቸው ብቻ ሳይሆን፣ ምናልባት በሥላሴ አስተምህሮ ላይ ጠንካራ ዕውቀት ስለሌላቸው ሊሆን ይችላል::

"ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" እኔ ዘንድ የሚመጡትን ሰዎች በቅድሚያ የምነግራቸው ከድርጅቱ ጋር የነበረኝ የራሴን የሕይወት ታሪክ ነው:: የእኔን ተሞክሮ ከሰሙኋቸው በኋላ የዮሐንስ ወንጌልን እንዲያነቡ፣ እንዲጸልዩ፣ የእግዚአብሔርን ርዳታ እንዲሹ አመክራቸዋለሁ:: ከዚያ በኋላ ነው ወደ ነገረ መለኮቱ ትንታኔ በሰፋት የምገባው:: በዚህ ዐይነቱ አካሄድ ብዙ ሰዎች ተመልሰዋል:: በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ረድቷቸው በኋላ አገልጋይ የሆኑ ብዙ ሰዎችን ዐውቃለሁ:: ሙስሊሞችንና እነርሱን መርታት የሚችለው ጸሎት፣ ፍቅርና መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው::

"በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አካባቢ ያስሄደኛል፣ መሠረተ እምነቴን ያጸናልኛል በሚሏቸው ጥቅሶች ላይ ክርክር ስለሚያስተምሯቸው፣ ብዙዎቹ ""የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማንያን ክርክር ይወዳሉ:: ሌላው ወገን ደግሞ ለክርክሩ መልስ የለውም:: ይህ የሚሆነው ግን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማንያንና የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች በቃለ እግዚአብሔር ላይ ጠንካራ ዕውቀት ስላላቸው ሳይሆን፣ በጣት የሚቈጠሩ ጥቅሶችን በቃል በማስጠናትና ክፍሎቹን በድርጅቱ አስተምህሮ መሠረት በመተንተን ተከታዮቻቸውን ስለሚያሠለጥኑ ነው:: ስለዚህ የድርጅቱ ሰዎች መከራከር ይወዳሉ:: የሥላሴ አማንያኑ ግን ለአስተምህሮው ከፍተኛ ትኩረት ስለማይሰጡ እንዲሁም በሌላ ድርጅት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ከአካሄዳቸው እንዲመለሱ በሌላ ወገን ያለውን ትምህርት ስለማያጠኑ እንዲሁም ቀዳሚ ሳልሆኑ ነገሮች ከፍተኛ ትኩረት ስለሚሰጡ እነርሉ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄና ትንተና መልስ ለመስጠት ይቸግራቸዋል::

## የእኔና የቤተ ሰቤ ቀጣይ ታሪክ

እንግዲህ በዚህ ሀይነት መንገድ ነው እግዚአብሔር እኔን ያሸነፈኝ:: ከነበርሁበት አስተምህሮ የአቋም ለውጥ ሳደርግ፣ ከአሁን በኋላ ምን ማድረግ አለብኝ? የሚለው ጥያቄ ቀዳሚው ጥያቄዬ ሆነ:: አቋሜን



መግለጥ ይፋ ማድረግ አለብኝ በሚለው ጉዳይ ላይ ውሳኔ አደረግሁ:: እኔና አምስት ሰዎች ከነቄስ ተክሌ በተለየን ጊዜ የእኛ ኅብረት ቄስ አማረ ዋቅቶላን የበላይ ኀላፊ አድርጎ እኔን ደግሞ የአዲስ አበባ መጋቢ አድርጎኝ ነበር:: ስለዚህ የእኔ አለቃ ቄስ አማረ ዋቅቶላ ስለነበር፣ ቄስ አማረንና አቶ ሰሎሞን ሎዳሞን በመጥራት አቋሜን አስታወቅኋቸው:: እስካሁን ድረስ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚጠመቁትን ሰዎች አልዳናችሁም ማለቴ በእግዚአብሔር ፊት ንስሓ ገብቻለሁ:: ሰዎች በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው ይድናሉ:: ስለዚህ እኔ በዚህ መንገድ የተናገርሁት የሰበክሁትም ትምህርት ሁሉ ትክክል አይደለም:: በዚህ መልክ ያሰናከልኋቸውና ከእምነታቸው ስላወጣኋቸው ሰዎች ንስሓ ገብቻለሁ፤ እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቄአለሁ:: እኔ እንግዲህ ከአሁን በኋላ ከእናንተ ጋር አይደለሁም፤ ልሆንም አልችልም አልኋቸው::

እነዚህ ሰዎች ግን ለዚህ ጉዳይ ብዙም ትኩረት የሰጡት አልመሰለኝም:: ይህ የሆነበት ምክንያት፣ ቀድሞ በነበረው እስጣገባ እንዲሁም በደረሰበት የኢኮኖሚ ችግር አእምሮው ተነክቶ ሊሆን ይችላል በማለታቸው ነው:: ምክንያቱም ንጉሤ ከማንም "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ሰዎች ይልቅ አስተምህሮውን ይተነትናል የምባልና ለብዙዎች እንደ ተምሳሌት የምታይ ሰው ነበርሁ:: እነርሱ ራሳቸው በጣም ኀይለኛ ተከራካሪዎች ሲመጡባቸው የሚልኳቸው እኔ ዘንድ ነበር:: ወደ እኔ የመጡትን ደግሞ ቢሆን ቢሆን፣ የሥላሴ እምነታቸውን አስጥላቸዋለሁ ወይም ደግሞ ከፋኛ አደናግራቸዋለሁ:: ከሁለት አንዱ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው:: በደርግ ዘመን ወደ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ነፍሳትን ለመስረቅ እሄድም ነበር:: በአጠቃላይ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንኳ በተለይ ከሳጋር መለስ ባሉት የአዲስ አበባ የሚገኙ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሰዎች ዘንድ እንኳ የታወቅሁ ነበርሁ:: በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ያለ ሰው፣ የድርጅቱን አስተምህሮ ለቆ ይሄዳል ብሎ ማሰብ በፍጹም የሚከብድ ነበር::

በ1979/80 ዓ.ም ላይ የቄስ ተክለ ማርያም ሚስት ወይዘሮ እርቅነሽ እናንተ ወደ እኛ እንድትመለሱ እግዚአብሔር ልኮናል ብላ በመምጣት ከእነርሉ ጋር የእርቅ ድርድር ለማድረግ ስምምነት ላይ ተደረሰ:: ምንም እንኳ እኔ አቋሜን ባሳውቃቸውም ከላይ በጠቀስሁት ምክንያት በድርድሩ ወቅት አብሬአቸው እንድሆን እነቄስ አማረ ስለጠየቁኝ በድርድሩ ወቅት አብሬአቸው ነበርሁ:: በድርድሩም ወቅት ከተነሡት

የትምህርተ መለኮት ውይይቶች መካል አንዱ "ስማያዊ ሥጋ" የሚለው የቄስ ተክሌ ትምህርት ነበር[7]:: ምክንያቱም ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሰዎች ይህን ትምህርት ተቃውመው ነበርና ነው:: ከቄስ ተክሌ ከተለየን በኋላ እንኳ ከቄስ ተክሌ ጋር ኅብረት እንፈጥርም ካልንባቸው ምክንያቶች መካል አንዱ፣ ቄስ ተክሌ "ስማያዊ ሥጋ" የሚባል የኑፋቄ ትምህርት ያስተምራል የሚለው ጉዳይ የመከራከሪያ ነጥባችን ነበር:: በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ክርክር አደረጉ:: እኔ ግን በክርክሩ ውስጥ አልነበርሁም:: ምክንያቱም እኔ ከእነርሱ ጋር በለማልቀጥል፣ ነውም አይደለምም የሚለው ጉዳይ ለእኔ መሠረታዊ ጉዳይ አልነበረም:: ቄስ ተክለ ማርያም ግን፣ "ይህን ትምህርት የገለጠልኝ እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ ለእናንተም አንድ ቀን ሊገልጥላችሁ ይችላል:: ነገር ግን መሠረታዊው በሆነው ትምህርት ላይ ተመሳሳይ አቋም ስላለን ይህ ትምህርት ሊለያየን የሚችል ጉዳይ አይደለም" በማለቱ ስምምነቱ እንዲካሄድ ተደረገ[8]::

---

[7] "በማያዊ ሥጋ" በመባል የሚታወቀው የቄስ ተክሌ አስተምህሮ፣ በቄስ ተክሌ የበላይ ጠባቂነት ሥር ባለችው ቤተ ክርስቲያንና በዓለም ሀቀፉ ቢሮ ዘንድ ትልቅ ልዩነት የፈጠረ እንዲሁም ቄስ ተክሌ በዓለም ሀቀፉ ቢሮ "መናፈቅ" ተብለው እንዲወገዙ ያደረገ፣ የቄስ ተክሌ መጽሐፍ፡ ድርጅቱ በሚገኝባቸው በሌሎች አገሮች እንዳይሸጥ በዓለም ሀቀፉ ቢሮ የበላይ ጠባቂ እንዲታገድ ያስደረገ ትምህርት ነው:: ስለዚህ ትምህርት ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የዚህን መጽሐፍ የመጀመሪያ ቅጽ ይመልከቱ::

[8] "ቄስ ተክሌ ይህን ትምህርት ማስተማር የጀመረው በ1970 ዓ.ም ላይ ነው:: ነገሩን በንስማ ትምህርቱ ትክክለኛ አይደለም ብለን ተቃውመናል:: ሲጀመር ግን ጥቃቅን መገለጥ እንጂ መሠረታዊ የነገረ መለኮት ትምህርት አልተወበደም:: የቄስ ተክሌን ስብከት ወይም ትምህርት የሚከታተል ሰው በግልጽ የሚረዳው ጉዳይ ትምህርቶቹ ሁሉ ከእግዚአብሔር በቀጥታ እንደ ተቀበለው አድርጎ ማቅረብ የተለመደ ነው:: አዳዲስ መገለጦችን የመሻት ናፍቆት ያለው ሰው ነው:: በመጀመሪያ ትምህርቱን የገለጸው እግዚአብሔር ይህን ጉዳይ ገለጠልኝ በሚል መልኩ ነው":: ይህን የቄስ ተክሌን ትምህርት ለዓለም ሀቀፉ ቢሮ ይፋ ያደረገው ሰው አሁን የዓለም ሀቀፉ ቢሮ ተወካይ ሆኖ እንዲሁም ከዓለም ሀቀፉ ቢሮ ጋር ተመሳሳይ አስተምህሮ በመያዝ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠራውና ከቄስ ተክሌ ኅብረት የተለየው ሰሎሞን ሉዳሞ ነው:: ይህ የሆነውም ባለቤቱን ዐይኗን ለማሳከም አሜሪካን አገር በተጓዘበት ጊዜ ነው:: ይህ ሰው በዚያን ጊዜ ቄስ ተክሌ ሲያወግዙን አብሮን የነበረ ሰው ነው:: ምናልባት ይህን ትምህርት በጥልቀት የሚያውቀው ሰሎሞን ነው ማለት ይቻላል:: ይህ ትምህርት በስሕተት እንደ ሆነም በርካታ ጊዜ አስተምሮአል::



እንግዲህ በዚህ መልክ እኔ ከእነርሱ ጋር የነበረኝን ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ አቋረጥሁ:: ከዚህ በኋላ የእኔ ትልቁ ጥያቄ፣ የእኔ ውሳኔ በእኔና በቤተሰቤ ቀጣይ ሕይወት ላይ ትልቅ ለውጥ በለሚያመጣ ምን ማድረግ አለብኝ በሚለው ነጥብ ላይ ያተኮረ ነበር:: ልጆቼ ጉፋ ሰፈር ወደሚገኘው "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ይሄዱ በለነበር፣ እነርሱንስ ምን ማድረግ አለብኝ? ይህ ሁሉ ሲሆን ባለቤቴ በቀድሞው እምነት ውስጥ ስላለች እርሷንስ በተመለከተ ማድረግ ያለብኝ ነገር ምንድን ነው? ጉዳዩን እንዴት ነው ላስረዳት የምችለው? ልጆቼ በቀድሞው ትምህርት እንቁያለን ቢሉ፣ ባለቤቴ የድርጅቱን ትምህርት ስሕተት መሆኑን ባትገነዘብ የማደርገው ነገር ምንድን? ነው የሚለው ጉዳይ በብዙ የሚያሳስበኝ ነበር:: የሚያስደንቀው ግን እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ አስቀድሞ ሠርቶአቸው በለነበር ጉዳዩ እንዳሰብሁት አስቸጋሪ አልሆነብኝም:: አንድ ቀን ለባለቤቴ ያለኝን አቋም ነገርኋት:: እርሷም፣ "አብና ወልድ የተለያዩ መሆናቸውን በተደጋጋሚ ነግሬህ ነበር:: እኔ ራሴ በድርጅቱ ትምህርት ላይ ብዙ ጥያቄ አለኝ አለችኝ":: እንግዲያውስ ይህ የእኔ አቋም መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከቀድሞው ድርጅትና እምነት ለመልቀቅ ወስኛለሁ አልኳት:: እርሷም በአቋሙ ተስማማች:: በአጠገባችን ቂርቆስ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በለነበር፣ ወደዚያ ሄደው ቃለ እግዚአብሔርን እንዲማሩ ለልጆቻችን በንገልጽላቸው ያላንዳች ቅሬታ ጉዳዩን ተቀብለው፣ ቂርቆስ መካነ ኢየሱስ በመሄድ ቃለ እግዚአብሔርን መማር ጀመሩ:: በዚህ ዐይነት መልክ ለቤተ ሰቤ የነበረኝ ጭንቀት በአስደናቂ ሁኔታ ዕልባት አገኘ::

## *በቅዱሳን ኅብረት መታቀፍ*

የእኔና የቤተሰቤ ቀጣዩ ጉዳይ የትኛው ቤተ ክርስቲያን እንሂድ የሚለው ሆነ:: የእኔ ምርጫ እምብዛም የማትታወቅ አንዲት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን በአባልነት መታቀፍ ነበር:: ነገር ግን ያቺ ቤተ ክርስቲያን የት እንዳለች፣ እንዴትስ እንደምትገኝ፣ እንዴትስ አባል ሊሆኗት እንደሚቻል የማውቀው ነገር አልነበረም:: በማንታወቅበት ቦታ ተጠልለን እግዚአብሔርን እያመለክን እንደማንኛውም ክርስቲያን ሥራችንን እየሠራን እኖራለን አልን:: እግዚአብሔር በዚህ መልኩ እንዲመራን ጸሎታችንን እናደርስ ነበር:: ይህ መሻታችን እውን እንዲሆን እኔና ቤተ ሰቤ አጥብቀን በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት እንቀርብ ነበር::

አንድ ቀን ሁለት እናቶች ቤታችን መጡ። አንደኛዋ እናት ከእኔ ጋር ይተዋወቃሉ። እኔ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ እንደሆንሁ ያውቃሉ። እርሳቸው ሰፈር አንዲት ታዋቂ የሆኑ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አባል፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት ውስጥ ሳለሁ አጥምቄአቸዋለሁ። እርሳቸው ደግሞ ይህንን ያውቃሉ። በተጨማሪም የእርሳቸው ሰፈር ሴት የሆኑና "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አማኒ የነበሩ ታዋቂ ሴት ዘንድ በመሄድ እንደማገለግላቸው ያውቃሉ። ነገር ግን እኚህ ሴት የፍቅር ሰው ስለነበሩ፣ መንገድ ላይ ሲያገኙኝ ሳይስሙኝ ዐልፈው አያውቁም። ልክ እንደ ራሳቸው ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አድርገው ጤናዬን እንዲሁም ቤተ ሰቤን ጠ ይቀውኝ ነው የሚያልፉት። እንግዲህ እርሳቸውና አንድ ሌላ እናት ናቸው እኔ ቤት ድንገት የመጡት። በጣም ገረመን። የት ቤተ ክርስቲያን ነው የምትሄዱት ሲሉ ጠየቁን። ነገሩ አስደነቀን፤ ምክንያቱም አሁን ስላሰን አቋም ከሰው ይረዱ ወይስ እግዚአብሔር ራሱ ይንገራቸው አልጠየቅናቸውም። ነገር ግን የትም ቤተ ክርስቲያን እንደማንሄድ፣ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን እንደ ተውን ሌላ ቤተ ክርስቲያንም እንደማንሄድ ገለጽንላቸው። እነርሱም "ሙሉ ወንጌል ኑ" ብለውን ተነሥተው ከቤት ወጡ። እነዚህን ሰዎች የላካቸው እግዚአብሔር ይሆንን? የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ፣ እኔና ባለቤቴ በአባልነት ጉዳይ ላይ መጸለይ ጀመርን። አገልግሎት የሚለው ነገር ግን ብዙ ዋጋ ስላስከፈለን አገልጋይ የመሆኑን ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ ሰርዘናል፣ የት ቤተ ክርስቲያን አባል እንሁን በሚለው ጉዳይ ብቻ ጸሎታችንን በእግዚብሔር ፊት ማቅረብ ጀመርን። በነገራችን ላይ አባል ልሆንበት ከማልፈልጋቸው ቤተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ነበር። ለምን እንደዚያ እንዳሰብሁ ግን አላውቅም። ኋላ ግን ወደ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን እንድንሄድ የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው የሚል እምነት በልባችን እየተፈጠረ መጣ። እቤታችን ከመጡት እናቶች በስተቀር ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጋር ትውውቅ የለንም። አካባቢያችን የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ እንዲሁም በደንብ የሚያቀን ሰው አለ። እርሱ ዘንድ በመሄድ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን እንደምፈልግ ነገርሁት። እርሱ ግን ደነገጠ። ይህ ሰው መስሎ ገብቶ ቤተ ክርስቲያን ሊበጠብጥ ነው የሚል እምነት እንዳደረበት ኋላ አጫውቶኛል። እሺ ብሎ እንዳችም እርምጃ ሳይወስድ ተወን። ከዚያ በኋላ እቤታችን ከመጡት ከአንደኛዋ እናት ጋር ግንኙነት ማድረግ



ጀመርን። እኔ እርሳቸው ቤት መሄድ ጀመርሁ፤ ቤተሰብ ሆንን። አብረን ቃለ እግዚአብሔርን እየተማማርን፣ በኅብረት እየጸለይን ቆየን፤ ምናልባትም የእርሳቸው አገልጋይ ሆንሁ ማለት ይቻላል። ጉዳዩን ለእከሌ ነገርሁት አልኋቸው። እኚ እናት ከቀድሞዎቹ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል አንዷ ስለነበሩ፣ መጋቢ መርድን በአካል ያውቁታል፤ ስለዚህ እኔ ራሴ ለመርድ እነግረዋለሁ አሉ። ደውለውም ስለጉዳዩ አጫወቱት። እርሱ ደግሞ ደውሎ አካባቢዬ ለሚገኘው ለዚያ ወንድም እንዲቀበለኝ ነገረው። ከዚያ በኋላ አንድ ወንጌላዊ እኔ ዘንድ ይልካሉ። ይህ ወንጌላዊም በእኚህ እናት ቤት ውስጥ ስለጉዳዩ ያነጋግረኛል። ጉዳዩን በግልጽ ባሳውቀውም እንኳ ሊያምነኝ ግን ይቸገራል። በሌላ ቀን እኛ እናት ጉዳዩ ምን ላይ ደረሰ ሲሉ ጠየቁኝ፣ እኔም እስካሁን ምንም አዲስ ነገር እንደሌለ ገለጽሁላቸው። ቆይ እኔ አሁንም ለመርድ ነግረዋለሁ አሉ። ለመጋቢ መርድ ሲነግሩት በቤት ኅብረት ውስጥ ይግባ ይላል። በዚያ ወንድም ቤት ውስጥ የቤት ለቤት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካሄድ ስለነበር ግለሰቡ ብዙ ፈቃደኛ ባይሆንም እንኳ፣ ጉዳዩ ከፓስተር መርድ ስለመጣ ብቻ ሊቀበለኝ ግድ ይሆንበታል። በዚህ መንገድ በኅብረቱ ውስጥ በመቀላቀል የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል ሆንሁ።

አሁን ወደ ደረስሁበት የአገልግሎት ደረጃ የመጣሁት ቀስ በቀስ ነው። የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በድቁና እያገለገልሁ ወርልድ ቪዥን እሠራ ነበር። ጉተራ በሚገኘው ጸሎተ ቤት ደግሞ የዲቆናት ሰብሳቢ ሆኜ ማገልገል ጀመርሁ። ቀድሞም በአገልግሎት ረጅም ጊዜ ስለቆየሁ በተጨማሪም ለማገልገል ትልቅ ሸክም ስለነበረኝ ንቁ አገልጋይ ሆኜ ነው የቀጠልሁት። በእግዚአብሔር ርዳታም የሰፋ የአገልግሎት በር ነገረኝ።

## *"የወንጌሉ አገልጋይ ሆንሁለት"*

በዚህ ሁኔታ እያለሁ እግዚአብሔር አገልግሎት መጀመር እንዳለብኝ ተናገረኝ። ቀድሞ ሕይወቴን ሰጥቼው የነበረው ትምህርት ኋላ ስሕተት ሆኖ ባገኘሁት ጊዜ እንዳዘንሁ ሁሉ፣ አሁንም የሙሉ ጊዜ አገልጋይ እንድሆን ጌታ ሲናገረኝ ቅሬታ ተሰማኝ። ምክንያቱም ከአገልግሎት አምልጬ እንደማንኛውም ሰው ንቁ የቤተ ክርስቲያን አባል ሆኜ እኖራለሁ የሚል አቋም ባለኝ ጊዜ ይህ ጉዳይ ወደ እኔ መምጣቱ

አሳዘነኝ፡፡ ወርልድ ቪዥን ውስጥ ሰባት ዓመት ካገለገልሁ በኋላ በ1989 ዓ.ም ላይ ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ወጣሁ፡፡ ለአገልግሎት መጠራቴን ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች አሳወቅሁ፡፡ እነርሱም በጉዳዩ ላይ ችግር አልነበረባቸውም፤ ምክንያቱም ከሚያዩት ነገር የተነሣ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ጉዳይ እንዳለው፣ ለወንጌል ሥራ የተጠራሁ ሰው መሆኔን ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይና ምዕመናን ያውቀው ስለነበር ነው፡፡ በአንዳንድ አገልጋዮች ላይ ደረሰ የሚባለው "መታሸት" በእኔ ላይ አልደረሰም፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለጊዜው የትራንስፖርት ገንዘብ በጥታ፣ በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ተቀብላ አሠማራችኝ፡፡ መጀመሪያ በወንጌላዊነት ቀጥሎም በመጋቢነት አገልግሎት ተሹሜ ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ፣ ተቀዳሚ መጋቢው ሲለቁ አሁን በዋና መጋቢነት በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡

የታሪካችን ባለቤት እግዚአብሔር ነው፡፡ ባለፍንባቸው ጉዳናዎች ሁሉ ያልተለየን በድካማችን የተሸከመን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፡፡ ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔ ይሁን፡፡



# ዋቢ መጻሕፍት

ለቅጽ 1 እና ለቅጽ 2 መጻሕፍት ዝግጅት በርካታ መጻሕፍትን የተጠቀምን ቢሆንም፣ ይህ የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር በግርጌ ማስታወሻነት የጠቀስናቸውን መጻሕፍት ብቻ ያካተተ ነው፡፡

## I. በ"ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ጸሓፍት የተዘጋጁ መጻሕፍት


ገዛኸኝ ተከስ ማርያም፣ *መለኮታዊ ኀይል*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1961፡፡

__________፣ *ቃሉ ይናገር*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1996፡፡

__________፣ *ኢየሱስን ማን ይሉታል*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1978፡፡

__________፣ *በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፊልጉ*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1974፡፡

__________፣ *አድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አዲስ ልደት*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1987፡፡

__________፣ *ጥያቄዎቻችሁና መልሶቻቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1974፡፡

__________፣ *አንድ መንጋ*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

__________፣ *የመልእክቶች አጠቃላይ ትምህርት*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992፡፡

ቄስ አማሬ ዋቅቶላ (አዘጋጅ) ዴቪድ በርናርድ፣ *ሐዋርያትና ክሊያት ምን አስተማሩ?*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1989፡፡

*የኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች*፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Bernard, David K. *Essentials of the New Birth*. Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1987.

_____________. *In the Name of Jesus.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1992.

_____________. Oneness *and Trinity A.D. 100-300: The Doctrine of God in Ancient Christian Writings.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1991.

_____________. *The Oneness of God.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1983.

Bernard, David, C. A. Brewer, and P. D. Buford. *Meet the United Pentecostal Church International.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1989.

Chalfant, William B. *Ancient Champions of Oneness: A History of the true Church of Jesus Christ.* Junction City, Kans., 1979.

Clanton, Charles, Crawford Coon, and Paul Dugas Bible Doctrines: Foundation of the Church. Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1984.

Clanton, Charles, Dennis Croucher, and Paul Dugas. *Salvation: Key to Eternal Life,* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1985.

Fauss, Oliver F. *Baptism in God's Plan.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1990.

Freeman, Nona. *Unseen Hands: The Story of Revival in Ethiopia.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1987.

Gezahgne, Teklemariam. *The Identity of Jesus Christ.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1989.

_____________. *Bible Wriers' Theology.* USA: Ozark Mountain Press, 1999.

_____________. *Bible Writers' Theology.* Hazelwood, Mo.: Apostolic Experience Publishing, 1989.

Hall, J. L. The United Pentecostal Church and the Evangelical Movement. Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1990.

Magee, Gordon. *Is Jesus in the Godhead or Is the Godhead in Jesus?* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1988.

Paterson, John. *God in Christ Jesus.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1966.

Reynolds, Ralph V. *Truth Shall Triumph: A Study of Pentecostal Doctrines.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1965.





Rugger, Gary C. *Oneness, Trinity, Arian: Which One Does Scripture Teach?* Bakersfield, Calif.: Sarah's Christian Books, 1988.

Visker, Jack. *The Baptism of the Holy Spirit.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1990.

Welch, D. L. *Contending for the Faith.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1988.

Williams, Carl E. *The Bible Plan of Salvation.* Hazelwood, Mo.: Word Aflame Press, 1989.


## II. በ"ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የተዘጋጁ በራሪ ጽሑፎች

- አንድ አምላክና ሰው አማኑኤል
- ልትድን ትወዳለህን?
- የማንን እንስማ?
- ጥምቀት ያድናል!
- የሐሰትና የእውነት ሃይማኖት
- መርምረኝ አትጣለኝ
- አንድ አምላክ አንድ አካል ብቻ
- መዳን በሐዋርያት ትምህርት ብቻ

## III. በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ላይ የተጻፉ መጻሕፍት


ተስፋዬ ሮበሌ፣ *ወበይት መናፍቃን፣* አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፣ 1993::

_____________፣ *የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና ትምህርተ ሥላሴ፣* አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፣ 1993::

_____________፣ *የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት፣* አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ተስፋ ዐቃብያን ክርስትና ማኅበር፣ 1996::

Boyd, Gregory A. *Oneness Pentecostals and The Trinity.* Grand Rapids: Baker, 1992.

Beisner, E. Calvin. *"Jesus Only" Churches.* Grand Rapids: Zondervan, 1998.

Dalcour, Edward L. *A Definitive Look at Oneness Theology: Defending the Tri-Unity of God.* Lanham Maryland: University Press of America, 2005.

Langon, Steve and Thomas D. Sheehey. *Oneness Pentecostalism: New Truth or Old Heresy?* 2000.

Fudge, Thomas A. *Christianity Without the Cross: A History of Salvation in Oneness Pentecostalism.* Parkland Florida: Universal Publishers, 2003.

## IV. አንድምታዎች/የትርጓሜ መጻሕፍት

Calvin, John. *Commentary on the Epistles of Paul the Apostle to the Corinthians.* Translated by John Pringle. Vol. 20 of Calvin's Commentaries. 1848. Reprint. grand Rapids: Baker, 1984.

Metzger, Bruce. *A Textual Commentary on the Greek New Testament.* 2nd ed. New York: United Bible Societies, 1994.

Lightfoot, J. B. *St. Paul's Epistles to the Colossians and to Philemon.* 1879. Reprint. Grand Rapids: Zondervan, 1974.

Lenski, R. C. H. *The Interpretation of John's Gospel.* Minneapolis: Augsburg, 1943.

Robertson, A. T. *Word Pictures in the New Testament.* 6 vols. Nashville: Broadman, 1932.

*The International Bible Commentary, with the New International Version.* Edited by F.F. Bruce. Grand Rapids: Zondervan, 1986.

Westcott, B. F. *The Gospel According to St. John.* 1881. Reprint. Grand Rapids: Eerdmans, 1991.

## V. የቋንቋና የሰዋስው መጻሕፍት

Bauer, Walter. *A Greek-English Lexicon of the New Testament and Other Early Christian Literature.* Translated by William F. Arndt and F. Wilbur Gingrich. Revised by F. Wilbur Gingrich and Frederick W. danker. 2d ed. Chicago: University of Chicago Press, 1979.



Brown, Colin, ed. *The New International Dictionary of New Testament Theology.* 4 vols. Grand Rapids: Zondervan, 1975-1985.

Dana, H. E., and Julius R. Mantey. *A Manual Grammar of the Greek New Testament.* 1927. Reprint. New York: Macmillan, 1955.

Liddell, Henry G., and Robert Scott, comps. *A Greek-English Lexicon.* Revised by Henry S. Jones and Roderick McKenzie et al. 9th ed. Oxford: Oxford University Press, 1940.

Metzger, Bruce M. *The Text of the New Testament.* 2d ed. Oxford: Oxford University Press, 1968.

__________. *A Textual commentary on the Greek New Testament.* New York: United Bible Societies, 1971.

Moulton, James H., and George Milligan. *The Vocabulary of the Greek New Testament.* 1930. Reprint. Grand Rapids: Eerdmans, 1976.

Robertson, A. T. *A Grammar of the Greek New Testament in the Light of Historical Research.* Nashville: Broadman, 1934.

Smith, J. B. *Greek-English Concordance to the New Testament.* Scottdale, Pa.: Herald Press, 1955.

Turner Nigel. *Syntax.* Vol. 3 of James H. Moulton, *A Grammar of New Testament Greek.* 4 vols. Edinburgh: T. & T. Clark, 1963.

Winer, George B. *A Grammar of the Idiom of the New Testament.* 7th ed. Andover: Warren F. Draper, 1881.

## VI. መዝገበ ቃላትና የዕውቀት ምድብሎች

Burgess, Stanley M., Gary B. McGee, and Patrick H. Alexander, eds. *Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements.* Grand Rapids: Zondervan, 1988.

*Dictionary of Paul and His Letters.* Edited by Gerald F. Hawthorne and Ralph P. Martin. Downers Grove: InterVarsity Press, 1993.

Smith, William, and Samuel Cheetham, eds. *A Dictionary of Christian Antiquities.* 2 vols. London: John Murray, 1875.

## VII. የታሪክ መጻሕፍት


Bethune-baker, J. F. *An Introduction to the Early History of Chrristian Doctrine to the Time of the Council of Chalcedon*. London: Methuen and Company, 1903.

Lightfoot, J. B., ed, and trans. *The Apostolic Fathers: Clement, Ignatius, and Polycarp, revised Texts with Introductions*, Notes, Dissertations, and Translations. 5 vols. Reprint. Peabody, Mass.: Hendrickson, 1989.

Lightfoot, J. B., and J. R. Harmer, trans. *The Apostolic Fathers: Revised Greek Texts with Introductions and English Translations*. Reprint. Grand Rapids: Baker, 1984.

Roberts, Alexander, and James Donaldson, eds. *The Ante-Nicene Fathers: Translations of the Writings of the Father down to A.D. 325*. 10 vols. Reprint. Grand Rapids: Eerdmans, 1975

Schaff, Philip, ed. *Nicene and Post-Nicene Fathers of the Christian Church*. 28 vols. Second Series. Reprint. Grand Rapids: Eerdmans, 1978.

Schaff, Philip, *The Creeds of Christendom*. 3 vols. Grand Rapids: Baker, 1977.


## VIII. የነገረ መለኮት መጻሕፍት/ሥነ አፈታት


Berkhof, Louis. *Introduction to Systematic Theology*. Reprint edition: Grand Rapids: baker, 1979. First published by Eerdmans, 1932.

———————. *Systematic Theology*. fourth edition, grand Rapids: Eerdmans, 1939.

Boice, James Montgomery. *Foundations of the Christian Faith*. Revised one-volume edition. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1986.

Bowman, Robert M., Jr. Why You Should Believe in the Trinity: An Answer to Jehovah's Witnesses. Grand Rapids: Baker Book House, 1989.

Calvin, John. *Institutes of the Christian Religion*. 2 vols. Ed. by John T. McNeill. Trans. and indexed by Ford Lewis battles. The Library of Christian Classics, Vols.20-21. Philadelphia: Westminster, 1960.





Crampton, W. Gary. *Biblical Hermeneutics*. Lakeland: Whitefield Press, 1986.

Erickson, Millard. *Christian Theology*. Grand Rapids: Baker, 1985.

Geisler, Norman L. and William E. Nix. *A General Introduction to the Bible*. Rev. ed. Chicago: Moody Press, 1986.

Grudem, Wayne. *Systematic Theology: An Introduction to Biblical Doctrine*. Ill.: InterVasity Press, 1994.

Harris, Murray J. *Jesus as God: The New Testament Usage of Theos in Reference to Jesus*. Grand Rapids, Baker, 1992.

Henry, Carl F. H. God, Revelation, and Authority. 6 vols. Waco, Tex.: Word, 1976-83.

Hodge, Charles. *Systematic Theology*. 3 vols. Grand Rapids: Eerdmans, 1973.

Ryrie, Charles. *Basic Theology*. Wheaton, Ill.: Victor, 1986.

White, James R. *The Forgotten Trinity: Recovering the Heart of Christian Belief*. Minneapolis: Bethany House, 1998.

# ጸሐፊው

ተስፋዬ ሮበሌ፣ "ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር" በመባል የሚታወቀው አገር በቀል ድርጅት መሥራችና ዳይሬክተር ሲሆን፣ ማኅበሩ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አባል ነው።

ተስፋዬ ሮበሌ በኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚና አርታኢ (Reviewer) ሆኖ የሠራ ሲሆን (አዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከማጥኛ ጽሑፉ ጋር)፣ በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ ክፍል ኃላፊና የቃለ ሕይወት መጽሔት ዋና አዘጋጅ በመሆንም አገልግሎአል።

ተስፋዬ ሮበሌ በዐቃቤ እምነት፣ በሥነ ምግባር እንዲሁም በነገረ መለኮት ላይ ከዐሥራ ሦስት በላይ መጻሕፍትን ጽፎአል። ከእነዚህም መጻሕፍት ውስጥ አብዛኞቹ በነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዲሁም በነገረ መለኮት ማስፋፋት (ትመማ) አገር ዐቀፍ ፕሮግራም ውስጥ የመማሪያ መጻሕፍት ናቸው።

***ወንድም ተስፋዬ ሮበሌን በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል***


ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
የመልእክት ሣጥን ቁጥር 23045 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

The Evangelical Society For Apologetics (TESFA)
Post Office Box 23045, Code 1000
Addis Ababa, Ethiopia

E-MAIL: **<apologetics@ethionet.et>**
**<tesfa_apologetics@yahoo.com>**

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ አስመልክቶ የተጻፈው ይህ መጽሐፍ ስሕተትን አጉልቶ ከማሳየት ባሻገር፣ ለአንባቢያን መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አፈታትን ጥበብ ያስጨብጣል:: እግዚአብሔር በቃሉ ያለውን በትክክል ለመረዳት በቂ ጥናት የማድረግን ባህል ያዳብራል:: ስለሆነም የዋህ አማንያን በስሕተት ትምህርት እንዳይወሰዱ፣ በሐሰት ትምህርት የተወሰዱ ቃሉን በትክክል ተረድተው እንዲመለሱ፣ ሊጠቀሙበት ይገባል:: በተጨማሪም በአገራችን ቋንቋ የተጻፉ መሰል ድርሰቶች እጅግ እናሳ በሆኑበት ጊዜ የዚህ ጽሑፍ መገኘት ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት፣ ለሰነበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎችና ለመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንዲሁም ለሁሉም አማኝ ጥሩ የምሥራች ነው:: እነዚህም ሁሉ የዚህ መግለጫ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ምኞቴና ጸሎቴ ነው::

*ማሞ ገብረ መስቀል*
*የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት*
*እንዲሁም የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ መንበር*

ተስፋዬ ሮበሌም ሰዎች አንድም ከቀጣ ይተርፉ ዘንድ፣ አንድም የሐሰት ትምህርትን በእግዚአብሔር እውነት ለመተካት ሲል ይህንን መጽሐፍ ጽፎአል:: ሐዋርያት ሳይሆኑ በሐዋርያነት ስም ለስተጠሩት ጉባኤያት፣ "የሚናገር እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር" (ሮሜ 12÷6) በማለት ዕዳውን አቅልሎአል:: የተቀረው፣ "የሚመለከተው ሁሉ" እያነበበው ይገረምበት፣ ይመከርበት፣ ይታረምበት ዘንድ በመጽሐፉ መጠቀም ነው:: ተስፋዬን እግዚአብሔር ለዐቃቤ እምነት ጠርቶታልና ይበረታበት ዘንድ ምክሬ ነው::

*ስሜ ታደሰ (መጋቢ)*
*ቤዛ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን*

ይህ የተስፋዬ ሮበሌ መጽሐፍ፣ "የሐዋርያትን ቤተ ክርስቲያን" ትምህረት በግሩም ሁኔታ የሚፈትሽና መልስ የሚሰጥ ነው:: ለስትምህርታቸውም፣ የሰማ በሰው ሳይሆን የቤተ ክርስቲያኒቷ መሪ የጻፋትን ትምህርቶች ቀጥታ በመጥቀስ ተገቢ መልስ ተሰጥቶበታል:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ጽሑፎች የአብየተ ክርስቲያናትን አስተምህሮ በመቃወም ብዙ የዘበዘቡ ቢሆንም፣ ዝምታ ፍርሓት የመሰሰበትን ሁኔታ የሚሰብር ሆኖ አግኝቼዋለሁ—ይህን መጽሐፍ:: የእነርሱን በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች እውነተኛ እምነት መስሰው የተደሳደሉትን መደሳድል የሚንጥና የሚንድ መጽሐፍ ነው፤ ስሕተቱን ለማየት በሩ እነሆ ተከፍቶአል!

መጽሐፉ ሲያውቁ ስተሳሳቱ መመለሻ፣ ስተደነጋገረባቸው መጽኛ፤ ለአሳቾችም ጥሩ የሚያነቃ በትር ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: ያንብቡት፣ ያስነብቡት::

*አፈወርቅ ኀይሉ*
*በኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ የነገረ መለኮት መምህር*

ሰው እንዴት ከኀጢአቱ ይድናል? እንዴት የዘላለም ሕይወት ያገኛል? የሚለው ጥያቄ በጣም መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: ይህን ጥያቄ በማያወላዳ መንገድ መመለስ መቻል፣ የክርስቲያን ሁሉ ኀላፊነት ነው:: ተስፋዬ ሮበሌ በነገረ ድነት ላይ የተምታቱ፣ የተውገረገሩ፣ መስመር የሳቱ አመለካከቶችን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ አንጻር የተቸበት ይህ መጽሐፍ፣ ጉዳዩን አጣርተን እንድንለይና ግልጽ አቋም እንዲኖረን የሚረዳ ሁነኛ አስተዋጽኦ ነው::

*ንጉሤ ቡልቻ*
*ቃለ እግዚአብሔር አንባብያን ማኅበር*

ወንድማችን ተስፋዬ ሮበሌ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" መሪዎች ጥምቀት ለድነት አስፈላጊ ነው በማለት ባነሷቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሳይ፣ እጅግ በሚያረካ መንገድ ትክክለኛውን የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት መንገድ በመከተል "ለሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ተከታዮችም ሆነ ለሌላው ሰው በሚጠቅም መንገድ አቅርቦአል:: እኔ ሳልሆን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይናገር ማለት ትልቅ ዐዋቂነት ነው:: ስለዚህ ይህችን እጅግ ጠቃሚ የሆነች መጽሐፍ እውነትን ለማወቅ የሚሻን ሁሉ በእጃቸው አስገብተው እንዲያነቧት አበረታታለሁ::

*ፍሬው ታምራት የኢቫንጀሊካል የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት (ETC)*
*አካዳሚክ ዲንና የነገረ መለኮት መምህር*

ዋጋው 15 ብር